
# የተቀናጀ የቅድመ አንደኛ ደረጃ

# ትምህርት መምህር መምሪያ

2017/2024



## ደረጃ አንድ




MINISTRY OF EDUCATION



# የተቀናጀ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት

# መምህር መምሪያ

## ደረጃ አንድ

2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

**FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**MINISTRY OF EDUCATION**

# የተቀናጀ ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት

## መምህር መምሪያ

## ደረጃ አንድ


### አዘጋጆች

መ/ር ደረጀ አብዲ

አቶ ሽመልስ መሀመድ

መ/ር ሰላማዊት ተስፋዬ

መ/ርት ደጊቱ በቀለ

መ/ርት ሀይማኖት ክንዴ

አቶ ደጉ ዘውዱ

ወ/ሮ የትናይት መርሻ

### አርታኢዎች

አቶ መኮነን አስማማው

መ/ር ተሾመ ቆንዳሌ

መ/ር ተሾመ በላይነህ

### ዲዛይነር

ታደሰ ድንቁ

### አስተባባሪ፡-

አቶ ኡመር ኢማም

ወ/ሮ ሂሩት ወ/ሚካኤል

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

## የባለቤትነት መብት

### የአዘጋጅው ባለቤትነት መብት የተረጋገጠ ነው።

ያለትምህርት ሚኒስቴር ፈቃድ በባለቤትነት መብት ህግ ከተፈቀደው ውጪ የመምህሩን መምሪያ የተወሰነ ክፍል ወይም ሙሉ በሙሉ መልሶ ማሳተም፣ ማባዛት፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸት እና መልሶ በማንኛውም መንገድና ሁኔታ መጨቀም ለሚደርሰው የመንግስትና የህዝብ ጉዳት በወንጀል ህግ ተጠያቂ ያደርጋል።

የመጀመሪያ ህትመት 2017 ዓ.ም ትምህርት ሚኒስቴር

## ምስጋና

ይህ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህር መምሪያ ለክልሎች ዝግጅት በናሙናነት እንዲያገለግል ታስቦ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ከክልሎች ጋር በጋራ የተዘጋጀ ነው። በዚህ የመምህር መምሪያ ዝግጅት ላይ ውድ ግዜያቸውን ለዝግጅቱ ጥራት ትኩረት በመስጠት በአዘጋጅነት፣ ገምጋሚነት፣ በአስተባባሪነት፣ በጥራት አስጠባቂነት እና በዲዛይን አዘጋጅነት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ላበረከቱ ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋና እናቀርባለን። በመቀጠል ስራው በጥራት እና በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛውን ድርሻ ቢወስድም በገንዘብ ድጋፍ እና በማማከር ያላሰለሰ ጥረት የደረጉ የሁል ግዜ አጋር የሆኑት አለም አቀፍ እና ሀገር በቀል ተቋማት ለሆኑት የአለም አቀፍ የህፃናት ተራድኦ ድርጅት (UNICEF)፣ አለም ባንክ (World Bank)፣ የኢትዮጵያ ስኩል ሬዲነስ ኢኒሸቲቭ (ESRI) እና ኢዱኬሽን ሰስተኔብል ድቭሎፕመንት (ESD) ያለንን ልባዊ ምስጋና በኢትዮጵያ ህፃናት ስም ማቅረብ እንወዳለን።

# ማውጫ


ክፍል አንድ........................................................................................1

አጠቃላይ መግለጫ ........................................................................................1

1.1. መግቢያ ........................................................................................1

1.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነትና አስፈላጊነት........................................3

1.2.1. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነት..................................................3

1.2.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት አስፈላጊነት................................................3

1.3. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሆዎች..................................................3

1.3.1. ሕጻናት-ተኮር አቀራረብ........................................................................3

1.3.2. ጨዋታ-ተኮር ትምህርት........................................................................4

1.3.3. የተቀናጀ ሥርዓተ-ትምህርት....................................................................4

1.3.4. አካቶ ትምህርት..............................................................................4

1.3.5. ሀገር በቀል እውቀት..........................................................................4

1.3.6. ከእድገታቸው ጋር ተስማሚ የሆኑ ተግባራት..................................................4

1.3.7. የወላጆች/አሳዳጊዎችና ማህበረሰብ ተሳትፎ................................................4

1.3.8. ጤናማና ምቹ የትምህርት አከባቢ..............................................................5

1.3.9. ሁለንተናዊና ቀጣይነት ያለው እድገት........................................................5

1.3.10. የተመጣጠነ አቀራረብ.........................................................................5

1.3.11. የህፃናት ተከታታይ ምዘና.....................................................................5

1.4. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ሥርዓት-ትምህርት አጠቃላይ ዳሰሳ.......................................5

1.5. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ሥርዓተ-ትምህርት አጠቃላይ ዳሰሳ... ..................................5

1.6. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ-ትምህርት ... .........................................6

1.6.1. የቋንቋ መዳበርና ተግባቦት....................................................................6

1.6.2. የቅድመ-ሂሳብ መዳበር.........................................................................6

1.6.3. አካባቢ ሳይንስ..................................................................................6

1.6.4. የግልና ማህበረ-ስሜታዊ መዳበር...............................................................7

1.6.5. አካላዊ መዳበርና ጤና....................................................................................7

1.6.6. የክወናና የእይታ ጥበባት...............................................................................7

1.7. የዕድገትና የመማር ብቃቶች.. ...............................................................................7

1.8. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህጻናት የባህርይ ገጽታ.........................................8

1.9. ሀገር በቀል (አካባቢያዊ) እውቀትን መሠረት ያደረገ ትምህርት...................................8

1.10. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውህደት (PPE Integration) ..................................9

1.11. የህጻናት ንቁ ተሳትፎ በትምህርት.......................................................................10

1.12. ህጻን-ተኮርና በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ትምህርት.................................................11

1.13. ህጻናትን ማዕከል ያደረገ ትምህርት ላይ የመምህራን ሚና.....................................12

1.14. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም የዕለት ተዕለት ተግበራት........................13

1.15. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ባህሪያት.....................................................16

1.15.1. የመማሪያ አከባቢ አደረጃጀት.........................................................................16

1.16. የህጻናት እድገትና ትምህርት ምዘና...................................................................17

1.17. የወላጅና አሳዳጊ ተሳትፎ በህጻናት ትምህርትና እንክብካቤ......................................19

1.18. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመምህር መምሪያ አጠቃቀም...............................19

1.18. የጊዜ አደላደል ................................................................................................20

ክፍል ሁለት፡-...........................................................................................21

አውድ አንድ ...........................................................................................21

ስለ እኔ.....................................................................................................21

መግቢያ ............................................................. ...........................................21

አንደኛ ሳምንት..............................................................................................23

ሁለተኛ ሳምንት..............................................................................................30

ሦስተኛ ሳምንት..............................................................................................36

አራተኛ ሳምንት..............................................................................................42

አምስተኛ ሳምንት ............................................................................................47

አውድ ሁለት...........................................................................................53

ቤቱና ቤተሰቦቹ.........................................................................................53

መግቢያ.....53

ስድስተኛ ሳምንት.....55

ሰባተኛ ሳምንት.....61

ስምንተኛ ሳምንት.....68

ዘጠነኛ ሳምንት.....75

አሥረኛ ሳምንት.....82

**አውድ ሶስት.....89**

**ጎረቤቶቼ እና ትምህርት ቤቴ.....89**

መግቢያ.....89

አሥራ አንደኛ ሳምንት.....91

አሥራ ሁለተኛ ሳምንት.....96

አሥራ ሶስተኛ ሳምንት.....104

አስራ አራተኛ ሳምንት.....110

አስራ አምስተኛ ሳምንት.....117

**አውድ አራት.....125**

**ቀለማት.....125**

አስራ ስድስተኛ ሳምንት.....127

አሥራ ሰባተኛ ሳምንት.....133

አሥራ ስምንተኛ ሳምንት.....139

አሥራ ዘጠነኛ ሳምንት.....145

ሀያኛ ሳምንት.....151

**አውድ አምስት ጓደኝነት.....157**

**ጓደኝነት.....157**

መግቢያ.....157

ሀያ አንድኛ ሳምንት.....159

ሀያ ሁለተኛ ሳምንት.....164

ሀያ ሶስተኛ ሳምንት.....171

ሀያ አራተኛ ሳምንት.....176

ሀያ አምስተኛ ሳምንት ....................................................................................182

ሀያ ስድስተኛ ሳምንት ....................................................................................189

**አውድ ስድስት ....................................................................................195**

**ጊዜ....................................................................................195**

መግቢያ....................................................................................195

ሀያ ሰባተኛ ሳምንት ....................................................................................197

ሀያ ስምንተኛ ሳምንት....................................................................................203

ሀያ ዘጠነኛ ሳምንት . ....................................................................................209

ሰላሳኛ ሳምንት ....................................................................................215

ሰላሳ አንደኛ ሳምንት. ....................................................................................222

ሰላሳ ሁለተኛ ሳምንት....................................................................................229

# ክፍል አንድ

# አጠቃላይ መረጃ

## 1.1 መግቢያ

የቀዳማይ ልጅነት ጊዜ የሰው ልጅ የዕድገት መሰረት የሚጣልበት ወሳኝ ወቅት ነው፡፡ የሰው ልጅ የህይወት ዘመን ስኬት የሚጀመረው በዚህ ጊዜ ነው፡፡ የዘርፉ ምሁራን እድሜያቸው ከ4 እስከ 6 ዓመት ክልል ውስጥ ለሚገኙ ህፃናት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጠት አጠቃላይ እድገታቸውን ለማጎልበት አስፈላጊ መሆኑን ይስማማሉ፡፡ በኢትዮጵያ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ለረጅም ጊዜ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን ዘመናዊው የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ከመምጣቱ በፊትም በአብነት እና ቁርዓን ትምህርት ቤቶች አማካይነት ህፃናት መሰረታዊ የንባብና የህይወት ክህሎቶችን እንዲማሩ ይደረግ እንደነበር ድርሳናት ይነግሩናል፡፡ በሀገራችን ዘመናዊ ትምህርት ከመጀመሩ (ከ1908 ዓ.ም) በፊት ለኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ሥራ የመጡ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ዜጎች ህጻናትን የሚያገለግል የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት በድሬዳዋ ከተማ ይሰጥ እንደነበረም ታርክ ያሳያል፡፡ በ1960ዎቹም ከአውሮፓ የተቀዱ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት በሀገራችን እንዲተገበሩ የተደረገ ሲሆን ህፃናት የትምህርት እድል እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተደራሽነት፣ ተገቢነትና ጥራት ጉዳይ ፈተና ሆኖ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን ችግር ለመፍታት በርካታ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ ከእነዚህ እርምጃዎች መካከል ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የኦ-ክፍል (የአንድ ዓመት መርሃ ግብር )፣ የህፃን ለህፃን ትምህርት፣ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የተፋጠነ የትምህርት ቤት ዝግጁነት እና የሶስት ዓመት መደበኛ የህፃናት ትምህርት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

የትምህርትና ስልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት ግኝትም የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የአጠቃላይ ትምህርት አካል አለመሆኑን፣ ለግልና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት የተተወ መሆኑን፣ መደበኛ ትምህርት ራሱን ችሎ ሳይሆን እንደ ተጨማሪ መርሃ-ግብር መታየቱን፣ በየደረጃው በባለድርሻ አካላት በቂ ትኩረት አለማግኘቱን እና ራሱን የቻለ አስተዳደር የሌለው መሆኑን አመላክቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ፕሮግራሙ ከአንደኛ ደረጃ ጋር ያለው ትስስር በግልጽ አለመቀመጡ የተጠያቂነት ችግር ማስከተሉን፣ ሥርዓተ ትምህርቱ አምዳዊና የጎንዮሽ ትስስሩ በሚገባ የጠበቀ አለመሆኑን፣ በህጻናቱ ሁለተናዊ ዕድገት ላይ ትኩረት ያላደረገ መሆኑን እና ሥርዓተ ትምህርቱ የተቀናጀ ሳይሆን

በአብዛኛው ለተወሰኑ የመማር ይዘቶች ማለትም ቁጥርና ቋንቋ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን ጥናቱ በግልጽ አሳይቷል፡፡

ሌላው የመማሪያ ማስተማሪያ ቁሳቁሶችና ተግባራት የህጻናትን የዕድገት ደረጃ እና ባህል ያገናዘቡ አለመሆናቸው፣ በዘርፉ በቂ የሰለጠኑ መምህራን አለመኖራቸው፣ መምህራን በቂ የሆነ ስልጠና አለማግኘታቸው፣ መምህራን በሚያስተምሩበት ቋንቋ ቅድመ ስልጠናው አለመሰጠቱ እንዲሁም መምህራን የሚያገኙት ደመወዝ አነስተኛ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ ፍልሰት መታየቱ ተግዳሮት መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል፡፡

አዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ግብረ-ገብን፣ ሀገር በቀል ዕውቀቶችንና የ21ኛ ክፍለ ዘመን ክህሎቶችንና ሀገራዊ ጉዳዮችን የፕሮግራሙ አካል በማድረግ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ህጻናት የሙያ እና የቴክኖሎጂ ትምህርት እንዲተዋወቁ ይጋብዛል፡፡ ፖሊሲው የፈጠራ ሥራዎች እንዲበረታቱ፣ ቅንጅታዊ ውህደትና ጨዋታ-መር የማስተማርያ ዘዴ እንዲኖር፣ የመማር ውጤቶች ብቃት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ይደነግጋል፡፡ በ2015 ዓ.ም በተከለሰው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ እድሜያቸው ከ5 እስከ 6 ዓመት ለሆናቸው ሕጻናት የ2 ዓመት ትምህርት የነጻና የግዴታ እንዲሆን እና እድሜያቸው 4 ዓመት የሞላቸው ህጻናት ደግሞ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርትን በሌሎች አማራጮች እንደሚማሩ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ እድሜያቸው 4 ዓመት ለሆኑ ሕፃናት አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ የሥርዓተ-ትምህርት ሰነዶች ባለመኖራቸው ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የ3 ዓመት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ከፍተኛ ፍላጎትና ጥያቄ ቀርበዋል፡፡ ከዚህ መነሻ የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመከተል የ4 ዓመት ህፃናትን ያካተተ የ3 ዓመት መርሀ-ግብር መርሀ-ትምህርት ተዘጋጅቷል፡፡ ይህንን መርሀ-ትምህርት መሰረት በማድረግ የ4 ዓመት ህፃናትን ታሳቢ ያደረገ፣ ተግባር-ተኮር/ህጻን-ተኮር እና ጨዋታ ላይ የተመሰረተ፣ ስድስቱን የእድገትና የመማር መስኮችን በአውድ ያቀናጀ፣ ሀገር በቀል እውቀቶችን ያካተተ፣ ንቁ ተሳትፎን የሚያበረታቱ የማስተማርያ ዘዴዎችን እና ህፃን-ተኮር የምዘና ስልቶችን ያካተተ የተቀናጀ የመምህር መምሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

ህጻናት እጅግ የተለያዩ የትምህርትና የዕድገት ፍላጎቶች ያሏቸው በመሆናቸው ለዚህ ደረጃ የተቀመጡ የመማርና የዕድገት ውጤቶችን ታሳቢ ያደረገ ትምህርት ያስፈልጋል፡፡ ይህ የመምህር መምሪያም ዕድሜያቸው 4 ዓመት (ከ3 ዓመት ከ9 ወር እስከ 4 ዓመት ከ8 ወር) ለሆናቸው ህጻናት የተዘጋጅ ስሆን ስያሜውም የተቀናጀ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ደረጃ አንድ የመምህር መምሪያ ይባላል፡፡

## 1.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነትና አስፈላጊነት

### 1.2.1. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ዕድሜያቸው ከ4 እስከ 6 ዓመት ለሚሆናቸው ህጻናት የሚደረግ እንክብካቤንና የሚሰጡ መሰረታዊ እውቀትና ክህሎቶችን ያካተተ የትምህርት እርከን ነው፡፡ መርሀ-ግብሩ ጨዋታ ተኮር በሆነ የአቀራረብ ዘዴ የህፃናቱን ሁለተናዊ እድገት (አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜት፣ ስነ-ምግባር) በማጎልበት የተሟላ የስብዕና እድገት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህፃናት የህይወት ዘመን ውጤታማነት የሚጀምርበት እና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ የሚሆኑበት ወሳኝ ምዕራፍ ነው፡፡

### 1.2.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት አስፈላጊነት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም የትምህርት እርከን መሰረት ነው፡፡ የዚህ እርከን ትምህርት የሚያስፈልግበት ዋነኛ ምክንያት የህፃናትን ሁለንተናዊ (አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ማህበረ-ስሜታዊ፣ የቋንቋና ሞራላዊ) ዕድገት ማረጋገጥ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ በተጨማሪ ህጻናት ዛሬን መኖርና ዓለም የራሳቸው እንደሆነች መገንዘብ መቻል አለባቸው፡፡ ይህ ማለት ህጻናት አስፈላጊ እንክብካቤና ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው ማለት ነው፡፡ ነገ የተሻለና የበለጸገ ማህበረሰብ እንዲኖር ከተፈለገም ዛሬ ለህጻናት የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤና ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ጥራት ያለው የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ሌላይኛውአስፈላጊነት ህጻናትን ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

## 1.3 የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሆዎች

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሕጻናት ዘላቂ ትምህርትና እድገት መሠረት የሚጣልበት ደረጃ ነው፡፡ መርሃ- ግብሩ ጥራት ያለውና ተደራሽነትን ያረጋገጠ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ጥሩ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚከተሉት ቁልፍ መርሆዎች ይኖሩታል፡፡ ህጻናትን በተገቢው ለመንከባከብና ለማስተማር እነዚህን መርሆዎች ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

### 1.3.1 ሕጻናት-ተኮር አቀራረብ

የሕጻናት ፍላጎትና ችሎታ ሊያሟሉ የሚችሉ ተግባራትን ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ ለህጻናት አካባቢያቸውን በማሰስ እንዲሁም በመሞከርና ንቁ ተሳታፊ በመሆን ተግባራትን በግል፣ በጥንድና በቡድን በማከናወን የሚማሩበትን ዕድል መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህም የፈጠራ ችሎታቸውንና የመማር ፍላጎታቸውን ለማሳደግ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

### 1.3.2. ጨዋታ-ተኮር ትምህርት

ጨዋታ የሕጻናት ቋንቋ ነው፡፡ ህጻናት ካልተጫወቱ በተገቢ ሁኔታ መማርና ማደግ አይችሉም፡፡ በመሆኑም አእምሯዊና ማህበራዊ እድገታቸውን ለማዳበር ያለውን ሚና በመረዳት ነጻ፣ መምህር መርና የተደራጁ/ የተዋቀሩ ጨዋታዋችን በመጠቀም የሕጻትን የመማር ፍላጎት ሊያሳካ በሚችል መልኩ መተግበር ያስፈልጋል፡፡

### 1.3.3. የተቀናጀ ሥርዓተ-ትምህርት

ለቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተመረጡ ሰድስት (6) የእድገትና የመማር መስኮችን (ቋንቋና ተግባቦት፣ መሠረታዊ ሂሳብ፣ አካባቢ ሳይንስ፣ ማህበረ-ስሜታዊ ዕድገት፣ ጤናና የአካል መዳበር እና ስነ-ጥበባት) ተቀናጅተው በቀረቡበት አውድ ከነባራዊ የሕይወት ልምድና ተሞክሮ ጋር በማዛመድ የሚማሩበትን እድል መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

### 1.3.4. አካቶ ትምህርት

ሁሉም ሕጻናት ያለምንም ልዩነት ጥራት ያለው የቅድመ-አንደኛ ትምህርት በእኩል ደረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥና ብዝሃነት (ከባህል፣ ከቋንቋ፣ ግለሰባዊ ልዩነትና ወዘተ.) በክፍልና ከክፍል ውጪ እንደሚኖር በመረዳት ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 1.3.5. ሀገር በቀል እውቀት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ እና ከራስ ወደ ቤት/አከባቢ የሚዘጋጅና የሚቀርብ ሂደትን ይከተላል፡፡ የሚቀርቡ ይዘቶች ህፃናቱ በአከባቢያቸው በሚያውቁት እና ቅርብ በሆኑ ቅድመ እውቀቶች ላይ በመመስረት የተቀመጠውን ብቃት መላበስ እንድችሉ መደረግ አለበት፡፡

### 1.3.6. ከእድገታቸው ጋር ተስማሚ የሆኑ ተግባራት

ከሕጻናት የእድሜና የእድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣሙ ተግባራትን በማዘጋጀት ሁለንተናዊ እድገታቸውን ማለትም አእምሯዊ፣ ስሜታዊ፣ ማህበራዊና አካላዊ እድገታቸውን ሊያዳብሩ በሚችሉ ተግባራት ላይ ትኩረት ማድረግ፡፡

### 1.3.7 የወላጆች/አሳዳጊዎችና ማህበረሰብ ተሳትፎ

ወላጆች የህጻናት የመጀመሪያዎቹ የህይወት መምህራን በመሆናቸው የዚህ ደረጃ ትምህርት ያለእነርሱ ንቁ ተሳትፎ ዋጋ አይኖረውም፡፡ ስለዚህ በመማር ማስተማር ሂደት ወላጆች/አሳዲጊዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታትና ከማህበረሰቡ ጋር የሕጻናቱን ትምህርትና እድገት ለመደገፍ የሚያስችል ጤናማ ግንኙነትን ከማህበረሰቡ ጋር መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

### 1.3.8. ጤናማና ምቹ የትምህርት አከባቢ

ለሕጻናት ምቹ፣ ንጹህና ጤናማ የመማር አካባቢ እንዲኖር በማድረግ ደህንነትና ምቾት እንዲሰማቸው የሚያስችል የትምህርት አከባቢ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ የክፍል ውስጥ አደረጃጀቱ ጣሪያ፣ ግድግዳዎቹና ወለሉ በመማሪያ መጫወቻ ቁሳቁሶች የበለጸጉ መሆን አለባቸው፡፡ የክፍል ውጭ አደረጃጀትም ለህጻናት አስፈላጊ ሁሉ ሁኔታዎች የተሟሉበት መሆን ያስፈልጋል፡፡

### 1.3.9. ሁለንተናዊና ቀጣይነት ያለው እድገት

የልጆች ሁለንተናዊ እድገትና ትምህርት የሚጀምረው ከማህፀን ውስጥ ጀምሮ ሲሆን ይህም በሕይወት ዘመናቸውም ቀጣይነት ያለው መሆኑን በመረዳት የልዩ ፍላጎትን ጨምሮ በቀዳማይ የልጅነት ጊዜ ጥሩ የስሜት ማነቃቂያና የቅድመ እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 1.3.10. የተመጣጠነ አቀራረብ

በእውቀት፣ በአመለካከት እና በችሎታ እንዲሁም በንድፈ ሀሳብ እና በተግባር መካከል የተመጣጠነ አቀራረብ መከተል እና በተጨማሪም የክፍል ውስጥና የክፍል ውጭ ተግባራትን ለሕጻናቱ መማር በሚጠቀም መልኩ አመጣጥኖ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

### 1.3.11. የህፃናት ተከታታይ ምዘና

የሕጻናትን ሁለንተናዊ እድገታቸውንና የመማር ሂደትን በምልከታና መደበኛ ባልሆነ የምዘና ስልት በመጠቀም መከታተል፣ እንደማህደረ-ተግባር፣ የመከታተያ ቅጾችና የመሳሰሉትን በመጠቀም ለውጣቸውን መመዝገብ፣ ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለው-ግብረ-መልስ መስጠት የሚያስችል የግንኙነት ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

## 1.4 የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ሥርዓት-ትምህርት አጠቃላይ ዳሰሳ

አዲሱ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት በ3 የትምህርት ደረጃዎች የተዋቀረ ነው፡ ፡ ደረጃ አንድ እድሜያቸው 3 ዓመት ከ9 ወር እስከ 4 ዓመት ከ8 ወር ለሆናቸው ህጻናት የተዘጋጀ ሲሆን ይህም ለቀጣይ የልጆች እድገትና የመማር ደረጃዎች መሠረት ሆኖ ያገለግላል:: በዚህ ደረጃ "ስለ እኔ"፣ "ቤቴ እና ቤተሰቦቼ"፣ "ጎረቤቶቼ እና ትምህርት ቤቴ"፣ "ቀለማት"፣ "ንደኝነት" እና "ጊዜ" የሚሉ የትምህርት አውዶች ተካተዋል:: ደረጃ 2 ዕድሜያቸው ከ4 ዓመት ከ9 ወር እስከ 5 ዓመት ከ8 ወር ላሉ ሕፃናት የተዘጋጀ ሲሆን "ማኅበረሰብ"፣ "እንስሳት"፣ "ሥራ"፣ "ውኃ"፣ "ጠፈር" እና "ወቅቶች" በሚባሉ ስድስት የትምህርት አውዶች የተዘጋጀ ነው:: ደረጃ 3 ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት ከ9 ወር እስከ 6 ዓመት ከ8 ወር ለሆናቸው ህጻናትን የተዘጋጀ ሲሆን በዚህ ደረጃ "ተክሎች"፣ "ቴክኖሎጂ"፣ "ባህል"፣ "ትራንስፖርት"፣ "ግብርና" እና "ሰላም" የሚባሉ ስድስት አውዶች ተካተዋል::

## 1.5 የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ-ትምህርት

መርሀ-ትምህርት በአንድ የትምህርት ዓይነት ወይም መርሃ-ግብር የሚሰጡ ይዘቶችን፣ ዓላማዎችንና የማስተማር ዘዴዎችን ያካተተ ዝርዝር የይዘት ሠንጠረዥ የያዘ ሰነድ ነው:: በዚህ መሠረት በዚህ ደረጃ የተዘጋጀው የቅድመ-አንደኛ ደረጃ መርሃ-ትምህርት ለየደረጃው የተለዩ ስድስት አውዶች፣

ስድስት የትምህርት መስኮችን፣ በየአውዱ መጨረሻ ከህፃናት የሚጠበቁ ውጤቶች፣ በሳምንት የተለዩ የትምህርት ይዘቶች፣ ሳምንታዊ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፣ የተቀናጁ ተግባራት፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የመማሪያና መጫወቻ ቁሳቁሶችና በመጨረሻም የምዘና ስልቶች በዝርዝር የቀረቡበት ሀገራዊ ሰነድ ነው፡፡ ሰነዱም የመምህር መምሪያና የህፃናት መለማመጃ ደብተር ለማዘጋጀት መሠረትና መሪ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡

## 1.6. የዕድገትና መማር መስኮች

ለቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተቀናጅተው የሚሰጡ ስድስት የእድገትና የመማር መስኮች ተለይተዋል፡፡ እነዚህ መስኮች የሕጻናትን ሁለንተናዊ እድገት ለማበልጸግ የሚያስችሉ ሲሆን እንደእድሜ ደረጃቸው ህጻናት አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ የቋንቋ፣ ግብረ-ገባዊ እና ስነ-ጥበባዊ ክህሎታቸውን ለማዳበር በማቀናጀት እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡ እነዚህ የዕድገትና የመማር መስኮችን እንደሚከተለው ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

### 1.6.1. የቋንቋ መዳበርና ተግባቦት

ህጻናት ቋንቋን በመጠቀም ተሞክሮዎቻቸውንና ስሜቶቻቸውን መግለጽ እንዲሁም እርስ በርስ መግባባት ይችላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ህጻናት በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍም የማዳመጥ፣ የመናገር እና የቅድመ ንባብ ክህሎቶቻቸውን ያዳብራሉ፡፡ ስለሆነም ይህ የዕድገትና የመማር መስክ በዋናነት የሚያተኩረው ማዳመጥና መናገር፣ ፊደላትን ማወቅ፣ የመጽሐፍ እውቀት፣ የህትመት ግንዛቤ፣ ድምጾችን መለየትና የተግባቦት ሥርዓት የሚሉት ላይ ነው፡፡

### 1.6.2. የቅድመ-ሂሳብ መዳበር

ህጻናት በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ የሂሳብ ፅንሰ ሐሳቦችን ይማራሉ፤ የሂሳብ ሀሳቦችን እና ሂደቶችን ይመረምራሉ፡፡ አካላዊና ማህበራዊ አካባቢያቸውን በመመርመር ከቀዳሚ ልምዶቻቸው አዲስ ዕውቀትን በንቃት ይገነባሉ፡፡ ስለዚህ ይህ የመማር መስክ ቁጥሮችን በመቁጠር፣ በመጻፍ፣ በማወዳደር፣ በቅደም ተከተል በመደርደርና በመመደብ እንዲሁም በመለካት፣ ቀላል የማመዛዘን (ጊዜን፣ ገንዘብንና ቅርጾችን) ችሎታዎችን እና ቀላል የሂሳብ ስሌቶችን (መደመርና መቀነስ) ያሉ ክህሎትን ማዳበር ላይ ያተኩራል፡፡

### 1.6.3. አካባቢ ሳይንስ

ህጻናት በዚህ የዕድገትና የመማር መስክ ስለአምስቱ የስሜት ሕዋሶቻቸውና ስለሰውነት ክፍሎቻቸው መማርና ግንዛቤ ማዳበር ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ህፃናት ስለተክሎች፣ እንስሳትና በአካባቢያቸው ስለሚሆኑ ቀላል ክስተቶች በዕይታና በቀላል እንቅስቃሴዎች በመማር አዎንታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩና በዕለት ተዕለት ህይወታቸው የቴክኖሎጂን አስፈላጊነት ለመማር እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ስለዚህ ይህ የዕድገትና መማር መስክ በሰው አካል ክፍሎች፣ በአካባቢያቸው በሚገኙ እንስሳት፣ እጽዋት፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ክስተቶች፣ ራስንና አካባቢን በመንከባከብ፣ በጥንቃቄና ደህንነት ጉዳዮች፣ ቀላል ቴክኖሎጂን በማስገንዘብ ማህበራዊ ግንኙነቶች በመረዳት ዙሪያ ያተኩራል ፡፡

### 1.6.4. የግልና ማህበረ-ስሜታዊ መዳበር

በዚህ የዕድገትና የመማር መስክ ህጻናት ራስን በመገንዘብ የራስን ማንነት መገንባት፣ ራሳቸው ለመቻል ጥረት ማድረግ እና ስሜቶቻቸውን መቆጣጠር የሚጀምሩ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ከሌሎች ጋር ውጤታማ በሆነ መንገድ መግባባትን፣ ሌሎችን ማክበርና መንከባከብን ይማራሉ:: ስለዚህ ይህ የዕድገትና የመማር መስክ የራስ ግንዛቤ፣ የግል ነፃነት፣ የማህበራዊ ግንዛቤ፣ የሞራል እሴቶችን መገንዘብ፣ የተግባቦት ችሎታ፣ ለደንብ መገዛት፣ ውሳኔ የመስጠት ክህሎትና የሀገር ፍቅር ስሜት ለማዳበር የሚረዱ ዕውቀትና ክህሎቶች እንደ የደረጃቸውና እድሜያቸው ተካተው ቀርበዋል::

### 1.6.5. አካላዊ መዳበርና ጤና

ህጻናት ጥሩ ልማዶችን በማዳበር ንቁና ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ማዳበር እንዲሁም መሠረታዊ የጤናና የደህንነት ጉዳዮችን በመረዳት ራሳቸውን መጠበቅን ይማራሉ:: በተጨማሪም ስለስሜቶቻቸውና አካባቢያቸውን ለመመርመር የስሜት ህዋሳቶቻውን የመጠቀም ችሎታን ያዳብራሉ:: ይህ የዕድገትና የመማር መስክ በጤና፣ በአመጋገብ፣ በአካላዊ ቅልጥፍና እድገት፣በቦታ ግንዛቤ፣ በአካል ብቃት እና በአካላዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኩራል::

### 1.6.6. የክወናና የእይታ ጥበባት

ይህ የዕድገትና የመማር መስክ ህጻናት የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና አከባቢያቸውን እንዲመረምሩና እንዲከታተሉ ይረዳቸዋል:: በተጨማሪም ህጻናት በዚህ ደረጃ የተለያዩ የኪነ-ጥበባት፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የሙዚቃ፣ የታሪክ፣ ተረት እና እንቅስቃሴን በመጠቀም ሀሳባቸውንና ስሜታቸውን ለመግለጽ የፈጠራ ችሎታቸውን ይጠቀማሉ፤ እንዲሁም የሥነ-ጥበብ ተሞክሮዎችንና ሰብዓዊ እሴቶችን ያደንቃሉ:: ስለሆነም ይህ የዕድገትና መማር መስክ በኪነ-ጥበባዊ ግንዛቤ፣ በፈጠራ አገላለጽ፣ በባህላዊ ቅርስ፣ ውበትን ማድነቅና ተገቢውን ዋጋ መስጠት ላይ ያተኩራል::

## 1.7 የዕድገትና የመማር ብቃቶች

የእድገትና የመማር ብቃቶች በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንደሚያመላክተው ልጆች በሶስቱም ደረጃዎች በእድገትና የመማር ተግባራት ላይ ማግኘት የሚገባቸውን ተፈላጊ እውቀትን፣ አመለካከትን እና ክህሎቶችን ያመላክታል:: እንደየደረጃውና አውዱ በዋና ዋና የብቃት ዘርፎች ሊደራጁ ይገባል:: ስኬታማነት፣ ጥልቅ አሳቢነትና ችግር ፈቺነት፣ተግባቦት፣ የመማር ቀጣይነትና የምዘና መሳሪያነት የአጥጋቢ የመማር ብቃቶች መሰረታዊ ባህሪያት ናቸው:: በተጨማሪም በዚህ የትምህርት ደረጃ ህጻናት መሠረታዊ የግል ክህሎቶች፣ የመማር ዝግጁነት፣ ችግር የመፍታት ክህሎት፣ በጥልቀት ማሰብና መመራመር፤ ተግባቦት፣ የፈጠራ ክህሎት፣ ትብብርን፣ በጋራ የመማርና የመስራት ክሂል፤ አመራርና ውሳኔ ሰጭነት፣ መሠረታዊ የዲጂታል ዕውቀትና ክህሎት፣ የአመራር እና ውሳኔ አሰጣጥ፣ ባህላዊ ማንነትና ዓለም አቀፋዊ ዜግነት ብቃቶችን ያዳብራሉ::

## 1.8. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህጻናት የባህርይ ገጽታ

የህጻናት የባህርይ ገጽታ የሶስቱም ዓመታት ቆይታ ውጤት ነው፡፡ ይህም ህጻናት ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ መሆናቸውን የሚለኩበት መነጽር ነው፡፡ በእያንዳንዱ ደረጃ ህጻናት የሚጠበቅባቸውን ብቃትና የዕድገትና የትምህርት ውጤት በማሟላት የራሳቸውን የባህርይ ገጽታ ይገነባሉ ተብለው ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም ይህ ፫ ዓመት ቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ሲጠናቀቅ ህፃናት፡-

- የቅድመ ስሌት፣ የቅድመ ንባብና ጽህፈት ክህሎቶችን ማዳበር፣
- መሰረታዊ የቴክኖሎጂ ክህሎቶችን መጠቀም፣
- ከተፈጥሮ እና ከማህበረ-ኢኮኖሚ አከባቢዎች ጋር ጤናማ መስተጋብር መፍጠር፣
- የአከባቢያቸውን ባህላዊ ልምዶችን መገንዘብ፣ ማድነቅ እና መስተጋብር መፍጠር፣
- ከሌሎች ጋር ለመገናኘትና ለመተባበር የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ክህሎትን መጠቀም፣
- መሰረታዊ የሥነ-ምግባር መገለጫዎችን ማለትም ታዛዥነት፣ ታማኝነት (ሀቀኝነት፣ መልካምነት፣ እውነተኝነት)፣ እራሳቸውንና ሌሎችን መንከባከብና አክብሮትን ማሳደግ፣
- ሀሳቦችንና ስሜቶችን በኪነጥበብ፣ በሙዚቃ እና በእንቅስቃሴ መግለፅ፣
- የግል ንጽህና ደህንነት እና የአከባቢ ጽዳት ለመጠበቅ መሰረታዊ የጤና ህግጋትን ማወቅ፣
- በዝቅተኛ ደረጃ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ማከናወን፣
- የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለመማር አስፈላጊ የሆኑ ዕውቀትንና ክህሎትን መጠቀም፡፡

## 1.9. ሀገር በቀል (አካባቢያዊ) እውቀትን መሠረት ያደረገ ትምህርት

የሀገር በቀል ዕውቀት እንደየአውዱና ደረጃው የተመጠኑ ባህላዊ ዕውቀቶች፣ ክህሎቶች፣ አመለካከቶች፣ ልምዶች እና እሴቶች ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው የሚተላለፉ ናቸው፡፡ ይህ እንደ ተረት፣ ባህላዊ ዘፈኖች፣ እንቆቅልሾች፣ የቃል ጨዋታዎች፣ እሴቶች፣ ደንቦች፣ ቁሳዊ ባህሎችና ስለተፈጥሮአዊ አካባቢዎች ዕውቀትን ጨምሮ የአገር በቀል የጨዋታ ልምዶችን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ የተዘረዘሩት ሀገር በቀል እውቀቶች በአምስት ሰፋፊ ምድቦች (በቃል የሚተላለፍ የሀገር በቀል ዕውቀት፣ በባህላዊ ልምዶች የሚተላለፍ የሀገር በቀል ዕውቀት፣ ቁሳዊ ባህል፣ የህዝብ ጥበባትና ሙዚቃ እና የአኗኗር ዘይቤ ወይም ትውፊት) ይመደባሉ፡፡ እነዚህ ዕውቀቶች ለህጻናት ተመጥነው ከቀረቡ የሚኖራቸው ዋና ዋና ጥቅሞች የሚከተሉትን ይጠቀሳሉ:-

- የሀገር በቀል እውቀት ወጪ ቆጣቢ የመማር ዘዴዎችን ያረጋግጣል፤
- እውቀትን ተደራሽ፣ ተገቢና ውጤታማ ያደርጋል፤
- የልጆችን ማህበራዊና ተፈጥሯዊ አካባቢን በተመለከተ ያላቸውን እውቀት ያሻሽላል፤

- ሕጻናትን ስለ ወይመረ ብዝሀነት አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ይረዳል፤
- በአካባቢው ተቀባይነትን ያገኙአዎንታዊ እሴቶችን እንዲያከብሩ ያደርጋል፡፡
- ስለሆነም ከላይ የተገለጹትን የተለያዩ የሀገር በቀል ዕውቀት ዓይነቶችን በመጠቀም ተቀናጅተው የቀረቡ የትምህርት መስኮችን በማስተማሪያ ዘዴነት መገልገል ከመምህራን ይጠበቃል፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን አቀራረቦች ማየት ይቻላል፡፡
- ከወላጆቻቸው ያዩዋቸውን ባህላዊ ጥበቦችንና እደ-ጥበባት ሥራዎችን እንዲሠሩ በማበረታታት፤
- በባህላቸው የሚገኙትንና በንድፍ የተዘጋጁ የእደ-ጥበብ ውጤቶች እንዲያቀርቡ በማድረግ፤
- በአካባቢው በሚከበሩ በዓላት ወቅት የሠሯቸውን በስጦታ መልክ እንዲሰጣጡ በማመቻቸት መከባበርን እንዲማሩ በማድረግ፤
- በአካባቢው ያሉ ታሪኮችን፣ አፈ-ታሪኮችን መምህራን፣ ወላጆች፣ የአካባቢው አርቲስቶች፣ ሽማግሌዎች እንዲነግሩዋቸው በማድረግ፤
- የአካባቢውን መዝሙሮች እንዲዘምሩ በማድረግና፣ቀላል የሆኑ የአካባቢ የሙዚቃ መሳሪያዎችን (ለምሳሌ ከበሮ) እንዲጫወቱ በማድረግ፤
- በአከባቢያው የሚዘወተሩ ልዩ ልዩ ውድድሮችን በጋራ እንዲጫወቱ በማድረግ መምህራን የህፃናቱን ትምህርት ተጨባጭ በማድረግ ማቅረብ ሳቢ እንደሚያደርገውና የክፍል ውስጥና ውጭ ተግባራትን አመጣጥነው ለማስተማር የሚኖረውን ፋይዳ በመረዳት እንደሚጠቀሙት ይጠበቃል፡፡

## 1.10. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውህደት (PPE Integration)

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውህደት የተለያዩ ይዘቶችን አንድ ላይ በማቀናጀት የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት የሚደግፍ የተቀናጀ አቀራረብ ነው፡፡ ውህደት የህጻናትን አዕምሯዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ እድገትን ጨምሮ የትምህርት ቤት ዝግጁነትን እውን የሚያደርግ ተመራጭ ሂደት ነው፡፡ በውህደት የማስተማር ሂደት የትምህርት ይዘቶች በተግባራት ውስጥ ተቀናጅተውና በአቀራረብ ዘዴዎች፣ ግብዓቶችና ምዘናዎች ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥተው ይቀርባሉ፡፡ ይህም ህጻናት በመዳሰስ፣ በመሞከር፣ በማብራራት እና በተግባር ልምምዶችን በአንድ ተግባር ውስጥ ልዩ ልዩ እውቀት፣ክህሎትና ልምድ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

የተቀናጀ አቀራረብ ለህፃናት ሰፊ ክህሎቶችን እና ችሎታን እንዲያዳብሩ ከመርዳት ባሻገር የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ ግብር ብዝሃነትን እንዲያስተናግድ ይረዳል፡፡ ህጻናት ይዘቶቹ ተቀናጅተው በሚማሩበት ጊዜ የችግር መፍታት፣ ፈጠራ እና ወሳኝ የማሰብ ችሎታን በቀላሉ ያዳብራሉ፡፡ የተቀናጀ የትምህርት አቀራረብ ህጻናት በልዩ ልዩ ተግባራት ውስጥ እንዲሳተፉ፣ እንዲመራመሩ፣ ሀሳብ

እንዲገልጹ፣ እንዲያብራሩና እንዲገመግሙ ማድረግን ይጠይቃል።

- የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚቀርብባቸው ሁለት የውህደት ዘዴዎች አሉ። እነሱም በአውድ ላይ የተመሠረተ ውህደት (Theme-based Integration) እና ሁለገብ ውሂደት (Interdisciplinary Integration for Standalone Competencies) በመባል ይታወቃሉ። የእኛ ሀገር የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ ግብር የሚከተለው በዓለም ላይ ብዙ ሀገራት የሚተገብሩትን በአውድ ላይ የተመሰረተ ውህደት ነው፡
- ይህ የውህደት ዓይነት መሰረት የሚያደርገው የተለያዩ የእድገትና የትምህርት መስኮችን በአንድ አቀናጅተው ማቅረብን ነው። አውድ በተለያዩ ብቃቶች ላይ የተመሰረቱ ይዘቶችን አቀናጅተው ለማቀፍ ያገለግላል። ለአብነት፣ 'ሁሉም ስለ እኔ' የሚለው አውድ ለዚህ ደረጃ ቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ከቀረቡ አውዶች አንዱ ነው። መምህራን ይህንን አውድ እንደ አቃፊ በመጠቀም የተቀናጁ ይዘቶችን እንዲያስተምሩ ይጠበቃል። ሳምንታዊ ብቃቶችን ለመተግበር እንደ ተረት፣ መዝሙር፣ እንቆቅልሽ፣ ጨዋታ፣ ጉብኝት፣ ሥራ፣ ውይይት፣ ፕሮጀክት እና የመሳሰሉት ዘዴዎች ይዘቶችን አቀናጅተው ለማቅረብ ሊጠቀሙ ይችላሉ።
- ለአብነት፦
- በአንድ መዝሙር፣ ተረት፣ ጨዋታ ወይም ሌላ ተግባር ውስጥ ሶስትና ከዚያ በላይ (ቋንቋና ተግባቦት፣ ቅድመ ሂሳብ፣ አከባቢን መገንዘብና ሌሎች) ይዘቶችን በማቀናጀት ህጻናት እየተጫወቱ እንደሆነ ብቻ እየተሰማቸው እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል።

## 1.11 የህጻናት ንቁ ተሳትፎ በትምህርት

በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህጻናት ንቁ ተሳትፎ የህጻናትን የመማር ፍላጎትና ጉጉት ደረጃን የሚያመላክት ስሆን የትምህርት አቀባበላቸውንና ዕድገታቸውን ለማፋጠን ይረዳል። የህጻናት ንቁ የትምህርት ተሳትፎ ለተሻለ አዕምሯዊ፣ አካላዊ፣ ቋንቋ፣ ሞራላዊ፣ ማህበራዊና ስሜት ዕድገት ወሳኝ ነው። ተሳትፏቸውን ከፍ ከሚያደርጉ ዘዴዎች ወሳኝ የሚባሉት ተግባር-ተኮር ትምህርት መስጠት፣ በጨዋታ ማስተማር፣ ጤናማ ማህበራዊ ግንኙነት መፍጠር፣ ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን መረዳት፣ አርአያ መሆንና ምቹና ሳቢ የመማሪያ አከባቢን መፍጠር ናቸው።

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ዋና ዋና ዓላማዎች የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ማረጋገጥ፣ ህጻናት ዛሬን መኖር እንዲችሉ ማድረግና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማዘጋጀት ናቸው። እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት የህጻናትና የመምህራን ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ ነው። በጨዋታ መማር ዓላማዎቹን ለማሳካት ከሚረዱ ዘዴዎች አንዱ ከመሆኑም ባሻገር የህጻናትን አዕምሯዊ ዕድገት (የማወቅ ጉጉት፣ የፈጠራ ችሎታና ችግር የመፍታት ክህሎት መዳበር) ይደግፋል። ይህም ህጻናት ተጨማሪ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ፣ በርካታ ሀሳቦችን እንዲያመነጩ፣ እንዲተነብዩ፣ መላምቶችን እንዲያዳብሩ፣ መረጃን እንዲተረጉሙና ችግሮችን እንዲፈቱ እድሎችን ይፈጥርላቸዋል።

## 1.12. ህጻን-ተኮርና በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ትምህርት

ጨዋታ ለህጻናት ቋንቋ፣ ልማድ፣ መብት፣ አሰራርና ተፈጥሮአዊ ስጦታ ነው። ህጻናት በጨዋታ አማካኝነት አካባቢያቸውን ይፈትሻሉ፤ ይረዳሉ፤ እንዲሁም ይተረጉማሉ። ጨዋታ በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ የህጻናትን ሁለንተናዊ እድገት እውን ለማድረግ ወሳኝ የማስተማርያ ዘዴ ነው። አንዳንዶች ጨዋታ የህጻናትን አካዳሚክ ክህሎቶች ሊያሻሽል እንደማይችል በስህተት በመገንዘብ ከእድገት ጋር ብቻ ያያይዙታል። ህጻናት ለመግባባት፣ ለመተርጎም፣ ትርጉም ያላቸውን ፅንሰ-ሀሳቦች ለመፍጠር፣ መረጃን ለማደራጀት፣ አዳዲስ ሀሳቦችን ለመገንባትና ለማስተናገድ የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ።

በጨዋታ ጊዜ የህጻናት እና የመምህራን ንቁ ተሳታፊ መሆን ውጤታማ መማርንና እድገትን እውን ለማድረግ ወሳኝ ነው። ህጻናት ራሳቸውን የመምራት እና በራሳቸው የመማር ተግበራትን (ነፃ ጨዋታ) የመጀመር እድል ሊኖራቸው ይገባል። መምህራን ደግሞ ህጻናት በራሳቸው ተነሳሽነት በሚጫወቷቸው ጨዋታዎች ውስጥ የመሳተፍ ሚና ይኖራቸዋል። በህጻናት ትምህርት የታቀዱ፣ ነጻና ድንገተኛ ጨዋታዎችንና ተግባራትን ማጣጣም ያስፈልጋል።

በዚህ ደረጃ ሊተገበሩ የሚችሉ የተለያዩ ህጻን-ተኮር ጨዋታዎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አፅምሯዊ ጨዋታዎች (ተግባራዊ ጨዋታ፣ እና የመርህ ጨዋታ) እና ማህበራዊ ጨዋታዎች (እንቅስቃሴ አልባ ጨዋታ፣ ለብቻ ጨዋታ፣ ትይዩ ጨዋታ፣ የቡድን ጨዋታ እና የትብብር ጨዋታ) በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ህጻናትን እያዝናኑ ለማስተማር ወሳኝ ናቸው።

የግል ሙከራዎች፣ የክፍል ውስጥ ጨዋታዎችና ተግባራት (መዝሙር፣ ተረት፣ እንቆቅልሽ፣ ውይይት)፣ ከክፍል ውጭ የሚደረጉ ጨዋታዎች፣ ጉብኝት፣ በፕሮጀክት ላይ የተመሰረቱ ተግበራት፣ በሥራ ላይ የተመሰረተ ትምህርት እና በማህበረሰብ ላይ የተመሰረቱ ተግበራት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ዋና ዋና ህጻን-ተኮር የማስተማሪያ ዘዴዎች ናቸው። በእነዚህ ሁሉ ተግበራት ህጻናት በራሳቸው ችግር እንዲፈቱና ተሳትፎዎቻቸውን እንዲያሳድጉ ተግባራትን እንዲያከውኑ ብቻ ሳይሆን ሀሳብም እንዲሰጡ ይደረጋል።

ህጻን-ተኮርና በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ትምህርት የሚከተሉት ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት ተብለው ይታሰባል።

- **በህጻናት የሚመሩ ተግባራት፡-** ህጻናት የራሳቸውን ተግባራት ሲመሩና ሲወስኑ የተሻለ ትምህርት ያገኛሉ። ስለዚህ መምህራን የሚያቀርቧቸው ተግባራት በህጻናት የሚተገበሩና የሚመሩ መሆን አለባቸው። ይህ አካሄድ የህጻናትን ፍላጎት ለማሟላትና ተግባሮቻቸውን ትርጉም ባለው መንገድ እንዲከታተሉ ለማድረግ ይረዳል።
- **ምርጫ፡-** ምንም እንኳን በተደራጀ ሥርዓተ ትምህርት በአብዛኛው የታቀዱ ተግባራት የሚከናወኑ ቢሆንም የህጻናትን ተሳትፎ ለማሳደግ በጨዋታና በተግባራት ወቅት

ፍላጎታቸውንና ምርጫቸውም ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- **የህጻናት ቋንቋና አስተሳሰብ፦** ህጻናት ሀሳባቸውን በቃልም ሆነ በምልክት ወይም በተግባር ሊገልጹ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ህጻናት ሀሳባቸውንና እይታቸውን በመረጡት ቋንቋና ተግባር መግለጽ እንዲችሉ የሚያግዙ ህጻን ተኮር ጨዋታዎችንና ተግባራትን ይሻሉ፡፡

- **ማስተዋል አና መጠቀም፦** በተግባር ተኮር ዘዴ ስናስተምር የምንጠቀምባቸው የመጫዎቻ ቁሳቁሶች ህጻናት አዳዲስ ሀሳቦችንና ክህሎቶችን እንዲማሩ የሚያግዙ በማስተዋል መጠቀም አለባቸው፡፡

- **መልሰን ልንጠቀማቸው የምንላቸው ቁሳቁሶች፡-** ህጻናት በመነካካት የሚማሩባቸው የመጫወቻ ቁሳቁሶች ያስፈልጓቸዋል፡፡ ቁሳቁሶቹ በአካባቢያቸው የሚገኙ፣ ከህጻናት ባህልና ዕድሜ ጋር የሚጣጣሙ እና መልሰው መጠቀም የሚችሏቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

- **የመምህራን/የወላጆች ድጋፍ፡-** በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመምህራንና የወላጆች ሚና ተግባራትን መምራትን፣ ማበረታታትን፣ ማመቻቸትንና መከታተልን ያካትታል፡፡ ይህንን በምናደርግበት ጊዜ የህጻናትን የማሰብ፣ የመፍጠርና የመመራመር ፍላጎታቸውንና ችሎታቸውን በማይገድብ መልኩ መሆን አለበት፡፡


## 1.13. ህጻናትን ማዕከል ያደረገ ትምህርት ላይ የመምህራን ሚና

ህጻናት አዲስ ነገር የሚማሩት በመፍጠር፣ በመዳሰስ፣ በመሳተፍ፣ በመሞከር፣ በመመራመር እና በማሰላሰል ነው፡፡ በዚህ ሂደት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን ንቁ የመማር አካባቢን ማዘጋጀት፣ መደገፍና መምራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ህጻናት በንቃት እየተሳተፉ እንደሆነ ማረጋገጥ፣ ምን እያደረጉ እንደሆነና እንዴት እየተማሩ እንደሆነ መከታተል እና ህጻናት ለራሳቸው ትምህርት ሀላፊነት እንዲወስዱ መምህራን ህጻናትን በማነሳሳትና አቅም በማሳደግ አጠቃላይ የትምህርት እንቅስቃሴውን መምራት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን ህጻናት ተሳትፎቸውን እንዲያዳብሩ በማድረግ፣ እንቅስቃሴዎቻቸውን በመመልከት፣ ተግባራቸዉን በመመዝገብ እና እንዲያንፀባርቁ በማድረግ ንቁ ተሳታፊ መሆን አለባቸው፡፡

ህጻናት ራሳቸው በመረጡት እና በራሳቸው የሚመሩ የጨዋታ ተግበራትን መመልከት እንዲሁም በነዚህ የጨዋታ ተግበራት ውስጥ መምህራን በንቃት መሳተፍ፣መምራትና ማገዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ መምህራን የመማሪያ አካባቢዎችን ማደራጀት (የተለያዩ ማዕዘናትን ማደራጀት)፤ የዕለት ተዕለት ተግባራትን በቅደም ተከተል ማደራጀት፤ ምቹና ደጋፊ የመማር አከባቢን ማደራጀት ፤ከህፃናት ጋር አዎንታዊ ግንኙነቶችን ማጎልበት፤ የህጻናትን ተሳትፎ እና ጽብረቃን ለማጎልበት አቅዶ መስራት፤ ህጻናት ያላቸውን ልምዶች በተለያዩ የዕለት ተዕለት ተግበራት ለማጠናከር መምህራን አቅደው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 1.14. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ-ግብር የዕለት ተዕለት ተግባራት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት በይዘት የተጨናነቀና በትምህርት ዓይነት የተደራጀ ባለመሆኑ የተለያዩ የዕለት ተዕለት ተግባራትን ያካትታል፡፡ ተግባራቶቹ ህጻን-ተኮር የማስተማር ዘዴን መሰረት ያደረጉ ሆነው በሁሉም ተግባራት ውስጥ የህጻናትና የመምህራን ሚና የጎላ ነው፡፡ ህጻናትን ከመቀበል እስከ መሸኘት ድረስ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት (የቁርስ፣ የመተኛትና የእረፍት ጊዜን ሳያካትት) የሚከተሉት ናቸው፡፡




ህጻናትን መቀበልና መሸኘት የሁል ጊዜ ተግባራት ናቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ቀሪዎቹ የዕለት ተዕለት ተግባራት እንደየአስፍላጊነታቸው በቀን ውስጥ ስድስቱ ብቻ) እየተመረጡ ይቀርባሉ፡፡ የእያንዳንዱ ተግባር ምንነትና ዝርዝር መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1. ህጻናትን መቀበል፡-

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ባህርያት ውስጥ አንዱ የመምህራንና የህጻናት ግንኙነት ነው፡፡ በዚህ ፕሮግራም የታቀፉ ህጻናት በራሳቸው ክፍል መጥተው ቁጭ ብለው የሚማሩ ባለመሆናቸው የወላጅና የመምህራን ቅብብሎሽ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለደህንነታቸው ሲባል ህጻናቱ ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡት በወላጅ ወይም በአሳዳጊ እገዛ ስሆን መምህራን እስከ ት/ቤቱ በር ድረስ ቀርበው ሊቀበሏቸው ይገባል፡፡ ይህ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ለሚያስተምሩ መምህራን ዋነኛና ቀዳሚ ተግባር ተደርገው ይወሰዳል፡፡ የመቀበያ ጊዜ ህጻናት ነጻ ጨዋታዎችን የሚጫወቱበት፣ የባንዲራ ሥነ-ሥርዓት የሚያከብሩበትና ብሔራዊ የህዝብ መዝሙር የሚዘምሩበት እንዲሁም መምህራን የህጻናትን ጤንነትና ስሜት የሚከታተሉበት ነው፡፡

### 2. የመዝሙር ጊዜ፡-

ይህ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተለያዩ ይዘቶች በዜማ ታጅበውና ተቀናጅተው ለህጻናት መንፈሳቸውንና ፍላጎታቸውን መቀስቀስ በሚያስችል መልኩ የሚቀርቡበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ተግባር

ህጻናት በሳምንት ውስጥ የተማሩትን የተቀናጀ ይዘት ሳይረሱ ለረጅም ጊዜ ማስታወስ ይችላሉ፡፡ በዚህ መምሪያ ውስጥ የተዘረዘሩ የሳምንት መዝሙሮች የሚቀርቡት የሚከተሉትን የድርጊት ቅደም ተከተል መሰረት ይሆናል፡፡

- በቅድሚያ የህጻናትን የመዘመር ፍላጎት በማነቃቂያ ጥያቄዎች መቀስቀስ
- በመቀጠል ሁል ጊዜ የዕለቱን መዝሙር ርዕስ ማስተዋወቅ
- አስቀድመው መዝመሩን ዘምረው አሊያም በቴፕ/ፍላሽ/ሞባይል ከፍተው ማሰማት
- ህጻናት ስንኝ በስንኝ ተከትለው እንዲዘምሩ ማበረታታት
- ከህጻናት ጋር አብረው መዘመር ከዚያም ህጻናት ለብቻቸው በጋራ እንዲዘምሩ ማድረግ
- ሁሉም ህጻናት በትክክል መዘመር መቻላቸውን ማረጋገጥ
- በመጨረሻም የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና መንገር ያስፈልጋል፡፡

### 3. የተረት ጊዜ፦

ተረት የፈጠራ ሥራ ሆነው የአንድን ማህበረሰብ አኗኗር፣ ባህል፣ ወግና እሴት ለትውልድ ማሻገር የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ሲማሩ ህጻናት የጊዜ ሂደትን፣ ታሪክን፣ የምክንያትና ውጤት ትስስርን እንዲሁም የተቀናጁ የትምህርት ይዘቶችን በቀላሉ ይገነዘባሉ፤ ያስታውሳሉም፡፡ ተረት በቃል፣ በንባብና በድራማ መልክ መቅረብ የሚችል ሲሆን የራሱ የሆነ ባህላዊ አተራረክ ዘዴ ያለው ነው፡፡ ዘዴው እንደየማህበረሰቡ ባህል የሚለያይ ቢሆንም ለምሳሌ በአማርኛ የሚቀርብ ተረት ቀጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ይከተላል፡፡

| አቅራቢ | ተቀባይ |
|---|---|
| • ህጻናትዬ ተረት እንስማ አይደል? | አዎ! |
| • እሺ ተረት! ተረት! | የላም በረት ወይም የመሰረት! |
| • በድሮ ጊዜ አንድ........ ነበር፡፡ | እሺ |
| • ከዚያ.............. | እሺ |
| • ተረቴን መልሱ! አፌን በዳቦ አብሱ! | |

4. **የክፍል ውጭ ጨዋታ ጊዜ፦**

ይህ ከክፍል ውጭ ደጅ ወይም ሜዳ ላይ የሚደረጉ አካላዊ እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ነጻና የታቀዱ ተግባራትን የሚያካትት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ህጻናት በግል፣ በጥንድና በትንሽና በትልቅ ቡድኖች እየተደራጁ ልዩ ልዩ የትንንሽና የትልልቅ ጡንቻዎች እንቅስቃሴን የሚፈልጉ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፤ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ እንደ ጭቃ ማቡካት፣ አባሮሽና ሌሎች ጨዋታዎች የዚህ ጊዜ አካል ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

5. **የክፍል ውስጥ ጨዋታ ጊዜ፦**

ይህ በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ በአብዛኛው የታቀዱ ትምህርታዊ ጨዋታዎችንና ተግባራትን የሚያካትት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ህጻናት በግል፣ በጥንድና በትንሽና በመጠነኛ ቡድኖች እየተደራጁ ልዩ ልዩ የትንንሽና የትልልቅ ጡንቻዎች እንቅስቃሴን፣ አዕምሯዊ ዝግጁነትንና ትኩረትን የሚፈልጉ ጨዋታዎችን ይጫዎታሉ፤ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ እንደእንቆቅልሽ ያሉ ጨዋታዎች የዚህ ጊዜ አካል ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

6. **የተግባር ልምምድ ጊዜ፦**

ህጻናት አዲስ ነገር ለማወቅ ካላቸው ጉጉት የተነሳ መጠየቅን፣ መመራመርን፣ መሞከርን፣ መነካካትን፣ ማዋሄድንና መለያየትን፣ መስበርና መጠገንን እንድሁም ሀሳባቸውን በቃልና በተግባር መግለጽን ዋነኛ ምርጫቸው ያደጋሉ፡፡ ከዚህ መነሻ በዚህ ጊዜ ለህጻናት ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን በማቅረብ በግል፣ በጥንድ፣ በትንሽና በትልቅ ቡድን እየሆኑ እንዲተገብሩ ይደረጋል፡፡

7. **የውይይት ጊዜ፦**

ውይይት ሀሳብ መለዋወጥንና መነጋገርን ያካትታል፡፡ ህጻናት በዚህ ጊዜ በተለያዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ በሰፊው ይነጋገራሉ፡፡ ይህ ተግባር የህጻናትን በራስ የመተማመን፣ የንግግር፣ ለአንድ ነገር ትኩረት መስጠትን፣ የማዳመጥና ሀሳብ የማፍለቅ ችሎታቸውን ያዳብራል፡፡

8. **በሥራ የመማር ጊዜ፦**

ለህጻናት ትምህርት ቤት ሌላይኛው ቤታቸው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም ህጻናት በዚህ ጊዜ በቤተሰባቸውና በማህበረሰባቸው ዘንድ የሚዘወተሩ የሥራ ዓይነቶችን መሰረት ያደረጉ ሥራዎችን በመስራት ልዩ ልዩ ክህሎቶቻቸውንና ችሎታቸውን ያሳድጋሉ ተብለው ይታመናል፡፡

9. **በፕሮጀክት የመማር ጊዜ፦**

ፕሮጀክት ታቅደውና ታስበው ረዘም ላለ ጊዜ ህጻናት ፈትሸው፣ ጠይቀው፣ ተመራምረው፣ ሠርተውና አስተካክለው የሚያመጧቸው የግል፣ የጥንድና የቡድን ሥራዎችን ያካትታል፡፡ መምህራን የህጻናትን ሥራ የሚከታተሉ ሲሆን ህጻናት ግን በስተመጨረሻ ሥራቸውን ለክፍሉ አቅርበው ማብራሪያና መግለጫ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

10. የመስክ ጉብኝት ጊዜ፦

ይህ ወደ ክፍል በቀላሉ ማምጣት የማንችላቸውንና ህጻናት ትምህርት ያገኙባቸዋል ብለን የምናስባቸውን ቅርሶች፣ ታሪካዊ ቦታዎችና ኩነቶች የምናስቃኝበት ሌላይኛው በክፍል ውጭ የታቀደ ምልከታ የሚናደግበት ወቅት ነው።

11. ህጻናትን መሸኘት፦

ህጻናት በራሳቸው ወደቤታቸው መሄድ ላይችሉ ይችላሉ። በመሆኑም መምህራን ደህንነታቸውን፣ ቁሳቁሶቻቸውን (የምሳ ዕቃ፣ መለማመጃ ደብተርና ወዘተ) በተገቢው መያዛቸውንና ለመሄድ ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠው ከወላጆቻቸው ወይም ከአሳዳጊዎቻቸው ጋር ያገናኟቸዋል።

## 1.15. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ባህሪያት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተቀናጅተው በሚቀርቡ ይዘቶች፣ በአቀራረብ ዘዴ፣ በመማሪያ አካባቢ አደረጃጀት፣ በመጫወቻ ቁሳቁሶች፣ በህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ስልት፣ በቤተሰብና ማህበረሰብ ተሳትፎ፣ በህጻናትና መምህራን ግንኙነት እንዲሁም በመምህራን አቅም ማጎልበት ረገድ ከሌላው የትምህርት እርከን እጅግ ለየት ይላል። ተቀናጅተው የሚቀርቡ ይዘቶችና የአቀራረብ ዘዴዎች ከላይ በዝርዝር የቀረቡ በመሆናቸው ቀሪ መገለጫዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

### 1.15.1. የመማሪያ አከባቢ አደረጃጀት

የዚህ ደረጃ ትምህርት ህጻናት በክፍል ውስጥ ብቻ ቁጭ ብለው የሚማሩ ባለመሆናቸው የመማሪያ አከባቢያቸውን ለሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን።

### ሀ. የክፍል ውስጥ አደረጃጀት

የክፍል ውስጥ አደረጃጀት የተለየ ሆነው የክፍሉ ጣሪያና ግድግዳ ጭምር ሳይቀር ትምህርታዊ ቁሳቁስን ያሉበት መሆን አለበት። የምከተለው በአውድ ላይ የተመሰረተ ውህደት ሥርዓት በመሆኑ የመማሪያ ክፍሎቻችንም በዚሁ ልክ የተደራጁ ይሆናሉ። የህጻናት ትምህርት ክፍል ሳቢ፣ ማራኪ፣ በመጫወቻ ቁሳቁስ የበለጸገና በማዕዘናት የተደራጀ መሆን ይጠበቅበታል። ስለሆነም የዚህ ደረጃ ትምህርት የሚማሩ ህጻናት የሚማሩበት ክፍል በዋና ዋና እድገት ዘርፎች የተደረጁ ማዕዘናት ያሉት ክፍል ይኖራቸዋል ማለት ነው።

አእምሯዊ መዳበር | አካላዊ መደባር | ማህበረ ስሜታዊ መዳበር | ቋንቋ መዳበር

- አእምሯዊ መዳበር፦ የማሰብ፣ማሰላሰል፣ምክንያታዊነትና ሌሎች ክህሎቶች የሚዳብሩበት ማዕዘን ነው። ለምሳሌ፦ ቁጥር፣ ፊደላት፣ አከባቢ ሳይንስ፣
- አካላዊ መዳር፦ የትልልቅና ትንንሽ ጡንቻዎች ዕድገትና መዳበርን በሚደግፉ ቁሳቁሶች እና ምግብ

ዓይነቶች ሊደራጅ ይችላል፡፡ ጤና፣የተመጣጠነ ምግብ አይነቶች፣ከአደጋ መጠበቅ፣ጥራጥሬዎች፣

- **መህበረ ስሜታዊ መዳበር፦** የማህበራዊ መስተጋብር፣ስሜት መረዳትና ሌሎች ክህሎቶች ይዳብሩበታል፡፡ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ተግባቦት፣
- **ቋንቋ መዳበር፦** የተግባቦትና ሌሎች የቋንቋ ክህሎቶች ሚዳብሩበት ማእዘን ነው፡፡ ፊደላት፣ቃላት፣

### ለ. የክፍል ውጭ አደረጃጀት

ይህ ሌላይኛው የመማሪያ አከባቢ ስሆን ብዙ ጊዜ ለታቀዱና ለነጻ ጨዋታዎች የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይደራጁበታል፡፡ መጫወቻ አካባቢው ከጎጂ ነገሮች የጸዳ መሆን አለበት፡፡ ውጭ መደራጀት ካለባቸው የመማሪያና መጫወቻ ቁሳቁሶች የተፈጥሮ (ሳር፣ አሸዋ፣ ቅጠል፣ ጠጠር፣ ፍሬ፣ ጭቃ፣ እጽዋት፣ ነፍሳትና ወዘተ) እና ሰው ሰራሽ (ብሎኮች፣ መሹለኪያዎች፣ ሸርተቴዎች፣ ዡዋዡዌዎች፣ ጎማዎች፣ ኳሶች፣ ገመድ፣ መወጣጫዎችና ወዘተ) ይጠቀሳሉ፡፡

## 1.16. የህጻናት እድገትና ትምህርት ምዘና

የህጻናትን የመማር እና የእድገት ደረጃ ምዘና በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ መምህራን ስለህጻናት ጥንካሬ፣ ችሎታ እና ፍላጎቶች መረጃን በመሰብሰብ፣ በመተንተን እና ከእሱ በመነሳት ለህጻናት በየቀኑ የጫወታና የትምህርት መርሃ-ግብሮችን በተመለከተ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ የሚረዳቸውን መደምደሚያዎችን ያካትታል፡፡ በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውስጥ የህጻናት መማር እና እድገት ምዘና ውስብስብ ቢሆንም የውጤታማ ማስተማርያ ዘዴና እድገት ልምዶች አካል ተደርገው ይወሰዳል፡፡

የህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ቀጥተኛ ምልከታን፣ ቃል-መጠይቆችን፣ ስታንዳርድ ፈተናዎችን፣ የደረጃ አሰጣጥ መለኪያዎችን እና ቼክ-ሊስቶችን፣ የህጻናትን የክፍል ሥራ ናሙናዎች መሰብሰብን እና የወላጅ አስተያየቶችን ያጠቃልላል፡፡ የምዘና ሂደቱ በቀጥታ ከሥርዓተ ትምህርት ይዘት እና በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ክፍል ውስጥ ከሚጠቀሙት የማስተማሪያ ስልቶች ጋር የሚያገናኝ ሰፊ አቀራረቦችን ይይዛል፡፡

የህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ሶስት ዓላማዎች አሉት፡፡ እነዚህም አንድ ልጅ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለመሳተፍ ብቁ መሆኑን ለመወሰን፣ ለዚያ ልጅ በክፍል ውስጥ ባለው አፈፃፀም ላይ በመመርኮዝ የግል የትምህርትና የእንክብካቤ እቅድ ለማዘጋጀት እና በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የልጁን መሻሻል ለመገምገም ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህጻናትን ለመለየትና አስፈላጊ ሁሉ ድጋፍና እገዛ ለማድረግ ልዩ ምዘና በባለሙያ ይሰጣል፡፡ በሌላ በኩል በቅድመ አንደኛ ደረጃ የሚማሩ ህጻናት እድገትና ትምህርት ደረጃ ለመለካት የተደራጁና ስታንዳርድ ቴስቶችን በአመቱ አጋማሽ ወይም መጨረሻ መስጠት ይቻላል፡፡ የህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ዘዴዎች በጨዋታ በፕሮጀክት እና በማህደረ-ተግባር ላይ የተመሠረተ ምዘናን ያካትታል፡፡

በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ምዘና ህጻናት ልዩ ለዩ ጨዋታዎችን እየተጫወቱ ሳሉና ከተጫወቱ በኋላ

የሚደረጉ ምልከታዎችንና የቃል ጥያቄዎችን ያካትታል፡፡ መምህራን ህጻናት ሲጫወቱ በስርዓት በመመልከት ስለእድገትና ስለትምህርት ብቃት ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ማግኘት ይችላሉ፡፡

በማህደረ-ተግባር ላይ የተመሠረተ ምዘና የህጻናትን የትምህርት እድገት ለመመዘን የሚያገለግል ሌላ ዓይነት አማራጭ ምዘና ሲሆን ይህም በእውቀታቸው፣ በፈጠራ ክህሎታቸው እና ችግር በመፍታት ችሎታቸው ላይ በማተኮር የህጻናትን አቅም መፈተሽን ያካትታል፡፡ ይህ የምዘና ሂደት መካከል የሚታየውን የአረዳድ ልዩነት ለማጥበብና በተቻለ መጠን ሁሉም ህጻናት አቅማቸውን እንዲያወጡ ይረዳቸዋል፡፡

በማህደረ-ተግባር ላይ የተመሰረተ ምዘና የህጻናትን የዕለት ተዕለት ተግባራትን አደራጅተው መያዝንና ከዚያ መነሻ ልጆቹ ያሉበትን ደረጃ የማየትና የማወቅ ሂደትን ያካትታል፡፡ ማህደረ-ተግባር ህጻናት በትምህርታዊ ተግባራት ላይ በሚሳተፉበት ጊዜ የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች የያዘ ስልታዊ እና የተደራጀ ስብስብ ነው፡፡ በማህደረ-ተግባሩ ውስጥ የተወከሉት የህጻናት ስራዎች የህጻናትን የመማር ብቃት ያለበት ደረጃን፣ የቀረቡ ይዘቶችን እና ስልቶችን ያንፀባርቃሉ፡፡ ማህደረ-ተግባራት በራሳቸው የግምገማ መሳሪያ አይደሉም፡፡ ስለህጻናት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በአግባቡ ማደራጀትና ተንትነው ለህጻናት አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን ይጠበቃል፡፡

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን የህጻናትን እድገትና ትምህርት ሲመዘኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች መርሳት የለባቸውም፡፡

- በማህደረ-ተግባር የምዘና ስልቶችን (ምልከታ፣ የቃል ጥያቄ፣ ማህደረ-ተግባር፣ ቼክ-ሊስት) መጠቀም
- ምዘናው ተግባር-ተኮርና ከህጻናት ዕድሜ፣ ባህልና ቋንቋ ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን ማድረግ
- አወንታዊ መማርንና እድገትን የሚደግፍ አካባቢ መፍጠር
- በምዘናው ሂደት ውስጥ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ያለውን ሚና መረዳትና ወላጆችን ማሳተፍ
- በህጻናት ሁለንተናዊ ዕድገትና የመማር ብቃቶች ላይ ትኩረት ማድረግ
- የምዘናን ውጤት ለህጻናት እድገትና ትምህርት መሻሻል መጠቀም
- የህጻናትን ደህንነትና ሚስጥር መጠበቅና ልጆቻቸው በተለይ በስታንዳርድ ፈተናዎች ሲመዘኑ ለወላጆች ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡

## 1.17 የወላጅና አሳዳጊ ተሳትፎ በህጻናት ትምህርትና እንክብካቤ

የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ለህፃናት አጠቃላይ ስኬት መሠረት እንደመሆኑ መጠን ትኩረት መስጠቱ አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ሕጻን ከሰዎች ጋር የሚኖረው መስተጋብር የሚጀምረው ከቤተሰብ አባላትና በቅርብ ከሚንከባከቡት ጋር ነው፡፡ እነዚህ የመጀመሪያ ግኑኝነቶች የማህበራዊ ግንኙነት ክህሎቶች እድገትና ልጆች ስለራሳቸው እና በዙሪያቸው ስላሉት ሰዎች የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስተማር ወሳኝ ጊዜያት ናቸው፡፡ ቤተሰቦች የልጆቻቸው የመጀመሪያ አስተማሪዎች በመሆናቸው በእድገታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳርፉ መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የቤተሰብ ተሳትፎ በልጆች ትምህርት ላይ ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑ ነው፡፡

ቤተሰቦች ለልጆቻቸው እድገትና መዳበር የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤና ግብዓቶች ያቀርባሉ፡፡ በዚህም የህጻናትን ጤና እና እድገት በማረጋገጥ ረገድ ቀዳሚ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ሌላው በቤተሰብ እና በትምህርት ቤቶች መካከል ቀጣይነት ያለው፣ በጋራ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተና፣ ጠንካራ አጋርነት ሲኖር የቤተሰብ ተሳትፎን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ የቤተሰብ ተሳትፎ በትምህርት ቤትና በቤተሰብ መካከል በሁለትዮሽ መተማመንና መከባበር ላይ የተመሠረተ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ በማድረግና ኃላፊነትን በመከፋፈል በቁርጠኝነት በመሥራት የልጆቻቸውን ትምህርትና እድገትን በንቃት መደገፍ ይገባል፡፡ ይህ በትብብር ላይ የተመሰረተ የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ግንኙነት ወላጆች እና አስተማሪዎች የልጆችን ብቃት ለማሳደግ፣ በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ የሚያጋጥማቸውን ችግሮቻቸውን ለመፍታት እና ግብዓትን በማሟላት በጋራ ጥረት እንዲያደርጉ መሰረት ይሰጣል፡፡

## 1.18. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመምህር መምሪያ አጠቃቀም

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን የመግቢያውን ክፍል፣ ስለ ቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት የተጻፉትን ጉዳዮች፣ የመመሪያዎቹን አተገባበር ቅደም ተከተል፣ የትምህርቱን ዓላማዎች እና መርሆዎችን በጥልቀት እንዲያነቡ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተጠቆሙትን ንቁ የመማር ዘዴዎች፣ ግብአቶች፣ በልጆች ላይ ያተኮረና በጨዋታ ላይ የተመሠረተ ትምህርት አጠቃቀም፣ የእድገት እና የመማር ዘርፎች፣ የልጆች እድገት እና የመማር ውጤቶች እና የተጠቆሙ መደበኛ የሆኑና ያልሆኑ የግምገማ ቴክኒኮችን ማወቅ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም መምህራን አካላዊ የመማር አካባቢዎችን እንዴት ማደራጀት እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው፤ የአከባቢ ቁሳቁሶችን የመጠቀም፣ የተለያዩ ማዕዘኖችን (የክፍል ውስጥ እና የውጭ ማዕዘኖችን) የማደራጀት እና ቤተሰብንና ማህበረሰብን የማሳተፍ ስልቶችን ተግባራዊ የማድረግ አስፈላጊነትን በመገንዘብ በስራ ሊያውሉት ይገባል፡፡ ከዚህም ጋር መምህራን የዕለት ተዕለት ተግባራትን እንዴት እንደሚያከናውኑ መረዳትና ዕለታዊ፣ ሳምንታዊ እና ዓመታዊ የትምህርት እቅዶችን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም መምህራን ይህን የመምህር መምሪያ ከህጻናት መለማመጃ ደብተር ጋር ትኩረት ሰጥተው በማቀናጀት መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

## 1.19. የክፍለ ጊዜ ድልድል አደላደል

ይህ የ4 ዓመት ህጻናት ማስተማሪያ፣ ማሳደጊያና ማዘጋጃ የመምህር መምሪያ እንደመሆኑ መጠን ከህጻናት እድመና የእድገት ደረጃ ጋር የሚቀራረብ ድርጊት የያዘ የጊዜ ድልድል ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ህጻናት በአንድ ነገር ላይ የሚኖራቸው የትኩረት ደረጃ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ የሚከናወኑ ተግባራት አሰልቺና ጊዜ የሚፈጁ መሆን እንደለለባቸው ይታመናል፡ ፡ በመሆኑም ከላይ እንደማስተማሪያ ዘዴዎች የተዘረዘሩ ተግባራት የሚከተሉት የጊዜ ድልድል ይኖራቸዋል ተብለው ይጠበቃል፡፡ የዚህ ደረጃ ትምህርት የተደራጀው በቀን 6 ክፍለ ጊዜ ኖሮት አንዱ ክፍለ ጊዜ ከ20 ደቂቃ በማይበልጥ ሁኔታ ነው፡፡ ተረት፣ መዝሙር፣ የክፍል ውስጥ ጨዋታና ውይይት በቀን 20 ደቂቃ ብቻ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን የመስክ ጉብኝት፣ በሥራ መማርና በፕሮጀክት መማር እንደየተግባራቱ ስፋትና ጥልቀት እንከ አንድ ሰዓት ልዘልቁ ይችላሉ፡፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ ግን ህጻናትን ወደውጭ ይዘው መውጣትን፣ የአካል እንቅስቃሴ ማድረግንና ነጻ ጨዋታዎችን የሚያካትት በመሆኑ በልዩነት የሁለት ክፍለ ጊዜያት ቆይታ ይኖረዋል፡፡ ይህም ማለት የክፍል ውጭ ጨዋታ በሚኖርበት ጊዜ 40 ደቂቃ ያክል ልፈጅ ይችላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አንድ ተግባር በሳምንት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚቀርብ ከሆነ ተግባሩ አንድ ዓይነት ቢሆንም በተሰጠው ክፍል ጊዜ መሠረት የማስተማር፣ የአቀራረብ እና የምዘና ስልትን በመቀያየር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የመማር አውዶች

## አውድ አንድ ስለ እኔ

አጠቃላይ የተሰጠ ጊዜ- 5 ሳምንት

ክፍለ ግዜ ብዛት- /150/

### 1.1 መግቢያ

ህፃናት ስለእኔ በሚለው ዓውድ ውስጥ መሰረታዊ ክህሎቶች የሚያዳብሩበት እና በዕድሜያቸው ሊያጎለብቱ የሚገባቸው አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ አዕምሯዊ እና ማህበራዊ ዕድገታቸውን ሊያዳብሩ የሚችሉበት የመማርያና ዕድገት ይዘቶች ተካተዋል፡፡ በአምስቱ ሳምንታት ውስጥ ለዓውዱ የተቀመጡትን አጥጋቢ የመማር ብቃቶች እና ዝርዝር የአተገባበር ስልቶችን መሰረት በማድረግ መምህራን የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ሲገቡ ህፃናት በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ የተለያዩ ተግባራትን (ለምሳሌ:- የግል ተግባር፣ ተረት፣ እንቆቅልሽ፣ መዝሙር፣ የክፍል ውጭ ጨዋታ፣ በፕሮጀክት መማር፣ በስራ መማር፣ ውይይት፣ የመስክ ጉብኝት፣ የክፍል ውስጥ ጨዋታ) በማከናወን ራሳቸውን እና ጓደኞቻቸውን ማስተዋወቅ እንዳለባቸውና ትህትናን በተላበሱ የአነጋገር ዘይቤዎች ሰላምታ እና ስንብትን በተገቢው ጊዜ እና ሰዓት መጠቀም እንዲችሉ እንዲሁም ራሳቸውን ከአደጋ ከሚያስከትሉ ነገሮች እንዲጠብቁና እና በራስ መተማመንን በማዳበር ወደ ተግባር መግባት ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 1.2 የሚጠበቁ ውጤቶች

ህፃናት በአውዱ ስር የተዘረዘሩ ይዘቶችን ካጠናቀቁ በኋላ:-

- ስማቸውን እና እድሜያቸውን ይናገራሉ
- የሳምንቱን ቀናት ይነጋራሉ
- የፊደላትን ድምጽ ይለያሉ
- ነጠብጣብ ፊደላትን ያያይዛሉ
- ስእሉን አይተው ድርጊቱን ምን እንደሆነ ይገልጻሉ

- እሰከ 9 ያሉ ቁጥሮችን በቁስ ይቆጥራሉ
- በነጠብጣብ የተጻፉ ቁጥሮችን ያያይዛሉ
- እስከ 9 ያሉ በቃላቸው ይቆጥራሉ
- በአከባቢቸው የተለመዱ ከ2-3 የሚሆኑ የምግብና የመጠጥ አይነቶችን ስሞች ይለያሉ
- የቤት እንሰሳት ስሞችን ይጠራሉ
- የጂኦሜትሪክ ስሞችን ይለያሉ፡፡
- የጨረቃ፣ የኮኮብ ፣የደመናና የጸሀይ ስሞችን ይለያሉ
- የግንባታ ብሎኮች ተጠቅመው ይገነባሉ
- ሞባይልን ከቴሌቭዥን ይለያሉ
- የሚወዱትና የማይወዱትን ነገር ይለያሉ
- ደስተኛ እና የተናደዱ የምስል ፊቶችን ይለያሉ
- ጥሩ እና መጥፎ ስራዎችን ይለያሉ
- በአዋቂዎች ድጋፍ ጥርስን መቦረሽና ልብስ መልበስ ይጀምራሉ ፡፡
- እርሳስን በትክክል ይይዛሉ
- መስመር ጠብቀው ይሞነጫጭራሉ፣ቀለም ይቀባሉ
- ሙዚቃዊ ምትን ጠብቀው ይንቀሳቀሳሉ

## 1.3 የዓውዱ አበይት ይዘቶች

- ራስን መገንዘብ
- ጤና መጠበቅና እራስን መከላከል
- አመጋገብና አካላዊ ዕድገት
- ቁሶችን መቁጠር፣ ማወዳደርና መለየት
- መሰረታዊ የጂኦሜትሪ ቅርጾች
- ባህል
- ግብረገብ
- ፈጠራና ህትመት
- አካባቢን ማወቅ
- ድምጽን መለየት
- ተግባቦትን ማሳደግ
- ፊደል መለየትና ቃላትን መጥራት

# አንደኛ ሳምንት

**የተሰጠው ሰዓት-10** **ክፍለጊዜ (30)**

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ስለ ራሳቸው ይናገራሉ
- ጓደኞቻቸውን ይለያሉ
- የሰውነት ክፍሎችን ይናገራሉ
- ምስል በማየት ድርጊቱን ይገልጻሉ
- ከአንድ እስከ አምስት ያሉ ቁጥሮችን በቃላቸው ይቆጥራሉ
- ያለገደብ ይሞነጫጭራሉ
- የግል ንጽህናቸውን መጠበቅ ይጀምራሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- እራስን ማስተዋወቅ
- እራስን ማወቅ
- የሰውነት ክፍሎች
- ጤና
- ቁጥር መቁጥር
- ጥበባዊ ግንዛቤ
- የህትመት ግንዛቤ

## ተግባር 1፡- የግል ተግባር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. እራስን ማስተዋወቅ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ራስን ማስተዋወቅ፣ ሰዎችን መለየት፣የሰውነት ክፍሎች
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ትምህርት የሚጀመሩበት ቀን በመሆኑ በመጀመሪያ ሰላምታ በመስጠት ራስዎን ለህፃናቱ በሚገባና በቀላል አገላለጽ ያስተዋውቋቸው፡፡ በመቀጠልም ህጻናት እራሳቸውን ሲያስተዋውቁ የሚያሳይ ቪድዮ ወይም የድምጽ ቅጂ በማዘጋጀት ያሳዮዋቸው/ ያሰሟቸው፡፡ ህጻናቱ ስማቸውን፣ የአባታቸውን ስም፣ የአናታቸውን ስም፣ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው በመቀጠልም የሰውነት ክፍላቸውን በመጠቀም አንድና ሁለት ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ህጻናት እራሳቸውን ሲያስተዋውቁ የሚያሳይ ቪድዮ የተቀረጸበት

ሲዲ፣/ፍላሽ/ሚሞሪ/፣ቴሌቪዥን፣ ካሜራ፣ መቅረጽ ድምጸ/ሞባይል፣ ስዕላዊ መግለጫዎች

- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡ ስማቸውን፣ ዕድሜያቸውን፣ የአባታቸውን ስም መጠየቅ፣ምልከታ የሰውነት ክፍላቸውን በምጠቀም ከአንድ እስከ አምስት ያሉ ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ በማድረግ)

## ለ. መሞነጫጨር (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ የሰውነት ክፍል፣ መሞነጫጨር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ይህ ክፍለ ጊዜ ህፃናቱ የየራሳቸውን የጽሁፍ ልምምድ የሚጀምሩበት የትምህርት ሰዓት ነው፡፡ ስለሆነም ህጻናቱ እርሳስ እንዴት መያዝ እንዳለባቸው ማሳየት፣ቁጥር ያለ ገደብ እንዲሞነጫጭሩ ተግባራቱን በተገቢው ሁኔታ እያከናወኑ ስለመሆናቸው አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡ የሰውነት ክፍላቸውን በመጠቀም ሶስትና አራት ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ ወረቀት
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ፡- ህጻናቱ እርሳሳቸውን በአግባቡ መያዛቸውንና ተግባራቱን ማከናወናቸውን መከታተል)

## ሐ. ሥዕል ማንበብ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ንጽህና፣ብዛት፣ጾታ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የጥርስ ንጽህና አጠባበቅን፣ የእጅ አስተጣጠብ፣ የጸጉር ንፅህናን አጠባበቅ እና የገላን አስተጣጠብ የሚያሳዩ ስዕሎችን አዘጋጅተው ለህፃናቱ በመስጠት ህፃናቱም የያዟቸውን ስዕሎች በየግላቸው በደንብ ከተመለከቱ በኋላ ተራ በተራ የስዕሉን ድርጊት፣ የምስል ብዛት እና ጾታ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የግል ንፅህና አጠባበቅን የሚያሳዩ ምስሎች፣የቁጥር ካርዶች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- የያዙትን ሥዕል ተግባር እና ብዛት መጠየቅ)

# ተግባር 2፡- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

## ሀ. ጎበዙ ተማሪ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የሰውነት ክፍሎች፣ጤና፣የግል ንጽህና
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ከዚህ በታች ያለውን ተረት ለህጻናቱ ድምጽዎትን ከፍ በማድረግና በመቀያየር ይንገሯቸው፡፡ እንዲሁም ህጻናቱ ተረቱን በአግባቡ ማዳመጣቸውን መከታተል ይጠበቅብዎታል፡፡

## ተረት ተረት!

አንድ በለጠ የሚባል የማያውቀውን መጠየቅ የሚወድ ጎበዝ ልጅ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አባቱን አባዬ ስንት አይን፣ ጆሮ፣ እግር፣ እጅ፣ ምላስ አለን ብሎ ጠየቃቸው፡፡ አባቱም በበለጠ ጉብዝና በጣም ተደንቀው "ጎበዝ የኔ ልጅ!" በማለት እኛ ሰዎች ሁለት አይን፣ሁለት እጅ፣ አንድ ምላስ እና ሁለት እግር አለን ብለው መለሱለት፡፡ በተጨማሪም እነዚህን የሰውነት ክፍሎቻችንን መታጠብና መንከባከብ ካልቻልን ሁልጊዜ ልንታመም እንችላለን ብለው ጤናውን መጠበቅ እንዳለበት አስረዱት፡ ፡ በለጠም ጥያቄው ስለተመለሰለት "አመሰግናለሁ አባዬ" በማለት አቅፎ ሳማቸው፡፡ ልጆች እናንተም የማታውቁትን ነገር መጠየቅ አለባችሁ እሺ!፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ተረቱን የሚገልጽ ምስል
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- ስንት እጅ አለን? ስንት እግር አለን?፣ የሰውነት ክፍሎቻቸውን እንዲያሳዩ መጠየቅ፣ በተረቱ ላይ እነማን አሉ?)

### ለ. ሶስቱ ውሾች (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ውሾች፣መታጠብ፣ደስታ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተረት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ከዚህ በታች ያለውን ተረት ህጻናቱ በሚስብ መልኩ ይተርቱላቸው፡፡

## ተረት ተረት!

አንድ ጎበዜ የሚባል ሰውዬ ከሶስት ውሾቹ ቡቺ፣ችሎ እና ቦቢ ጋር በአንድ ጫካ አጠገብ ይኖራል፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን የጎበዜ ውሾች ምግብ ፍለጋ ወደ ጫካ ሄዱ፡፡ በዚህን ጊዜ ሶስት ሽፍቶች ጎበዜን ብቻውን አግኝተው ያዙትና "ልንገርፍህ ነው" አሉት፡፡ ጎበዜም "እሺ ከመግረፋችሁ በፊት እንድጮህ ፍቀዱልኝ" አላቸው፡፡ ሽፍቶቹም "ምን ችግረን ጩህ" አሉት፡፡ ጎበዜም ድምጹን ከፍ አድርጎ ቡቺ፣ ችሎ፣ ቦቢ ድረሱልኝ በማለት ሶስት ጊዜ ጮኸ፡፡ ሽፍቶቹም እየሳቁ "የምን ችሎ፣ የምን ቦቢ ብትጮህ ማን ይደርስልሃል?" እያሉ ሲቀልዱበት ሶስቱ ውሾች ደረሱና ሽፍቶቹን ቦጫጭቀው ጎበዜን ከመገረፍ አዳኑት፡፡ ጎበዜም በጣም ደስ ብሎት እነቦቢን እቅፍ አድርጎ በማሻሸት ደስታውን ገልጾላቸው ምግብ ሰጣቸው፡፡ እጁን ታጥቦ ለራሱም መብላት ጀመረ፡፡ ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ!

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ተረቱን የሚገልጽ ሥዕል፣የተረት መጽሃፍ
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- ጎበዜ ስንት ውሾች አሉት፣ ያያችሁት ሥዕል የምን ሥዕል ነው? ጎበዜ ስንት ጊዜ ጮኸ? ከተረቱ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር 3፡- መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ልሂድ ትምህርት ቤት (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል፣ ቁጥር፣ ንጽህና
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ በማለማመድ ስለ ራሳቸው መግለጽ፣ ንጽህና ስለመጠበቅ እና የመቁጠር ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ያግዟቸው፣ሁሉም ህጻናት ግጥሙና ዜማውን እስኪይዙት ድረስ ደጋግመው ያዘምሯቸው፡፡

ልሂድ ት/ቤት

ልሂድ ት/ቤት (2)፣

እውቀት ለመገብየት፡፡

በ - ሰ - እማራለሁ፣

ስሜን እገልጻለሁ፣

አንድ፣ሁለት፣ ሶስት፣አራት፡፡

ቁጥር እቆጥራለሁ፣

ጥርሴን ቦርሻለሁ፤

እጆቼን ታጥቤ፤

ቁርሴን እበላለሁ፣

ደስተኛ እሆናለሁ (2)

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ተቆጣሪ ነገሮች፣ ፊደል፣ ንጽህና አጠባበቅ የሚሳይ ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ሲዘምሩ እየተከታተሉ እርማት መስጠት...)፣እና የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- በመዝሙሩ ውስጥ ስላሉ ነገሮች መጠየቅ...)

### ሐ. ጎበዝ ልጅ ነኝ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል፣ ቁጥር፣ መታጠብ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ከዚህ በታች ያለውን መዝሙር ከህጻናቱ አብረው በመዘመር ያለማምዱዋቸው፡፡

እኔ ጎበዝ ልጅ ነኝ

እኔ ጎበዝ ልጅ ነኝ

የሚሉኝን የምሰማ

የሚወዱኝአባባና እማማ

ፊደሎች እንድለይ

ያግዙኛልያበረታቱኛል

ቁጥር እንድቆጥር

ያለማምዱኛል

እጄን እንድታጠብ

ሁሌም ያደርጉኛል

እኔም ጎበዝ ሁኛለሁ

1፣2፣3፣4 ብዬ እቆጥራለሁ

በ፣ ሰ፣ ሸ በማለት ፊደል እለያለሁ (2)

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የሚቆጠሩ ነገሮች፣ውሃና ሳሙና፣ የእናት ፊደላት ፍላሽ ካርድ
- የምዘና ስልት፡- ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ፡- በቡድንና በግል ሲዘምሩ መከታተል) እና የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- ከ1-5 በቃል እንዲቆጥሩ መጠየቅ፣ እጃቸውን መቼ መቼ እንደሚታጠቡ መጠየቅ)

## ተግባር 4- የውጭ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. እጅ ለእጅ ተያይዘን (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ስም፣ጓደኛ፣ቁጥር፣ጤና
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱ ወደ ውጭ ይዘው በመውጣትሁለት ክብ እንዲሰሩ ያድርጉ፡ ፡ ከዚያም መጀመሪያ  ቡድን አንድ በመቀጠል ቡድን ሁለት እጅ ለእጅ ተያይዘን የሚለውን ጨዋታ ይጫወቱ፡፡ በጫወታው ሁሉም በየተራ የራሳቸውን ስም እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

እጅ ለእጅ ተያይዘን

እጅ ለእጅ ተያይዘን፤

እንወዛወዛለን፡፡

መሰረት እባላለሁ፤

መጨፈር እችላለሁ፤

ጤናዬን እጠብቃለሁ፤

ቁጥር መቁጠር እወዳለሁ፡፡

ጓደኛዬን አውቃታለሁ፤

ጓደኛዬን አውቀዋለሁ፤

አብሬ እጫወታለሁ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ህጻናት ክብ ሰርተው ሲጫወቱ የሚሳይ ሥዕል፣ ቪድዮ
- **የምዘና ስልት፡- ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ፡-** በትክክል እየተጫወቱ መሆኑን መከታተል) እና **የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡-** የተዋወቋቸውን ጓደኞቻቸውን ስም፣ዕድሜ፣ፆታ መጠየቅ)

### ለ. እንጫወት (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ስም፣ ቁጥር፣ መታጠብ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን ከክፍል በማስወጣት አምስት አምስት ሆነው ክብ ሰርተው እንዲቆሙ ያድርጉ:: ከአንድ እከክ አምስት ቁጥር ይስጧችው:: ቁጥራቸው ሲጠራ የራሳቸውንና የጓደኛቸውን ስም እንዲጠሩ ያድርጉ:: በመቀጠልም ከአንድ እሰከ አምስት ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ተራ በተራ እንዲጠሩ ያድርጉ:: ማለትም የመጀመሪያው/ዋ ህጻን አንድ፣ ሁለተኛው/ዋ ሁለት፣ ሶስተኛው/ዋ ሶስት፣ እያሉ እስከ አምስተኛው ይቀጥሉ:: ቅደም ተከተሉን የተሳሳተ ህጻን የሳተውን/ችውን ቁጥር ያህል ጡብ ጡብ ብሎ/ላ ወደ ጨዋታው እንዲመለስ/እንድትመለስ ያድርጉ:: በመጨረሻም እጃቸውን በውሃና በሳሙና ታጥበው ወደ ክፍላቸው እንዲገቡ ያድርጓቸው::
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ገመድ/ሲባጎ፣ ፊሽካ፣ውሃ፣ሳሙና
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ፡- ጨዋታውን በመከታተል በትክክል የተገበሩና ያልተገበሩ ህጻናትን መለየት...) እና የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- ቁጥሮችን በቃል እንዲጠሩ መጠየቅ...)

## ተግባር 5፡- ፕሮጀክት(3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የህጻን ምስልን ከጭቃ መስራት (ክፍለ ጊዜ 3)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ምስል፣ቁጥር፣ ንጽህና፣ ጥበባዊ ግንዛቤ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ የሚሰሩበትን ቦታ በማመቻቸት የጓደኞቻቸውን ምስል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው:: ህጻናቱ የሰሩት ምስል የማን እንደሆነ ይናገሩ:: እንዲሁም ምስሎቹን ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩና ስንት እንደሰሩ እንዲናገሩ በማድረግ የቁጥር እና የጥበብ ግንዛቤያቸውን እንዲያዳብሩ ያድርጓቸው:: በመጨረሻም እጃቸውን በውሃና በሳሙና ታጥበው ንጽህናቸውን በመጠበቅ ወደ ክፍላቸው እንዲገቡ ያድርጓቸው::
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ውሃ አፈር፣ ሰው ሰራሽ ጭቃ (ከተገኘ)፣ ሳህን
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የሰሩትን ምስል ጾታ፣ ስንት ምስል እንደሰሩ፣ የሰሩትን ምስል የሰውነት ክፍሎችን እንዲያሳዩ፣ ስራ ከሰሩ በኋላ እጃቸውን መታጠብ ለምን እንደሚጠቅም መጠየቅ...)

**ማስታወሻ፡-** መምህር/ት እባክዎ ህጻናት ጭቃውን ወደ አፋቸው እንዳያደርጉት እንዲሁም ልብሳቸውን እንዳያቆሽሹ ክትትል (ጥንቃቄ) ያድርጉ::

# ተግባር 6- በስራ መማር (4 ክፍለ ጊዜ)

## ሀ. ንጽህና አጠባበቅ (4 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የውሀ ቀለም፣ዕዳት፣ህትመት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በስራ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ቀጣዩን ተግባር ለመስራት አስፈላጊ የሆኑ የንጽህና መሳሪያዎች ማዘጋጀት፣ ከ3 እስከ 5 ህጻናትን በቡድን መመደብ፣ በክፍላቸውና ከክፍላቸው ውጭ ያሉ የወዳደቁ ወረቀቶች፣ ቅጠላ ቅጠሎች፣ ትናንሽ እንጨቶች እንዲለቃቅሙ ያድርጓቸው የለቀሙትን ቁሳቁስ በቆሻሻ መጠራቀሚያ ውስጥ ያከማቹ፡፡ ሁሉንም ዕዳት ካጠናቀቁ በኋላ ውሃና ሳሙና ተጠቅመው እጃቸውን በአግባቡ እንዲታጠቡ ያድርጉ፡፡ እርሶም የተወሰነ ንጹህ ቅጠሎችን ወደ ክፍል ይዘው በመግባት የውሃ ቀለም ቅጠሉ ላይ እየቀቡ ለህጻናቱ በመስጠት በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ የህትመት ስራ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** መጥረጊያ፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ ውሃ እና ሳሙና ውሃ ቀለም
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ንጽህናን መጠበቅ ለምን ያስፈልጋል?፣ የግልና የአካባቢ ንጽህና ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ እቃዎችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣ የሰሩትን ህትመት ብዛት መጠየቅ)

# ሁለተኛ ሳምንት

## የተሰጠው ሰዓት-10 ክፍለ ጊዜ (30)

### የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- በቀላል እገዛ የምሳ እቃቸውን ይከፍታሉ
- በቀላል እገዛ እፅዋትን ውሃ ያጠጣሉ
- ጥቃቅን የዕለት ከዕለት ተግባራትን ያከናውናሉ፣ስሜታቸውን በመለየት የተሰማቸውን ይናገራሉ፣ የድምጽ አቅጣጫዎችን ይለያሉ፣ የቤት ክፍሎችን ይለያሉ
- ከ2-3 የተለመዱ ምግቦችን እና መጠጦችን ይናገራሉ
- እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን በቃላቸው ይቆጥራሉ
- ቀላል ዘፈኖችን በማዳመጥ እያዜሙ ይደንሳሉ
- በወረቀት እና በአሸዋ ላይ ጽሁፍ ይጽፋሉ

### ንዑስ ይዘቶች

- እራስን መቻል
- እራስን መቆጣጠር
- ድምፅ መለየት
- ቅርብ አካባቢ
- የተመጣጠነ ምግብ
- ቁጥር እና ቁሶችን መቁጠር
- የፈጠራ አገላለጽ

## ተግባር 1- የግል ተግባር (8 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. አሻንጉሊቶቻቸውንና ንብረቶቻቸውን ማፅዳት (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ራስን መቻል፣ ጽዳት፣ ስሜትን መግለጽ፣መቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለተግባር ስራው የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ በማዘጋጀት ሁሉም ህጻናት ራሳቸውን በመቻል በየግላቸው አሻንጉሊቶቻቸውን (መጫዎቻቸውን) እና ሌሎች እቃዎቻቸውን በፎጣዎች/በቁርጥራጭ ጨርቆች እንዲያጸዱ ያበረታቱዋቸው፡፡ በመቀጠልም ያጠፏቸውን/ ያጸዷቸውን/ ቁሶች እንዲቆጥሩና ወደ ቦታቸው እንዲመልሱ ያድርጉ ሲጨርሱ የተሰማቸውን ስሜት እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** አሻንጉሊት፣ የምሳ ዕቃ፣ የውሃ ዕቃ፣ ቦርሳ፣ የመጫወቻ ዕቃዎች፣ፎጣዎች/ጨርቆች

- የምዘና ስልት፡- ምልከታ (ለምሳሌ፡- ህጻናቱ አሻንጉሊቶቻቸውን /መጫዎቻቸውን/ እና ሌሎች ዕቃዎቻቸውን ሲያጸዱ መከታተል፣ በደንብ ያጸዱና ያላጸዱትን ለይቶ ማገዝ፣ ስሜታቸውን መጠየቅ)

### ለ. እስትንፋስ መቆጣጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ቀላል ዘፈኖች፣ ስሜት
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በግል ተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ተግባራቱን በየግላቸው ሲተገብሩ እርስዎ በተገቢው ሁኔታ እያከናወኑ ስለመሆናቸው አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያድርጉ፡፡ ህጻናቱ እየተነፈሱ ቁጥር እስከ ዘጠኝ እንዲቆጥሩ ያበረታቱዋቸው፡፡ ይህንንም ሲሰሩ ስሜታቸውን በማየት የተሰማቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ይህ ቀላል እንቅስቃሴ ትኩረት እንዲኖራቸው እና አተነፋፈሳቸውን እንዲቆጣጠሩ፣ መዝናናት እና መረጋጋት እንዲኖራቸው ያግዛል፡፡ በመቀጠል ቀላል ዘፈኖችን ይክፈቱላቸው እና ዘፈኑን በማዳመጥ እያዜሙ በጋራ እንዲደንሱ ያድርጓቸው፡፡
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- መቅረጸ ድምጽ፣ ሞባይል፣ቴፕ ሪከርደር፣
- የምዘና ስልት፡- ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ፡- ህጻናቱ እየተነፈሱ ሲቆጥሩ መከታተል፣ ቀላል ዘፈኖችን ይክፈቱላቸውና ስሜታቸውን በማየት የተሰማቸውን እንዲናገሩ ማድረግ)፡፡

### ሐ. ብሎኮች (የግንባታ ቁሳቁስ) መቆጣጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- መቆጣጠር፣ የቤት ክፍሎች፣ የፈጠራ አገላለጽ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር ስራ
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ለግንባታው የሚሆኑ ቁሳቁስ በማዘጋጀት እና የመገንቢያ ቦታ በማመቻቸት ህጻናቱ የተለያዩ ጡቦችን/ብሎኮችን በመጠቀም ክፍሎችን በመገንባት እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡የሚሰሩትም ክፍል የትኛው የቤት ክፍል እንደሆነ እንዲገልጹ እና የፈጠራ አገላለጻቸውን /ችሎታቸውን / እንዲያጎለብቱ ያግዟቸው፡፡የተግባር ስራውን በሚሰሩበት ወቅት በተገቢው ሁኔታ እያከናወኑ መሆኑን በመመልከት ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የእንጨት እና የካርቶን ብሎኮች
- የምዘና ስልት፡- የቃልጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- የገነቡትን ክፍሎች በየተራ ማስቆጠር፣ ምን ምን እንደገነቡ መጠየቅ...)

## ተግባር 2- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. አባትና ሁለት ልጆቹ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ክፍት ቦታ፤ ጤና፣ድምጽ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተረት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! የህጻናትን ስሜት በሚስብ አተራረክና ድርጊቱን በሚገልጽ የፊት ገጽታ ተረቱን ይንገሯቸው፡፡

# ተረት ተረት!

በአንድ ሀገር ውስጥ አባት ከሁለት ልጆቹ ጋር ይኖር ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አባት ልጆቹን ጠርቶ ዛሬ አንድ ጥያቄ እጠይቃችኋለሁ፡፡ ጥያቄውን በትክክል የመለሰ ይሸለማል አላቸው፡፡ ልጆቹም ጥያቄውን በጉጉት መጠበቅ ጀመሩ፡፡ አባትም ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ ባዶ ባልዲ ሰጣቸውና ምንም የቀረ ስፍራ ሳይኖር በፈለጋችሁት ነገር ሙሉት አላቸው፡፡ትልቁ ልጅ ሲቀመጥ ውሎ የአባቱን ድምጽ ከሩቅ ሲሰማ ቶሎ ብሎ የተሰጠውን ባልዲ በአምስት ኳሶች ሞላ፡፡ አባትየው ባልዲውን ሲያይ ያልተሞላ ክፍት ቦታ ስለነበረ አልተደሰተም፡፡ ቀጥሎ ወደ ታናሽየው ሲሄድ ባልዲው በውሃ ተሞልቶ ያገኛል፡፡ አባትየውም በጣም ተደስቶ ለምን ውሃ ሞላህ እንደ ወንድምህ ለምን በሌላ ነገር አልሞላህም ብሎ ጠየቀው እሱም ውሃ ብዙ ጥቅም አለው/ለምሳሌ ፤ለመጠጣት፣ሰውነታችንን ለመታጠብና ጤናችንን ለመጠበቅ... /ለዛም ነው የመረጥኩት ብሎ መለሰለት አባቱም አቅፎ ሳመውና ሽልማቱን ሰጠው ይባላል፡፡ ተረቱን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ!

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የተረት መጽሃፍ፣ባልዲ፣ኳስ፣ውሃ
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ምሳሌ፡- አባት ስንት ልጆች አሉት፣ ውድድሩን ያሸነፈው ማነው፣ትልቁ ልጅ የተሰጠውን ባልድ በስንት ኳሶች ሞላ)

## ለ. ጥጋበኛዋ አህያ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ድምጽ፣ ምግብ፣ ስሜት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የህጻናትን ስሜት በሚስብ አተራረክና ድርጊቱን በሚገልጽ የፊት ገጽታ ተረቱን ይንገሯቸው፡፡

# ተረት ተረት!

በጥንት ጊዜ አህያ፣ ውሻና ድመት አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ከአሳዳጊያቸው ስለተጣሉ ከቤት ወጥተው ጠፉ፡፡ ሲሄዱ ሲሄዱ ውሻውና ድመቷ የሚበሉትን ምግብ ስላላገኙ አንድ አጥር ስር ተጠግተው ተኙ፡፡ አህዩት ለምለም ሳር ስላገኘች ግጣ ስትጠግብ ስሜቷን መቆጣጠር ስላልቻለች “ዛሬ ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! እያልኩ ማናፋት እፈልጋለሁ” በማለት ለውሻውና ለድመቷ ነገረቻቸው፡፡ “እባክሽ አትጨሂ! አሁን መሽቷል! ጅቦ መጥቶ ስለሚበላሽ ይቅርብሽ” አሏት፡፡ አህያዋ ግን እምቢ በማለት እየዘለለች ድምጽዋን ከፍ አድርጋ” ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! “ እያለች ማናፋት ጀመረች፡፡ በዚህ ጊዜ አያ ጅቦ ድምጹን ወደሰማበት አቅጣጫ ተጠጋ፡፡ አህያዋም ለሁለተኛ ጊዜ ስታናፋ ሰምቶ አያ ጅቦ ይዟት ሄደ ይባላል፡፡ ተረቱን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ!

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተረት መጽሃፍ፣ተረቱን የሚገልጽ ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ምሳሌ፡- ጓደኛሞቹ ስንት ናቸው፣ ጠግቦ የጮኸው ማነው...)

## ተግባር 3- መዝሙር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቤቴ ቤቴ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ደስታ፣ ክፍሎች፣ምግብ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በመዝሙር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! መዝሙሩን በመዘመር እና ህጻናቱን በጋራና በግል እንዲዘምሩና የሚጠበቅባቸውን ብቃት እንዲጎናጸፉ ያበረታቷቸው፡፡

ቤቴ ቤቴ<br>
ይህ ቤታችን ደስ ይለኛል፤<br>
በልዩ ዕቃዎች አምሮልኛል፡፡<br>
ክፍሎቹ ሶስት ናቸው፣<br>
ደስ ይለኛል ሳጸዳቸው፡፡<br>
ሁልጊዜ ምንበላቸው፣<br>
እንጀራና ዳቦ ናቸው፡፤

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ከካርቶን እና ከመሳሰሉት የተሰራ የቤት ሞዴል፣የተመጣጠነ ምግብ የሚያሳይ ቻርት
- የምዘና ስልት፡-የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ምሳሌ፡-የቤት ክፍሎችን እየቆጠሩ እንዲዘረዝሩ...)፣ምልከታ፡- ከካርቶን እና ከመሳሰሉት ልዩ ልዩ ክፍሎች ያላቸው ቤት ሲሰሩ መከታተል...

## ተግባር 4- የክፍል ውስጥ ጨዋታ (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ስሜትን መግለጽ (3 ክፍለ ጊዜ)


- ቁልፍ ቃላት፡- ስሜት፣መቆጥር
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በጨዋታ
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ሶስት የህጻናት የፊት መገለጫዎችን ሥዕል የሚያሳዩ ካርዶች ከታች ባለው ሥዕል ዓይነት በማዘጋጀት ጠረጴዛ ላይ በሥዕሉ በኩል በማስቀመጥ ህጻናቱ አንዳንድ ሥዕል በማንሳት የሥዕሎቹን ስሜቶች (ደስታን፣ ሀዘንን፣ ንዴትን) በፊት ገጽታ እያሳዩ እንዲጫወቱና ያዩትንም ገጽታ ቆጥረው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ይህም የራሳቸውን ስሜት እንዲያውቁ እና እንዲቆጣጠሩ እንዲሁም የሌሎችን ስሜት እንዲረዱ ያግዛቸዋል፡፡



- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተለያዩ ስሜቶችን የሚወክሉ ሥዕሎች
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ:- ስሜቶችን በፊት ገጽታ እንዲያሳዩ መጠየቅ፣ሰዕሎቹ ላይ የተመለከቱትን ማስመሰል እንደሚችሉ መጠየቅ፣ ሌሎቹ ህጻናት የጓደኛቸውን ፊት በማንበብ ፍቺ እንዲሰጡ በመጠየቅ...

### ለ. ቢንጎ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት:-** ድምጽ ፣ቁጥር፣ቀላል ዘፈኖች
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ከታች ባሉት ሥዕሎች አይነት አምስት ህጻናትን የሚያጫውቱ የተለያዩ ድምፆችን በሚወክሉ ሥዕሎች/የቢንጎ ካርዶችን/ ያዘጋጁ:: በቢንጎ ካርዶቹ ላይ ያሉትን ሥዕሎች የድምፅ ቅጂዎች በእጅ ስልክዎት ያዘጋጁና ለህጻናቱ ተራ በተራ ያሰሟቸው: : ህጻናቱም የሰሟቸውን ድምፆች ከቢንጎ ካርዶቻቸው ሥዕሎች ጋር በማዛመድ በቅደም ተከተላቸው በማስቀመጥ ብዛታቸውን እንዲቆጥሩ ያድርጉ:: ሥዕሎች ከድምፆቹ ጋር በትክክል ያዛመደና በትክክል የቆጠረ ህጻን አሸናፊ ይሆናል:: በመጨረሻም ቀላል ዘፈኖችን ይክፈቱላቸውና እያዜሙ እንዲወዛወዙ ያበረታቷቸው::



- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የቢንጎ ካርዶች፣ሞባይል
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ (ለምሳሌ:- ምስሎቹን የሚወክሉ ድምፆችን በማሰማት ድምጹን መለየታቸውን መረጋገጥ፣እንዲቆጥሩ ማድረግ...)

## ተግባር 5- ፕሮጀክት (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. በአሸዋ ላይ ጽሁፍ ማለማመድ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** አሸዋ፣ መጻፍ፣መቁጠር፣መታጠብ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! የዕለቱን ተግባር ከመጀመርዎት በፊት በሰፊ ፕላስቲክ ሳህን የተሞላ ወይም ወለል ላይ የተነጠፈ አሸዋ ለህፃናቱ ይስጧቸው:: በጣታቸው የፈለጉትን እንዲጽፉ ያበረታቷቸው:: የፃፉትን በካሜራ/ስልክ ቀርጸው ያስቀምጡ:: ህጻናቱ ጽፈው ሲጨርሱ በቃላቸው ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጉ በመጨረሻም እጃቸውን በውሃና በሳሙና እንዲታጠቡ የበረታቷቸው::
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** አሸዋ፣ሳህን፣ሳሙና፣ ውሃ

- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ ስራቸውን መከታተል፣መቅረጽ፣ በቃል ማስቆጠር.. በጥያቄ / ለምሳሌ፡- የጻፉት ምን እንደሆነ መጠየቅ...

### ለ. በወረቀት ላይ ጽሁፍ መለማመድ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መጻፍ፣መቁጥር፣ ቀላል ድጋፍ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለተግባሩ አስፈላጊ የሆኑ ወረቀት/ክላሰር፣እርሳስ አዘጋጅተው ለህጻናቱ በማከፋፈል እና የእርሳስ አያያዝ በማሳየት የፈለጉትን እንዲጽፉና ምን እንደጻፉ፣ ስንት እንደጻፉ ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጓቸው። ሲጽፉ በካሜራ/ስልክ ቀርጸው ያስቀምጡ። በመጨረሻም የሰሩባቸውን ዕቃዎች በየቦታቸው እንዲያስቀምጡ ቀላል ደጋፍ/እገዛ/ ያድርጉላቸው። የወዳደቁ ወረቀቶችን ሰብስበው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ውስጥ እንዲጥሉ ይምከሯቸው።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ወረቀት/ ክላሰር፣እርሳስ፣ቅርጫት ካሜራ/ስልክ
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ ስራቸውን መከታተል፣መቅረጽ፣ጽሁፋቸውን ሰብስቦ ማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ማስር) የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ ምን እንደጻፉ መጠየቅ...)

## ተግባር 6- በስራ መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ተክሎችን መንከባከብ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ቅርብ አከባቢ፣ስሜት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በስራ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለተግባሩ አስፈላጊ የሆኑትን በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ /በቅርብ አከባቢ/ የተተከሉ አበባዎችን እና ሌሎች ተክሎችን ለህጻናቱ በማከፋፈል ያስረክቡዋቸው። ለእያንዳንዱ ህጻን በግማሽ ሊትር የፕላስቲክ ጠርሙስ ውሃ በመሙላትና ክዳኑን በመብሳት ጠዋት ጠዋት የየራሳቸውን ተክሎች በቀዳዳው እያፈሰሱ ውሃ በማጠጣት እንዲንከባከቡ፣ የተሰጣቸው ተክል ምን ያህል እንደሆነ እንዲቆጥሩ፣ ሰርተው ሲጨርሱ የተሰማቸውን ስሜት እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። በመጨረሻም እጃቸውን በውሃና በሳሙና እንዲታጠቡ ያድርጉ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የፕላስቲክ ጠርሙስ፣ ውሃ፣ ተክሎች፣ ውሃና ሳሙና
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፤አበቦችን/ተክሎችን እንዲቆጥሩ ማድረግ...) በቃል መጠየቅ፤ (ለምሳሌ ስራው ላይ የነበራቸውን ስሜት መጠየቅ)

# ሦስተኛ ሳምንት

**የተሰጠ ሰዓት-10** **ክፍለ ጊዜ (30)**

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- እራሳቸውን ከአደገኛ ነገሮች መጠበቂያ ዘዴዎች ውስጥ ሶስት ይናገራሉ
- የሳምንቱን ቀናት ስም ይናገራሉ
- እርሳስን በትክክል ይዘው ያሳያሉ
- ከቤት እንስሳት ውስጥ አምስቱን በስማቸው ይጠራሉ።
- አምስት ነገሮችን በመጠን እና በብዛት በማወዳደር ትልቅ እና ትንሽ/አጭርና ረጅም በመለየት ያሳያሉ።
- ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያያዎች ውስጥ የሶስቱን ስም ይለያሉ

ንዑስ ይዘቶች

- ደህንነት እና ጥበቃ
- ቃላት
- እንስሳት
- ትንንሽ ጡንቻዎች መዳበር
- እቃዎችን ማወዳደር እና መደርደር
- ባህላዊ ቅርሶች

## ተግባር 1- የግል ተግባር (8 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የትራፊክ ደህንነት (4 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ደህንነት፣የሳምንቱ ቀናት፣ባህላዊ ሙዚቃ መሳርያዎች
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን በሰባት ቡድን ይክፈሏቸው። የቡድኑን ስም በሳምንቱ ቀናት ስም ይሰይሙ። በመቀጠል ለአሻንጉሊት መኪኖች እና ለትራፊክ ምልክቶች ትንሽ መለማመጃ ቦታ ያዘጋጁ። መንገድን ከማቋረጥ በፊት ሁለቱንም አቅጣጫ መመልከት እና የእግረኛ መንገዶችን መጠቀምን የመሳሰሉ መሰረታዊ የመንገድ ደህንነት ህጎችን ይንገሯቸው። እነዚህን ህጎች በአሻንጉሊት መኪኖቻቸው እንዲለማመዱ ያበረታቷቸው። በመቀጠልም የባህላዊ ሙዚቃ ይክፈቱላቸው። ከባህላዊ ሙዚቃ መሳርያዎች ውስጥ አምስቱን ስም እንዲጠሩ ለየቡድኑ እድል ይስጧቸው።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** አሻንጉሊት መኪኖች፣ የትራፊክ ምልክቶች ሞዴል፣ባህላዊ ሙዚቃ መሳርያ፣ሞባይል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- መንገድ እንዴት ማቋረጥ እንዳለባቸው መጠየቅ፣የትራፊክ ምልክቶችን ትርጉም መጠየቅ፣ ባህላዊ ሙዚቃ መሳርያ ዓይነቶች መጠየቅ፣የሳምንቱን ቀናትን መጠየቅ...)

### ለ. እራሳቸውን ከአደጋ መጠበቅ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** አድራሻ፣ማወዳደር፣ክብደት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን አምስት አምስት አድርጎ ቡድን በመፍጠር አድራሻቸውን (ስማቸውን፣ የእናታቸውንና የአባታቸውን ስም እና ስልክ ቁጥራቸውን፣ሰፈራቸውን ወዘተ...) እርስ በርሳቸው እየተነጋገሩ እንዲለማመዱ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠልም የመማሪያ ቁሳቁስ ማዕዘን ላይ የሚገኙ አምስት ክብደታቸው የተለያየ ነገሮችን በማዘጋጀት ህጻናቱ እንዲያወዳድሩ ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ ከባድ እና ቀላል፣ትንሽ ትልቅ፣አጭር ረጅም/ እንዲለዩ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** መጠናቸው የተለያየ ቁሳቁስ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- ስማቸውን፣የእናታቸውንና የአባታቸውን ስም እና ስልክ ቁጥራቸውን፣ ሰፈራቸውን መጠየቅ፣አምስት ነገሮችን እንዲያወዳድሩና እንዲለዩ መጠየቅ...)

## ተግባር 2- ተረት (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. አውራ ዶሮና ቀበሮ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ድምጽ፣ምግብ፣መሞኘት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ተረቱን በአካል እንቅስቃሴ የድርጊቱን አፈጻጸም በሚያሳይ መልኩ ይንገሯቸው፡፡

## ተረት! ተረት!

በድሮ ጊዜ በጫካ ውስጥ የሚኖር አንድ ጆሮው ረጅም አይኖቹ ትላልቅ የሆነ ቀበሮ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ቀበሮው ምግብ ፍለጋ ወደ መንደር ሄደ፡፡ አንድ አውራ ዶሮ አጥር ላይ ቆሞ ኩኩሉ! ኩኩሉ! ሲል ሰማና ቀበሮው ወደ አውራ ዶሮው በመጠጋት ድምጽህ በጣም ደስ ይላል፡፡ እባክህ አንድ ጊዜ ከአጥሩ ላይ ውረድና ኩኩሉ በልልኝ ሲለው አውራ ዶሮውም ደስ ብሎት ከአጥሩ ላይ ወርዶ ኩኩሉ ሊል አፉን ሲከፍት ቀበሮው አንገቱን ይዞ ወደ ጫካው ሮጠ፡፡ የመንደሩ ልጆች ዶሮውን ለማስጣል ቀበሮ ቀበሮ እያሉ ጮሁ፡፡ በዚህን ጊዜ አውራ ዶሮው ቀበሮውን የናንተ ዶሮ አይደለም በላቸው አለው፡፡ ቀበሮውም የናንተ ዶሮ አይደለም ሊላቸው አፉን ሲከፍት አውራ ዶሮው ብርር ብሎ አመለጠው፡፡ ቀበሮውም በመሞኘቱ እያዘነ ወደ ቤቱ ተመለሰ ይባላል፡፡ ተረቴን መልሱ አፋን በዳቦ አብሱ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተረት መጽሃፍ፣ተረቱን የሚገልጽ ሥዕል፣ የቤት እንሰሳት ስእሎች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- አውራ ዶሮው ከቀበሮው እንዴት አመለጠ?፣ የቤት እንሰሳሰው የትኛው እንደሆነ መጠየቅ?)

## ተግባር 3- መዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. የሳምንቱ ቀናት (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የሳምንቱ ቀናት፣ባህላዊ ጥንካሬ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ከህጻናቱ ጋር በመዘመር ህጻናቱ በጋራና በግል እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡

የሳምንቱ ቀናት

ቀናቶችን እወዳለሁ፣

በስም መጥራት እችላለሁ

ከሰኞ እስከ አርብ እማራለሁ፤

ቅዳሜና እሁድ እዝናናለሁ፡፡፤፡፡

እሁድ ጠዋት እሮጣለሁ፤

ጥንካሬን አገኛለሁ፡፡

ባህላዊ ቅርስም አለኝ፤

የትም ብሄድ የሚያኮራኝ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** መቅርጸ ድምጽ፣ሞባይል፣ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- የሳምንቱ ቀናት ስንት እንደሆነ መጠየቅ፣ የሳምንቱን ቀናት ስም ተናገር/ሪ?፣ ስለ ባህላዊ ቅርስ፣ የአካል ዕድገት ጥንካሬ መጠየቅ፣መዝሙሩን በአግባቡ መዘመራቸውን መከታተል...)

### ለ. የቤት እንስሳት (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የቤት እንሰሳት፣ባህል፣ቅርስ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለመዝሙሩ ዜማ በማውጣት ከህጻናቱ ጋር በመዘመር ህጻናቱ በጋራና በግል እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡

የቤት እንስሳት

የቤት እንስሳት ምን ይላሉ፤

መዘመር ይችላሉ፡፡

ድመት ትዘምራለች፤

ሚያው! ሚያው! ትላለች፡፡

እኔም መዝፈን እችላለሁ፤

ባህሌንም አውቂያለሁ፤

ስለ ቅርስም ተምሬያለሁ፡፡

በከበሮ፤ ክራር፤ ዋሽንት

በሙዚቃም እዝናናለሁ፡፡


- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቤት እንስሳት ድምጽ፣ ሞባይል፣ የሙዚቃ መሳርያን የሚያሳይ ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- የቤት እንሰሳትን ስም ጥራ/ሪ?፣ የሙዚቃ መሳርያን የሚያሳይ ሥዕል በማሳየት ስማቸውን መጠየቅ)

## ተግባር 4- የክፍል ውስጥ ጨዋታ (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቢንጎ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** እንስሳት፣ እራሳቸውን መጠበቅ፣ ቃላት፣ የሙዚቃ መሳሪያ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለተግባሩ አስፈላጊ የሆኑትን ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች /የእንሰሳትና ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያ/ ቢንጎ ካርዶች ላይ በማዘጋጀት ለህጻናቱ ያከፋፍሉዋቸው፡፡ እርስዎም የሥዕሎቹን ስም በካርድ ላይ ያዘጋጁ፡፡ እርስዎ ከካርዶቹ ላይ የተጻፉትን ቃላት ሲጠሩ ህጻናቱ የተጠራውን ቃል የሚወክለውን የቢንጎ ካርድ ሥዕል ጠረጴዛ ላይ እንዲደረድሩ ያድረጉ፡፡ ሁሉንም በትክክል የደረደረ አሸናፊ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም ከተሠጡዋቸው የቢንጎ ካርዶች አደጋ ሊያደርሱባቸው የሚችሉትን እንሰሳት እንዲለዩና እራሳቸውን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡





- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቢንጎ መጫወቻ ካርዶች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- የስዕሎቹን ካርዶች ተራ በተራ እንዲያሳዩ መጠየቅ፣የእንስሳትና ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያ ስማቸውን መጠየቅ...)

### ለ. ሙዚቃ እና ዳንስ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሙዚቃ፣ እንቅስቃሴ፣ጥንቃቄ፣ብሔር ብሄረሰቦች
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የተለያዩ ብሔር ብሄረሰቦች ሙዚቃዎችን ከቴፕ/ከስልክዎ በማሰማት ህጻናቱ ዜማውን በመከተል እንዲደንሱ/እንዲንቀሳቀሱ ያበረታቷቸው፡፡ ህጻናቱ እንዳይገፋፉና እንዳይወድቁ ጥንቃቄ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም በስንት ብሔር ብሄረሰቦች ዘፈን እንደጨፈሩ ይጠይቋቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ቴፕ ሪከርደር/ስልክ
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (እያዜሙ እንዲንቀሳቀሱ መጋበዝ...) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ስንት ጭፈራ እንደጨፈሩ መጠየቅ...)

## ተግባር 5- እንግዳ በመጋበዝ (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ባህል (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ባህላዊ ወጎች፣ ከአደገኛ ነገር መጠበቅ፣የአካል ዕድገት ማዳበር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** እንግዳ በመጋበዝ ባህላዊ ወጎችን እና እራሳቸውን ከአደገኛ ነገሮች መጠበቅያ ዘዴዎችን ለህጻናቱ እንዲያካፍሉ በማድረግ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ወላጆችን ወይም ከተለያዩ አካባቢ የመጡ የማህበረሰብ አባላትን በመጋበዝ እራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ከህጻናቱም ጋር እንዲተዋወቁ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ባህላዊ ወጎችን፣ እራሳቸውን ከአደገኛ ነገር መጠበቅያ ዘዴዎችን፣የአካል ዕድገትን እንዴት

ማዳበር እንደሚለማመዱ ለህጻናቱ  እንዲያካፍሉ ያድርጉ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** መቅረጸ ድምጽ፣ ሞባይል
- **የምዘናስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- ከሰሙት ታሪኮች ውስጥ የሚያስታውሱትን መልሰው እንዲናገሩ ማበረታታት)

## ተግባር 6- ፕሮጀክት (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ነገሮችን መለየት (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መጠን፣ መለየት፣ መደርደር፣ ማወዳደር፣ ባህላዊ ቅርሶች
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** ህጻናቱ በራሳቸው እንዲማሩ በማድረግ፣ በማሳተፍ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለህጻናቱ የነገሮች ስብስብ (ለምሳሌ፡- አዝራሮች፣ ጨሌዎች፣ ቆርኪዎች፣ የእንጨት ቁርጥራጮች፣ የፕላስቲክ ጠርሙሶች) ይስጧቸው እና ዕቃዎቹን እንዲቆጥሩ፣ እንዲለዩና እንዲደረድሩ ያበረታቷቸው፡፡ ከዚያም ዕቃዎቹን እንደ ቀለም፣መጠን ባሉ ልዩ ባህሪያት ላይ በመመስረት እንዲመድቡ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም  ባህላዊ ቅርሶች ሥዕል በማዘጋጀት  ስማቸውን፣የት እንደሚገኙ በማስረዳት እየቆራረጡ ካርቶን ላይ እንዲለጥፉ ይርዷቸው፡፡
- **የመማርያ እና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያዩ ነገሮች ስብስብ
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ ማድረግ (ስራቸውን መቅረጽና ማስቀመጥ...)፣  እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የተለያዩ የፕላስቲክ ጠርሙሶችን በማቅረብ በቁመታቸው እንዲደረድሩመጠየቅ...)

# አራተኛ ሳምንት

## የተሰጠው ሰዓት-10 ሰዓት (30 ክፍለ ጊዜ)

### የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ከሌሎች ህጻናት ጋር ይጫወታሉ
- ለሰሙት ነገር ምላሽ ይሰጣሉ
- የእጽዋት ክፍሎችን ስም ይናገራሉ
- የመሰረታዊ ጂኦሜትሪ ምስሎችን ስም ይለያሉ
- በትንሽ እርዳታ/ቀላልደጋፍ/ ትናንሽ የዕለት ተዕለት ተግባሮችን ያከናውናሉ
- ነጠላ ድግግሞሻዊ ቅደም ተከተል ሰርተው ያሳያሉ
- ሙዚቃዊ ምትን በመከተል በተመሳሳይ አቅጣጫ ቀላል እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ

### ንዑስ ይዘቶች

- የተግባቦት ክህሎት
- ተክሎች
- ድምጽ መለየት
- የትናንሽና ትላልቅ ጡንቻዎች መጎልበት
- የሙዚቃ ምትን የተከተሉ እንቅስቃሴዎች መስራት
- ድግግሞሻዊ ቅደም ተከተል (Patterns)
- ቅርጻ ቅርጽ
- ለኪነ ጥበብ ዋጋመስጠት (Artistic value)
- እራስን መቻል

## ተግባር 1- የግል ተግባር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ድምጽ ልየታ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ድምጽ፣ እንቅስቃሴ፣ የሙዚቃ ምት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የተለያዩ ነገሮች ቀለም በተቀቡ የፕላስቲክ መያዣዎች ውስጥ ያስቀምጡ (ለምሳሌ፡- በሁለቱ ውስጥ ሩዝ፣ በሁለቱ ውስጥ ባቄላ፣ በሁለቱ ውስጥ ጤፍ)፡፡ ህጻናቱ በየተራ እያንዳንዱን ጠርሙስ እያወዛወዙ የሚሰሙትን ድምፅ ለማስታወስ ይሞክሩ፡፡ ከዚያም ተመሳሳይ ድምጽ የሰሙባቸውን ጠርሙሶች እንዲያዛምዱ የበረታቷቸው፡፡ በመጨረሻም ሙዚቃ ይክፈቱላቸው ምቱን ተከትለው ቀላል እንቅስቃሴ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- የፕላስቲክ ጠርሙሶች፣ በውስጣቸው የሚጨመሩ (ጥራጥሬዎች) ነገሮች፣ ሞባይል
- የምዘና ስልት:- የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ ድምጾቹን መለየታቸውን መጠየቅ...)

### ለ. ንድፍ /ቅጥ/ (pattern) (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:-ንድፍ፣ እራስን መቻል፣ቀለማት
- የማስተማርያ ዘዴ:- በተግባር
- የመምህር ሚና:- መምህር! የተለያዩ ቀለማትን የተቀቡና የተለያየ ቅርፅ ያላቸው ነገሮች ያዘጋጁ:: ከዚያም ህጻናቱ ቅደም ተከተል በመጠቀም ቀላል ንድፍ (Pattern) እንዲፈጥሩ ያበረታቷቸው::

(ለምሳሌ:- 1. (አረንጓዴ፣ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ቀይ...)



(ለምሳሌ:- 2. (ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ቀይ፣ አረንጓዴ...)



በመጨረሻም የሰሯቸውን ድግግሞሽ (pattern) እራሳቸውን ችለው ማዕዘናት ላይ እንዲያስቀምጡ ያበረታቷቸው::

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- የተለያዩ ቀለማት የተቀቡ የተለያየ ቅርፅ ያላቸው ነገሮች
- የምዘና ስልት:- ንድፉን በግል እንዲሰሩ መጠየቅ... ምልከታ በትክክል መስራት መቻላቸውን መከታተል...

## ተግባር 2- ተረት (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ተክሎች (4 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- ተግባቦት፣ተክሎች፣ ድምጽ
- የማስተማርያ ዘዴ:- በተረት
- የመምህር ሚና:- መምህር! ተረቱን ህጻናቱን በሚስብ መልኩ በአካል እንቅስቃሴ የድርጊቱን አፈጻጸም በሚያሳይ መልኩ ይንገሯቸው

## ተረት! ተረት!

ከዕለታት አንድ ቀን በጣም የሚዋደዱ አበበ፣ ፋጡማ እና አብረሃም፣ የሚባሉ ጓደኛሞች በድ ንገት ተጣሉ:: ፋጡማ እና አብረሃም እኛ እየለፋን የብረቱካኑን ተክል ውሃ እያጠጣን እና እየ ተንከባከብን ተክሉ ፍሬ ሲያፈራ ከኛ እኩል ይበላል አሉ:: ከአበበ ጋር ከምንጣላ ዛፉን መን ከባከብ እናቁም አሉ:: ከትንሽ ጊዜ በኃላ የተክሉ ቅጠሎች መጠውለግ ጀመሩ:: ዛፉ ሲንቀሳ ቀስ ይሰሙት የነበረው ድምጽ አቆመ::ከዛፉጥላ ስር ከሌሎች ጓደኞቻቸው መጫወት አልቻሉም:: ተክሉም ፍሬ ማፍራት አቆመ:: በዚህም ምክንያት በጣም ተናደው ይጨቃጨቁ ጀመር:: በመጨረሻ ጭቅጭቃቸውን ሲያዳምጥ የነበረው ጓደኛቸው ተው! ይሄ ጥል ለሁላችንም አይጠቅምም ተግባብተንና ተስማምተን አብረን ተክሉን ውሃ በማጠጣት መንከባከብ ይሻለናል ብሎ በመምከር አስታረቃቸው ይባላል::

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተረት መጽሀፍ፤ስዕላዊ መግለጫ
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ (ተረቱን ደግመው እንዲናገሩ እድል መስጠት፣ምን ያህል እንደተከታተሉ ለማረጋገጥ...) የቃል ጥያቄ (የተጣሉት እነማን ናቸው?፣ያስታረቃቸው ማነው?...)

## ተተግባር 3 ርመዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. አሻንጉሊት (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ተክሎች፣መተባበር፣ድምጽ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! መጀመሪያ መዝሙሩን ከዘመሩላቸው በኋላ ህጻናቱን በቡድንና በግል ያዘምሯቸው

ይቺ አሻንጉሊት  
ይቺ አሻንጉሊት በጣም ቆንጆ ናት (2)  
እኔና አንተ እንጫወትባት፤  
ስንነካካት ጥሩ ድምጽ አላት፤  
አሻንጉሊትህን እኔ ልያዛት፤  
የኔንም እንካ ተጫወትባት::  
በግቢያችን ውስጥ ያለውን ተክል፤  
ውሃ እያጠጣን ሌላም እንትከል፤  
ጓደኛ መሆን በጣም ደስ ይላል፤  
ተባብሮ መስራት ያጠናክራል:: (2)

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ቴፕ ሪከርደር /የእጅ ስልክ/፣ተንቀሳቃሽ ሥዕል
- **የምዘና ስልት:-** የግል ተግባር መስጠት (ለምሳሌ:- በግል እንዲዘምሩ መጠየቅ፣ ስለጓደኛቸው እንዲገልጹ መጠየቅ፣ የጓደኝነትን ጥቅም መጠየቅ...)

### ለ. እኛ ህጻናት (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ጨዋታ፣ስራ፣ማክበር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! መጀመሪያ ዜማ በማዘጋጀት መዝሙሩን ከዘመሩላቸው በኋላ ህጻናቱ በቡድንና በግል ያዘምሯቸው፡፡

እኛ ህጻናት

እኛ ህጻናት እንዋደዳለን፣
አንድ ላይ ሆነን እንጫወታለን፡፡
ሁሌም ደስታ የለም መጣላት፣
እናከብራለን እናትና አባት፡፡
ጠዋት ተነስተን፣
ፊታችን ታጥበን፣
ቀላል ስፖርትም እንሰራለን፡፡
በዕረፍት ጊዜያችን ሁሌም ጨዋታ፣
ስራ እንሰራለን ስንገባ ማታ፡፡
በፀባይና በትምህርታችን፣
ይመኩብናል መምህሮቻችን፡፡ (2)

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ቴፕ ሪከርደር/የእጅ ስልክ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል (ለምሳሌ፡- የመከባበር፣ ከሌሎች ህጻናት ጋር መጫወት…)

## ተግባር 4- ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የጓደኞች ጨዋታ

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መግባባት፣ ቅርጽ፣ እንቅስቃሴ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን ወደ ውጭ በማስወጣት አምስት አምስት ሆነው በቡድን የተለያየ ቅርጽ እንዲፈጥሩና ቀላል እንቅስቃሴ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ፖሊስ፣ ሐኪም፣ ነጋዴ፣ መምህር ወይም የመኪና አሽከርካሪ የመሳሰሉትን በማስመሰል እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን ያመቻቹ፡፡ የተሰጣቸውን ተግባራት ለማከናወን ህጻናቱ በመግባባት እንዲጫወቱ ያበረታቷቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** አልባሳት (ጋዋን፣የደምብ ልብሶች፣ የህክምና ማሰሪያ ሞደሎች) እና ሌሎች ከሙያውዎች ጋር የሚሄዱ ቁሳቁስ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- ስሜታቸውን እንዲገልፁ መጠየቅ፣ የቡድኖችን ብዛት መጠየቅ፣ የሚወዱትን ሙያ መጠየቅ…)

## ተግባር 5- ፕሮጀክት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ሙዚቃ እና እንቅስቃሴ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- አቅጣጫ፣ ቀላል እንቅስቃሴ፣ ጡንቻ መዳበር
- የማስተማርያ ዘዴ:- ሙዚቃ በማሰማት ህጻናቱ ነጻ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ማሳተፍ
- የመምህር ሚና:- መምህር! ህጻናቱን በአምስት ቡድን በመክፈል በጋራ የሙዚቃ ምትን በመከተል በተመሳሳይ አቅጣጫ ቀላል እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ የሚጋብዝ ባህላዊ ሙዚቃ ያሰሙዋቸው:: ይህም ጡንቻቸውን ለማጠንከር እንደሚረዳ ግንዛቤ ይስጧቸው:: ይህንንም የቡድናቸው ተለማምደው እንዲጨፍሩ ያድርጉ::
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-ቴፕ ሪከርደር /የእጅ ስልክ/
- የምዘና ስልት:- ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- የሙዚቃ ምቱን በመከተል በየግላቸው እንዲንቀሳቀሱ መጠየቅ፣ የሚያውቋቸውን ባህላዊ ዘፈኖች እንዲዘፍኑ መጠየቅ...

### ለ. የመልበስ ልምምድ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- እንቅስቃሴ፣ ቁልፍ መፍታት፣ መቆለፍ፣ድምጽ
- የማስተማርያ ዘዴ:- በጨዋታ
- የመምህር ሚና:- መምህር! በመጀመርያ ህጻናቱን ለማነቃቃት ቀለል ያሉ እንቅስቃሴዎች ያሰሯቸው:: በመቀጠልም መልበስና ማውለቅ እንዲለማመዱ ያበረታቷቸው:: ለምሳሌ እንደ ካልሲ ወይም ጫማ ማድረግና ማውለቅ ካሉ ቀላል ተግባራት ጀምሮ ቀስ በቀስ እንደ ሸሚዞች መልበስ፣ ማውለቅ፣ ቁልፍ መፍታት እና መልሶ መቆለፍ መሸጋገር:: በመጨረሻም ድምጾችን ያሰሚቸውና የሰሙትን ነገር ምላሽ እንዲሠጡ ያበረታቷቸው::
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- ሞዴል ልብሶች፣ጫማዎችና አሻንጉሊቶች
- የምዘና ስልት:- በግል የሚሰሩ ተግባራትን መስጠት (ለምሳሌ:- ሸሚዞች እንዲለብሱ፣ እንዲያወልቁ፣ ቁልፍ ፈተው እንዲቆልፉ፣ጫማቸውን ፈተው እንዲያስሩ መጠየቅ)

## ተግባር 6- በስራ መማር (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የዕፅዋት እንክብካቤ (4 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- እጽዋት፣ ሙዚቃ፣ ዳንስ
- የማስተማርያ ዘዴ:- በስራ
- የመምህር ሚና:- መምህር! ህጻናቱ ወደ ውጭ ይዘዋቸው ይውጡ አምስት ሆነው ቡድን እንዲሰሩ ያዘጋጇቸው በመቀጠልም ግማሽ ሊትር በሚይዙ የፕላስቲክ ጠርሙሶች ክዳናቸውን በመብሳት ውኃ ሞልተው ይክደኑና ለህጻናቱ ይስጧቸው:: ህጻናቱ በክዳኖቹ ቀዳዳዎች እያንጠባጠቡ አትክልቶችንና እና አበቦችን ውኃ በማጠጣት በእጽዋት እንክብካቤ ውስጥ እንዲሳተፉ ያድርጉ:: ህጻናቱ የሚያጠጧቸውን ዕጸዋቶች አካል ክፍል እንዲለዩ ያግዟቸው:: በመጨረሻም በሚወዱት ሙዚቃ እየደነሱ ወደ ክፍላቸው እንዲመለሱ ያድርጉ::
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- የፕላስቲክ ጠርሙስ፣ውሃ፣ተክሎች፣ቴፕ ሪከርደር/ሞባይል
- የምዘና ስልት:- የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- የተክሎች ክፍሎችን ስም መጠየቅ፣ የቡድናቸውን አባላት ብዛት መጠየቅ፣ የሚወዱትን ዳንስ እንዲያሳዩ መጠየቅ)::

# አምስተኛ ሳምንት

የተሰጠው ሰዓት-10 ክፍለ ጊዜ (30)

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ለጥሩ እና መጥፎ ስራዎች ምሳሌ ይሰጣሉ
- የእናት ፊደሎችን ድምፆች ይለያሉ
- አምስት ሰው ሠራሽ ቁሳቁስን ይለያሉ
- በአቀማመጣቸው ላይ በመመስረት ከ3-5 የሰውነት ክፍሎችን ያሳያሉ
- የተሰጧቸውን ነገሮች በሚጠየቁት መሰረት በሁለት ምድቦች ይከፍላሉ
- ከ5-9 በሰማይ ላይ ያዩዋቸውን ነገሮችን ስም ይናገራሉ
- ስለ ተፈጥሮ ቀለሞች በቡድን በመዘመር በዳንስ ያሳያሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- የሥነ ምግባር እሴት
- የድምፅ ግንዛቤ
- የተፈጥሮእናሰው ሰራሽ አካባቢዎች
- የቦታ ግንዛቤ
- መለየት እና መመደብ
- ግንኙነት፣ዝምድና እና መተግበሪያ

## ተግባር 1- የግል ተግባር (8 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የፊደሎች ድምጽ (4ክ/ገዜ)


- **ቁልፍ ቃላት፡-** እናት ፊደላት፤የፊደላት ድምጽ፣ምድብ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ድምጻቸው በእናት ፊደላት የሚጀምሩ የተለያዩ ስዕሎችን ፍላሽ ካርዶች ከታች ባለው ሥዕል አይነት ያዘጋጁና ለህጻናቱ ያድሉ፡፡ እርስዎ ደግሞ እናት ፊደላት የተጻፉበት ካርድ (ለምሳሌ በ፣ሰ፣ሸ፣ከ) በመያዝ ተራ በተራ የእናት ፊደላቱን ድምጽ ያስሟቸው፡ ፡ በሰሙት ድምጽ የሚጀምሩ ስዕሎችን እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፡፡ የተሰጧቸውን ሥዕሎች በሚጠየቁት መሰረት በሁለት ምድቦች ይክፈሏቸው (ለምሳሌ፤አራት እግር ያላቸውንና ሁለት እግር ያላቸው)፡፡



- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ፍላሽ ካርዶች፣መቅረጸ ድምጽ/ሞባይል
- **የምዘና ስልት:- ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:-** በእናት ፊደላት የሚጀምሩ ነገሮችን ስም በመጥራት ድምጹን እንዲናገሩ መጠየቅ፣የተሰጧቸውን ነገሮች በሚጠየቁት መሰረት በሁለት ምድቦች እንዲመድቡ ማድረግ፣ የተፈጥሮ ቀለሞችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ...)

## ለ. መለየት እና መመደብ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** መለየት፣ቅርጽ፣ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተግባር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! የተለያየ ቀለም እና ቅርጽ ያላቸውን የጅኦሜትሪ ምስሎችን በቀለማቸውና እና በቅርጻቸው ከታች ባለው አይነት ደበላለቀው ካስቀመጡ በኋላ ህጻናቱን ሶስት ሶስት ሆነው መጀመሪያ በቀለም ከዚያም በቅርጻቸው እንዲለዩና እንዲመድቡ ያበረታቷቸው። በተጨማሪ የተለያየ መጠን ያላቸው ነገሮች በመሰብሰብ ተመሳሳይ ቁመት ያላቸውን ለይተው እንዲመድቡ የተግባር ስራ ሊሰጧቸው ይችላሉ።



- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ለመለየትና ለመመደብ የሚሆኑ ከካርቶን የተቀረጹ የጅኦሜትሪ ቅርጾች
- **የምዘና ስልት:-** ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- የተለያዩ የጅኦሜትሪ ቅርጾችን በማቅረብ ልየታና ምደባ እንዲያከናውኑ መጠየቅ...)

## ተግባር 2- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ማሪቱ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፣ መልካምነት
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተረት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! በመጀመርያ ህጻናቱን የግብረገብ ዕሴቶች ላይ ለምሳሌ ቅንነት፣ታማኝነት፣መልካምነት... ላይግንዛቤ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ተረቱን ይንገሯቸው፡፡

## ተረት! ተረት!

በትምህርት ቤታችን ማሪቱ የምትባል ደግ ልጅ ነበረች፡፡ ማሪቱ ከወላጆቿ ጋር ትኖር ነበር፡፡ የነማሪቱ ቤት ወንዝ ዳር ነው፡፡ በዚህም ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮችን በቀላሉ ማየት ትችላለች፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን የነማሪቱ ቤት በድንገት ሌባ ገባ፡፡ ማሪቱና ወላጆቿ የቤት ቁሳቁስን ለመግዛት ሄደው ስለነበር እቤት ማንም አልነበረም፡፡ ነገር ግን የማሪቱ ቤተሰቦች በጣም መልካምና ከጎረቤቶቻቸው ጋር ጥሩ ግንኙነት ስለነበራቸው ሁሉም ተሯሩጠው ሌባውን በመያዝ ለፖሊስ አስረከቡት፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተረት መጽሃፍ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- የነማሪቱ ቤተሰብ ከጎረቤቶቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ዐይነት እንደሆነ መጠየቅ፤የነማሪቱ ቤት መገኛ ቦታ የት ነው?፤ ማሪቱና ወላጆቿ ወደ ገበያ የሄዱት ለምንድን ነው?)፡፡

### ለ. ታማኙ ልጅ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ታማኝነት፣ጥሩ ባህሪ፣ስነ ምግባር
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተረት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! በመጀመርያ ህጻናቱን የስነ ምግባር እሴቶች ላይ ግንዛቤ ያስጨብጡ (ለምሳሌ፣ታማኝነት፣ ቅንነት...) በመቀጠል ተረቱን ድርጊቱን በሚገልጽ እንቅስቃሴና የፊት ገጽታ ለህጻናቱ ይንገሯቸው፡፡

ተረት! ተረት!

በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖር ማርቆስ የሚባል ልጅ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ማርቆስ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ አንድ በገንዘብ የተሞላ ቦርሳ መንገድ ላይ ወድቆ አገኘ፡፡ ማርቆስ ያገኘውን ቦርሳ ቢሮ ወስዶ ለመምህሩ አስረከበ፡፡ መምህሩም በማርቆስ ታማኝነት በመደነቅ ሰልፍ ላይ ስለ ጥሩ ባህሪያት ለህጻናቱ በመንገር ሁሉም እንደ ማርቆስ ታማኝ እንዲሆኑ መከሯቸው፡፡ማርቆስም በዚህ ስነ-ምግባሩ እንዲቀጥል አበረታቱት፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-**የተረት መጽሃፍ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- አስተማሪዋ ማርቆስን ለምን አበረታቱት?፣ አንተ/አንቺ ክፍል ውስጥ እርሳስ ወድቆ ብታገኝ/ኚ ምን ታደርጋለህ/ጊያለሽ?... በማለት ይጠይቁ)፡፡

## ተግባር 3- መዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ጎበዝ ልጅ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ስነ ምግባር፣ጥሩ፣ መጥፎ፣ ንጽህና
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በመዝሙር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! መዝሙሩን በቴፕ ሪከርደር/ በእጅ ስልክ በማሰማት ህጻናቱን በቡድንና በግል ያዘምሩ፡፡

ጎበዝ ልጅ
እኔ ጎበዝ ልጅ ነኝ፣
በስነ ምግባር ያደኩኝ፡፡
ጥሩና መጥፎን እለያአለሁ፣
ቤተሰቤንም አከብራለሁ፡፡
ሁሌ በጠዋት በመነሳት፣
ለምጃለሁ እስፖርት መስራት፡፡
ፊትና እጄን እታጠባለሁ፣
ንጹህ መሆኑን አሳያለሁ፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ቴፕሪከርደር/የእጅ ስልክ
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- ህጻናቱ ጥሩ ባህሪያትን እንዲናገሩ መጠየቅ፣ እጃቸውን ለምን እንደሚታጠቡ መጠየቅ…)

### ለ. ተፈጥሮ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፤ድምጽ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በመዝሙር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህጻናቱን በቡድንና በግል ያዘምሯቸው

ተፈጥሮ
ፀሃይ በጠዋት ወጣች፣
ምድርን አደመቀች፡፡
ጨረቃም በማታ፣
ፀሃይን ተክታ፡፡
ክዋክብትም ደምቀው፣
ይታያሉ ርቀው፡፡
እናድንቅ ተፈጥሮን፣
ያዝናናል አዕምሮን፡፡
ሰውም የሰራቸው፣
ስልክ ቴሌቪዥን፣
ድንቅ ስራ ናቸው፣
ሁሌ ስሰማቸው፣
ይገርማል ድምጻቸው፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- ቴፕ ሪከርደር /ሞባይል፣ ተፈጥሮንና ሰው ሰራሽ ነገሮችን የሚሳዩ ሥዕላዊ መግለጫ (ሰማይ፣ኮከብ፣ ጨረቃ፣ ፀሀይ…መኪና፣ ሞባይል፣…)
- የምዘና ስልት:- የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- የሚያውቁትን ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ የሆኑ ነገሮችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ…)

## ተግባር 4- ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ሚና ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- ሥነ ምግባር፣ ዕሴቶች፣ጥሩ ስራ፣ መጥፎ ስራ፣መለየት፣ መመደብ
- የማስተማርያ ዘዴ:- በጨዋታ
- የመምህር ሚና:- መምህር! እንደ ጀግንነት፣ ታማኝነት ወይም ርህራሄ ያሉ አዎንታዊ የሥነ ምግባር ዕሴቶችን ከሚያሳዩ ታሪኮች ወይም እውነተኛ የበጎነት ገፀ-ባህሪያትን ይምረጡ:: ልጆች እነዚህን ገፀ ባህሪያት እንዲላበሱ እና እነዚህን እሴቶች የሚገለጹ ድርጊቶችን/ሚና ጨዋታ እንዲያሳዩ ያድርጉ:: በመጨረሻም ጥሩና መጥፎ ስራዎችን መለየትና መመደብ እንዲችሉ ያግዟቸው::
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- ታሪኩን የሚገልጹ አልባሳት፣ታሪካዊ መጽሃፍ
- የምዘና ስልት:- የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- የሚያውቋቸውን በበጎ ስራና በጀግንነት የሚታወቁ ግለሰቦችን ስም እነዲጠሩ መጠየቅ…)

## ተግባር 5- ፕሮጀክት (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ግንባታ (4 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- የቦታን ግንዛቤ፣ የተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ
- የማስተማርያ ዘዴ:- በፕሮጀክት
- የመምህር ሚና:- መምህር! የግንባታ ብሎኮችን ወይም የግንባታ መጫወቻዎችን ያቅርቡላቸው:: ለሁሉም ምቹ ቦታ ይምረጡላቸው:: የቦታን ግንዛቤ እንዲኖራቸውም ያድርጉ:: የሚሰሩትን ተግባር ያስረዷቸው ቤቶች፣ ህንጻዎች፣ መንገዶች እና ድልድዮችን እንዲገነቡ ያግዟቸው:: እንደ ተራሮች እና ወንዞች ያሉ የተፈጥሮ አከባቢዎችን ወደ ፈጠራቸው እንዲያካትቱ ያበረታቷቸው:: ከጨረሱ በኋላ በሁለት ምድቦች እንዲከፍሏቸው ያድርጉ::
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- የካርቶን ጡብ፣ የእንጨት ብሎኮች፣ ካርቶን፣ ማርከር
- የምዘና ስልት:- የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ የሆኑ አከባቢዎችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ… /

## ተግባር 6- በስራ መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. በሰማይ ላይ የሚገኙ ነገሮችን መስራት (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- ሰማይ፣ መታጠብ፣ህይወት ያላቸው፣ ህይወት የሌላቸው

- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በስራ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናት ከክፍል ውጪ ሰፊ እና ምቹ የሆነ ቦታ ይስጧቸው:: ከወረቀት፤ ከጭቃ፤ ወይም ቀለል ባሉ ዕቃዎች በመጠቀም በሰማይ ላይ የሚታዩ ከ5 - 9 ያሉ ነገሮችን  ፀሃይ፤ ጨረቃ፤ አውሮፐላን፤ የተለያዩ ወፎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው:: እነሱንም ህይወት ያላቸውና የሌላቸውን በሁለት ምድብ እንዲመድቧቸው ያድርጉ:: ከወረቀት በሰሩት አውሮፕላን  ወደ ላይ በመወርወር እንደ አውሮፕላን እንዲያበሩ በየተራ እድሉን ይስጧቸው:: ተግባሩን ሲጨርሱ እጃቸውን በውሃና በሳሙና ይታጠቡ::
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ወረቀት፣ክላሰር፣ካርቶን፣አፈር፣ውሀ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡-በሰማይ ላይ የሚገኙ ነገሮችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣የሰሩትን ነገሮች ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ በማለት በሁለት ምድቦች እንዲከፍሉ መጠየቅ...)::

### የአውዱ ማጠቃለያ የምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም ------------------------------ጾታ-------- እድሜ ------ደረጃ-------

መግለጫ፡- ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሟሉት ብቃት ትይዩ የ “√” ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ::

| ተ.ቁ | የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት | ጥሩ | በ/ጥሩ | እ/በ/ጥሩ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ስማቸውን እና እድሜያቸውን መናገር | | | | |
| 2 | የሳምንቱን ቀናት መናገር | | | | |
| 3 | የፊደላትን ድምጽ መለየት | | | | |
| 4 | ነጠብጣብ ፊደላትን ማያያዝ | | | | |
| 5 | እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን በቁስ መቁጠር | | | | |
| 6 | በአከባቢቸው የተለመዱፉ  የምግብና የመጠጥ አይነቶችን ይናገራሉ | | | | |
| 7 | የቤት እንሰሳትን ስሞች ይጠራሉ | | | | |
| 8 | የጂኦሜትሪ ምስሎችን ይለያሉ | | | | |
| 9 | የሚወዱትና የማይወዱትን ነገር ይለያሉ | | | | |
| 10 | ጥሩ እና መጥፎ ስራዎችን ይለያሉ | | | | |
| 11 | በአዋቂዎች ድጋፍ ጥርስን መቦረሽና ልብስ መልበስ | | | | |
| 12 | እርሳስን በትክክል መያዝ | | | | |
| 13 | መስመር ጠብቀው መሞነጫጨር | | | | |
| 14 | መስመር ጠብቀው ቀለም መቀባት | | | | |
| 15 | ሙዚቃዊ ምትን ጠብቀው መንቀሳቀስ | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፡- ______________________________________________

______________________________________________________________________

____________________________

# አውድ ሁለት

# ቤቴና ቤተሰቦቼ

አጠቃላይ የተሰጠው ጊዜ- 5 ሳምንት

የክፍለ ጊዜ ብዛት-150

## 2.1 መግቢያ

ቤቴና ቤተሰቦቼ በሚለው አውድ ውስጥ የተካተቱ የትምህርት መስኮች የሕፃናቱን አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ስነልቦናዊና ማህበራዊ ዕድገትን ማዳበር የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በትምህርት መስኮቹ ስለራስ እና ማህበራዊ ግንዛቤ ማዳበር፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ ራስን መግዛትና የመልካም ስነምግባር ምንነት፣ ፊደላትንና ቁጥሮችን ማንበብና/መጥራትና መፃፍ፣ የጤንነት ግንዛቤ፣ የጥበብ ሥራ ግንዛቤ፣ አከባቢን፣ ተክሎችንና እንስሳትን ማወቅ፣ አመጋገብን መለማመድ፣ እንዲሁም የሰውነት ክፍሎችን፣ ቃላትን፣ ድምፆችን፣ የጅኦሜትሪያዊ ቅርጾችን፣ ተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ነገሮችን መለየት ተካተውባቸዋል፡፡ መምህራን በዚህ አውድ ስር የተቀመጡትን አጥጋቢ የመማር ብቃቶችንና የትግበራ ስልቶችን መሰረት በማድረግ በአምስቱም ሳምንታት ውስጥ የዕለት ተዕለት ተግባራትን ማለትም መዝሙር፣የግልተግባር፣ተረተረት/እንቆቅልሽ፣ከክፍል ውጪ ጨዋታ፣በፕሮጀክት መማር፣ በስራ መማር፣በውይይት መማር፣በመስክ ጉብኝት፣በክፍል ውስጥ ጨዋታ መማር እና የተፈለገውን ዕድገትን ማዳበር እንድችሉ ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡፡

## 2.2 የአውዱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ፊደልን ለይተው ይጠራሉ
- ፊደልን ይጽፋሉ
- 1-5 ያሉ ቁጥሮችን በቁሳቁስ ይቆጥራሉ
- ቁሳቁስንበመጠንናበዓይነትይለያሉ
- ቁሳቁስን በመጠን አወዳድረው ያስቀምጣሉ/ይደረድራሉ
- የመጓጓዣዓይነቶችንበስም ይጠራሉ
- አትክልትና ፍራፍሬ ዓይነቶችን በስም ለይተው ይጠራሉ
- ሰው ሰራሽ ነገሮችን ለይተው ይጠራሉ

- የተቆራረጡ ነገሮችን በክፍል በክፍል በመግጠም ቅርጽ ያወጣሉ
- ከመምህራንና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሰለምታ ይለዋወጣሉ
- ከጓደኞቻቸው ጋር ተራ ጠብቀው ማውራትን፣መስራትንና መጫወትን ይጀምራሉ
- በትህትና መመለስንና መጠየቅን ይጀምራሉ
- ስሜታዊንግግርንይለያሉ /የሃዘንን፣ የደስታን፣የፍርሃትንየድንጋጤን/
- የሰውነት ክፍሎችን በስም ይጠራሉ
- የእጅ መታጠብን /ከምግብ በፊትና በኋላ እንዲሁም ከሽንት ቤት መልስ/ይጀምራሉ
- ስማቸውንናዕድሜአቸውንይናገራሉ ሲጽፉ እርሳሳቸውን በአግባቡ ይይዛሉ
- ቅርፃቅርጾችን ቀለም ይቀባሉ
- ቁሳቁስንበቀለም፣በቅርጽ፣ በለስላሳና በሸካራነት ተረድተው ይለያሉ

## 2.3 የአውዱ ዓበይት ይዘቶች

- ስለራስ እና ማህበራዊ ግንዛቤ ማዳበር
- ራስን ማስተዋወቅ
- ራስን መግዛትና መልካም ስነምግባር ማዳበር
- የግል ሰውነት ክፍሎችን መለየትና መጥራት
- ፊደልና ቁጥርን ማንበብ/መጥራትና መፃፍ
- የግል ንጽህና መጠበቅ
- የጥበብ/ፈጠራ ሥራዎች ግንዛቤ ማዳበርና ማሳወቅ
- አከባቢን ማወቅ
- ድምጾችን መለየት
- ያለ ዕገዛ አመጋገብን መለማመድ
- አካላዊ እድገት ማዳበር
- ቃላትን መጥራት
- እንስሳትን መለየት
- ተክሎችን መረዳት
- የቁሳቁስና መሠረታዊ የጅኦሜትሪዊቅርጾችን መለየት
- ተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ነገሮችን መለየት

# ስድስተኛ ሳምንት

የተሰጠው ሰዓት-10 ክፍለ ጊዜ (30)

## አጥጋቢ የመማር ብቃት

- የሚወዱትንና የማይወዱትን ነገር ይለያሉ
- ከቤተሰቦቻቸውና ከመምህራኖቻቸው ጋር ሰላምታ ይለዋወጣሉ
- የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ይጠራሉ
- የግል ንፅህና አጠባበቅን ተግባራዊ ያደርጋሉ
- ቀለሞችን፣ ሸካራነት፣ ቅርጾችን ጋር ይለያሉ
- ቁጥር ይቆጥራሉ
- ቁጥር ይጽፋሉ
- ቁጥር ይለያሉ
- ፊደላት በመለየት ይጽፋሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ራስን ማወቅ
- ራስን ማስተዋወቅ
- ቁጥሮችን መጻፍና ማንበብ
- የሰውነት ክፍሎች
- ጤና
- ቁጥሮችን መቁጠር
- ፊደላትን መለየትና መፃፍ
- ስዕሎችን መገንዘብ

## ተግባር 1- የግል ተግባር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቁጥር "1ን" በነጠብጣብ ማያያዝ /3 ክፍለ ጊዜ /

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ መጻፍ፣ የሚወዱትንና የማይወዱት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ሥዕሎችን ያሳዩአቸው ከስዕሉም መካከል የሚወዱትንና ይማይወዱትን እንዲለዩ ያድረጉ ህጻናት በአየር ላይ "1" ቁጥርን እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፣ ህጻናቱ የመለማመጃ ደብተራቸውን እንዲያወጡ ያድርጓቸውና በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ "1" ቁጥር ነጠብጣብን እንዲያደምቁ/እንዲያያይዙ ቀለም እንዲቀቡ በማድረግ የጹሑፍ ልምምድ እንዲያደርጉ እጃቸውን እንዲያፍታቱና የእርሳስ አያያዝ

እንዲለማመዱ ያግዟቸው:: ይህንን ተግባር በቤታቸው እንዲለማመዱት ይምከሯቸው::

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ ሥዕል
- **የምዘና ስልት:- ምልከታ (ለምሳሌ:-** ህጻናቱ እርሳሳቸውን በአግባቡ መያዛቸውን እና በመስመሩ ላይ ማድመቃቸውን መከታተል... እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- የፃፉት ቁጥር ስንት እንደሆነ ይጠይቋቸው...)

## ለ. ፊደልን በነጠብጣብ ማያያዝ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ፊደል፣ቀለም፣ጽሁፍ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተግባር
- **የመምህርሚና:-** መምህር! በአየር ላይ ፊደል እንዲፅፉ ያበረታቱ ህጻናቱ የመለማመጃ ደብተራቸውን እንዲያወጡ ያድርጓቸውና የ "በ" እና የ "ሰ" ፊደላትን ነጠብጣብን እዲያደምቁ/ እንዲያያይዙ ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ:: የጹሑፍ ልምምድ እንዲያደርጉ እጃቸውን እንዲያፍታቱና የእርሳስ አያያዝ እንዲለማመዱ ያግዟቸው:: በመቀጠልም ስለ ሰውነት ክፍሎቻቸው እንዲገልጹ ያበረተቷቸው::
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ መቅረጸ ድምጽ፣ ሞባይል
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ:- ህጻናቱ እርሳሳቸውን በአግባቡ መያዛቸውን እና በመስመሩ ላይ ማድመቃቸውን መከታተል... እና የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- የፃፏቸውን ፊደል ማን እንደሆነች ይጠይቋቸው...

## ሐ. ጤና /2 ክፍለ ጊዜ /

- **ቁልፍ ቃላት:-** ጤና፣ የሠውነት ክፍሎች፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ የግል ንጽህና
- **የማስተማርያ ዘዴ:-**በተግባር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! በካርቶን የተሠሩና የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ሳጥኖችን ያዘጋጁ: :ሳጥኖቹንም ጤና፣ የሠውነት ክፍሎች፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ የግል ንጽህና ብለው ይሰይሙ ቁጥርም ይስጧቸው ከዛም ሣጥኖቹንና ህፃናቱን ወደ ደጅ ይዘዋቸው ይውጡ:: ህጻናቱን በ4 ቡድን ይክፈሏቸው :: ለህፃናቱም ትንንሽ ኳሶችን በመስጠት እየወረወሩ የሚፈልጉት ሳጥን ውስጥ እንዲከቱ ያድርጉ ለእያንዳንዱ ህጻን የጊዜ ገደብ ያስቀምጡ:: የደረሰው ህፃን የወረወረው የጤና ሳጥን ውስጥ ከሆነ እጃችንን እንዴት መታጠብ እንዳለብንና የወረወረበት ሳጥንም ስንት ቁጥር እንደሆነ እንዲያብራራ ትዕዛዛቱን ያስረዷቸው:: ይህንን በሁሉም ሳጥኖች ላይ እንደየይዘቶቹ ተግባራዊ ያድርጉ:: ተግባራቱን በሰዓት ያስጀምሩ በትክክል ትዕዛዙን ተከትሎ የጨረሰውን በጭብጨባ ያበረታቱ:: ተግባራቱን ሲጨርሱ እጃቸውን በውሃ እና በሳሙና እንዲታጠቡና ወደ ክፍል እንዲገቡ ያድርጉ:: ::
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ኳሶች፣ ሳጥኖች፣ ውሃና ሳሙና
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ:- ህጻናቱ ኳሶቹን በአግባቡ መያዛቸውንና በሳጥኑ ውስጥ መክተት መቻላቸውን መከታተል... የቃልጥያቄ የሳጥኑን ስያሜ ማን እንደሆነ መጠየቅ...)

## ተግባር 2- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. እኔ ፋጡማ ነኝ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ንፅህና፣ቁጥር፣ ራስን ማስተዋወቅ
- የማስተማርያ ዘዴ ፡- በተረት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ከዚህ በታች ያለውን ተረቱን ለህጻናቱ ድምጽ ከፍ በማድረግና በመቀያየር በሥዕል አስደግፌው ሳቢ በሆነ አቀራረብ ይንገሯቸው፡፡

### ተረት ተረት

ፋጡማ የ4 ዓመት ህፃን ነች፡፡ ትምህርት ቤት ገብታ መማር ጀምራለች፡፡ ፋጡማ በጣም ደስተኛ እና ጤነኛ ልጅ ነች፡፡ ፋጡማ ቤተሰቦቿ ባለማመዷት መሰረት ዘወትር የፀጉሯን፣ የሰውነቷን፣ የአፏን እና የጥርሷን፣ የእጇን እና የእግሮቿን እንዲሁም የልብሷን ንፅህና በአግባቡ ትጠብቃለች፡፡ ምግብ ስትመገብ ልብሷ ላይ ሲንጠባጠብባት ስለማትወድ ሳህኗን ወደ ራሷ አስጠግታ በጥንቃቄ መመገብ ትወዳለች፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን በክፍል ውስጥ መምህሯ ለተማሪዎቹ ሰላምታ ከሰጠቻቸው በኋላ ፋጡማ እራሷን እንድታስተዋውቅ ጋበዘቻት፡፡ ፋጡማም በደስታ ለጓደኞቿ ሰላምታ በመስጠት "ፋጡማ አሊ እባላለሁ፡፡ ዕድሜዬ 4 ነው፡፡ በጣም የምወደው ምግብ ገንፎ ነው፡፡ ወተትም መጠጣት እወዳለሁ፡፡ ንፁህ መሆን ያስደስተኛል፡፡ መቆሸሽ አልወድም፡፡ የሰውነት ክፍሌን አውቃለሁ፡፡ 2 ጆሮዎች፣ 2 ዓይኖች፣ 1 አፍንጫ፣ 2 እግሮች አሉኝ፡፡ የሰውነት ክፍሎቼ ብዙ ናቸው፡፡ ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ ብላ ተቀመጠች፡፡ የክፍሉ ተማሪዎች ሁሉ አጨበጨቡላት፡፡

- የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡- ስዕላዊ መግለጫ ያለው የተረት መጽሐፍ
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡-የሰውነት ክፍሎቻቸውን ስም እንዲናገሩ መጠየቅ...)

### ለ. ተመስገንና ሄራን (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍቃላት፡- ሸካራነት፣ ቅርፆች፣የማይወደውንናየሚወደውን ሥዕልበማንበብ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- ተረቱን በሥዕል አስደግፎ ማውራት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ከዚህ በታች ያለውን ተረት ቀድመው በመዘጋጀት ለህጻናቱ ድምጽዎን ከፍ በማድረግና በመቀያየር ሳቢ በሆነ አቀራረብ ያቅርቡላቸው፡፡

### ተረት ተረት

ተመስገን የ1ኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ እቤቱ የሚሰራው የቤት ሥራ ተሰጥቶት ነበር፡፡ እሱም ሸካራነትን መለየትና ቅርፆችን በማዛመድ መሥራት ነበር፡፡ እህቱ ሄራን ከት/ቤት ስትመለስ ጠዋት ወንድሟን ትንሽ አሞት እንደነበረ አስታወሰች፡፡ሁል ጊዜ እንደምታደርገው እንዴት ዋልክ ወንድሜ አለችውና ሳመችው፡፡ የማይወደውን ምግብ ተመግቦ እንዳመመውና ከዚህ በኋላ የሚወደውን ምግብ ብቻ እንደሚበላ ነገራት፡፡ ሄራን በሀሳቡ ተስማምታ የለበሰችውን ዩኒፎርም አወላልቃ፣ ተጣጥባ፣ መክሰስ በልታ ቦርሳዋን ይዛ ወደ ወንድሟ ተመለሰች፡፡ እሱ የሚሰራውን ተመለከተችና የራሷን መስራት ጀመረች፡፡ እሷ የተሰጧትን ስዕሎች በማንበብ ፊደላትን ጻፈች ፡፡

- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ:-** ስዕላዊ መግለጫ ያለው የተረት መጽሐፍ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ ( ለምሳሌ:- ተመስገን የታመመው በምን ምክንያት ነው ?...)

## ተግባር 3- መዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ራሴን አውቀዋለሁ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ጤና፣ ክፉት ተንኮል፣መልካም መሆን
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያግዟቸው።

ራሴን አውቀዋለሁ

እኔ ራሴን አውቀዋለሁ፣

በደንብ መግለፅ እችላለሁ፤

ሁሌ በጠዋት እነሳለሁ፤

ሰውነቴን አፍታታለሁ።

ሁልጊዜ ጤነኛ ነኝ፣

ለወደፊት ተስፋ ያለኝ።

ንፁህ ሆኜ እየተማርኩ፣

ተረቶችን እያነበብኩ፤

መልካም መሆን ደስ ይለኛል፣

ክፉት ተንኮል ያስጠሉኛል።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ቴፕ፣ ሞባይል /ቴሌቭዥን
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ:- ሲዘምሩ መከታተል...) እና የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- በመዝሙሩ ውስጥ ስላሉ ነገሮች መጠየቅ...)።

### ለ. ቁጥር መቁጠር/3 ክፍለ ጊዜ /

- **ቁልፍ ቃላት:-**መቁጠር፣ ሸካራና ለስላሳ፣ የሚወዱትን የማይወዱትን፣ ንባብ፣ ቀለማት፣ ቅርፆች
- **የማስተማርያ ዘዴዎች :-**በማዘመር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! እባክዎ ከዚህ በታች ላለው ግጥም ዜማ በማውጣት ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ በማለማመድ ቁጥር መቁጠር፣ፊደላትን እንዲፅፉ፣ ሸካራና ለስላሳ ነገሮች እንድለዩ፣ ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ፣ የጂኦሜትሪ ቅርጾች ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ያግዟቸው።

ቁጥር መቁጠር

ቁጥር መቁጠር እወዳለሁ፣

አንድ ሁለት ሶስት እቆጥራለሁ፣

ፊደላትን እፅፋለሁ፤

ማንበብንም እወዳለሁ።

አረንጓዴ ክቧ ሳህን፣

ሳጥኑ ነው አራት ማዕዘን፣

ሶስት ማዕዘኗ መስታወቴን።

የማይባት ሰውነቴን፣

ገዛችልኝ ውዷ እናቴ።

አሸዋማ ሸካራ ነው፣

ሶፍቱ ደግሞ ለስላሳ ነው።

መቁጠር ማንበብ እወዳለሁ፣

ለማወቅም እጥራለሁ።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ቁጥር፣ ባለቀም ቅርፅ፣ ሶፍት፣አሸዋ፣ መስታወት
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ (ለምሳሌ:- ሲዘምሩ መከታተል...) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- በመዝሙሩ ውስጥ ስላሉ ነገሮች መጠየቅ...)

## ተግባር 4- የክፍል ውጪ ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ሥዕል ማንበብ (2 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት:-** የሰውነት ክፍል፣ የግል ንፅህና አጠባበቅ፣ ቁጥር፣ ፊደል፣ንባብ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! አስፈላጊ የሆኑትን ስዕሎች ማለትም (የሰውነት ክፍሎችን፣ የግል ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ፣ ቁጥር፣ ፊደል የያዘ ሥዕል) አዘጋጅተው ለህፃናቱ በመስጠት ህፃናቱም የያዟቸውን ሥዕሎች በየግላቸው በደንብ ከተመለከቱ በኋላ ተራ በተራ እንዲገልፁ ያድርጓቸው። በዚህ ወቅት መምህር ተመሳሳይ የሆኑ ስዕሎችን በመያዝ ቀድመው ሥዕሉን እና በሥዕሉ ላይ የሥዕል ብዛት/ቁጥር በመግለጽ በተመሳሳይ መልኩ ህፃናቱም አንድ በአንድ የያዙትን ሥዕል እና ድርጊት እንዲናገሩ ያድርጉ። ተግባራቱን በቤታቸው በደንብ ተለማምደው እንዲመጡ ያበረታቷቸው።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** (የሰውነት ክፍሎችን፣ የግል ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ፣ ቁጥር፣ ፊደል የያዘ ሥዕል/ሞዴል)

- **የምዘና ዘዴ፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- እያንዳንዱ ህፃናት የያዙትን ሥዕል ተግባርና ብዛት መጠየቅ፣...) እና ምልከታ (ለምሳሌ፡- ሲያቀርቡ/ሲገልፁ መመልከት...)

## ተግባር 5- የሙከራ ተግባር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. መለጠፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ንፅህና መጠበቂያ፣ የሰውነት ክፍሎች፣ ቀለማት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የተቆራረጡ የሰውነት ክፍሎችን ሥዕል፣ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ፣ ቀለማትን በማዘጋጀት ለህጻናቱ ይስጧቸው፡፡ ህጻናቱ ማጣበቂያ ኮላ/ግሉ በመጠቀም በወረቀታቸው/በደብተራቸው ላይ እንዲያጣብቁ ያበረታቷቸው፡፡ በመጨረሻም እጃቸውን መታጠብ እንዳለባቸው ይንገሯቸው፡፡
- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የሰውነት ክፍሎችን የሚያሳይ ሥዕል፣ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ፣ ቀለማት፣ የተቆራረጡ ወረቀቶች፣ ደብተር/ወረቀት ማጣበቂያ ኮላ/ግሉ/ሙጫ
- **የምዘና ስልት-** በቃል መጠየቅ /ለምሳሌ ምን እንደሰሩ መጠየቅ...ጥያቄ (የገጣጠሙት ሥዕል የምን እንደሆነ መጠየቅ) እና ምልከታ(ለምሳሌ ተግባራቱን በየግላቸው ሲተገብሩ እርስዎ በተቻለ መጠን የተሰጣቸውን ጊዜ ተጠቅመው ተግባራቱ በተገቢው ሁኔታ እያከናወኑ ስለመሆናቸው አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያድርጉ...

## ተግባር 6- በሥራ መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ሚና ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የሰውነት ክፍል፣ ንፅህና መጠበቂያ፣ ገዢና ሻጭ፣ፊደል ቁጥር፣
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** ጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ሁሉንም ህፃናት በቡድን ሆነው እንዲደራጁ ይንገሯቸው፡፡ ይህንን ተግባር በራሳቸው እንዲያደርጉ እድል ይስጧቸው፡፡ ከዚያም ህፃናቱ ተመራርጠው ሲጨርሱ የእርስዎ ተግባር የመጫወቻ ቁሶችን በመስጠት በጋራ በመሆን ጨዋታ እንዲጫወቱ ያበረታቷቸው፡፡ በእያንዳንዳቸው ቡድን ውስጥ ስንት የቡድን አባላት እንዳሉ ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ እርስ በርስ እንዲተዋወቁ ያድርጉ፡፡ ገዢና ሻጭ በመሆን የተለያዩ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ፣ የሰውነት ክፍሎች የያዘ ሥዕል፣ "1" ቁጥር እና " በ፣ሰ፣ ሸ፣ከ፣ ኸ፣ ለ " ፊደላትን በሱቅ ማዕዘን እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም ቡድኖቹ የተጫወቱበትን መጫዎቻዎች በቦታቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡
- **የምዘና ስልት፡-** በቃል መጠየቅ (ሻጭ እና ገዢ የገዙትንና የሸጡትን እቃ እንዲዘረዝሩ መጠየቅ) እና ምልከታ በትክክል መስራት መቻላቸውን መከታተል...

# ሰባተኛ ሳምንት

የተሰጠው ሰዓት......10 ክፍለ ጊዜ (30)

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ስሜታቸውን ይገልጻሉ
- ድምጽ የሰሙበትን አቅጣጫ ይለያሉ
- የቤት እንሰሳትን ድምጾች ይለያሉ
- የቤት ቁሳቁስን ይለያሉ
- ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን ስም ይለያሉ
- ፊደላትን ያነባሉ ፤ በነጠብጣብ የተጻፉ ፊደላትን ያደምቃሉ
- ቁጥር “2ን” ይለያሉ፣ በነጠብጣቡን ያደምቃሉ፣ ያቀልማሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- እራስን መቆጣጠር (ስሜትን)
- ድምጽን መለየት
- አካባቢ
- የተመጣጠነ ምግብ
- ፊደላትን ማንበብና መጻፍ
- ቁጥር መጻፍ
- ፈጠራን መግለጽ

## ተግባር 1- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቆንጂት እና ቤተሰቦቿ (3 ክፍለ ጊዜ )

- ቁልፍ ቃላት፡- የቤት እንስሳት ፣ የእንስሳት ድምፅ፣ ምግቦች፣ስሜት
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተረት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ተረቱን ለህጻናቱ በሚገባ መልኩ መተረት

## ተረት ተረት

ቆንጂትን እናት እና አባቷ በጣም ይወዷታል፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ቆንጂትን በመጥራት “ወደ ገበያ ልንሄድ ስለሆነ ምን እንግዛልሽ?” አሏት፡፡ ቆንጅትም በጣም ደስ ብሏት ድምፅ የሚያወጡ የቤት እንስሳት አሻንጉሊት እንድትገዙልኝ እፈልጋለሁ አለች፡፡ አባትና እናቷም መጫወቻ የሚሸጥበት ሱቅ በመግባት ቆንጂት የጠየቀችውን መጫዎቻ ገዙላት ነገር ግን አንድ መጫዎቻ ሱቅ ውስጥ ስለአጡ ሳይገዙላት ቀሩ፡፡ ቢሆንም ግን የምግብ አይነቶችን ገዝተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡ ለቆንጂት የገዙላትን መጫወቻዎች አውጥተው ሰጧት፡፡ ቆንጂትም መጫወቻዎቹን ስትመለከት ያልተገዛላት

እንዳለ ስትረዳ በጣም ተናደደች፤ አዘነችም፡፡ አባቷም ለሌላ ጊዜ የምትፈልጊው መጫወቻዎች ካተገዙልሽ ለምን እንዳልተገዛልሽ በመጠየቅ መረዳት አለብሽ እንጂ መናደድና ማዘን ተገቢ አይደለም አሏት፡፡ ቆንጂትም በቤተሰቦቿ ምክር ተስማምታ የተገዛላትን መጫወቻዎች እያንዳንዱን እያነሳች መጫወት ጀመረች፡፡ ድመቷን ስታነሳት ሚያው! ሚያው! የሚል ድምፅ ስታሰማ በጣም ደስ አላት፡ ፡ ውሻውም እንደዛው በጣም ተገርማ ስለተገዛላት መጫወቻ ቤተሰቦቿን አመሰገነች፡፡ ከዚያም እጇን በውሀና በሳሙና ታጥባ የተገዙላትን ምግቦችን ከቤተሰቧ ጋር መመገብ ጀመረች፡፡

- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቤት እንሰሳትን የያዘ ሥዕል፣ የእንስሳትን ድምፅ የያዘ ቪዲዮ፣ ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን የያዘ ሥዕል
- **የምዘና ስልት-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- ቆንጂት ለምን አዘነች? የቆንጂት ድመት ምን ምን እያለች ድምፅ አወጣች? ያያችሁት ምስል የምን ምስል ነው? (የድመት፣የውሻ..)፣ ደስተኛ፣ ሀዘን፣ የመናደድ እና ፍርሀትንየያዘነ ምስል በማሳየት መጠየቅ፣በተረቱ ላይ እነማን አሉ?..)

## ለ. መምህርትና በለጡ /3 ክፍለ ጊዜ /

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፈጠራ ፣ ቁጥር፣ የቤት ዕቃዎች፣ ምግብ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የቀረበላቸውን ተረት በጥሞና እንዲያዳምጡ በማድረግ ያዳመጡት ተረት ፍሬ ሓሳቦች እንዲገልፁ ያግዟቸው፡፡

ተረት ተረት

በለጡ የደረጃ 1 ተማሪ ናት፡፡ ሁል ጊዜ ማጥናትና የቤት ሥራዋን መስራት ስትጀምር እናቷ ስራ እንድታግዛት ጠራቻት፡፡ በለጡም እናቷን ታግዛለች፡፡ ታዲያ አንድ ቀን የቤት ዕቃዎችን ስታጥብ አምሽታ ስለደከማት የቤት ስራዋን ሳትሰራ አደረች፡፡ የቤት ስራዋም የ2 ቁጥር ነጠብጣቦችን ማያያዝና ማድመቅና የምትፈልገውን የፈጠራ ስራ መስራት ነበር፡፡ እሷግን ጠዋት እሰራለሁ ብላ ተኛች፡፡ ነገር ግን ጠዋት ረፈደባትና ሳትሰራ ወደ ት/ቤት ሄደች፡፡ መምህርቷም ክፍል ገብታ ሠላምታ ከሰጠች በኋላ ደብተራቸውን ማየት ጀመረች፡፡ የፈጠራ ስራ የሰሩትንም እያስጨበጨበች ተቀበለቻቸው፡፡ በለጡ ደንግጣ ላለማልቀስ እራሷን ተቆጣጠረችና ለመምህረቷ ለምን እንዳልሰራች አስረዳቻት እሷም ከዚህ በኋላ ሠርታ እንድትመጣ ነገረቻት፡፡ መምህርቷም ለጤና ተስማሚ ስለሆኑ ምግቦች ምን ምን እንደሆኑ በመጠየቅ ማስተማር ጀመረች፡፡ ከዚያ በኋላ በለጡ የቤት ስራ ሳትሰራ ወደ ት/ቤት ሄዳ አታውቅም፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቤት ቁሳቁስ የያዘ ሥዕል፣ ድምፅ የያዘ ቪዲዮ፣ ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን የያዘ ሥዕል፣ የተረት መጽሐፍ
- **የምዘና ስልት- የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡-** ፍርሀትን የያዘ ሥዕል በማሳየት መጠየቅ፣ በተረቱ ላይ እነማን አሉ?...)ምልከታ ለምሳሌ በትክክል እያዳመጡ መሆኑን በመመልከጥ...

# ተግባር 2- መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ)

## ሀ. ድመቴ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ጤና፣ስም፣ሞዴል፣
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና:-** -መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ በመዘመር የቤት እንሰሳት፣ የድምጽ እና የቁጥር ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ያግዟቸው።

### ድመቴ

እኔ ድምት አለችኝ

ሚያው ሚያው እያለች የምታጫዉተኝ።

ወተት በሳህን እሰጣታለሁ፣

ስሟን ውሮ እላታለሁ፤

ሁሌ በጠዋት እነሳለሁ፣

ውርዬንም እጣራለሁ።

እኔም ውሮም ጤነኛ ነን፣

ንጹህ ምግብ እንበላለን።

ካርቶኖችን እቆርጣለሁ፣

የሷን ሞዴል እሰራለሁ።

ይህንንም በመፍጠሬ፣

አሳያለሁ ለመምህሬ።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የእንስሳት ድምፅ የያዘ ቪዲዮ፣ ሞባይል/ ቴሌቭዥን፣ የእንስሳት ሥዕል
- **የምዘና ስልት-** **ምልከታ** (ለምሳሌ:- ሲዘምሩ መከታተል...) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- በመዝሙሩ ውስጥ ስላሉ ነገሮች መጠየቅ፣የድመት ድምጽ እንዲያሰሙ መጠየቅ):

## ለ. በቤታችን (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ፊደል፣ ማንበብ፣ መገጣጠም፣ የተመጣጠነ ምግብ፣ ፈጠራ፣ አከባቢ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ በጋራና በግል በመዘመር የተመጣጠነ ምግብ፣ የቤት እንስሳት፣ ድምጽ እና የአከባቢ ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ያግዟቸው።

## በቤታችን

በአከባቢ በኛ ሰፈር፣
ደስ ብሎን ነው የምንኖር።
ሁሌ ፍቅር ሁሌ ሰላም፣
በደስታ ነው አንጣላም።
ፊደል ማንበብ እንችላለን፣
አገጣጥመን እንሠራለን።
የውሻዬን ድምጽ እሰማለሁ፣
ያለበትን እረዳለሁ።
በምንወደውሳህናችን፣
ተመጣጥኖ ምግባችን፣
ይሰጠናል በእናታችን፣
ፈጠራንም እንፈጥራለን፣
በወረቀት እንሠራለን።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተቀረጸ ድምፅ የያዘ ቪዲዮ፣ ሞባይል/ቴሌቭዥን
- **የምዘና ስልት- ምልከታ ምድረግ (ለምሳሌ፡-** ሲዘምሩ መከታተል...) እና **የቃል ጥያቄ መጠየቅ** (ለምሳሌ፡- በመዝሙሩ ውስጥ ስላሉ ነገሮች መጠየቅ፣ በአካባቢያችሁ የሚገኙ ነገሮችን ዘረዝሩ ...)

## ተግባር 3- የክፍል ውስጥ ጨዋታ (4 ክፍል ጊዜ)

### ሀ. ሻጭ እና ገዢ (4 ክፍል ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የቤት ቁሳቁስ፣ ቁጥር፣ሻጭና ገዢ፣ምግቦች
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱ በራሳቸው በቡድን እንዲደራጁ ያድርጉ። ከዚያምየመጫወቻ ቁሶችን በማቅረብ ሻጭና ገዢ በመሆን የሚና ጨዋታ እንዲጫወቱ ያግዟቸው። በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ስንት አባላት እንዳሉ ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጉ። የቤት ቁሳቁስ፣ ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን እንዲሸጡና እንዲገዙ ያበረታቷቸው። በመጨረሻም ቡድኖቹ መጫወቻዎቹን በቦታቸው እንዲመልሱ ያድርጉ።
- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያዩ የቤት ቁሳቁስ (ድስት፣ መክተፊያ፣ሳህን፣ ብርጭቆ) የምግብ አይነቶች የሚወክሉ ሞዴል ምስሎች፣ ሞዴል የብር ኖቶች።
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ ሻጭ የነበረው ማን እንደሆነ፣ ምን እንደገዛ

መጠየቅ፣የገዟቸውን እቃዎች አይነት መጠየቅ፣የገዟቸውን እቃዎች ብዛት መጠየቅ)እና ምልከታ ማድረግ ለምሳሌ፡- ተግባሩን መጫወት መቻላቸውን በመከታተል...

## ተግባር 4- በፕሮጀክት መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. በጭቃ ቅርጾችን መሥራት (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍቃላት፡- የቤት ቁሳቁስ፣ ፊደላት ፣ቁጥር
- የማስተማርያ ዘዴ፡-በፕሮጀክት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህጻናቱ እርስ በእርስ እንዲተጋገዙ፣ የቤት ቁሳቁስ፣ ፊደላት እና ቁጥር እንዲሰሩ እና የሰሯቸውን ቁሶች እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡ የፕሮጀክቱን ስራ ከታች ባለው ቅደም ተከተል እንዲያከናውኑ የድርሻዎትን ያበርክቱ፡፡

1. ለፕሮጀክቱ ስራ የሚስፈልጉ ቁሳቁስ ውሃ፣ አፈር፣ ሳህን (ሰው ሰራሽ ጭቃ) ያዘጋጁ
2. ህጻናቱ የሚሰሩበትን ሰፋ ያለ ቦታ ይምረጡ
3. ህጻናቱ ምን እንደሚሰሩ እና እንዴት እንደሚሰሩ ያሳዩዋቸው
4. የቤት ቁሳቁስ ሞዴል ካለ ያሳዩዋቸው፤ የተዘጋጀውን ጭቃ ለህፃናቱ በእኩል አካፍለው በተዘጋጀው ቦታ ያስቀምጡላቸው
5. ህጻናቱ በሚሰሩበት ጊዜ በየመሃሉ ክትትል ያድርጉ፡፡

- የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡- ጭቃ (የተፈጥሮ/ሰው ሰራሽ)፣ የፊደል፣የቁጥር እና የቤት ቁሳቁስ ሞዴል፣ አሻንጉሊት፣ ቅርፅ ማውጫ
- የምዘና ስልት- የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የሰሩትን ሥዕል ቅርጽ መጠየቅ፣ የስንት ሥዕል ቅርጽ እንደሰሩ መጠየቅ...)ምልከታ ( ምን እየሰሩ እንደሆነ መከታተልና መመዝገብ...)

## ተግባር 5- የግል ተግባር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. “2” ቁጥር ነጠብጣብ ማያያዝ (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ ቀለም፣የምግብ ዓይነቶች
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡-መምህር! በአየር ላይ “2” ቁጥርን እንዲፅፉ ያበረታቱ፡፡ በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ “2” ቁጥር ነጠብጣብን ከመስመር ሳይወጡ እዲያደምቁ/ እንዲያያይዙና ቀለም እንዲቀቡ፣ የጽሁፍ ልምምድ እንዲያደርጉ፣ እጃቸውን እንዲያፍታቱና የእርሳስ አያያዝ እንዲለማመዱ ያግዟቸው፣ በመቀጠልም የተመጣጠነና ለጤናችን ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን ይግለጹላቸውና እያንዳንዳቸው “2” የምግብ ዓይነቶችን እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡ በዕለቱ የተማሩትን ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲለማመዱት ይንገሯቸው፡፡
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ
- የምዘና ስልት፡- ምልከታ (ለምሳሌ፡- ህጻናቱ እርሳሳቸውን በአግባቡ መያዛቸውን እና በመስመሩ ላይ ማድመቃቸውንና መቀባት መቻላቸውን መከታተል...የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የፃፉት ቁጥር ስንት እንደሆነ ይጠይቋቸው...)

### ለ. ሥዕል መሳል (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ስሜት፣ መቁጠር፣ ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተግባር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! የተለያዩ ስሜቶችን የሚያሳዩ ሰዎችን ሥዕል እንዲስሉ፣ ስዕሎቹን ቀለም እንዲቀቡ፣ ስሜታቸውን መግለጽ እንዲለማመዱ የተለያዩ ስሜቶች የሚያሳዩ ሰዎች ሥዕሎች በማዘጋጀት ያሳዩዋቸው።
- **የመማርያና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ (ማርከር) ወረቀት፣ ምስልና ወረቀት
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- የሚወዱትን ከለር መጠየቅ...) እና ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ:-ምስሉን በአግባቡ ማቅለማቸውን መመልከት...)

### ሐ. ሥዕል ማንበብ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** የቤት ቁሳቁስ፣ ስሜት ገላጭ፣ ጤናማ ምግብ፣ ቁጥር፣ ፊደል
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተግባር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ለተግባሩ አስፈላጊ የሆኑ ሥዕሎች ማለትም (የቤት ቁሳቁስ፣ስሜት ገላጭ፣ ጤናማ ምግብ፣ ቁጥር፣ ፊደል የያዘ ሥዕል) አዘጋጅተው ለህፃናቱ ይስጡ። ህፃናቱ የያዟቸውን ስዕሎች በየግላቸው በደንብ ከተመለከቱ በኂላ ተራ በተራ የምስሉን ብዛት እና ድርጊት እንዲናገሩ ያድርጉ።
- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ:-** የቤት ቁሳቁስ፣ ስሜት ገላጭ፣ የምግብ ዓይነቶች፣ ቁጥር፣ ፊደል ሥዕል
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ ምን እንደሰሩ መጠየቅ...) እና ምልከታ (ለምሳሌ በህፃናቱ አቅም ህግና መመሪያን መከተላቸውን ማረጋገጥ)

## ተግባር 6- የክፍል ውጭ ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. አረንጓዴ አረንጓዴ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ፊደል፣ቁጥር፣ቡድን
- **የስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህፃናቱን ወደ ውጭ ይዘው በመውጣት በራሳቸው በአምስት ቡድን ሆነው እንዲደራጁ ይንገሯቸው። ህፃናቱ ተመራርጠው ሲጨርሱ ክብ እንዲሰሩ ያድርጉ፡ ፡ በክቡ ውስጥ ፊደላትን እና ቁጥርን የያዙ ካርዶችን በማስቀመጥ ህፃናቱ አረንጓዴ አረንጓዴ እያሉ በክቡ ዙሪያ በሶምሶማ እንዲሮጡ ያድርጉ። ከዚያም ቀይ ሲሉ ህጻናቱ በአጠገባቸው የሚገኘውን ፊደል/ቁጥር ከመሬቱ ላይ እያነሱ ያነሱትን ፊደል/ ቁጥር ስም እንዲናገሩ ያበረታቱ። በተጨማሪም ቁጥር የያዙ ልጆችን ከቁጥሩ አጠገብ ያለውን ሥዕል ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጉ።በመጨረሻም ቡድኖቹ ጨዋታውን ተጫውተው ሲጨርሱ የተጫወቱበትን መጫወቻዎች ወደ ቦታቸው ይመልሱ።
- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ:-** የፊደል እና የቁጥር ካርዶች
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- በጨዋታው ውስጥ ያገኘከውን/ሽውን ፊደሎች ስም ጥራ/ሪ) እና ምልከታ (ለምሳሌ:- ምን እንደተጫወቱ መጠየቅ... እና ምልከታ ማድረግ

ተግባሩን በትክክል መሰራት መቻላቸውን መከታተል...)

ለ/ድምፅ የመጣበትን አቅጣጫ መለየት እና መናገር (2 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት-** አቅጣጫ፣ እንስሳት፣ ድምፅ፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-**መምህር! ህፃናቱን ወደ ውጭ ይዘው በመውጣት በክብ እንዲቀመጡ ያድረጉ፡፡ በመቀጠልም በክቡ መሀል አንድ ፈቃደኛ ህፃን እንዲቆም/እንድትቆም ያድርጉ፡፡በክብ ከተቀመጡት መካከል በተለያዩ አቅጣጫ ለተቀመጡ 2 ህፃናት ለእያዳንዳቸው የተለያየ የቤት እንስሳ፣ የሳቅ፣ የለቅሶ ድምጽ እንዲያሰሙ ያድርጉ ፡፡በክቡ መሀል የቆመው/ችው ህፃን የምን ድምፅ እና ከየት አቅጣጫ እንደመጣ እንዲናገር /እንድትናገር ያበረታቱ፡፡እንዲህ በማድረግ ሁሉንም ህፃናት በማሳተፍ ጨዋታውን እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያዩ የቤት እንስሳት፣ የሳቅ፣ የለቅሶ ድምጽ ቅጂ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ህፃናቱ ስንት ድምፅ እንደሰሙ፣ የምን ድምፅ እንደሰሙ መጠየቅ) እና ምልከታ (ለምሳሌ፡- ተግባሩን በትክክል መሰራት መቻላቸውን ማረጋገጥ)

# ስምንተኛ ሳምንት

**የተሰጠው ጊዜ 10ሰዓት** **ክፍለ ጊዜ (30)**

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- የመጓጓዣ ዓይነቶችን ስም ይለያሉ
- የቤት እንስሳት ስሞችን ለይተው ይናገራሉ
- ወረቀትና ትናንሽ ቁሶችን ማጠፍ ወይም መጠቅለል ይጀምራሉ
- ቁሶችን በመጠናቸው ያወዳድራሉ
- ፊደላትን ጮክ ብለው ያነባሉ
- የ3 ቁጥርን ነጠብጣብ ማያያዝ እና ቀለም ይቀባሉ
- ተራ በመጠበቅ ተግባራትን ያከናውናሉ
- መዝሙሮችን ይዘምራሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ቃላት
- እንስሳት
- ትናንሽ ጡንቻዎች
- ቁጥሮችን ማወዳደርና መደርደር
- ፊደላትን መፃፍ
- ቁጥሮችን መፃፍ
- ባህላዊ ቅርስ
- የመግባባት ችሎታ

## ተግባር 1- የግል ተግባር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ሥዕል ማንበብ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መጓጓዣ፣ የቤት እንስሳት፣ ቁጥር፣ ፊደል
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና- መምህር!** ለተግባሩ አስፈላጊ የሆኑትን ሥዕሎች ማለትም የቤት እንስሳት፣ የመጓጓዣ ዓይነቶች፣ ቁጥር 3 እና ፊደል የያዘ ሥዕል/ ካርዶችን አዘጋጅተው ለህፃናቱ በመስጠት ህፃናቱ የያዟቸውን ስዕሎች በየግላቸው በደንብ ከተመለከቱ በኋላ ተራ በተራ እንዲገልፁ ያድርጉ። በመቀጠል በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ 3 ቁጥርን እንዲያደምቁና ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቤት እንሰሳት፣ መጓጓዣ ዓይነቶች፣ ቁጥር 3 እና ፊደል የያዘ ሥዕል/ካርዶች

- የምዘና ዘዴ፡- የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ህፃናቱ የያዙትን ሥዕል እንዲቆጥሩ፣የሥዕሎቹን ስም እንዲናገሩ መጠየቅ...)

ለ. ቁጥር 3- ነጠብጣብ ማያያዝ (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ መጻፍ፣ ቀለም፣ መንጓጓዣ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! በአየር ላይ "3" ቁጥርን እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡ ህጻናቱ በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ "3" ቁጥር ነጠብጣብን እንዲያያይዙ እና ቀለም እንዲቀቡ በማደረግ የጹሁፍ ልምምድ እንዲያደርጉ እጃቸውን እንዲያፍታቱና የእርሳስ አያያዝ እንዲለማመዱ ያግዟቸው፡፡ በመቀጠልም እያንዳንዳቸው "3" የመጓጓዣ ዓይነቶችን እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣
- የምዘና ስልት፡- ምልከታ (ለምሳሌ- ህጻናቱ እርሳሳቸውን በአግባቡ መያዛቸውን እና በመስመሩ ላይ ማድመቃቸውን መከታተል... እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የፃፉት ስንት ቁጥርን እንደሆነ ይጠይቋቸው...)፡፡

ሐ. ነጠብጣብ ፊደልን ማያያዝ (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ መጻፍ፣ ነጠብጣብ፣ ማያያዝ፣መጻፍ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በግል ተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! በአየር ላይ ፊደል "ሽ እና ለ" እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡ ይህም ትንንሽ ጡንቻዎቻቸው እንዲያዳብሩ ያግዛል በመቀጠል በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ፊደል "ሽ እና ለ" ነጠብጣብን እዲያደምቁ /እንዲያያይዙ ቀለም እንዲቀቡ በማደረግ የጹሑፍ ልምምድ እንዲያደርጉ እጃቸውን እንዲያፍታቱና የእርሳስ አያያዝ እንዲለማመዱ ያግዟቸው፡፡
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ መቅረጸ ድምጽ፣ሞባይል
- የምዘና ስልት፡- ምልከታ (ህጻናቱ እርሳሳቸውን በአግባቡ መያዛቸውን እና በመስመሩ ላይ ማድመቃቸውን መከታተል...) እና በቃል መጠየቅ (የፃፏቸው ፊደል ማን እንደሆነች መጠየቅ...)

## ተግባር 2- መዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ )

ሀ. ልጆች ልጆች (ክፍለ ጊዜ 3)

- ቁልፍ ቃላት፡- መጓጓዣ፣ የቤት እንስሳት፣ ጭፈራ፣ባህል
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በመዝሙር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ በማለማመድ ስለ መጓጓዣ፣ ስለቤት እንስሳት፣ ስለ ባህል እና የቁጥር ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ያግዟቸው፡፡

## ልጆች ልጆች

ልጆች! ልጆች! አቤት! አቤት!
እንሂድ ወደ ትምህርት ቤት፡፡
በመኪና እንሄዳለን፣
ፈጥን ብለን እንደርሳለን፡፡
በፈረስም እንጋልባለን
በጀልባ እንዝናናለን
ባህላችንን እናውቃለን፣
መጨፈርም እንችላለን፡፡
ጓደኞቻችንም ይወዱናል፣
ዕቃቃም ያጫውቱናል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የእንስሳት ሥዕል፣ የመጓጓዣንና ባህልን የሚገልፅ ሥዕል/ ሞዴል
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ሲዘምሩ መከታተል) በቃል መጠየቅ (ለምሳሌ የምታውቁትን የመጓጓዣ አይነቶች ዘርዝሩ)

### ለ. በመግባባት (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መግባባት፣ የቤት እንስሳት፣ መቁጠርና መጻፍ፣ ባህል፣ ቅርስ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ በማለማመድ ስለ ቅርሶች፣ የቤት እንስሳት፣ መግባባት እና የቁጥር ግንዛቢያቸውን እንዲያሳድጉ ያግዟቸው፡

## በመግባባት

በመግባባት በአንድ ሃሳብ፣

ቅርሶቻችን እንሰብስብ፡፡

የሚያምር ባህል ያለን፣

እኛኮ ኢትዮጵያዊ ነን፡፡

ይህን ሁሉ እማራለሁ፣

መምህሬን አከብራለሁ፡፡

አቤት ደግሞ እንደ ደርስኩ፣

እጅና እግሬን እንደ ታጠብኩ፤

ፊደልና ቃላቶችን አነባለሁ፣

ቁጥርም እጽፋለሁ፤

ሥዕሌንም እቀባለሁ፡፡

ቶሎ ብዬ ጨርስና፣

ውሻ ድመቴን ፈልግና፣

ከነሱም ጋር እዘላለሁ፣

እራሴንም አዝናናለሁ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የእንስሳት ድምፅ የያዘ ቪዲዮ፣ ሞባይል/ቴሌቭዥን
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ሲዘምሩ መከታተል...)የቃል ጥያቄ(የምታውቁትን የቤት እንስሳት ስም ዘርዝሩ...)

## ተግባር 3- የክፍል ውስጥ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. መጠን ማወዳደር /2 ክፍለ ጊዜ /

- **ቁልፍ ቃላት-** ቁጥር፣ ማወዳደር፣ መጠን፣የቤት እንስሳት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱ በሶስት በቡድን እንዲደራጁ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ህፃናቱ ተመራርጠው ሲጨርሱ የመጫወቻ ቁሶችን በመስጠት በጋራ እንዲጫወቱ ያበረታቷቸው ፡፡

እያንዳዳቸው ቡድን ውስጥ ስንት የቡድን አባላት እንዳሉ ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡የተለያየ መጠን ያላቸው የቤት እንስሳት ሥዕል፣ ከ1-3 ቁጥር የተጻፉባቸው ፍላሽ ካርዶች፣ ረዥምና አጭር ቀጭንና ወፍራም መጠን ያላቸው ቁሶች በማዘጋጀት እንዲያወዳድሩ ያበረታቷቸው፡፡ ይህን ተግባር ሁሉም በቡድን የተደራጁ ህፃናት እንዲያከናውኑ ያድርጉ፡፡በመጨረሻም ቡድኖቹ የተጫወቱበትን መጫወቻዎች በቦታቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያየ መጠን ያላቸው የቤት እንስሳት እና የመጓጓዣ ዓይነቶች፣ የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣ ረዥምና አጭር፣ ቀጭንና ወፍራም መጠን ያላቸው ቁሶች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ረጃጅሞቹን እና አጫጭሮቹን ቁሶች በመለየት እንዲቆጥሩ መጠየቅ)

### ለ. እንቆቅልሽ (2 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት-** መጓጓዣ፣ የቤት እንስሳት፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን አሰልፈው ወደ ውጪ ይዘዋቸው በመውጣት ክብ ሰርተው እንዲቀመጡ ያድርጉ፡፡ የመጓጓዣ ዓይነቶች፣ የቤት እንስሳት እና የቁጥር ፍላሽ ካርዶች ከህፃናቱ ፊት ለፊት በማስቀመጥ እያንዳዱን ካርድ እያነሱ እንቆቅልሽ እንዲጠያየቁ ያድርጉ፡፡ ሌሎች የሳምንቱን የመማር ብቃት ለመተግበር የሚረዱ እንቆቅልሾችን ያዘጋጁ፡፡

**እንቆቅልሽ!**

1. ሶስት ጎማዎች አሉኝ የመጓጓዣ ዓይነት ነኝ። ሰዎችን ከቦታ ቦታ አጓጉዛለሁ። እኔ ማነኝ? ባጃጅ
2. የሰዎች መኖሪያ ነኝ። የተለያዩ ክፍሎች አሉኝ። እኔ ማን ነኝ? ቤት
3. ከቤት እንሰሳት እመደባለሁ ለመጓጓዣነት አገለግላለሁ። ሰዎች ይጋልቡኛል። እኔማነኝ? ፈረስ
4. በተለያየ ነገር እደመጣለሁ /በሞባይል፣በቴፕ፣በሬድዮ/ሰዎችን አዝናናለው፣ አስጨፍራለሁ። እኔ ማን ነኝ ? ሙዚቃ

- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመጓጓዣ ዓይነቶች፣ የቤት እንስሳት እና የቁጥር ፍላሽ ካርዶች /አሻንጉሊቶች
- **የምዘና ስልት-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (የሚያውቁትን እንቆቅልሽ እንዲጠያየቁ ማድረግ)

## ተግባር 4 የክፍል ውጭ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. መጫወቻዬን ያያችሁ አላየንም እባካችሁ (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደላት፣ ቁጥር፣ እንስሣት
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡- መምህር!** ህፃናቱን ወደ ውጭ ይዘዋቸው ይውጡ። ለተግባሩ አመቺ ቦታ ይምረጡ። ሁሉም ህፃናት በሶስት ቡድን እንዲደራጁ ይንገሯቸው። ቀጥሎም ሶስት ካርቶኖች ያዘጋጁ። በተዘጋጁት ካርቶኖች ወስጥ በክፍል ውስጥ ያስለዩዋቸውን ፊደላት፣ቁጥር፣የእንስሣት ሥዕል በማርከር ጽፈው ቆራርጠው ያስቀምጡ። ከቡድኑ ውስጥ አንድ ህፃን ይምረጡ። የተመረጠው/ችው ህጻን ፊደሌን ያያችሁ ሲል/ስትል አላየንም እባካችሁ እያሉ በክብ እንቅስቃሴ ያድርጉ። ህጻኑ/ኗ ከሳጥኑ አንድ ፊደል ሲያወጣ/ስታወጣ ሁሉም ይቁሙ። ይህቺ ምንድን ናት ሲላቸው/ስትላቸው እነሱም የፊደሉን ስም ይነግራሉ፡ ፡ ለምሣሌ በ-ከሆነች ይህቺ ፊደል በ-ነች ይላሉ-በዚሁ መሰረት የቁጥሩንና የእንሣትን ሥዕል ሁሉም ተራቸውን እየጠበቁ እንዲያከናውኑ ያድርጉ።
- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ካርቶን፣ ፍላሽ ካርድ፣ እስራስ፣ ቀለም
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (በትክክል መስራታቸውን ማረጋገጥ...) እና የቃል ጥያቄ (ስንት ፊደል አየህ/ሽ፣ ምን ምን ፊደልን አየህ/ሽ)

## ተግባር 5- ተረት (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ሦስቱ ጓደኛሞች (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት-** እንሰሳት፣ መጓጓዣ፣ ባህል፣ ቁጥር፣ መግባባት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የቀረበላቸውን ተረት በጥሞና እንዲያዳምጡ በማድረግ ያዳመጡት ተረት ደግመው እንዲናገሩ ማበረታታት

## ተረት ተረት!

ባጃጅ፣ ባቡር እና ፈረስ የሚባሉ ሦስት ጓደኞሞች ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ባጃጅ እንዲህ ሲል ለጓደኞቹ ተናገረ፡፡ “እኛ ጓደኞች ነን፡፡ ስለ ስራዎቻችን ዛሬ ብንወያይ ምን ይመስላችኋል?” በማለት ጠየቃቸው፡ ፡ ባቡር እና ፈረስም በባጃጁ ሀሳብ ተስማሙ፡፡ ከዚያም ባጃጅ ቀጠለ “እኔ ባለ 3 እግር  እና አጭር ተሽከርካሪ ነኝ ከ 3 - 5 ሰዎችን ከቦታ ቦታ አጓጉዛለሁ አለ፡፡” ፈረስም ተናገረ “እኔ ከቤት እንስሳት እመደባለሁ፡፡ ህይወት አለኝ፤ ሰዎች በእኔ ላይ ተቀምጠው ይሄዳሉ፡፡ ባህላዊ የመጓጓዣ ነኝ” በማለት ተናገረ፡፡ ባቡርም በተራው “እኔ ደግሞ ከባጃጅ በጣም ረዥም ነኝ ብዙ ሰዎችን ከቦታ ቦታ አጓጉዛለሁ፡፡ በሀዲድ ላይ እሄዳለሁ” በማለት ተናገረ፡፡ ከዚያም ባጃጅ “ለዛሬ ይበቃናል ለሌላ ጊዜ ስንገናኝ እንጫወታለን” ካላቸው በኂላ ብዙ ሰዎች እየጠበቁን ስለሆነ ወደ ስራችን እንሂድ ተባብለው ተመሰጋግነው ተለያዩ፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የባጅ፣ባቡር፣ፈረስ ሥዕል የያዘ ፍላሽ ካርድ
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥ (ለምሳሌ፡- በተረቱ ላይ እነማን አሉ? በህላዊ መጓጓዣ የሆነው ማነው?...)

### ለ. ለማ (3 ክፍለ ጊዜ )

- ቁልፍ ቃላት፡- ትንንሽ ጡንቻዎች፣ መጓጓዣ፣  ቅርሶች፣ ቁጥር፣ ፊደላት፣
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተረት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! የቀረበላቸውን ተረት በጥሞና እንዲያዳምጡ በማድረግ ያዳመጡት ተረት ደግመው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው

## ተረት ተረት

ለማ በጠዋት በመነሳት ትንንሽ ጡንቻዎቹን የሚያጠነክርለትን እንቅስቃሴ ይሰራል፡፡ ይህንንም ሲሰራ ሁልጊዜ መዝሙር ያዳምጣል፡፡ ውሻው ሁልጊዜ አላሰራ እያለው ያስቸግረዋል፡፡ እርሱም እንስሳትን ስለሚወድ ምንም አይለውም፡፡ የሚማርበት ትምህርት ቤት እሩቅ ስለሆነ የሚሄደው በመኪና  ነው፡፡ ለማ ሁሉንም የመጓጓዣ ዓይነቶች ስም ያውቃል፡፡ ስማቸውን ለእናትና አባቱ ይነግራል፡፡ ሁል ጊዜ ከትምህርት ቤት ሲመለስ ወረቀቶችን በማጣጠፍ ጀልባ፣ አውሮፕላን ይሰራል፡፡  ለማ ከአባቱ ጋር በአውሮፕላን አክሱም በመሄድ ቅርሶችን መጎብኘት ችሏል፡፡ ዛሬ የተሰጠው የቤት ስራ  3 ቁጥርን ነጠብጣቦችን ማያያዝና ቀለም መቀባት በመሆኑ እሱን መስራት ጀመረ፡፡ ፊደላትንና ቁጥሮችንም መፃፍ ይወዳል፡፡ እናንተም እንደ ለማ በጣም ጎበዝ መሆን አለባችሁ፡፡  ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የቤት እንስሳትን እና የመጓጓዣ ዓይነቶችን የያዘ ሥዕል፣ የተረት መጽሐፍ፣ መለማመጃ ደብተር
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ  (ለምሳሌ፡- ለማ ለጉብኝት የት ሄደ? ለማ አክሱም በምን ሄደ?)

# ተግባር 6- ፕሮጀክት (3 ክፍለ ጊዜ )

## ሀ. ወረቀት መጠቅለልና ነገሮችን በመጠናቸው ማወዳደር (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** መጠን፣ ብዛት፣ የጂኦሜትሪ ቅርፆች፣ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ለተግባሩ አስፈላጊ የሆኑትን የጂኦሜትሪ ምስሎችን ማያያዝ እንዲችሉ በመጠናቸው የተለያዩ ወረቀቶችን ማለትም (ረዥም፣ አጭር፣ ወፍራም እና ስስ ወረቀቶች) አዘጋጅተው ያስቀምጡ። ህፃናቱ በየተራ አራት አራት ወረቀት እንዲወስዱ ያድርጉ። ህፃናቱም የያዟቸውን ወረቀቶች መጠን በየግላቸው በደንብ ከተመለከቱ በኋላ ተራ በተራ (ረዥም፣ አጭር፣ ወፍራም እና ስስ ወረቀት) እያሉ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። የያዙትን ወረቀት የሚወዱትን ቀለም እንዲቀቡና የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ረዥም፣አጭር፣ ወፍራም እና ስስ ወረቀቶች
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- ረዥም፣ አጭር፣ ወፍራም እና ስስ ወረቀቶች ለይተው እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው) ምልከታ (ምን እየሰሩ እንደሆነ፣ በትክክል እየሰሩ እንደሆነ መከታተል...)

# ዘጠነኛ ሳምንት

የተሰጠው ሰዓት-10 ክፍለ ጊዜ (30)

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- የትህትና አገላለጾችን /ይጠቀማሉ
- ስሜትን አገላለጽን ያሳያሉ
- የፍራፍሬና የአትክልት ስሞች ለየተው ይጠራሉ
- የጂኦሜትሪ ምስሎችን ያያይዛሉ
- 4 ቁጥርን ነጠብጣብ በማያያዝ ቀለም ይቀባሉ
- ፊደላትን በመለየት የሳያሉ
- የስነ ጥበብ ስራዎችን በአቅማቸው ይሠራሉ
- ሀገራዊ ምልክቶችና መለያዎችን ይለያሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ራስን ማወቅ
- ፊደላትን መጻፍ
- ራስን መግለፅ
- ቅርፅ
- እጽዋት(ተክሎች)
- ቁጥርን መፃፍ
- የትናንሽ ጡንቻዎች እድገት
- የስነ-ጥበብ እሴት
- ሀገር መውደድ
- የህትመት ግንዛቤ

## ተግባር 1- የግል ተግባር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቁጥር 4ን በነጠብጣብ ማያያዝ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥርን፣ ቀለም፣ ሃገራዊ ምልክቶች
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በአየር ላይ 4 ቁጥርን እንዲፅፉ ያበረታቱ፡፡ በመቀጠል እርሳስ እንዴት መያዝ እንዳለባቸው በማሳየት፣ ከመስመር ሳይወጡ በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ 4 ቁጥር ነጠብጣብ እዲያደምቁ /እንዲያያይዙ እና ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም የሃገራዊ ምልክቶችን /የባንዲራ ቀለም/ እንዲገልጹና እያንዳንዳቸው 4 ቀለም እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ ከለር፣ ቀለም

- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ህጻናቱ እርሳሳቸውን በአግባቡ መያዛቸውን እና በመስመሩ ላይ ማድመቃቸውንና መቀባታቸውን መከታተል እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የፃፉት ቁጥር ስንትን እንደሆነ መጠየቅ፣የኢትዮጵያ ባንዲራ ቀለማትን መጠየቅ....)፡፡

### ለ. እራስን መግለጽ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ራስን ማስተዋወቅ፣ሃገራዊ ምልክቶች፣ ሃገርን መውደድ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-መምህር!** ህፃናቱን በማነቃቃት ለዕለቱ ተግባር ዝግጁ እንዲሆኑ ያድርጓቸው፡፡ በዕለቱ የሚሰሩትን ስራም ያብራሩላቸው፡፡ በመጀመሪያ እርስዎ እራስዎን ያስተዋውቁና ሕፃን በነበሩበት ጊዜ ምን መሆን ይፈልጉ እንደነበር፣ ለምንስ መሆን ይፈልጉ እንደነበር፣ አሁን በሚሰሩት ሥራም ምን ያህል ደስተኛ እንደሆኑ ይግለጹላቸው፡፡ በመቀጠል ህፃናቱን በማስነሳት ስለራሳቸውና ስለወደፊት ዓላማቸው ለሃገራቸው ስላላቸው ፍቅር ምን ሠርተው የሃገራቸውን ባንዲራ ማስጠራት እንደሚፈልጉ ለጓደኞቻቸው እንዲያብራሩ ያድርጉ፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ የስሜትን አገላለጽን ይለኩ፡፡ ወረቀት በማዘጋጀት የወደፊት ራዕያቸውን መመዝገብ ማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ያስቀምጡ፡፡ በመቀጠልም በመለማመጃ ደብተራቸው ፊደላትን "አ፣ ዘ፣ ዠ" ፊደላትን በድምጽ እንዲተዋወቁ እና "4" ቁጥርን እንዲጽፉ ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡
- **የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ ሥዕል፣ ባንዲራ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ራዕያቸውን መጠየቅ)፡፡

### ሐ. ፊደል በነጠብጣብ ማያያዝ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የፊደል እውቀት፣ መጻፍ፣ ቀለም፣ የሥነ ጥበብ እሴቶች
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በግል ተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በመጀመሪያ በአየር ላይ ፊደል እንዲፅፉ ያበረታቱ፡፡ በመቀጠል በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ነጠብጣብን እዲያደምቁ/ እንዲያያይዙና ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡ ከዚያም የስነ ጥበብ እሴቶችን እንዲያዳብሩ የአክሱም ሐውልትን ወይም ሌላ የጥበብ ውጤት በሥዕል በማሳየት እንዲያደንቁ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ ሞባይል
- **የምዘና ስልት፡-** ህጻናቱ እርሳሳቸውን በአግባቡ መያዛቸውን እና በመስመሩ ላይ ማድመቃቸውን መከታተል እና የፃፉት ፊደል ማን እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡

## ተግባር 2- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. እማማ ጀሚላ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፍራፍሬ፣ስሜትን መግለጽ፣ቅርፃ ቅርፅ፣ቀለማት፣መጻፍ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የቀረበላቸውን ተረት በማዳመጥ መልሰው መናገር እንደሚጠበቅባቸው ይንገሯቸው፡፡

## ተረት ተረት

እማማ ጀሚላ 4 ልጆች አላቸው፡፡ ቤተሰቦቻቸውን የሚያስተዳድሩት አትክልት እና ፍራፍሬ በመሸጥ ነው፡፡ ደንበኛቸው በለጡ ፍራፍሬ ለመግዛት ልጇን እሙን ይዛ ከቤቷ ወጣች፡፡ በለጡ "እማማ ጀሚላ እንደምን አደሩ" አለቻቸው፡፡ ደህና እንዴት ነሽ? በለጡ በማለት ከመቀመጫቸው በመነሳት ለሰላምታዋ ምላሽ ሰጧት፡፡ በለጡም "እባክዎ ጎመን እና ቲማቲም ማግኘት እችላለሁ?" ብላ ጠየቀቻቸው፡፡ እማማ ጀሚላ በለጡ የጠየቀቻቸውን አትክልት ሰጧት፡፡ እሙ ያየቻቸውን ፍራፍሬዎች በቀለማቸው ወደደቻቸው፡፡ ቀለማቸውንም መቁጠር ጀመረች፡፡ በለጡ ዋጋውን በመጠየቅ ከፍላ እቃዋን ይዛ በማመስገን ተሰናብታ ሄደች፡፡ እሙ እናቷ እስክትገዛ ዞር ዞር ስትል ከፊት ለፊት ያለው ሱቅ የቅርፃ ቅርፅ መሸጫ መሆኑን አስተዋለች፡፡ እናቷንም አብረው እንዲያዩ ጠይቃ ማየት ጀመረች፡፡ ብዙ ቅርፃ ቅርፅ ስላየች ደስ አላት፡፡ "እማዬ! እንዳይ ስለ ፈቀድሽልኝ አመሰግናለሁ፡፡ በጣም ደስ ብሎኛል! አለቻት፡፡ በለጡ የሱቁን ባለቤት በማመስገን ተሰናብታ ሄደች፡፡ እቤት እንደደረሱም እሙ ያየቻቸውን የፍራፍሬና የአትክልት ቀለሞች መቀባት ቁጥርም መጻፍ ጀመረች፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የአትክልት እና ፍራፍሬ ሥዕላዊ መግለጫ፣ የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ በለጡና እናቷ የት ሄዱ?፣ምን ገዙ?... እና ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ፣ተረቱን በትክክል እየተከታተሉ መሆኑን መከታተል...)

### ለ. ቀስተ ደመና (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ትህትና፣ቀለማት፣ቁጥር፣አከባቢ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህርሚና፡-** መምህር! ህጻናቱተረቱን በአግባቡ እንዲያዳምጡ ማድረግ፣ተረቱን በሥዕል አስደግፎ ማውራት፣ ተረቱን ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ

## ተረተ ተረት

ዮሴፍ የሚባል በጣም ጎበዝና አስተዋይ ልጅ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን የዮሴፍ እናት በጣም ታመሙና ምግብ የሚሰራላቸው አጡ፡፡ የዮሴፍ እናት ሰው አክባሪ ስለነበሩ ጓደኞቻቸውና ጎረቤቶቻቸው እቤታቸው እየመጡ ምግብ በመስራት ተንከባከቧቸው፡፡ እሳቸውም ህመማቸው እየተሻላቸው መጣ፡ ፡ ዮሴፍ በጣም ደስ አለው፡፡ እናቱ ሲልኩት ዮሴፍ ደስ ብሎት ይታዘዛል፡፡ ዛሬም እንደተለመደው ጠሩትና በአከባቢያቸው ወደ አለ መንደር ዕቃ እንዲገዛ ላኩት፡፡ ወቅቱ ብርድ ስለነበር ሹራብ ደርቦ እየሮጠ ሄደ፡፡ ድንገት ቀና ሲል በሠማይ ላይ የሚያምሩ ቀለማት ያላቸው ቀጫጭን መስመሮች አየ፡፡ ዮሴፍ ደስ አለውና ማን ይሆን ሠማይ ላይ ወጥቶ ያስቀመጣቸው በማለት ተገረመ፡፡ በጣቶቹ በማመልከት መቁጠር ጀመረ፡፡ 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ ብሎ አቆመና እንዴ ሌላም አለ ቆይ ብሎ አምስት ጣቶቹን አወጣና እንደገና ሲቆጥር ከአምስት እንደሚበልጡ ተገነዘበ፡፡ ዕቃውን ገዝቶ ሲመለስ ስላየው ነገር ለእናቱ ነገራቸው፡፡ እናቱም ቀስተ ደመና እንደሆነና 7 ቀለማት እንዳሉት አስረዱት፡፡ ስለ ቀስተ ደመና ታሪክ ነገሩት፡፡ ዮሴፍ እናቱ የነገሩትን ለጓደኞቹ ነገራቸው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ስዕላዊ መግለጫ፣ የተረት መጽሐፍ

- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ ዮሴፍ ሰማይ ላይ ምን አየ? ቀስተ ደመና ስንት ቀለሞች አሉት?)

## ተግባር 3- መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. ጓደኛዬ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፍራፍሬ፣ ሃገርመውደድ፣ ስነ ጥበብ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

**ጓደኛዬ**

ጓደኛዬ ጓደኛዬ የኔ ጓደኛ፣
እኔ ወድሻለሁ ውደጂኛ፡፡
ነይ እንብላ ፍራፍሬ፣
ይሰጠናል ጥንካሬ፡፡
ነይ እንስራ ህትመት፣
ስንጨርስ ለመደሰት፡፡
ሁሌ መስራት ፈልጋለሁ፣
ሃገሬንም እወዳለሁ፡፡
ስነ ጥበብ ደስ ይለኛል፣
እንድፈጥር ያደርገኛል፡፡/2/

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የፍራፍሬ ዓይነቶችን የያዘ ካርድ፣ ለህትመት ሥራ የሚያገለግሉ ቁሶች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ በካርዶቹ ላይ ያሉ ፍራፍሬዎች ስም መጠየቅ)

### ለ. “ሀ” ብለን (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል፣ቁጥር፣ቅርጾች፣ጥበብ፣ራስን ማስተዋወቅ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በጋራና በግል እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡

“ሀ” ብለን

“ሀ” ብለን እንጀምር መማር ፊደልን፣
ቁጥርም እናውቃለን እግረ መንገዱን፡፡
1 - 2 - 3 - 4 ቁጥርን ከተማርን፤
ትምህርት ማጣፈጫ ጥበብም አለን፡፡
ጂኦሜትሪ ቅርጾች ምስልም እናይና፣
መጻፍ እንችላለን ሁሉን እንደገና፡፡

ሃገር መውደድ ጥሩ ለሕጻናት እድገት፣
ራስን ማስተዋወቅ የምንችልበት፡፡
ይህን ሁሉ ተምረን በውቀት በልጽገን፣
እናስጠራታለን ሃገራችንን፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የፍራፍሬ ሥዕል፣ ጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾች የያዘ ካርድ /ሞዴል/፣የቁጥር ፍላሽ ካርድ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ ቁጥሮችን እና ፊደላትን መጠየቅ፣ ስለፍራፍሬ አይነቶች መጠየቅ...

### ሐ. እኔ ሚጡ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፍራፍሬ፣ ፊደላት፣ ቁጥር፣ሀገሬን እወዳለሁ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! መዝሙሩን ለለልጆቹ ቀላል በሆነ ዜማ ማለማመድ

## እኔ ሚጡ

እኔ ሚጡ እባላለሁ፣

ቤተሰቤን እወዳለሁ፡፡

ሁሌ አትክልት እበላለሁ፣

ሙዝ ብርቱካን እወዳለሁ፡፡

ቁጥር መጻፍ እችላለሁ፣

ፊደላትን እጽፋለሁ፡፡

ሀገሬን እወዳለሁ፣

መምህሮችን አከብራለሁ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** መቅረፀ ድምፅ፣ የፍራፍሬ ዓይነት የያዘ ካርድ፣ ቁጥርና ፊደላት የያዘ ፍላሽ ካርድ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ ሚጡ የምትወደው ምንድን ነው ?...)

## ተግባር 4- የክፍል ውጭ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. ሥዕል ማንበብ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት ፡-** ፊደል፣ ቁጥር፣ ፍራፍሬ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱን ወደ ውጭ ይዘው በመውጣት ክብ እንዲሠሩ ይንገሯቸው፡፡ በክቡ ውስጥ ፊደላት፣ ቁጥር፣ ፍራፍሬ፣ አትክልት፣ ባንዲራ፣ አክሱም

ሐውልት የፋሲል ግንብ ያስቀመጡ፡፡ ህፃናቱ በክቡ ዙሪያ እንዲሮጡ ፊሽካ በመንፋት ማስጀመር፡፡ ከዚያም ትንሽ እንደሮጡ በድጋሚ ፊሽካ ሲነፋ ሥዕሉን በማንሳት እያንዳንዱ ልጅ በተራ የያዙትን ሥዕል እንዲያነቡ ማበረታታት፡፡ በመጨረሻም ጨዋታውን ተጫውተው ሲጨርሱ መጫወቻውን በቦታው እንዲመልሱ ማድረግ፡፡

- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ፊደል፣ቁጥር፣ፍራፍሬ፣አትክልት፣ሀገራዊ ምልክቶችን የሚያሳዩ ካርዶች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (በካርዶቹ ላይ ያሉትን ስዕሎች እንዲያነቡ መጠየቅ)

### ለ. ተክሎች (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ተክሎች፣ ቅርጾች፣ ቁጥር፣ ህትመት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በተለያዩ ቅርጾች የተቆራረጡ ካርቶኖች፣ ወረቀት፣/ኮላ /ኡሁ/፣ የውሃ ከለር የዘጋጁ፡፡ ህጻናቱን በቡድን ይመድቧቸው፡፡ ከክፍላቸው ውጭ ያሉ ተክሎችን ምንነትና እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ያስገንዝቧቸው፡፡ እያንዳንዱ ቡድን አራት አራት ቅጠል እንዲያመጡ ያድርጉ፡፡ የያዙትን የተክል ቅጠል በውሀ ከለር ውስጥ እየነከሩ በተዘጋጀው ካርቶን ላይ እንዲለጥፉ በማድረግ የህትመት ሥራ እንዲሠሩ ያሳዩዋቸው፡፡ ተግባሩን ካጠናቀቁ በኋላ የተጠቀሙበትን እቃዎች ወደ ቦታቸው ይመልሱ፡፡ በመጨረሻም ውሃና ሳሙና ተጠቅመው እጃቸውን በአግባቡ እንዲታጠቡ ያበረታቷቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡-** በጂኦሜትሪ ቅርጾች የተቆራረጡ ካርቶኖች፣ ወረቀት፣ /ኮላ/ ኡሁ/፣ መለማመጃ ደብተር፣ የውሃ ከለር፣ ውሃ እና ሳሙና
- **የምዘና ስልት፡-**ምልከታ ተግባሩን ሲያከናውኑ መመልከት፣ የቃል ጥያቄ ለምሳሌ፡- ስንት የህትመት ስራ ሰራችሁ?...

## ተግባር 5- የቡድን ተግባር (3 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. ቅርፆችን መለጠፍ

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቅርፆች፣መታጠብ ፣ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በቡድን ስራ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የተቆራረጡ ቅርፆችን ማለትም ክብ፣ ጎነ ሶስት፣ ጎነ አራት እና ካሬ ለእያዳንዱ ቡድን በመስጠት ቀለም በመቀባት በወረቀት ላይ እየለጠፉ እንዲለማመዱ ያግዟቸው፡ ፡ በተጨማሪም ቅርፆችን በመገጣጠም የተለያዩ ቅርፆችን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ፡- ጎነ ሶስት እና ጎነ አራትን በመገጣጠም በመለጣጠፍ ጎጆ ቤት እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡ በመቀጠልም ቅርፆችን ማጣበቂያ ኮላ/ግሉ በመጠቀም ወረቀታቸው/ደብተራቸው ላይ እንዲያጣብቁ ማድረግ እና ማበረታታት፡ ፡ በተገቢው ሁኔታ እያከናወኑ ስለመሆናቸው አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም ሁሉም ሕጻናት እጃቸውን መታጠብ እንዳለባቸው ይንገሯቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የጂኦሜትሪ ቅርፅ፣ የተቆራረጡ ወረቀቶች፣ ደብተር/

ወረቀት ማጣበቂያ ኮላ/ግሉ

- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (የሰሩት ምን እንደሆነ፣ ስንት እንደሆነ፣ ስንት ቅርፆችን እንዳጣበቁ ይጠይቋቸው) እና ምልከታ (ለምሳሌ:- ተግባሩን በትክክል መስራት መቻላቸውን መከታተል፣ፎቶ በማንሳት ማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ማሰር...)

## ተግባር 6- በሥራ መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ/ሥዕልን በቀለም ማቅለም (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ፍራፍሬ፣ አትክልት፣ የጆኦሜትሪ ቅርፅ፣ ባንዲራ፣
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተግባር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ወረቀት እና ባለ ቀለም እርሳስ ለህፃናቱ በመስጠት የተለያዩ ፍራፍሬ፣ አትክልት፣ የጆኦሜትሪ ቅርፆች፣ ባንዲራ፣ ሥዕሎችን በመሳል እንዲያቀልሙ ያድርጉ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳስ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ስንት ቅርፆችን፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንደቀቡ .መጠየቅ)

# አሥረኛ ሳምንት

**የተሰጠው ሰዓት- 10 ሰዓት** **የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት-30**

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ጓደኞቻቸውን ያከብራሉ
- ማዳመጥን ይለምዳሉ ፤ ቀላል ታሪኮችን ደግመው ይናገራሉ
- 5 ቁጥርን ነጠብጣብ አያይዘው ይቀባሉ
- ፍደላትን ይጽፋሉ
- ቁሶችን በተለያዩ ምድቦች ይደረድራሉ
- የሰውነት ክፍሎችን በመጠቀም 2-3 የተለያዩ ቅርፆችን ይፈጥራሉ
- የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ቁሶችን (ለምሳሌ ዛፍ፤ አፈር፣ ውሃ...ቤት፣ መኪና፣ ኮምፒውተር፣ ጠረጴዛ ወዘተ)ይለያሉ
- በቡድን ሚና መጫወት ተግባራት ውስጥ ይሳተፋሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ግብረ-ገብ እሴት
- የድምጽ እውቀት
- የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አካባቢ
- የቦታ ግንዛቤ
- ፊደላትን መፃፍ
- ቁጥሮችን መፃፍ
- በአይነታቸው መለየትና መመደብ
- ማያያዝ፣ ግንኙነት እና መተግበር

## ተግባር 1- የግል ተግባር (7 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. ቁጥር “5” ማያያዝና መጻፍ /4 ክፍለ ጊዜ /

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መጻፍ፣ ቀለም፣ ቅርጽ፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በአየር ላይ 3 የተለያዩ ቅርጸችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡ ፡ በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ በተዘጋጀው ነጠብጣብ 5 ቁጥርን ከመስመር ሳይወጡ እንዲያያይዙና ቀለም እንዲቀቡ ያግዟቸው፡፡ ጓደኞቻቸውን እንዲያከብሩ፣ የመማሪያ ቁሶች ያላቸው ለሌላቸው ልጆች እንዲያውሱ ያበረታቱዋቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ ፍላሽ ካርዶች

- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ (ህጻናቱ የቁጥር ነጠብጣብ ማያያዝና ቀለም መቀባት ተግባራት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ መከታተል) የቃል ጥያቄ (የጻፉት ቁጥር ስንት እንደሆነ መጠየቅ...)

### ለ. ፊደላትን መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍቃላት:-** መጻፍ፣ ቀለም፣ ምድብ፣ መደርደር፣ የቦታ ግንዛቤ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በግል ተግባር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! በአየር ላይ የ "ዠ" እና "ደ" ፊደል እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡ ፡ ህጻናቱ የመለማመጃ ደብተራቸውን እንዲያወጡ ያድርጓቸውና በነጠብጣብ የተጻፉ የ "ዠ" እና "ደ" ፊደል ቅርፅን እንዲጽፉ፣ ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡ ማዕዘናትን በመጠቀም ቁሶችን በተለያየ ምድብ እንዲደረድሩ በማድረግ የቦታን ግንዛቤ እንዲረዱ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ የተለያዩ ቁሶች
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ (ህጻናቱ እርሳሳቸውን በአግባቡ መያዛቸውን እና በመስመሩ ላይ ማድመቃቸውን መከታተል)፡፡ የቃል ጥያቄ (የፃፉትን ፊደል ስም መጠየቅ)

## ተግባር 2- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. መምህር የሺ እና ተማሪዎቻቸው (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት-** ማንበብ፣ተፈጥሮ፣ሰው ሠራሽ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተረት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ ተረቱን በአግባቡ እንዲያዳምጡ እና ደግመው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ተረት ተረት

መምህር የሺ ወደ መማሪያ ክፍል ገብታ "እንደምን አደራችሁ ተማሪዎች?" አለች፡፡ ተማሪዎቹም ከመቀመጫቸው ተነስተው "ደህና እንደምን አደሩ መምህር"? አሉ፡፡ መምህር የሺ "ቁጭ በሉ ተማዎሪች አመሰግናለሁ" አለች፡፡ ተማሪዎቹም "እናመሰግናለን" መምህር ብለው ተቀመጡ፡፡ መምህር የሺ ልጆች ዛሬ ስዕሎችን እናነባለን በማለት ከቦርሳዋ ብዙ የሥዕል ካርዶችን አወጣች፡ ፡ ከዚያም ሰማይ፣ ጨረቃ፣ አፈር፣ አሸዋ፣ ሰው፣ ቤት፣ መኪና፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ፊደል "በ፣ ሰ፣ ሸ፣ አ፣ ለ፣ ከ፣ ዘ፣ ዠ፣ ደ" እና "5" ቁጥር ያለባቸውን ካርዶች ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠች፡ ፡ ልጆች በተፈጥሮ የምናገኛቸው ሰማይ፣ ጨረቃ፣ አፈር፣ አሸዋ... ሲሆኑ ሰው ሰራሽ የሚባሉት ደግሞ ቤት፣ መኪና፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር ... ናቸው አለቻቸው፡፡ ከዚያም ሥዕሎቹን ላይ ያዩትን ለጓደኞቻቸው እንዲነግሯቸው ጠየቀቻቸው፡፡ ህጻናቱ እርስ በእርስ እየተጋገዙ ሥዕሎቹን አነበቡ፡፡ ህጻናቱ በጣም ተደሰቱ፡፡ መምህር የሺንም አመሰገኗት፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ሰማይ፣ ጨረቃ፣ አፈር፣ አሸዋ፣ ሰው፣ ቤት፣ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ፊደል እና 5 ቁጥር የያዙ ካርዶች እና የተረት መጽሐፍ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ሰው ሰራሽ የሚባሉት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ፣ በተፈጥሮ የምናገኛቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ መጠየቅ...)

### ለ. አበበና አያቱ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** አክባሪ፣ ቅርጽ፣ ግብረ ገብ፣ የሰውነት ክፍሎች፣ ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተረት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ ተረቱን በአግባቡ እየተከታተሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በየመሀሉ ቆም እያሉ ጥያቄ ይጠየቋቸው።

## ተረት ተረት

አበበ እድሜው 6 ዓመት ነው። በጣም ትሁትና ሰው አክባሪ ነው። የእናትና የአባቱን እግር እያጠበ ሁልጊዜ የሚመረቅ ልጅ ነው። በትምህርቱም በጣም ጎበዝ በመሆኑ መምህራን ይወዱታል። እቤታቸው አያቱ አብረዋቸው ይኖራሉ። እሳቸውም ጥሩና ግብረ ገብ ያለው ልጅ እንዲሆን ምክር ይሰጡታል። ሁልጊዜ ቀላልና እሱን ያስተምራሉ ብለው የሚያስቡትን ተረትና ታሪኮች ይነግሩታል። እርሱም የሰማውን ለጓደኞቹና ለመምህራኑ ይነግራል። አያቱ ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮችን ያስረዱታል። በዚህም ልዩ የፈጠራ ተሰጥዖ እንዲኖረው አድርጎታል። አበበ ሁልጊዜ ከትምህርት ቤት ሲመለስ የአያቱን ጉልበት ስሞ ይመረቃል። እሳቸውም በእድሜያቸው ትልቅ ሰው ስለሆኑ ዛሬ ምን እንደተማረ ሲጠይቁት የሰውነት ክፍሎቹን በመጠቆምና ቅርፆችን በመስራት ያሳያቸዋል። አበበ አያቱን በጣም ይወዳቸዋል። ከሳቸውም ብዙ ዕውቀት አግኝቷል።

- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቁሶች የያዙ ካርዶች እና የተረት መጽሐፍ፣
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ከእነ አበበ ጋር አብረው የሚኖሩት ማን ናቸው፣ ስለ ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮች ለአበበ የነገረው ማነው)

## ተግባር 3 መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. እኔ ጎበዝ እሆናለሁ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ማክበር፣ መውደድ፣ መፃፍ፣ ማንበብ፣ ቅርጽ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! በግልና በጋራ እንዲዘምሩ በማድረግ የመከባበር፣ የመረዳዳት፣ የመፃፍ፣ የማንበብ፣ የመቁጠር፣ የመናገር እና የማዳመጥ ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ያግዟቸው።

እኔ ጎበዝ እሆናለሁ

ቤተሰቤን አከብራለሁ፣
ጓደኞቼን እወዳለሁ፣
ለመምህሬም እታዘዛለሁ።
ለአባቴ እታዘዛለሁ።/2/
በጋራ እንጫወታለን፣
ፊደሎችን እንጽፋለን።
እቃዎችን በመደርደር፣
ቁጥር መቁጠር እንችላለን።

1 2 3 4 5

መፃፍ ማንበብ እንችላለን፣
ተረቶችን በማዳመጥ
ደግመን ማውራት እንችላለን፤
እጆቻችን በመጠቀም
ቅርጽን መስራት እንችላለን፡፡

- **መማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመዝሙሩ ቅጂ፣ ሞባይል፣ የፊደልና ቁጥር ፍላሽ ካርዶች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ ( እቃዎችን ማስቆጠር፣ ፊደላትን እንዲያነቡ ማድረግ...፣ በምልከታ (መዝሙሩን ሲዘምሩ በመቅዳት ማስቀመጥ)

## ለ. መምህሮቼ (2 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ግብረ ገብ፣ ሰው ሰራሽ፣ተፈጥሮ፣ታሪክ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-**መምህር! መዝሙሩን በጋራና በግል እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው

መምህሮቼ

እምወዳችሁ ውድ መምህራን፣

የምታግዙኝ በእውቀት ብርሃን፡፡

እንዳድግ በግብረ ገብ፣

አስተምሩኝ ሁሌም በደንብ፡፡

ጓደኞቼን ስወዳቸው፣

ሲያከብሩኝ ሳከብራቸው፤

በተፈጥሮ ተደንቀናል፣

ሰው ሰራሽም ጎብኝተናል፡፡

እረፍት ላይ ስናርፍማ፣

በጋራ ነው ታሪኮችን የምንሰማ፡፡

- **መማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ሞባይል፣ ሰው ሰራሽ ቁሳቁሶች፣ ተፈጥሮን የሚያሳዩ ሥዕሎች/መጽሐፍ/
- **የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ፤**- ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ነገሮችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ ...

## ሐ. ልጆች እንማር (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-**ፊደል ፣ቁጥር ማክበር፣ሥነ ምግባር፣ ሰው ሰራሽ፣ ተፈጥሮ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር

- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ከህጻናቱ ጋር በመዘመር ያበረታቷቸው እንግር

ፊደል መጻፍ ቁጥር መቁጠር፣
ቀለም ማቀለም መመራመር፣
ታዛዥ መሆን ታላቅ ማክበር፣
ሥነ መግባር ስኬት ሚስጥር፡፡
ልጆችየ ልንገራችሁ፣
ትምህርት ቤት ከሄዳችሁ፣
ታውቃላችሁ ተምራችሁ፡፡
ከተፈጥሮ ሰማይ ምድሩን፤
ጨረቃና ከዋክብቱን፤
ከሰው ሰራሽ ኮምፒውተሩን፤
መንኮራኩር ሮኬቱን፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ሰው ሰራሽና ተፈጥሮን የሚያሳዩ ሥዕሎች ( ኮሚውተር፣ መንኮራኩር፣ሰማይ፣ ከዋክብት፣ጨረቃ....)
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (የተፈጥሮኛ ሰው ሰራሽ ነገሮችን እንዲለዩ መጠየቅ፣ የጥሩ ስነ ምግባር መገለጫዎችን መጠየቅ...)

## ተግባር 4- የክፍል ውጭ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. የዕቃዎች ቦታ (2 ክፍል ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ ቅርፅ፣ቦታ ግንዛቤ፣ አቅጣጫ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱን ከክፍል ውጭ ይዘው በመውጣት በክብ እንዲቆሙና እጆቻቸውን ወደ ላይ ከፍ በማድረግ እና በማያያዝ የክብ ቅርፅ እንዲሰሩ ያድረጉ፡፡ በመቀጠልም መሬት ላይ 3 ልጆች በጀርባቸው እንዲተኙ በማድረግ ጎነ ሶስት እና ሌሎች ቅርጾችን ያሰሯቸው፡፡ ስለ ቦታ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከቆሙበት አጠገብ የተለያዩ ስዕሎችን (ሰማይ፣ ጨረቃ፣ አፈር፣ አሸዋ፣ ሰው፣ ቤት፣ መኪና፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር ፊደል እና 5 ቁጥር) በማስቀመጥ የሥዕሎቹን አቀማመጥ በመጠየቅ አቅጣጫን እንዲለዩ በስተቀኝ፣ በስተግራ፣ ከፊት፣ ከጎን፣ ከኋላ ... እያሉ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** (ሰማይ፣ ጨረቃ፣ አፈር፣ አሸዋ፣ ሰው፣ ቤት፣ መኪና፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር ፊደል እና 5 ቁጥር) የያዘ ካርድ (ሞዴል)
- **የምዘና ስልት -** ምልከታ (ጨዋታውን ሲጫወቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ መጠየቅ እና ለሚጠይቁት ጥያቄ ምላሽ መስጠት) የቃል ጥያቄ (እረስ በእርሰ በመያያዝ የተለያዩ ቅርፆችን እንዲሰሩ መጠየቅ)

ለ. መስሎ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ግብረ ገብ፣ ሀገር ተረካቢ፣ስነ ምግባር
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በጨዋታ
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህፃናቱን ከክፍል ውጭ ይዘው በመውጣት በ 5 ቡድን ያደራጇቸው፡፡ ተግባራቱን ሲሰሩ የሞያው ስነ ምግባር እንዲኖራቸው ግንዛቤ ይፍጠሩ፡ ፡ በመቀጠል ከየቡድኑ ውስጥ በየተራ ለሁሉም የሥራ ድርሻ ይስጧቸው፡፡ ለምሳሌ ገበሬ፣ ፖሊስ፣ ሀኪም፣ መምህር፣ እናት፣ አባት በመሆን እንዲለማመዱ ያግዟቸው፡፡ በየተራ እየወጡ የተዘጋጁትን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ ገበሬው እኔ ገበሬ ነኝ! መሬት ቆፍሬ አለስልሼ የተለያዩ ሰብሎችን ዘርቼ የሃገሬን ህዝብ እመግባለሁ በስራዬም እኮራለሁ ….. እኔ መምህር ነኝ! ህፃናትን በማስተማር ሀገር ተረካቢ ትውልድ እፈጥራለሁ …የመሳሰሉትን እንዲጫወቱ ያድርጓቸው፡፡
- የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡- የተለያዩ ሙያዎች የስራ አልባሳት እና ቁሳቁሶች
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ የገበሬ፣ የፖሊስ፣ የሀኪም፣ የመምህር፣ የእናትና አባት የስራ ድርሻ መጠየቅ…፣ ምልከታ (ተግባራቱን ሲከውኑ መከታተል፣ ፎቶ ማንሳት፣ መቅረጽ…)

## ተግባር 5- በፕሮጀክት መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

ሀ. ሥዕልን በቀለም ማቅለም (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- የተፈጥሮ ቁሳቁስ፣ ሰው ሠራሽ ቁሳቁስ፣ ቁጥር፣ ፊደል
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በፕሮጀክት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! የተለያዩ ሥዕሎች የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቁሳቁስ (ደመና፣ ኮከብ፣ ሰው፣ ቤት፣ መኪና፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ፊደል "አ፣ ለ፣ ከ፣ ዘ፣ ዠ፣ ደ" እና 5 ቁጥር ሥዕሎች) መርጠው እንዲስሉና እንዲያቀልሙ ያድርጉ፡፡
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ: የመለማመጃ ደብተር፣ ባለቀለም እርሳስ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቁሳቁስ ሥዕል
- የምዘና ስልት፡- ምልከታ ለምሳሌ (ተግባራቱን በተገቢው ሁኔታ እያከናወኑ ስለ መሆናቸው አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ)፡፡ ጥያቄ (በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ምን ያህል ሥዕል እንደሳሉና እንዳቀለሙ መጠየቅ)

## ተግባር 6 በሥራ መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

ሀ. የጓሮ አትክልቶችን መንከባከብ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- መንከባከብ፣ የጓሮ አትክልት፣ በቤታቸው አከባቢ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በስራ
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህጻናቱን በቤታቸው ወይም በትምህርት ቤታቸው ግቢ ስለሚገኙ የጓሮ አትክልቶች ጥቅሞችና እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ገለጻ ያድርጉላቸው፡

፡ በመቀጠል ህጻናቱን ወደ ትምህርት ቤቱ የእርሻ /የአትክልት/ ቦታ በመውሰድ ስለ ሚንከባከቡት የጓሮ አትክልት አይነት በማሳየት ትንንሽ አረምን እንዲነቅሉ፣ አትክልቱን አፈር እንዲያስታቅፉና በትንንሽ መኮትኮቻ እንዲኮተኩቱና ወሃ እንዲያጠጡ በማድረግ እንዲንከባከቡ ያበረታቷቸው፡፡ ስራውን ሲያጠናቅቁ በቤታቸውአከባቢ የሚገኙ አትክልቶችን በመንከባከብ ቤተሰቦቻቸውን መርዳት እንድላበቸው ይግለጹላቸው፡፡ በመጨረሻም እጃቸውን ታጥበው ወደ ክፍል እንዲገቡ ያድርጓቸው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** (ትንንሽ የትክልት መኮትኮቻ፣ ውሃ ማጠጫ)
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ተግባሩን ሲያከናውኑ መከታተል) የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ ውሀ ያጠጣችሁት ተክሎች ምን ምን ናቸው?...) በማንሳት ማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ማሰር)

ማስታወሻ! ህጻናቱ ተግባሩን ሲያከናውኑ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ክትትል ያድርጉ፡፡በትምህርት ቤቱ የጓሮ አትክልት ከሌለ በሌላ የስራ አይነት በመቀየርይችላሉ፡፡

## የአውዱ ማጠቃለያ የምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም ------------------------------ጾታ-------- እድሜ ------ደረጃ-------

መግለጫ፡- ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሟሉት ብቃት ትይዩ የ "√" ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ፡፡

| ተ.ቁ | የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት | ጥሩ | በ/ጥሩ | እ/በ/ጥሩ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ፊደልን ለይተው መጥራት | | | | |
| 2 | ፊደልን መጻፍ | | | | |
| 3 | 1-5 ያሉ ቁጥሮችን በቁሳቁስ መቁጠር | | | | |
| 4 | ቁሳቁስን በመጠንና በዓይነት መለየት | | | | |
| 5 | ቁሳቁስን በመጠን አወዳድረው ማስቀመጥ/መደርደር | | | | |
| 6 | የመጓጓዣዓይነቶችንበስም መጥራት | | | | |
| 7 | አትክልትና ፍራፍሬ ዓይነቶችን በስም መጥራት | | | | |
| 8 | ሰው ሰራሽ ነገሮችን ለይተው መጥራት | | | | |
| 9 | የተቆራረጡ ነገሮችን በመግጠም ቅርጽ ማውጣት | | | | |
| 10 | ከመምህራንና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሰላምታ መለወጥ | | | | |
| 11 | ከጓደኞቻቸው ጋር ተራ ጠብቀው መጫወትን መጀመር | | | | |
| 12 | በትህትና መመለስና መጠየቅ | | | | |
| 13 | የሰውነት ክፍሎችን በስም መጥራት | | | | |
| 14 | ስማቸውንና ዕድሜአቸውን መናገር | | | | |
| 15 | ቅርፃ ቅርጾችን ቀለም መቀባት | | | | |
| 16 | ቁሳቁስን በቀለም፣ በቅርጽ፣ መለየት | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፡- ______________________________________________

______________________________________________

______________________

# አውድ ሶስት

# ጎረቤቶቼ እና ትምህርት ቤቴ

አጠቃላይ የተሰጠው ጊዜ- 5 ሳምንት

የክፍለ ጊዜ ብዛት- 150

## 3.1 መግቢያ

ጎረቤቶቼና ትምህርት ቤቴ በሚለው አውድ ውስጥ ያሉት የትኩረት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸውማለት ራስን ማወቅ፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ ራስን መቆጣጠር፣ የግል ንጽህ፣ ማህበራዊ ግንዛቤ፣ ራስን እና የቅርብ አካባቢን መንከባከብን መግለጽ በሚያስችላቸውን መሰረታዊ ክህሎቶችና ሁለተናዊ እድገታቸውን ሊያዳብሩ የሚችሉበት የመማርያና የዕድገት መስኮች ተካተዋል፡፡ ህጻናቱም ከላይ የተገለጹትን የመማርና የእድገት ብቃቶች እንዲያሳኩ  የተቀመጡትን ተግባራት በመጠቀም ከጎረቤቶቻቸውና ከት/ቤት ልምዶችን እንዲቀስሙና እንዲተገብሩ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም የህጻናቱ ሁለንታዊ እድገት እንዲጎለብት የትምህርት ቤት ቆይታቸውን ከአውዱ ጋር አስተሳስረው በማጫወትና በማለማመድ የሚጠበቀው ውጤት እንዲመጣ አስፈላጊዉን ጥረት ማደረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

## 3.2 የሚጠበቁ የመማሪያና ዕድገት ውጤቶች

ህጻናት በአውዱ ስር የተዘረዘሩ የመማሪያና ዕድገት ይዘቶችን ካጠናቀቁ በኃላ፤-

- ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያነባሉ
- ፊደላትን ይለያሉ
- በነጠብጣብ የተጻፉትን ፊደላት ይገጣጠማሉ ቀለም ይቀባሉ
- ከ1_9 ያሉቁጥሮችን ይቆጥራሉ፣ የተቆራረጡ መስመሮችን ይገጣጥማሉ፣ቀለም ይቀባሉ
- በነጠብጣብ የተሳሉ የጂኦሜትር ቅርጸ ቅርጾችን ይገጣጥማሉ( ክብ፣ ሶስት መዓዘን፣ ካሬ፣ አራት ማዕዘን
- ነጠላ ንድፍ/ ነጠላ ቅጥ/ ነጠላ ስርዓ ተጥለት/ (sengle pattern) ይሰራሉ
- የአትክልት ዓይነቶችን ይለያሉ
- ስለሚያውቋቸው ነፍሳት ይናገራሉ

- የመኖሪያ አከባቢያቸውን ይንከባከባሉ
- ስሜቶቻቸውንለመምህራኖቻቸውይገልጻሉ
- የቤተሰብአባላትን ስሞችን ይጠራሉ
- ተራን ጠብቀው ይናገራሉ
- የብሄራዊ ምልክቶችን እና በጎ ስራ የሚሰሩ ሰዎች ስሞችን ይጠራሉ
- የተለይዩየሰውአካልክፍሎችንይጠራሉ
- ከመመገባቸው በፊትና ከተመገቡ በኋላ እጃቸውን ይታጠባሉ
- አፍንጫቸውን በክንዳቸው ሸፍነው ያስነጥሳሉ
- የሀገራቸውን ሰንደቅ ዓላማ ቀለማት ይለያሉ

## 3.3 የዓውዱ አበይት ይዘቶች

- ራስን ማወቅና ማስተዋወቅ
- ማህበራዊ ግንዛቤ
- ስሜትን መቆጣጠር
- ጤናና ምግብ
- የሰውነት ክፍሎች
- የቤተሰብ አባላት
- ከ1-9 ቁጥሮችን መቁጠርና መጻፍ
- ፊደላተን መጻፍ
- የተለያዩ የቤት እንስሳት ድምጾችን መለየት
- ጥበባዊና የፈጠራ አገላለጽ
- ጂኦሜትሪና ባህላዊ ቅርጻ ቅርጽ
- የህትመት ግንዛቤ
- መለየትና መመደብ
- ሰው ሰራሽና ተፈጥሮ አከባቢ
- የሀገር ፍቅርና ሰንደቅ ዓላማ

# አሥራ አንደኛ ሳምንት

## የተሰጠው ሰዓት- 10 ሰዓት (30 ክፍለ ጊዜ)

### የሚጠበቁ የመማርያና የዕድገት ብቃት

- ስሜታቸውን ይገልጻሉ (ደስታ፣ ሀዘን፣ፍርሃት፣ቁጣን ስለራሳቸው ያወራሉ
- የቤተሰብ አባላትን ስም ይጠራሉ
- ከመምህራንና ከቤተሰባቸው ጋር ሰላምታ ይለዋወጣሉ
- የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ስም ይጠራሉ
- መሰረታዊ የግል ንጽህናን ይጠብቃሉ
- 6 ቁጥርን ይለያሉ፣ በነጠብጣብ የተጻፈውን ቁጥር ይገጣጥማሉ፣ ቀለም ይቀባሉ
- በነጠብጣብ የተጻፉ ፊደላትን ይገጣጥማሉ፤ ቀለም ይቀባሉ
- የቤተሰብ አባላት ድምጽን ይለያሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ራስን ማወቅ
- ራስን ማስተዋወቅ
- የሰውነት ክፍሎች
- ጤና
- ቁጥር መቁጠርና መጻፍ
- ፊደል ማንበብና መጻፍ
- ጥበባዊ አገላለጽ

## ተግባር 1- ውይይት (3 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. ስለ ራስ መግለጽ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ድምጽ፣ ቤተሰብ፣ ቁጥር
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በውይይት
- የመምህሩ ሚና፡- መምህር! በዚህ ክፍለ ጊዜ ህጻናቱ እየተነሱ ስለራሳቸውና ስለቤተሰቦቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ፡- እርሶ ቀጥሎ ያለውን እንደ ምሳሌ ያቅርቡላቸው፡፡

### ታሪክ

“እኔ ሜላት እባላለሁ፡፡ የአባቴ ስም ተስፋዬ ሲሆን የናቴ ስም ደግሞ መሰረት ይባላል፡፡ አንድ እህት እና ሁለት ወንድሞች አሉኝ፡፡ በጠቅላላው የቤተሰባችን ቁጥር ስድስት ነው፡፡” እናትና አባታችን ከስራ ሲመጡ ገና ከሩቁ ድምፃቸውን ለይተን እናውቃለን፡፡ የእናቴ ድምጽ ቀጭን ሲሆን ሁሌ ማታ ማታ መዝሙር ትዘምርልናለች፡፡ የአባቴ ድምጽ ደግሞ ወፍራም ነው፡፡ ድምፁን እየቀያየረ ተረት ይነግረናል፡፡ መምህር ህጻናቱ እንደ ሜላት ስለ ራሳቸው እና ስለ ቤተሰባቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

- **የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቤተሰብ ምስል፣ ሞባይል
- **የምዘና ስልት፡-** ቼክ ሊስት በማዘጋጀት (ለምሳሌ፡- ህፃናቱ ስለራሳቸው ሲገልጹ መመልከትና መመዝገብ...) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ስንት እህት አለህ/ሽ? ስንት ወንድም አለህ/ሽ? የቤተሰብህ/ሽ ቁጥር ስንት ነው?...)

## ተግባር 2- ተረት (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ማህሌት (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ማዘን፣መደሰት፣ ንፅህና መጠበቅ፣ የሰውነት ክፍሎች
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የሚነገራቸውን ተረት በጥሞና እንዲያዳምጡ በማድረግ ያዳመጡትን ተረት ደግመው መናገር እንዳለባቸው ይንገሯቸው፡፡

### ተረት ተረት!

ማህሌት የደረጃ አንድ ተማሪ ናት፡፡ የሰውነት ክፍሎቿን መጥራት እና ማሳየት ትችላለች፡፡ የሰውነት ክፍሎቿን ንፅህና በደንብ ትጠብቃለች፡፡ አልፎ አልፎ ሰፈር ስትጫወት የቤት ስራዋን ሳትሰራ ትምህርት ቤት ስትሄድ የሰሩ ልጆች ሲጨበጨብላቸው ስታይ በጣም ታዝናለች፡፡ አንድ ቀን መምህሯ ለምን የቤት ስራዋን እንደማትሰራ ስትጠይቃት ማህሌትም እኔ ከትምህርት ቤት ስመለስ ከጎረቤታችን ኤልሳ ጋር ስጫወት እረሳዋለሁ አለች፡፡ መምህሯም አይዞሽ ከጎረቤቶችችን ጋር መጫወት መልካም ነገር ነው፡፡ ቢሆንም ግን ለሁሉም ነገር ጊዜ መመደብ አለብን ስለዚህ ከአሁን በኋላ መጀመሪያ የቤት ስራችሁን ሰርታችሁ ስትጨርሱ መጫወት ትችላላችሁ እሺ! አትዘኚ አለቻት፡፡ ማህሌትም በጣም ደስ አላት፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ ማህሌትና ኤልሳ የቤት ስራቸውን ሰርተው ሲጨርሱ በደስታ አብረው ይጫወታሉ ይባላል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተረት መጻህፍት፣ የቤተሰብ መኖርያ አካባቢ ሥዕል፣ የሰውነት ክፍል ሥዕል፣ የግል ንፅህና ሲጠብቁ የሚያሳይ ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የሰውነት ክፍላቸውን ስም እንዲጠሩ መጠየቅ፣ የጓደኞቻቸውን ስም መጠየቅ፣ንፅህናቸውንእንዴት እንደሚጠብቁ መጠየቅ...)

## ተግባር 3- የግል ተግባር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ፊደል መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል፣ ቀለም መቀባት፣ ነጠብጣብ መገጣጠም
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር፣ሰርቶ በማሳየት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! እባክዎን በህጻናቱ መለማመጃ ደብተር ላይ "ጀ" እና "ጰ" ፊደላትን እንዲተዋወቁ ካደረጉ በኋላ በነጠብጣብ በመጻፍ ነጠብጣቡን በእርሳስ እንዲገጣጥሙ እና የተለያዩ ቀለማትን እንዲቀቡ ያደርጉ፡፡ እንዲሁም የሰሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ እና የሰሩትን እንዲገልጹ እድል ይስጧቸው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የቁጥር ገበታ፣ ሎቶ/ ማዛመጃ ሰሌዳ/፣ ከለር፣ መለማመጃ ደብተር /ወረቀት/፣ እርሳስ
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ:-"ጀ" እና "ጰ" ፊደላትን ሲጽፉ በመመልከት...) እና የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- የፃፉችሁት ፊደል ማን ነው ? ምን አይነት ቀለም ቀባችሁ? )

### ለ. ቁስ መቁጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-**ቁሳቁስ፣ ሰላምታ፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ መቁጠር
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተግባር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ከህፃናቱ ጋር በመሆን አንድ ጠረጴዛ ከፊት ለፊት አዘጋጅተው የሚቆጠሩ ቁሶችን ያስቀምጡ፡፡ እራቅ አድርገው ሌላ ባዶ ጠረጴዛ ያዘጋጁ፡፡ ከዚያም ህጻናቱ ተራ በተራ ከቦታቸው በመነሳት ፊት ለፊት ወጥተው እራሳቸውን በማስተዋወቅ ለመምህራቸው እና ለጓደኞቻቸው ሰላምታ ያቅርቡ፡፡ በመቀጠል የተዘጋጀውን ቁስ ስድስት እስኪሞላ ድረስ ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ እየቆጠሩ ወደ ተዘጋጀው ባዶ ጠረጴዛ ይውሰዱ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** እስከ 6 ድረስ ሊቆጠር የሚችል ቁስ (የፕላስቲክ ኩባያ፣ ቆርኪ፣ ጠጠር....) እና ጠረጴዛ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- ስትቆጥሩ የትኛውን የሰውነት ክፍል ተጠቀማችሁ?፣ ስንት ነገሮችን ቆጠራችሁ? እቃዉን ያነሳችበት የሰውነት ክፍል ምንድን ነው? )

## ተግባር 4- የክፍል ውስጥ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. እንቆቅልሽ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ትምህርት ቤት፣ ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ደስተኛ፣ የሰውነት ክፍል
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በእንቆቅልሽ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱን እንቆቅልሽ በመጠየቅ በመልሱ ላይ እንዲሳተፉ ያድርጉ፡፡ የመማር ብቃቶቹን መሰረት ያደረጉ ሌሎች እንቆቅልሾችን መጠየቅ ይችላሉ፡፡

### እንቆቅልሽ

1. የቤተሰብ አባል ነኝ ለቤተሰቦቹ ምግብ እሰራለሁ፣ ልጆቼን ቁርስ አብልቼ ወደ ት/ቤት እሸኛለሁ፣ ህፃኑስ ቸ ልጄን ጡት አጠባለሁ እኔ ማነኝ? --- እናት
2. የሰው አካል ክፍል ነኝ፤ በቁጥር አንድ ስሆን ሁለት ቀዳዳ አለኝ፣ ጥሩና መጥፎ ሽታን እለያለሁ፣ አየር አስገባለሁ አስወጣለሁ፣ እኔ ማነኝ? --- አፍንጫ
3. ትምህርት ቤት አብረን እንሄዳለን፣ እንማራለን፣ እንጫወታለን፣ እናጠናለን በዚህም በጣም ደስተኛ ነን በአንድ አካባቢም እንኖራለን እኛ ማነን? ........ጓደኛሞች

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** መጽሃፍ፣ ከእንቆቅልሾቹ ጋር የሚሄዱ ምስሎች፣ የሰውነት ክፍሎች ሥዕል፣ የቤተሰብ ፎቶ /የእናትን ሚና የሚያሳይ ቤተሰብ ፎቶ/ሥዕል
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- ልጇን የምታጠባ ማን ናት? በአንድ አከባቢ የሚኖሩ ምን ይባላሉ ? ) ምልከታ (በትክክል ማዳመጥና መመለስ መቻላቸውን ማረጋገጥ)...

## ተግባር 5- መዝሙር (6 ክ/ ጊዜ)

### ሀ. እኔና ጎረቤቴ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ደስታ፣ ጎረቤት፣ ሰላምታ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በመዝሙር
- **የመምህሩ ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ በቡድንና በግል እንዲዘምሩ ያግዟቸው፡፡

**እኔና ጎረቤቴ**

በጠዋት ተነስቼ፣ ፊቴን ተጣጥቤ፣
ቁርሴንም በልቼ ልብሴን ለባብሼ፡፡
ደብተሬን ከትቼ ቦርሳዬን አንግቼ፣
ውድ ጓደኛዬን ከጎረቤት ጠርቼ፡፡

ትምህርት ቤት ሄድን በጣም ተደሰትን፣

ክፍል ውስጥ ገብተን ቦታችንን ያዝን፣

ለአስተማሪያችን ሰላምታ አቀረብን፣

እየተጫወትን አብረንም ዘመርን፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- መቅረፀ ድምፅ፣ ሞባይል/ሞንታርቦ /ጂፓስ
- የምዘና ስልት:- የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- ሰላምታ የሚቀርበው ለማን ነው?፣ ወደ ትምህርት ቤት ከማን ጋር እንደመጡ መጠየቅ፣ ጠዋት ሲነሱ ምን እንደሚያደርጉ መጠየቅ)

### ለ. መምህራኖቼ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- መቁጥር፣ የሰውነት ክፍል፣ ሰላምታ
- የማስተማርያ ዘዴ:- በመዝሙር
- የመምህሩ ሚና:- መምህር! ህጻናቱ በቡድንና በግል ሲዘምሩ ማየት እና ተገቢ ቃላት መጠቀማቸውን ይከታተሉ፡፡

**መምህራኖቼ**

መምህራኖቼ በጣም ነው የሚወዱኝ፤
ገና ከሩቅ ሲያዩኝ ሰላምታ እየሰጡኝ፡፡
አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት
አምስትና ስድስት ብለው አስቆጠሩኝ፤
የሰውነት ክፍሌን ስም እየነገሩኝ፡፡
እጅ፣ እግር፣ አፍንጫ አይንና ጆሮ፤
አንገትና ራሴን ወገቤን ጨምሮ፡፡
እኔም በደስታ ትምህርቴን ተማርኩኝ፤
ከጓደኞቼ ጋር እየተጫወትኩኝ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የቁጥር ገበታ፣ የሰውነት ክፍሎችን የሚሳይ ሥዕል
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- ቁጥሮችን መጠየቅ፣ የሰላምታ አባባሎችን መጠየቅ (ጠዋት መምህራኖቻችንን ስናገኝ እንዴት ሰላም እንላለን .....?/

## ተግባር 6- የውጭ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. ስሜት

- **ቁልፍ ቃላት:-** ስሜት፣ ቁጥር፣ ቡድን
- **የማስተማሪያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህሩ ሚና:-** መምህር! ህጻናቱን ወደ ውጪ ይዘው በመውጣት 5 አባላት ባላቸው ቡድን እንዲደራጁ ያደርጓቸው፡፡ ይህንን ተግባር በራሳቸው እንዲያከናውኑ ዕድል ይስጧቸው፡፡ በመቀጠልም ከታች ባለው መመሪያ መሰረት በቅደም ተከተል ይተግብሩ፤

1. ለጫዋታው የሚመች ቦታ በመፈለግ በአንድ ቡድን 5 አባላትን ያደራጁ፤
2. የቡዱን ስም በጋራ ያውጡ (ለምሳሌ:- መደሰት፣ መገረም፣ ጎረቤቴ፣ ትምህርት ቤቴ) የመሳሰሉ፤
3. አያንዳንዱ ቡድን አራት የተለያዩ ስሜቶች የሚሳዩ ህጻናትን እንዲመርጡ ያድርጉ፤
4. ለእያንዳንዱ ቡድን አባላት በሚስጥር የተለያዩ የስሜት አይነቶችን (ደስታን፣ ሀዘን፣ ፍርሃት እና ቁጣን) የሚያሳዩ ሚና እንዲከፋፈሉ ያድርጉ
5. ለእያንዳንዱ የቡድን አባላት ተራ ቁጥር ይስጡ (1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛእና 4ኛ … ሲባል የሚያቀርብ ተረኛ)
6. መ/ር አንድ ዙር ጨዋታውን ያሳዩዋቸው
7. መ/ር በቡድኑ መጠሪያ ስም መሰረት ለአባላቱ የተሰጠውን ቁጥር ተራ በተራ በመጥራት ያጫውቷቸው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ስሜትን የሚሳይ ሥዕል፣የቁጥር ካርድ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- ከጨዋታው በኂላ ምን አይነት ስሜት እንደተሰማቸው መጠየቅ፣ ወክለው የተጫወቱትን ስሜት መጠየቅ፣ የቡድናቸውን ስምና የተሰጣቸውን ቁጥር መጠየቅ…)ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ምዘና ማድረግ…

## ተግባር 7፡- ፕሮጀክት (5 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ከጭቃ ቁጥሮችን መስራት (5 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት:-** ቅርፅ፣ መቁጠር፣ መታጠብ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በፕሮጀክት
- **የመምህሩ ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ በጭቃ ብዙ ቅርጻ ቅርጽ መስራት እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡ የዛሬው ፕሮጄክት በጭቃ የፈለጉትን የሰውነት ክፍል ቅርፅ መስራት እንደሆነ ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠልም ጭቃ/ አርቴፊሻል ጭቃ/፣ አፈርና ዉሃ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም ጭቃውን ካቦኩ በኂላ ህጻናቱ መስራት የፈልጉትን ቅርፅ እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡ ጭቃውን ወደ አፋቸው እንዳያስገቡ ይጠንቀቁ ፡፡ የሰሩትንም በመቁጠር ስንት እንደሰሩ ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሳዩ፡፡ ተግባሩን ካጠናቀቁ በኂላ የተጠቀሙባቸውን እቃዎች በቦታቸው ይመልሱ፣ አካባቢውን ያፅዱ በመጨረሻም እጃቸውን በአግባቡ እንዲታጠቡ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** አፈር፣ ዉሃ፣ ሳህን፣ ጭቃ/አርቴፊሻል ጭቃ/፣ የቁጥር ካርድ
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ:-ምን እንደሰሩ እና እንዳቃታቸዉ…) የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- ስንት ቁጥርን ሰራችሁ፣ እንዴት ሰራችሁ)

# አሥራ ሁለተኛ ሳምንት

የተሰጠው ሰዓት- 10 ሰዓት (30 ክፍለ ጊዜ )

## የሚጠበቁ የመማርያና የዕድገት ብቃት

- ጥሩ ያልሆኑ (ለምሳሌ የብስጭት) ስሜቶችን ይቆጣጠራሉ
- የተለያዩ የቤት እንስሳት ድምጽን ይለያሉ
- ድምጽ የሰሙበትን አቅጣጫ ይናገራሉ
- የመማሪያ ክፍል ቁሳቁስን ይለያሉ
- የአትክልት አይነቶችን ይለያሉ
- 7 ቁጥርን ቀለም ይቀባሉና የ7 ቁጥር ነጠብጣቦች ያገናኛሉ
- በነጠብጣብ የተጻፉ ፊደላትን ቀለም ይቀባሉ
- የሃገራቸውን ሰንደቅ አላማ ቀለማት ይቀባሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ራስን መቆጣጠር
- ድምጽን መለየት
- የቅርብ አካባቢ
- ተመጣጣኝ ምግብ
- ቁጥሮችን መጻፍ
- ፊደልን መጻፍ
- የፊጠራ አገላለጽ

## ተግባር 1- የግል ተግባር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቁጥሮች ማጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- ቁጥር፣ መደሰት፣ መገጣጠም
- የማስተማርያ ዘዴ:- በግል ተግባር
- የመምህሩ ሚና:- መምህር! 7 ቁጥርን ጠረጴዛ ላይ በማስቀመጥ ወይንም ግድግዳ ላይ በመለጠፍ ህጻናቱ እንዲያዩትና በእጃቸው እንዲነካኩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም 7 ቁጥርን በወረቀት ላይ በነጠብጣብ ይፃፉና ይስጧቸው፡፡ ህጻናቱ ነጠብጣቡን በመገጣጠም ቀለም ከቀቡ በኋላ ግድግዳ ላይ እንዲለጥፉ ያግዟቸው፡፡ እግረ መንገዳቸውን ክፍሉ ውስጥ ያለውን ቁሳቁስ በደንብ እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ በሂደቱ ውስጥ የተደሰቱበት ወይም ያልተደሰቱበት አጋጣሚ ካለ ከነምክንያቱ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- እርሳስ፣ ወረቀት /ደብተር/፣ 7 ቁጥር (በፍላሽ ካርድ/በቻርት) የተለያዩ ስሜቶችን የሚያሳዩ ስዕሎች፡፡

- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- በክፍሉ ውስጥ ሲዘዋወሩ የሚያከናውኑትን ተግባር በመመልከጥ...) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ስንት ቁጥር አቀለምክ/ሽ/?ያንቺ/ያንተ እድሜ ስንት ነው?፣ ስትዘዋወሩ ክፍሉ ውስጥ ምን አያችሁ? ...)

### ለ. የኢትዮጲያን ሰንደቅ አላማ ቀለም መቀባት (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ነጠብጣብ መገጣጠም፣ ቀለም፣ መቀባት፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በግል ተግባር
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! ለህጻናቱ የተግባሩን ህግ ማሳወቅ፣ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ የሚያስፈልጉ ቁሳቁስን ማቅረብ፣ በመከታተል፤ ስለ ሰንደቅ አላማ ቀለማት የሀገራችንን ሰንደቅ አላማ ማሳየት ይጠበቅቦታል፡፡ ለክፍለ ጊዜው ተግባር የሚሆኑ ቁሳቁስን ያዘጋጁ፡፡ ከዚያም በካርድ /በወረቀት/ ላይ በነጠብጣብ የተሰራ የሰንደቅ አላማ ሥዕል ስለው ለህጻናቱ በማከፋፈል ነጠብጣቡን በመገጣጠም አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለም በትክክለኛ ቦታቸው እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡ የቀለማቱን አይነትና ቁጥር እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ ሲጨርሱ የሰሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ካሳዩ በኋላ በማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ይሰሩላቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** በወረቀት /በካርድ በነጠብጣብ የተዘጋጀ ሰንደቅ አላማ፣ እርሳስ፣ አረንጓዴ፣ ቀይ እና ቢጫ ቀለም
- **ምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ሲያደምቁና ሲቀቡ መመልከት...)፣ የቃል ጥያቄ (ምን አደመቃችሁ?፣ ምን አይነት ቀለም ቀባችሁ?፣ ስንት አይነት ቀለም ቀባችሁ?....)

### ሐ. ፊደል 'በ'ን በነጠብጣብ መፃፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቀለም፣ ፊደል፣ ስሜት
- **የማስተማር ዘዴ፡-** በግል ተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በመጀመርያ ህፃናቱ የብስጭትና አስቸጋሪ ስሜቶችን እንዴት መቆጣጠር እንደሚችሉ ግንዛቤ ይስጧቸው፡፡ (ለምሳሌ ነገሮችን በጉልበት አለመውሰድ፣እኔ ብቻ ልጠቀም የመሳሰሉ አስቸጋሪ ስሜቶችን ...) በመቀጠልም የፊደል አፃፃፍን የሚለማመዱበት ሰዓት በመሆኑ ለተግባራቱ የሚሆን ቁሳቁስ ያዘጋጁ፡፡ ከዚያም ፊደል 'በ' ን በወረቀት ላይ በነጠብጣብ ይፃፉና ይስጧቸው፡፡ ህጻናቱ ነጠብጣቦቹን አገናኝተው ቀለም እንዲቀቡ ያግዟቸው፡ ፡ ሲጨርሱ የፃፉትን ፊደል እና የቀቡትን ቀለም ለክፍል ጓደኞቻቸው ተራ በተራ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** በወረቀት /በካርድ በነጠብጣብ የተዘጋጀ የፊደል "በ" ቅርፅ፣ እርሳስ፣ የተለያዩ ቀለማት
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የፃፋችሁት ፊደል ማናት ምን አይነት ቀለም ቀባችሁ?፣ በጻፋችሁት ፊደል የሚጀምር የእንስሳት ስም ጥሩ) ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ፡- በአግባቡ እየሰሩ መሆኑን መመልከት...)

## ተግባር 2- መዝሙር (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ትንሿ ውሻዬ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ተክሎች፣ ድምጽ፣ ደስታ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በጋራና በግል እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

**ትንሽዋ ውሻዬ**

ትንሽዋ ውሻዬ በጣም ነው የምወድሽ፤

ቡቺይዬ ብዬ ስም አወጣሁለሽ፡፡

ካንቺጋር መጫወት ዘና ያደርገኛል

ው… ው… ው… ስትይ ድምፅሽ ደስ ይለኛል፡፡

ከአጠገቤ አትጠፊም ሳዝንና ስከፋ፣

የኔዋ ቡችዬ ነሽ እኮ ቀልጣፋ፡፡

በግቢያችን ተክሎች ዙሪያ እየዘለልን፤

የአበቦቹን ውበት ደግሞ እያደነቅን፡፡

ትምህርት ቤት ስሄድ ትናፍቂኛለሽ፣

እስክመጣ ድረስ በአይኔ ትመጫለሽ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የውሻ ሥዕል፣ቴፕ ማጫወቻ፣ በሞባይል የተቀረፀ የውሻ ድምፅ፣ የውሻ አሻንጉሊት
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- በመዝሙሩ ውስጥ ስላሉት ነገሮች መጠየቅ (የውሻ ድምፅ ማስመሰል የሚችል ማነው?

### ለ. ፊደላት (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል፣ ጓደኛ፣ ድምጽ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን በአግባቡ እንዲዘምሩ ያግዟቸው

ድምፅ ሰማሁ

ፊደል "ተ" አለች ተ ተ ተ

ፊደል "ቸ" አለች ቸ ቸ ቸ

ፊደል "ቀ" አለች ቀ ቀ ቀ

ፊደል "ገ" አለች ገ ገ ገ

አዲስ ድምጽ ሰማሁ ከኋላ

የጓደኛዬ ነበር የላላ

ሌላ ድምጽ ሰማሁ ከበር

ሚያው ሚያው የውሮ ነበር /2/

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የድመት ሥዕል፣ አሻንጉሊት፣ በሞባይል የተቀረፀ መዝሙር፣ የፊደላት ፍላሽ ካርድ
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ:- ሲዘምሩ መከታተል) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- "ቸ" ስንት እግር አላት፣ "ቀ" ስንት እግር አላት፣ ድመት ስንት እግር አላት) የድመት ድምጽ እንዴት ነው…)

## ተግባር 3:- የውጪ ጨዋታ (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ድምፁ የማነው (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ድምፅ፣ ቁጥር፣ተራ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ከክፍል ውጪ ወዳለው የመጫወቻ ስፍራ ይዘዋቸው ይውጡ፡፡ በመቀጠልም ድምጹ የማነው የሚለዉን ጨዋታ ለማጫወት የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች ይከተሉ

1. የተለያዩ እንስሳት (በግ፣ የላም፣ የውሻ፣ የዶሮ፣ የድመት) ምስል ያለበት የፊት ጭንብል በጠንካራ ወረቀት ሰርተው ያዘጋጁ፡፡
2. በስዕሉ ጀርባ ቁጥር ይፃፉበት እና በሳጥን /በሳህን/ ውስጥ ያስቀምጡ፡፡
3. ከዚያም ህጻናቱ አምስት አምስት እየሆኑ በየተራ ወጥተው አንድ ማስክ በማንሳት ፊታቸው ላይ በማድረግ ከጀርባው ያለውን ቁጥር ተናግረው የእንሰሳውን ድምጽ እንዲያሰሙ ያድርጉ፡ :
4. ሥዕል የሚሻማ ህጻን ከጨዋታ እንደሚወጣ ይንገሯቸው፡፡
5. በዚሁ መሰረት በየተራ እንዲጫወቱ በማድረግ ሲጨርሱ የተጠቀሙበትን እቃ ወደ ክፍል እንዲያስገቡ ያድርጉ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተለያዩ እንስሳት (በግ፣ የላም፣ የውሻ፣ የዶሮ፣ የድመት) ሥዕል ያለበት የፊት ጭምብል፣ የተቀረጸ እንስሳ ድምጽ
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ (ለምሳሌ:- ሲጫወቱ በመመልከት የተመለከቱትን በመመዝገብ ተግባሩን ያላከናወኑ ህፃናት ተመልሰው እንዲሰሩ በማድረግና የሚጠበቀው ብቃት ላይ ማድረስ) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- የበግ ድምፅ አሰሙ፣ የውሻ ድምጽ አሰሙ፣ስንት እንስሳትን ተዋወቅን እነማናቸው? …)

ለ. ድምፁ ከየት መጣ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** አቅጣጫ፣ ድምፅ፣ ተክሎች፣ እንስሳት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለዚህ ጨዋታ የእንስሳቱን የፊት ጭምብል እና ንፁህ ፎጣ /ሻሽ/ ያዘጋጁ፡፡

1. ለአንድ ዙር ጨዋታ አምስት ህጻናት ያዘጋጁ፡፡
2. አንዳቸውን አይናቸውን ይሸፍኑ፡፡ አራቱ ህፃናት የደረሳቸውን የእንስሳት የፊት ጭንብል አጥልቀው በተለያየ አቅጣጫ እንዲቆሙ ያድርጉ፡፡
3. ተራ በተራ በአይን ምልክት እየሰጡ ተጫዋቾቹ የደረሳቸውን እንስሳ ድምጽ እንዲያሰሙ ያድርጉ፡፡
4. አይኑን የታሰረ ህጻን ድምጹ ከየትኛው አቅጣጫ እንደመጣ እንዲናገር ያድርጉ (ከፊት ነው፣ ከኋላ፣ ከጎን …..)
5. ለዛሬ ግማሾቹ ህፃናት ከተጫወቱ በኋላ ድምጻቸውን ያሰሙት እንስሳት የሚመገቡትን ተክሎች ስም እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ያልተሳተፉትን ህጻናት በሚቀጥለው ቀን እንዲሳተፉ ያድርጉ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቤት እንስሳ ሥዕል ጭንብል፣ ፎጣ /ሻሽ/፣ የተቀረጸ የእንስሳ ድምጽ የያዘ ሞባይል
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ ማድረግ እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡-/ ድምጾቹ የተሰሙበትን አቅጣጫ መጠየቅ፣ ምን አይነት እጽዋት/ተክሎች እንዳዩ መጠየቅ)

## ተግባር 4፡- ተረት (10 ክፍለ ጊዜ)

ሀ. እመቤትና አሊ (5 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፍራፍሬ፤ ቀለማት፣ጣእም፣ጤና
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የቀረበላቸውን ተረት በጥሞና አዳምጠው ደግመው መናገር እንዳለባቸው ያስረዷቸው፡፡

### ተረት ተረት!

እመቤትና አሊ ጎረቤታሞች ናቸው፡፡ በአንድ ት/ቤት ይማራሉ፡፡ ሁልጊዜ ከጨዋታ መልስ እጃቸውን በውሃ እና በሳሙና ይታጠባሉ፡፡ በዚህ የተነሳ መምህራቸው ሁልጊዜ ታስጨበጭቡላቸዋል፡፡ ቅዳሜና እሁድ አብረው ይጫወታሉ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ከጨዋታ ሲመለሱ የአሊ እናት አንድ ፓፓዬ፣ ሁለት ሙዝ፣ አንድ ፖም፣ እና ሶስት ብርቱካን ሰጠቻቸው፡፡ እመቤት ብርቱካን እና ሙዝ እየመረጠች በላች፡፡ አሊ ግን ሁሉንም አይነት ፍራፍሬ በላ፡፡ የአሊ እናት ሁኔታውን አይታ ምነው ቤቲ! ፓፓያ እና ፖሙን አልወደድሽውም እንዴ! ብላ ጠየቀቻት፡፡ ‹እመቤትም አዎ አልወድም፡፡ እኔ የምወደው ብርቱካን እና ሙዝ ነው አለች፡፡ የአሊ እናትም እሙዬ ፍራፍሬዎች ሁሉ የራሳቸው የሆነ ቀለም እና ጣዕም አላቸው፡፡ ሁሉም ለጤናችን በጣም ያስፈልጉናል፡፡ አንቺም ሁሉንም መመገብ መለማመድ አለብሽ አለቻት ይባላል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ስሜትን የሚገልጹ ስእሎች (የደስታ፣ የሃዘን..) ፍራፍሬዎችን የያዘ ፍላሽ ካርድ/ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- ጎረቤታሞቹ ማንና ማን ናቸው?፣ የማትወደው ፍራፍሬ ምን ነበር?፣ እናንተስ ያማትወዱት ፍራፍሬ አለ?፣ ፍራፍሬ መመገብ ለምን ይጠቅማል?፣ ስንት ፍራፍሬ ሰጠቻቸው?...)

### ለ. አቤልና ከድር (5 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ድምጽ፣መረጋጋት፣ድምጽ፣መናደድ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ተረቱን በአግባቡ እንዲያዳምጡ ይከታተሉ

## ተረት ተረት!

አቤልና ከድር ጓደኛሞች ናቸው፡፡ አንድ ቀን መምህርቷ ክፍል በመግባት ድምጽ የማስመሰል ጨዋታ እንደሚጫወቱ ነገረቻቸው፡፡ አቤልን የውሻ ድምጽ፣ ከድርን ደግሞ የድመት ድምጽ እንዲያሰሙ ነገረቻቸው፡፡ አቤል ቶሎ ብሎ እንደ ድመት ጮኸ፡፡ ከድር ተናዶ አቤልን ገፈተረው፡፡ አቤልም ተናደደ፡፡ መምህርቷም አቤል በጣም እንደ ተናደደ ስለ አየች ቁጭ አድርጋ አየር እያስገባ እና እያስወጣ እንዲተነፍስ አድርጋ አረጋጋችው፡፡ ከድርን እንዲቀመጥ አድርጋ የፈፀመው ተግባር ተገቢ አለመሆኑን አስረዳችው፡፡ ከድርም በሰራው ተገባር በጣም አዘነ፡፡ እኔ ድመት ስለምወድ ነው እንደዚህ ያደረኩት በጣም ይቅርታ ብሎ መምህራቸውን፣ አቤልን እና የክፍል ጓደኞቹን ይቅርታ ጠየቀ ይባላል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የእንስሳት ሥዕል፣ የተቀረፀ የእንስሳት ድምፅ፣ የተለያዩ ስሜት ገላጭ ስዕሎች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የተሳሳተው ማነው?፣ ይቅርታ የጠየቀው ማነው?፣ ይቅርታ ለምን ጠየቀ?)

## ተግባር 5፡- ውይይት (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ጤናማ ምግብ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፍራፍሬ፣አትክልት፣መቁጠር፣መቀባት፣መሳል
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በውይይት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በቅድሚያ ፍራፍሬ፣ የጓሮ አትክልቶች፣ ጥራጥሬ፣ ውሃ፣ ወተት የመሳሰሉትን በተገቢ መጠን መመገብ ለጤና ጠቃሚ መሆኑን ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠል እነሱ የሚያውቁትን ፍራፍሬ፣ የጓሮ አትክልት እና ጥራጥሬ እንዲዘረዝሩ ያድርጉ፡፡ ስንት የፍራፍሬ አይነቶች፣ ስንት የጓሮ አትክልቶች አይተው እና በልተው እንደሚያውቁ ይቁጠሩ፡፡ በመጨረሻም ወረቀት እና እርሳስ በመስጠት የፈለጉትን የፍራፍሬ አይነት በመሳል እና ከለር በመቀባት ቆጥረው ለክፍል ጓደኞቻቸው ይንገሩ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የፍራፍሬ፣የጓሮ አትክልቶች፣ የጥራጥሬ አይነቶች ፣ወተት.... በሥዕል /ሞዴል/

- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ለጤና አስፈላጊ የሆኑ የምግብ አይነቶችን ዘርዝሩ፣ የፍራፍሬ አይነቶች እነማን ናቸው...)

## ተግባር 6፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. እንቆቅልሽ

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ ፊደል፣ የቤት እንስሳ፣ ቀለማት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በእንቆቅልሽ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን እንቆቅልሽ በመጠየቅ መልሶቻቸውን እንዲመልሱ ያድርጉ፡ ፡ ቀጥሎ እነሱ ሁለት ሁለት እየሆኑ እርስ በርስ እንዲጠያየቁ ያድርጉ፡፡ የመማር እና እድገት ብቃቶቹን መሰረት ያደረጉ ሌሎች እንቆቅልሾችን መጠየቅ ይችላሉ፡፡

እንቆቅልሽ

1. ከቤት እንስሳት ውስጥ አንዱ ነኝ፡፡ ግቢ ውስጥ ታስሬ እውላለሁ፡፡ ሌባን እጠብቃለሁ፡፡ ስጋ እበላለሁ፡፡ አጥንትም እቆረጥማለሁ፡፡ እኔ ማን ነኝ ? ውሻ
2. ፊደል ነኝ፡፡ ሁለት እግር አለኝ፡፡ በግ እና በሬ ይፃፍብኛል፡፡ እኔ ማነኝ-?-- ‹‹በ››
3. ከጨርቅ እሰራለሁ፡፡ ሀገር እወክላለሁ፡፡ ሶስት ቀለማት ረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ተቀብቻለሁ፡፡ እኔ ማነኝ? --- ‹‹የኢትዮጲያ ሰንደቅ ዓላማ››
4. ከ1-8 ካሉት ቁጥሮች ውስጥ ነኝ፡፡ ቅርጼ ከዘራ የመስላል፡፡ እኔ ማን ነኝ--- 7

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** እንቆቅልሹን የሚወክል ሥዕል፣ፊደሎች፣ ባንዲራ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ ውሻ ስንት እግር አለው?፣ ውሻ ምን ይበላል?)

## ተግባር 7- የግል ተግባር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቁጥሮች ማጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ ስሜት፣ መገጣጠም
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በግል ተግባር
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! መምህር! ህጻናቱ 7 ቁጥርን ጠረጴዛ ላይ በማስቀመጥ ወይንም ግድግዳ ላይ በመለጠፍ ህጻናቱ እንዲያዩትና በእጃቸው እንዲነካኩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም "7" ቁጥርን በወረቀት ላይ በነጠብጣብ ይፃፉና ይስጧቸው፡፡ ህጻናቱ ነጠብጣቡን በመገጣጠም ቀለም ከቀቡ በኋላ ግድግዳ ላይ እንዲለጥፉ ያግዟቸው፡፡ እግረ መንገዳቸውን ክፍሉ ውስጥ ያለውን ቁሳቁስ በደንብ እንዲመለከቱ ያደርጉ፡፡ በሂደቱ ውስጥ የተደሰቱበት ወይም ያልተደሰቱበት አጋጣሚ ካለ ከነምክንያቱ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- **የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** እርሳስ፣ ወረቀት /ደብተር/፣ 7 ቁጥር (በፍላሽ ካርድ/በቻርት) የተለያዩ ስሜቶችን የሚያሳዩ ስዕሎች፡፡
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- በክፍሉ ውስጥ ሲዘዋወሩ የሚያከናውኑትን ተግባር

በመመልከጥ...) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ስንት ቁጥር አቀለምክ/ሽ/?ያንቺ/ያንተ እድሜ ስንት ነው?፣ ስትዘዋወሩ ክፍሉ ውስጥ ምን አያችሁ? ...)

ለ. የኢትዮጲያን ሰንደቅ አላማ ቀለም መቀባት (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ነጠብጣብ ማድመቅ፣ ቀለም መቀባት፣ ቁጥር
- የማስተማሪያ ዘዴ፡- የግል ተግባር/በማሳየት፣ በማስረዳት/
- የመምህሩ ሚና፡- መምህር! ለህጻናቱ የተግባሩን ህግ ማሳወቅ፣ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማቅረብ፣ በመከታተል፤ስለ ሰንደቅ አላማ ቀለማት የሀገራችንን ሰንደቅ አላማ በማሳየት ይንገሯቸው፡፡ ለክፍለ ጊዜው ተግባር የሚሆኑ ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ፡ ፡ ከዚያም በካርድ /በወረቀት/ ላይ በነጠብጣብ የተሰራ የሰንደቅ አላማ ስዕል ስለው ለህጻናቱ በማከፋፈል ነጠብጣቡን በመገጣጠም አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለም በትክክለኛ ቦታቸው እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡ የቀለማቱን አይነትና ቁጥር እንዲናገሩ ያድርጓቸው ሲጨርሱ የሰሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ካሳዩ በኂላ በማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ይሰሩላቸው፡፡
- የመማሪያኛ የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- በወረቀት /በካርድ በነጠብጣብ የተዘጋጀ ሰንደቅ አላማ፣ እርሳስ፣ አረንጓዴ፣ ቀይ እና ቢጫ ቀለም
- ምዘና ስልት፡- ምልከታ (ሲያደምቁና ሲቀቡ መመልከት...)፣ የቃል ጥያቄ (ምን አደመቃችሁ?፣ ምን አይነት ቀለም ቀባችሁ?፣ ስንት አይነት ቀለም ቀባችሁ?....)

ሐ. ፊደል “ተ፣ቸ፣ ቀ” ን በነጠብጣብ መፃፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ቀለም፣ ፊደል፣ ብዛት
- የማስተማር ዘዴ፡- የዕለቱን ተግባር ማስተዋወቅ፣ ማሳየት፣ ማስረዳት...
- የመምህር ተግባር/ሚና፡- ህጻናቱ የፊደል አፃፃፍን የሚለማመዱበት ሰአት በመሆኑ ለተግባራቱ የሚሆን ቁሳቁሶች ያዘጋጁ፡፡ በመቀጠል ፊደል “ ተ፣ቸ፣ቀ” ን በወረቀት ላይ በነጠብጣብ ይፃፉና ይስጧቸው፡፡ ህጻናቱ ነጠብጣቦቹን አገናኝተው ቀለም እንዲቀቡ ያግዟቸው፡፡ ሲጨርሱ ስለፃፉት ፊደል ብዛት እና ስለቀቡት ቀለም አይነት ለክፍል ጓደኞቻቸው ተራ በተራ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- የመማሪያኛ የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- በወረቀት /በካርድ በነጠብጣብ የተዘጋጀ የፊደል “‘ተ፣ቸ፣ ቀ ” ቅርፅ፣ እርሳስ፣ የተለያዩ ቀለማት
- የምዘና ስልት፡- ምልከታ (ለምሳሌ፡- በአግባቡ እየሰሩ መሆኑን መመልክት...)የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ምን ምን ፊደላትን ተዋወቃችሁ ? የጻፋችሁት ፊደላት ብዛት ስንት ናቸው)

# አሥራ ሶስተኛ ሳምንት

**የተሰጠዉ ሰዓት- 10** **ክፍለ ጊዜ (30)**

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

- ልብስ መልበስኛ ጫማ ማሰር የመሳሰሉትን ክህሎቶች ያዳብራሉ
- የቤት ቁሳቁስን ይለያሉ
- የትራንስፖርት አይነቶችን በስም ይለያሉ
- ማጨብጨብና በእግር ጣት በመቆም ይችላሉ ያሳያሉ
- መፅሐፍን በትክክል ይገልጣሉ
- 8 ቁጥርን በነጠብጣብ ያገናኛሉ፣ ቀለም ይቀባሉ
- ፊደላትን በነጠብጣብ በማገናኘት ቀለም ያቀልማሉ
- ቁሶችን በመጠናቸው ያወዳድራሉ ከ 1 እስከ 3 ቁጥሮችን በቀደም ተከተል ያስቀምጣሉ
- መፅሀፍ በትክክል ይይዛሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ራስን መቻል
- ቃላት
- እንስሳት
- ትንንሽ ጡንቻዎች
- ቁጥር ማወዳደርና መደርደር
- ባህላዊ ቅርሶች
- ቁጥር መፃፍ
- ፊደላትን መፃፍ
- የጽሁፍ ግንዛቤ

## ተግባር 1፦ የግል ተግባር (11 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ፊደላት (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፦** ቃላት፣ ነጠብጣብ፣ ፊደላትን ማያያዝ
- **የማስተማርያ ዘዴ፦** በተግባር
- **የመምህር ሚና፦** መምህር! ህጻናቱ በትምህርት ቤት መማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ያሉ የትም/ት ቁሳቁስ ምን ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ያድርጓቸው ( ለምሳሌ፦ ፍላሽ ካርዶች፣ የተለያዩ የመጫዎቻ ቁሶች.... ):: ህጻናቱ በመለማመጃ ደብተራቸዉ ላይ ያሉትን ፊደላት እንዲገጣጥሙ ያድርጉ፣ በፍለሽ ካርድ (በአሸዋ የተሰሩ) “ገ፣ ፐ እና ነ” ፊደላትን አዘጋጅተው የፊደሉን ድምፅና ቅርፅ እንዲለዩ፣ በነጠብጣብ የተጻፉ ገ፣ ፐ እና ነ ፊደላትን እንዲያያይዙ

ያድርጉ፡፡ በፊደላቱ ቀላል ቃላት በስእል አስደጋፊው እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው( ገ....ገበሬ፣ ገመድ፣ ፐ......ፐዝል ፣ ነ... ነብር) ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** እርሳስ፣ በአሸዋ የተሰራ ፊደል፣ ፍለሽ ካርድ፣ የፊደል ገበታ
- **የምዘና ስልት፡- ምልክታ (ለምሳሌ፡-** ደብተራቸውን በአግባቡ መግለፃቸውን በማየት፣ ሲጽፉ እና ሲቀቡ በማየት እርማትና እገዛ ማድረግ) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የመሰረታችሁትን ቃላት ተናገሩ፣ በካርዱ ላይ ያሉትን ፊደሎች ዘርዝሩ...)

## ለ. ቁሶችን መደርደር (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የቤት ቁሳቁስ፣ መጠን፣ መቁጠር፣መደርደር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የዕለቱን ተግባራት ለመተግበር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች የቤት ቁሳቁስ (ዝርግ/ጎድጓዳ ሳህን፣ ኩባያ፣ ሹካ፣ ማንኪያ፣ ጭልፋ...) በማዘጋጀት ለማወዳደር እንዲመች በመጠን የተለያዩ መሆን እና ከየቁሱ ቢያንስ ከሁለት በላይ የሚደጋገሙ ቁሶችን ማዘጋጀት ይጠበቃል፡፡ ቁሶቹ የተለያየ ቀለም እና መጠን፣ ያላቸዉ መሆን አለባቸው፡፡

1. ህጻናቱ በቅድሚያ በመጠን እንዲደረድሩ ያድርጉ፡፡ የሰሩትን እያዩ እርማት ይስጡ፡፡ ቀጥሎ የተደረደሩትን ቁሳቁስ በማየት ስሙን፣ ትልቁ፣ ትንሹ፣ መካከለኛው የቱ ነው፣ ስንት ደረደራችሁ... በማለት እያንዳንዱን ይጠይቁ፡፡
2. ሁሉም ህጻናት የያዙትን የቤት ቁሳቁስ ስም፣ ልዩነታቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲነግሩ ያድርጉ፡፡ እስከ ስምንት ድረስ ቀላቅለው እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ሥዕል፣ ነጠላ ረድፍ የሚያሳይ ሥዕል ፖስተር
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- በመጠን ሲደረድሩ በማየት እገዛ ለሚያስፈልገው እገዛ ማድረግ ማስተካከል) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ምን ምን የቤት ቁሳቁስ ነበሩ?፣ ትልቁን ኩባያ አሳዩኝ?፣ ትንሹን... ስምንት የቤት ቁሳቁስ ቁጠሩ?...)

## ሐ. ተግባራትን ማከናወን (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሸሚዝ መቆለፍ፣ዚፕ መዝጋት፣ ጫማ ማሰር
- **የመስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በዚህ ክፍለ ጊዜ ህፃናቱ እራሳቸውን ችለው ድርጊቶችን እንዲያከናውኑ የተለያዩ የአልባሳት ሞዴሎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ ባለ ቁልፍ ሸሚዝ፣ ባለ ማሰሪያ ጫማ፣ ዚፕ) እርሶ እንዴት እንደሚዘጉና እንደሚከፈቱ፣ እንዲሁም ጫማ እንዴት እንደሚታሰር ፊት ለፊት በመሆን ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ያሳዩዋቸው፡፡
    1. በየጠረጴዛቸው ላይ የሚለማመዱበትን የተለያየ ሞዴል ያስቀምጡ፡፡ ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ እየተቀያየሩ ይለማመዱ፡፡
    2. ሶስት ሶስት ህፃናትን በማስወጣት ያወዳድሩ፡፡
    3. ይህንን ተግባር እቤት ውስጥ በቤተሰባቸው እገዛ ጠዋት ጠዋት ዩኒፎርማቸውን መልበስ ተለማምደው እንዲመጡ በማድረግ ራስን የመቻል ክህሎት እንዲያጎለብቱ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የልብስ ሞዴሎች ተግባሩትን ሲከናወኑ የሚያሳይ ፊልም / ፎቶ ፣ስእል

- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ማሰር፣/መቆለፍ/ /መዝጋት መክፈት ሲተገብሩ ማየት፣ የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ስንት ቁልፍ ቆለፍክ/ሽ፣ ስንት ቁልፍ ከፈትክ/ሽ

### መ. ሥዕል ማንበብ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የእንስሳት ስም፣መቁጠር፣ጥቅም፣የእንስሳት መኖርያ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! ለተግባሩ አስፈላጊ የሆኑትን የተለያዩ የቤት እንስሳት ሞዴሎች / ስዕሎች አዘጋጅተው በየጠረጴዛቸው ላይ ያስቀምጡ፡፡ ህፃናቱ ስዕሎቹን በየግላቸው በደንብ ከተመለከቱ በኋላ ተራ በተራ እንዲገልፁ ያድርጓቸው፡፡ የእንስሳቱን ስም የት እንደሚኖሩ ምን እንደሚጠቅሙን ብዛታቸውን ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የእንስሳት ሥዕል /ሞዴል/፣ ስለ እንስሳት የሚያሳዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቅ (ለምሳሌ፡- የአንድ እንስሳት ሥዕል በማሳየት ስም መጠየቅ) እና ምልከታ (ለምሳሌ፡- ሲናገሩ ተገቢ ቃላት መጠቀማቸውን መከታተል)

## ተግባር 2፡- በስራ መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. በራስ ማቀድ መለማመድ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ማቀድ፣ጥንቃቄ፣ ማጽዳት፣ መናገር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በስራ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በዚህ ክፍለ ጊዜ ህፃናቱ ተግባራትን በራሳቸው አቅደው የሚሰሩበት ነው፡፡ ህፃናቱ አጠገባቸው ባለው ነገር ተጠቅመው ምን መስራት እንደሚፈልጉ የሚያስቡበት ጥቂት ደቂቃዎች ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል
  1. ሁሉም ህፃናት ላቀዱት ተግባር የሚሆናቸውን ነገሮች እንዲያዘጋጁ ጊዜ ይወስኑላቸው፡፡
  2. የተሰጠው ጊዜ ሲያበቃ ሁሉም እንዲያቆሙና ከመጀመሪያው ጀምሮ ያቀዱትን፣ የሰሩትን፣ የደረሱበትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ይንገሩ፡፡
  3. ሲጨርሱ የተጠቀሙበትን ቁሳቁስ በየቦታው ይመልሱ፡፡ ከዚያም በቡድን በመከፋፈል ክፍላቸውን በጋራ እንዲያፀዱ ያድርጉ፡፡
  4. ሲያጸዱ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የጥንቃቄ መንገዶችን ይንገሯቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ህፃናቱ ላቀዱት ተግባር የሚያስፈልግ ማንኛውም ጉዳት የማያስከትሉ ነገሮች፡፡
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ምን ሰራህ/ሽ/?፣ ምን አቀድሽ/ህ ነበር?፣ እንዴት ሰራህ /ሽ/?...)

## ተግባር 3፡- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የሀፊዝ ቤተሰቦች (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መጓጓዣ፣ ጎረቤት፣ሰፈር፣ታሪክ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት

- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ተረቱን በጥሞና እንዲያዳምጡ እና መልሰው እንዲናገሩ ያግዟቸው፡፡

## ተረት ተረት!

ከዕለታት አንድ ቀን የሀፉዝ ቤተሰቦች የድሮ ሰፈራቸው የነበሩትን ጎረቤታቸውን ለመጠየቅ አውቶቢስ ተሳፍረው ሄዱ፡፡ ሀፊዝ ብዙ አይነት መኪኖች በማየቱ እናቱን እማዬ እኛ ያለንበት መኪና ትልቅ ነው እዛጋ ያለችው ግን ትንሽ ናት፡፡ ስማቸው ግን ማን ይባላል በማለት ጠየቃቸው፡፡ እኛ ያለንበት አውቶቢስ ያኛው ደግሞ ታክሲ ይባላሉ፡፡ ያች ሁለት ጎማ ያላት ደግሞ ሞተር ሳይክል ትባላለች አሉት፡፡ ብዙ ከተጓዙ በኋላ ጎረቤታቸው መንደር ደርሰው ከአውቶቢሱ ወርደው ወደ ጎረቤታቸው ቤት ገቡ፡፡ ጎረቤታቸውም ሊጠይቋቸው ስለመጡ በጣም ደስ አላቸው፡፡ ስለ ድሮ ታሪካቸው እየተሳሳቁ ሲጫወቱ ዋሉ፡፡ ሃፊዝም ወደ ጓደኛው ሮጦ በመሄድ በመንገድ ላይ ሰላያቸው የመጓጓዣ አይነቶች ነገረው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያዩ የመጓጓዥያ አይነቶች ሞዴል /ሥዕል/፣ እርሳስ፣ ቀለማት፣ ወረቀት
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- እነሃፊዝ በእረፍት ቀናቸው የት ሄዱ?፣ በመንገድ ላይ የያቸው መጓጓዣዎች ምን ምን ነበሩ)

### ለ. ሞካሪዋ ዘሪቱ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍቃላት፡-** ሞካሪ፣ መልበስ፣ መመገብ፣ አካላዊ ጥንካሬ፣
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ተረቱን እንዲያዳምጡ እና መልሰው እንዲናገሩ ያግዟቸው፡፡

## ተረት ተረት!

ዘሪቱ የምትባል የአራት አመት ልጅ ነበረች፡፡ ዘሪቱ ሞካሪዋ ልጅ በመባል ትታወቃለች፡፡ ዘሪቱ በትምህርት ቤቷና እና በጎረቤቶቿ የምትወደድ ህጻን ስትሆን ነገሮችን በራሷ ለማከናወን በጣም ትሞክራለች፡፡ በዚህም ሞካሪዋ ልጅ የሚል ቅጽል ስም ጓደኞቿ አዉጥተዉላታል፡፡ ቤተሰቦቿም ሆኑ መምህራኖቿ የሚያሳዩዋትን ተግባር ለምሳሌ፡- ልብስ መልበስ፣ ጫማ ማድረግ እና ማሳር፣ ምግቧን ተጠንቅቃ መመገብ የመሳሰሉትን ተግባራት በራሷ ለመተግበር ትሞክራለች፡፡ ዘሪቱ መምህሯ የሰጠቻትን የቤት ስራ በአግባቡ በመስራት ትታወቃለች፡፡ በዚህ ባህሪዋ መምህሯና ቤተሰቦቿ በጣም ይወዷታል፡፡ በተጨማሪም አካላዊ ጥንካሬ እንዲኖራት ከወንድሟ ጋር ስፖርት ስለምትሰራ በጣም ጠንካራ ልጅ ነች፡፡ ዘሪቱ ጎበዝ በመሆኗ በትምህርት ቤቷ በተደረገው የሩጫ ውድድር አንደኛ ወጥታ ዋንጫ ተሸለመች፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስዕሎች፣ ፎቶ፣ የትምህርት ቤት ሥዕል፣ እርሳስ፣ ከለር
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ዘሪቱ ምን ምን ነገሮችን ትሞክራለች?፣ ምን ማድረግ ትወዳለች ? ዋንጫ የተሸለመችው በምን ዉድድር አሸንፋ ነው)

## ተግባር 4፡- የክፍል ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ማወዳደር (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ መጠን፣ መደርደር፣ ማዛመድ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! የተለያዩ መጠን ያላቸውን ሶስት ዱላዎች  እና ከ1 እስከ 3 ቁጥር የተጻፋበቻው ካርዶች በየጠረጴዛቸው (ከፊት ለፊታቸው) ያስቀምጡላቸው፡፡ ዱላዎቹን በቁመት መደርደር፡፡ ቀጥሎ ቁጥሮቹን በቅደም ተከተል ይደርድሩ፡፡ ከዚያ ትልቅ እና ትንሽን ይለዩ፡፡ ትንሹን ዱላ ከትንሹ ቁጥር (1)፣ ትልቁን ዱላ ከትልቁ ቁጥር (3)፣ መካከለኛውን ዱላ ከመካከለኛው  ቁጥር (2) ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ባለቀለም ዱላዎች፣ ቁጥሮች
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- በየጠረጴዛቸው እየተዘዋወሩ እንዴት እየሰሩ እንዳለ መመልከት፣ እርስ በእርስ እየተደማመጡና እየተግባቡ መስራታቸውን ማጤን እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ከአንድ እና ከሁለት ትንሹ የቱ ቁጥር ነው፣ ሁለት ዱላዎችን በማሳየት ረጅሙ የቱ ነው...)

## ተግባር 5- መዝሙር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ባህላዊ ቅርሶች (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቅርሶች፣ የቤት እቃ፣ጎረቤት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ቀጥሎ ያለውን መዝሙር ህጻናቱ በቡድንና በግል እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡

**ባህላዊ ቅርሶች**

ውቢቷ ሀገሬ እኔ የምወድሽ፣

የሚወራላቸው ብዙ ቅርሶች አሉሽ፡፡

የአክሱም ሃውልት የሶፍ ዑመር ዋሻ፣

ጢያ ትክል ድንጋይ ቱሪስት መዳረሻ፡፡

የቤት እቃዎቹ ከሸክላ የሚሰሩ፣

የሰፌድ መሶቡ በጣም የሚያምሩ፡፡

የዶሮ ወጣችን ይሰራ በሸክላ፣

በመሶብወርቃችን ማዕዱ ይበላ፡፡

ይፈላ ቡናው ይሰብሰብ ጎረቤት፣

ወጉን እያወጉ አብሮ ለመደሰት።

እናጨብጭብ በእጃችን፣

እንቁም በእግራችን።

ምርቃቱ ይሰጥ ከአባቶቻችን፣

እናክብር እንጠብቅ የባህል ቅርሳችን። (2 )

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** መቅረፀ ድምፅ፣ ሰፌድ፣ ሸክላ ድስት፣ መሶብና መሶብ ወርቅ የተሳሉ ስዕሎች
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ሲዘምሩ በመመልከት) እና የቃል ጥያቄ (በመዝሙሩ ውስጥ ምን የቤት ቁሳቁስ አለ?፣ ቡና ሲፈላ እነማን ይጠራሉ?...)

## ተግባር 6፡- የውጭ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. መጓጓዣ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መጓጓዣ፣ የእንስሳት፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱን ወደ ውጭ ይዘው በመውጣት ስለሚጫወቱት ጨዋታ ገለፃ ያድርጉላቸው። እንዲሁም የጨዋታውን ህግ በተገቢ ይንገሯቸው። ለጫዋታው የሚሆን የመጓጓዣ ዐይነቶች ሥዕል/ሞዴል (ባስ፣ ሚኒባስ ታክሲ፣ ባጃጅ፣ ሞተር ሳይክል፣ የጭነት መኪና፣ የቤት መኪና፣ ሳይክል) እና ከ 1 --- 8 ቁጥር በፍላሽ ካርድ ይዘጋጁ።

1. አምስት አባላት ያሉት ቡድን ይመስርቱ። የመጓጓዣ አይነቶችን እና አንዳንድ ቁጥር ይስጡዋቸው። እንዲሁም አንድ የቤት እንስሳት በራሳቸው ምርጫ ይምረጡ (እያንዳንዱ ቡድን አንድ መኪና ሥዕል፣ በፍላሽ ካርድ ቁጥር እና የመረጡት አንድ እንስሳ ስም፡- ላም፣ ዶሮ ፣ድመት፣ ውሻ፣ በግ፣ አህያ፣ ፈረስ፣ ፍየል)
2. ከየቡድኑ አንድ ሾፌር ይመረጡ። ሾፌሩ የመኪናውን ሥዕል ይይዛል። ከኋላ የሚሰለፉት ቁጥር ይይዛሉ። ሌሎቹ ልክ መኪና ላይ እንደተጫነ እንስሳ በመያያዝ የሾፌራቸውንና እርስ በርስ ልብሳቸውን ይይዛሉ።
3. ካሉበት ቦታ 7 ሜትር መዳረሻ ምልክት ያስቀምጡ። ሁሉም ቡድን ከጀመረበት ተነስቶ የሚጨርስበት ይሆናል።
4. አንድ ሲባል አንድ ቁጥር የያዙት በሾፌራቸው አማካኝነት የመኪናውን ሥዕል እንደመሪ በመጠቀም እና የደረሳቸውን የእንስሳ ድምፅ እያሰሙ (ድመት ከሆነ መዳረሻቸው ጋር እስኪደርሱ ሚያው...ሚያው ይላሉ)። መኪናቸውን እየነዱ ይሄዱና መዳረሻቸው ጋር ሲደርሱ አጨብጭበው የመኪናቸውን ሥዕል እና ቁጥራቸውን ከፍ አድርገው በነበረው ሰልፋቸው ይቆማሉ። በዚህ መሰረት ሁሉም ቡድኖች ይሰራሉ።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመጓጓዣ ሥዕል፣ የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣የቀረጸ የእንስሳት ድምፅ
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ተግባራቱን ሲሰሩ በማየት፣ የተባለውን ህግ እየተከተሉ መሆናቸውን፣ በመተባበር እና በመደማመጥ መስራታቸውን) እና፣ የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ሚኒባስ የነዱት ስንት ቁጥር ይዘው ነበር?፣ እንደፈረስ የጮሁት መኪናቸው ማን ይባላል?፣ ስንት ቁጥር ነው የያዙት?....)

# አስራ አራተኛ ሳምንት

የተሰጠው ሰዓት- 10 ሰዓት (30 ክፍለ ጊዜ)

## የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- ለመምህራኖቻቸው ስሜታቸውን ይገልጻሉ
- የትህትና አገላለጾችን ያሳያሉ
- የጅኦሜትሪ ምስሎችን መገጣጠም (ክብ፣ ሶስት ጎን፣ አራት ጎን ሁለት ጎን) ያሳያሉ
- 9 ቁጥርን በመገጣጠም፣ ይቀባሉ
- ፊደላትን በመገጣጠም ቀለም ይቀባሉ
- ብሔራዊ ምልክቶችን እና መገለጫዎች ስሞችን ይጠራሉ
- ቢያንስ ከ3-5 አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ያሳያሉ
- በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ያሉ የእጽዋት ዓይነቶችን ይለያሉ
- ቁሶችን ድግግሞሽ በመጠበቅ ይደረድራሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ማህበራዊ ግንዛቤ
- ተክሎች
- ትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር
- መደርደር (Patteren)
- ቅርጽ
- ቁጥሮችን መጻፍ
- ፊደላትን መጻፍ
- የጥበብ ዋጋ
- የሀገር ፍቅር

## ተግባር 1፡- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. መልካሟ ልጅ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ጂኦሜትሪ ቅርፅ፣ ትሁት፣ መጫወት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ቀጥሎ የቀረበውን ተረት ልክ እንደ ከዚህ ቀደሙ ህፃናቶቹን በማሳተፍ ያቅርቡ

### ተረት ተረት!

ሀሊማ የደረጃ አንድ ተማሪ ናት፡፡ ሀሊማ በቤተሰቦቿ እና በጎረቤቶቿ የምትወደድ ትሁትና ተወዳጅ

ልጅ ናት፡፡ ትምህርት ቤት ውስጥም የተሰማትን ለመምህራኖቿ ታስረዳለች፡፡ ለቤተሰቧቿ 3ኛ ልጅ ናት፡፡ በክፍል ውስጥ ስለማትረብሽና ተሳታፊ ስለሆነች ተወዳጅ ናት፡፡ ሀሊማ ገመድ መዝለል፣ ሚዛን መጫወት እና ሩጫ መወዳደር ትወዳለች፡፡ በተጨማሪም የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጽ መስራት ደስ ይላታል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ስእል፣ የጂኦሜትሪ ቅርፆች፣ ፒዝል
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- ሀሊማ ምን አይነት ባህሪ ያላት ልጅ ናት፣ ሃሊማ የተሰማትን ስሜት ለማን ትነግራለች፣ ሀሊማ ምን ትወዳለች)

### ለ. ያሬድ (3 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት:-** ባንዲራ፣ እነቅስቃሴ፣ ታዋቂ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተረት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! የቀረበላቸውን ተረት በጥሞና እንዲያዳምጡ በማድረግ ያዳመጡት ተረት ፍሬ ሓሳቦች መልሰው እንዲናገሩ ያግዟቸው፡፡

## ተረት ተረት

ያሬድ የደረጃ 1 ተማሪ ነው፡፡ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት ከታላቅ ወንድሙ ጋር ቀላል አካላዊ እንቅስቃሴዎችያደርጋል፡፡ ከዚያም ትምህርት ቤት በመሄድ የባንዲራ ስነ ሥርዓት ላይ ይሳተፋል፡፡ ሃገሩን በጣም እንደሚወድና ወደፊት ሯጭ በመሆን እንደታዋቂው ሻለቃ ኃይሌ ገ/ስላሴ የሃገሩን ባንዲራ ማውለብለብ እንደሚፈልግ ለመምህራን ስለነገረ ያበረታቱታል፡፡ ቤተሰቡንና መምህራንን ለማስደሰት ሁልጊዜ ያጠናል፡፡ የቤት ስራውን በሰአቱ ይሰራል፡፡ በጨዋታ ሰአቱ ከወንድሙ ጋር ይጫወታል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ሥዕል፣ ባንዲራ፣ ገመድ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- ያሬድ ምን አይነት እንቅስቃሴ ያደርጋል፣ ያሬድ እንደ ማን መሆን ይፈልጋል...)

## ተግባር 2:- የክፍል ውስጥ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. እንቆቅልሽ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** አትክልት፣ የጂኦሜትሪ ቅርፅ፣ ቁጥር፣ ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** እንቆቅልሽ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! የእንቆቅልሽ መጠይቆችን ህጻናቱን ይጠይቁ፡፡

## እንቆቅልሽ

1. የጂኦሜትሪ ቅርፅ ነኝ ከሶስት ቀጥታ መስመሮች እሰራለሁ እኔ ማነኝ ---- ሶስት ጎን
2. ከአትክልት ውስጥ እመደባለሁ፡፡ ሲበሉኝ ምላስን ቀይ አደርጋለሁ፡፡ ተቀቅዬና ተጠብሼ እበላለሁ፡፡ እኔ ማን ነኝ ---- ቀይ ስር

3. ከጂኦሜትር ቅርጽ ውስጥ አንዱ ነኝ፡፡ ብርትኳን እመስላለሁ፡፡ ኳስም ትመስያለሽ ይሉኛል፡፡ እኔ ማን ነኝ--- ክብ

4. ቁጥር ነኝ የምገኘው ከስምንት ቀጥሎ ነው እራሴ ላይ ቀለበት አለኝ እኔ ማነኝ ---9 ቁጥር

- የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጽ፣ቀይ ስር፣ብርትኳን፣ኳስ
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- የብርቱካን ቅርጽ ምን አይነት ነው፣የቀይ ስር ቀለም ምን አይነት ነው

## ተግባር 3፡- መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. መምህሮቼ (4 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- እውቀት፣ ፊደል፣ ቁጥር፣ ስሜት፣ ተክሎች
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በመዝሙር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ከህጻናቱ ጋር በመዘመር ያለማምዷቸው፡፡

መምህራኖቼ

መምህራኖቼ የእውቀት ወላጆቼ፣

በአካል በስሜት እዳድግ በርትቼ፣

ትሁት ልጅ እንድሆን መንገድ መሪዎቼ፡፡

ፊደሎች እንድለይ ቁጥር እንድቆጥር፣

ያመላከቱኛል ቁሶች ስደረድር፡፡

ስለጤንነቴም የሚጨነቁልኝ፣

የተክሎችን አይነት የሚያመላክቱኝ፡፡

ሁሌም የሚያግዙኝ የደስታዬ ምንጮች፣

እውቀት የሚሰጡኝ በብዙ አማራጮች፡፡

የትኛውን ብዬ የቱን ልበላችሁ፣

በጣም የምንወዳችሁ፣

የብዙ ህጻናት ወላጆች ናችሁ፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- መቅረጸ ድምጽ፣ የተለያዩ ከብቃቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስዕሎች
- የምዘና ስልት፡- ምልከታ (ለምሳሌ፡- በቡድንና በግል ሲዘምሩ መከታተል) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- መምህራኖች ምን ያደርጉላቸኋል)

ለ. ሃገሬ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሃገር፣ ቀለም፣ ተክሎች፣ ባንዲራ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ከህጻናቱ ጋር በመዘመር ያለማምዷቸው፡፡

ሀገሬ

ሀገሬ ነሽ ክብሬ፣

ሳዛሬ መኖሬ፡፡

ሰላምን እሻለሁ፣

ጸብን እጠላለሁ፡፡

ትምህርቴን ተምሬ ሃገር አስጠራለሁ፣

ተክሎችን በመትከል አስውብሻለሁ፡፡

ባንዲራሽ ቀለሙ በጣም ደስ ይለኛል፣

አረንጓዴ ቢጫ ቀይም ይታየኛል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** መቅረጸ ድምጽ፣ የተለያዩ ከብቃቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሥዕሎች
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ ማድ (ለምሳሌ፡- በቡድንና በግል ሲዘምሩ መከታተል) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የኢትዮጵያ ባንዲራ ቀለም ምን አይነት ነው ...)

## ተግባር 4፡- የውጪ ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ)

ሀ. የቁጥር ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ )


- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ እንቅስቃሴ፤ተቆጣሪ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በቅድሚያ ቀላል አካላዊ እንዲያከናውኑ ያድርጉ (ቁጭ ብድግ፣ መዝለል፣ መተጣጠፍ፣ ኳስ ቅብብል...) ይህ ሁኔታ ቀጣዩን ጨዋታ በቅልጥፍና እንዲሰሩ ያግዛቸዋል፡፡ ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት ህጻናቱ ከሚቀመጡበት ፊት ለፊት በጠረጴዛ ላይ 1-9 የቁጥር ፍላሽ ካርድ ማስቀመጥ

  1 ቁጥር በፍላሽ ካርድ 1 ህጻን ይይዛል

  2 ቁጥር በፍላሽ ካርድ 2 ህጻናት ይይዛሉ

  3 ቁጥር በፍላሽ ካርድ 3 ህጻናት ይይዛሉ በዚሁ አይነት እስከ 9 ይቀጥላል

ለምሳሌ፡-




## የጨዋታው ቅደም ተከተል

1. የመጫዋቻ ቦታውን ምቹ ማድረግ ህጻናቱን በቡድን መክፈል
2. ተቆጣሪ ቁሶችን  በማዘጋጀት
3. በቡድን የተከፈሉትን ህጻናት እያንዳንዳቸው እጣ እንዲያነሱ ማድረግ
4. ያነሱትን ቁጥር ለማንም ሳይሳዩና ሳይነግሩ ከቡድናቸው ይቀላቀሉ
5. በቡዱኑ ውስጥ ያሉት ህጻናት የያዙትን እጣ በማየት ከፍ ባለ ድምጽ የያዙትን ቁጥር መጥራት
6. አንድ አይነት የቁጥር ድምጽ የያዙ ህጻናት በአንድ ቦታ ይሰበሰባሉ፡፡ በያዙት ቁጥር ልክ ከተዘጋጁት ቁሶች ቆጥረው ይወስዳሉ
7. ህጻናቱ የያዙትን ቁጥር ያስተያያሉ ከነሱ ጋር የማይመሳሰለውን ያስወጣሉ

ለምሳሌ፡- 3 ቁጥር የያዙ 3 ህጻናት መሆናቸውን መምህሩ ማረጋገጥ ይኖርበታል

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- 1-9 ያሉ ቁጥር ፍላሽ ካርድ/ በአሻዋ የተሰራ 1-9 ቁጥር/፣ ወረቀትና እርሳስ፣ከለር የሚቆጠሩ ቁሶች
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የእለቱ ጫዋታ ምን በር፣ ሶስት ቁጥር የያዙት ስንት ህጻናት ናቸው)

### ለ. ቁሶችን መደርደር (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ቀለማት፣ ቁሶች፣ መደርደር፣ እንቅስቃሴ፣ መቁጠር፣ ዕጸዋት
- የማስተማርያ ዘዴ፡-  በጨዋታ
- የመምህሩ ሚና፡- መምህር! ህጻናቱን ወደ ውጪ ይዘው በመውጣት በቡድን ሆነው እንዲደራጁ ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠል ለጨዋታው የሚያስፈልጉ የተለያዩ ቀለም ያላቸው ዘጠኝ ዘጠኝ ባለቀለም ኳሶች ( አረንጓዴ ዘጠኝ፣ቢጫ ዘጠኝ) ቀጥሎ በጊቢያቸው ባለው የመጫወቻ ስፍራ በአምስት ሜትር ርቀት በነጠላ ወደ ጎን እንዲደረድሩ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎ በተደረደሩት በለቀለም ኳሶች ተርታ ዘጠኝ ህጻናት  በሁለት ቡድን ይሰለፋሉ፡፡
  1. ጨዋታው ፍጥነት ባለው እንቅስቃሴ /ሩጫ/ ከአረንጓዴው ያለውን ወደ ቢጫው ከቢጫው ያለውን ደግሞ ወደ አረንጓዴው መውሰድ እና መደርደር ነው፡፡ ከሁለቱ ቡድን አንዳንድ ህፃናት  ያመጡትን ኳሶች እየቆጠሩ በመደርደር ይወዳደራሉ፡፡ ቀድሞ በትክክል ደርድሮ የጨረሰው አሸናፊ ይሆናል፡፡
  2. ሲጨርሱ ለትንሽ ደቂቃ በግቢያቸው ውስጥ ያሉትን እፅዋቶች  እንዲያዩ እድል ይስጡ ስማቸውንም ይንገሯቸው፡፡
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- በለቀለም ቁሶች፣ የተለያዩ እጽዋቶች
- የምዘና ስልት፡-  ምልከታ  (ለምሳሌ፡- ጨዋታው ሲጫወቱ በመመልከት) እና የቃል ጥያቄ

(ለምሳሌ፡- ጨዋታው ምን ነበር፣ ማን አሸነፈ፣ ስንት ኳሶች ደረደራችሁ ያያቹት እፅዋቶች ስማቸው ማነው ...)

## ተግባር 5፡- የክፍል ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የባህል መገለጫ (2 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የባህል ልብስ፣ ባህላዊ ዘፈን፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! አንድ ቀን ቀደም ብለው ህፃናቱ በየቤታቸው ያላቸውን የባህል ልብሶች ይዘው እንዲመጡ ያድርጉ፡፡ ያመጡትን አልባሳት የወንድና የሴት ለየብቻ ይክፈሉ፡፡ ስንት አልባሳት እንደሆነ ይቁጠሩ፡፡ በመቀጠል ህጻናቱ ስለሀገራቸው ባህል መገለጫዎች ስለሚያውቁት ነገር ይጠይቋቸው፡፡ ከዚያም ህፃናቱን በየተራ ከወንድና ከሴት በመጋበዝ አልባሳቱን ለበሰው ትህትና በተሞላበት መንገድ ስለ ልብሳቸው እንዲግልፁ እና ከለበሱት ልብስ ጋር የሚሄድ የሀገር ባህል ጨዋታ በመክፈት ህፃናቱ እንዲወዛወዙ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ባህላዊ አልባሳት፣ ባህላዊ ሙዚቃ፣ ሌሎች ከተግባሩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቪዲዮ/ምስል/፣
- **የምዘና ስልት፡-** የሚያውቁትን ባህላዊ ጭፈራ እንዲጨፍሩ መጠየቅ

### ለ. ቅርጽን መለየት (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የጂኦሜትሪ ቅርጽ፣ ትህትና፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! መጀመሪያ የጂኦሜትሪ ቅርጾችን ስም እንዲያስታውሱ ህፃናቱን ይጠይቁ፡፡ በመቀጠል ወረቀትና እርስሳስ በመስጠት ቅርፆቹን እያስደገፉ እንዲስሉና ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡ መምህር ለሁሉም ህፃናት የተለያየ የጂኦሜትሪ ቅርጽ እና የተለያያ ከለር ይስጡና የሚፈልጉትን እርስ በርስ እንዲዋዋሱ ያድርጉ፡፡ በሚዋዋሱበት ጊዜ መጠቀም ስለሚገባቸው ትህትና የተሞላባቸው የአክብሮት ቃላትን እንዲጠቀሙ ያድርጉ (እባክህ /እባክሽ/፣ይቅርታ ክብ ቅርጽን መውሰድ እችላለሁ...... ፣አመሰግናለሁ...) የመሳሰሉት መጠቀማቸውን በደንብ ያረጋግጡ በመጨረሻም ምን ያህል እንደሰሩ ቆጥረው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- **የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የጂኦሜትር ቅረጻ ቅርጽ፣ ሥዕል፣ ፍለሽ ካርድ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ከለር
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- እንዴት እንደሚሰሩ ምን አይነት የትህትና ቃላትን እንደተጠቀሙ) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የሰራቹት ቅርፅ የምንድነው፣ ምን ተዋሳቹ ስትዋሱ እንዴት ጠየቃቹ...)

## ተግባር 6፡- ውይይት (3 ክፍለ ግዜ)

### ሀ. ብሄራዊ መገለጫ (3 ክፍለ ግዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ትምህርት ቤት፣ ቤተሰብ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በውይይት
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! በዕለቱ ውይይት ሁሉም ህፃናት ተሳታፊ መሆን እንዳለባቸውና የተሰማቸውን እና የሚመስላቸውን ሃሳብ ማቅረብ እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡ ስለ ራሳቸው፣ ስለ ቤተሰባቸው፣ ስለ ትምህርት ቤታቸው፣ ስለ ሰንደቃላማ ቀለም አይነት

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ስለ ማህበራዊ ግንኙነት የሚያሳዩ ቪዲዮ/ምስል/ ባንዲራ፣ የጀግኖች ሰዎች ፎቶ...
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ ስለ ራሳቸው፣ ስለ ትመህርት ቤታቸው እንዲናገሩ መጠየቅ

## ተግባር 7፡- በፕሮጀክት መማር (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ሥርዓተ ንድፍ(Pattern)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሥርዓተ ንድፍ /ፓተርን /፣ ቀለም፣ ቅርጽ
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በፕሮጀክት
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! ይህ ፕሮጀክት ህጻናቱ ወረቀት መለጠፍ የተለያዩ ከለር ያላቸውን ወረቀቶች ቆራርጦ በተለያየ ቅርጽ በመለጠፍ እና በመደርደር ሥረዓተ ንድፍ (Pattern) የሚሰሩበት ነው፡፡ (ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጄ፣ ጥቁር) ባለቀለም ወረቀቶች እና የፕላስቲክ መቀስ እና ማጣበቂያ እንዲሁም ጠንካራ በክብ /በአራት ጎን የተዘጋጀ ፍሬም ያዘጋጁላቸው፡፡ ህፃናቱ በራሳቸው የፈለጉትን ተከታታይነት ያለው ሥርዓተ ንድፍ በማዘጋጀት በተሰጣቸው ፍሬም ላይ እንዲለጥፉ ያግዟቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** መቀስ፣ ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ እና ጥቁር ወረቀቶች ፣ማጣበቂያ ከጠንካራ ካርቶን የተዘጋጀ ፍሬም
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ምሳሌ፡- በስንት አይነት ቀለማት ሰራቻሁ፣ ስንት ቅርጾች ሰራቻሁ)

## ተግባር 8 በስራ መማር (2 ክፍለ ግዜ)

### ሀ. ፊደላትን ማስተዋወቅና በነጠብጣብ ማያያዝ (2 ክፍለ ግዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቃላት፣ መገጣጠም፣ፊደል
- **የአተገባበር ዘዴ፡-** በስራ
- **የመምህር ሚና፡-** ውድ መምህር! ህጻናቱ በትምህርት ቤት መማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ያሉ የትምህ/ት ቁሳቁስ ምን ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ያድርጓቸው ( ለምሳሌ፡- ፍላሽ ካርዶች፣ የተለያዩ የመጫዎቻ ቁሶች.... )፡፡ ደብተራቸውን በአግባቡ እንዴት መያዝ እንዳለባቸው ያሳዮቸው፡፡ በፍለሽ ካርድ (በአሸዋ የተሰሩ) "ኘ ፣ ጎ እና የ " ፊደላትን አዘጋጅተው የፊደላቱን ድምፅና ቅርፅ እንዲለዩ ያድርጉ፣ በመቀጠል መለማመጃ ደብተራቸዉ ላይ በነጠብጣብ የተጻፉ "ኘ ፣ ጎ እና የ " ፊደላትን እንዲያያይዙ ያድርጉ፣
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** እርሳስ፣ በአሸዋ የተሰራ ፊደል፣ ፍለሽ ካርድ፣ የፊደል ገበታ
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ደብተራቸውን በአግባቡ መግለፃቸውን በማየት፣ ሲጽፉ እና ሲቀቡ በማየት እርማትና እገዛ ማድረግ) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የፃፉችሁት ፊደል ማን ትባላለች፣ ስንት ፊደል ፃፋችሁ .....)

# አስራ አምስተኛ ሳምንት

## የተሰጠው ሰዓት- 10 ሰዓት (30 ክፍለ ጊዜ)

**የሚጠበቁ የመማር ብቃት**

- አካባቢያቸውን ይንከባከባሉ
- የማመሪያ ክፍሎቻቸውን ያጸዳሉ
- የፊደሎችን ድምጽ ይለያሉ
- የፊደሎችን እንደገና ይጽፋሉ
- በአከባቢያቸው ስለሚያዉቋቸው ነፍሳት ይናገራሉ
- ሰው ሠራሽ ቁሶችን ይለያሉ
- በአንድ ቦታ ሆነው ተግባራትን ያከናውናሉ (ለመሳሌ፤- እንደ ሌሎችን ሳይገፉ በክፍል ውስጥ በትክክል መቀመጥ)
- ከ1-9 ያሉ ቁጥሮችን ይቆጥራሉ
- በነጠብጣብ የተጻፉ ከ1-9 ያሉ ቁጥሮችን ይገጣጥመሉ
- በቡድን ሚና-ተጫዋች እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይሳተፋሉ
- ቁሳቁስን በጋራ ባህሪያቸው ይመድባሉ
- መራመድ፣ መዝለል፣ መነተት፣የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎችን
- ሙዚቃዊ ምትን ተከትለው ያከናውናሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ራስን እና መኖሪያ አካባቢን መንከባከብ
- የድምፅ ግንዛቤ
- የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አካባቢዎች
- የቦታ ግንዛቤ
- መደርደር እና መመደብ
- ቁጥሮችን መጻፍ
- ፊደላትን መጻፍ
- ማያያዝ፣
- ግንኙነት

## ተግባር 1፡- የክፍል ጨዋታ (8 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የእንስሳት ድምጽ መለየት (4 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- የእንስሳት ድምፅ፣ የፊደል ድምፅ፣ መፃፍ

- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለዚህ ተግባር የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ የእንስሳት ምስል የፊደል እና የእንስሳ ድምፅ ቅጂ ያዘጋጁ። የእንስሳ ድምፅ እና የፊደል ድምፅ ለህፃናቱ ተራ በተራ ያሰሙ። በመቀጠል ሁለት ሁለት ልጆችን በመምረጥ ለአንዳቸው የእንስሳ፣ ለአንዳቸው ደግሞ የፊደል ድምፅ በቀስታ ያሰሙ። የትኛውን ፊደልና እንስሳ ድምፅ እንደሰሙ ከፍላሽ ካርዱ በማንሳት ለክፍሉ ህፃናት ያሳዩ። በዚህ መሰረት ሁሉም ህፃናት ድምጹን እየሰሙ ከፍላሽ ካርዱ እየመረጡ ያሳዩ። ድምፁን ደግመው ያሰሙ። በመጨረሻም በመለማማጃ ደብተራቸው ፊደሉን ደግመው እንዲፅፉ ያድርጉ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** መቅረፀ ድምፅ፣ የንስሳት ምስል፣ የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ እርሳስ ደብተር
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ሲናገሩ፣ ፊደልና የእንስሳቱን ምስል ከሰሙት ድምጽ ጋር ማገናኘታቸውን፣ ፊደሉን ደግመው ሲፅፉ ...) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ፍላሽ ካርዱን በማሳየት ይህቺ ፊደል ማነች፣ ይሄ እንስሳ ማነው...)

### ለ. ቁሶችን በባህሪ መመደብ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል፣ ቁጥር፣ ቅርጾች፣ ነፍሳት፣ እንስሳት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱን በቡድን ይክፈሉ። የተለያዩ ቁሶችን ያዘጋጁ። ከእያንዳንዱ አይነት ሶስት ሶስት ነገሮችን የቡድኑ ጠረጴዛ ላይ ያስቀምጡላቸው። ለምሳሌ ከፊደል እና ከቁጥር ፍላሽ ካርድ ሶስት ሶስት፣ ከጂኦሜትሪ ቅርጾች ሶስት፣ ከሰው ሰራሽ የቤት ቁሳቁስ ሶስት፣ ከተለያዩ ነፍሳት እና እንስሳት ሥዕል ፍላሽ ካርዶች ሶስት ያስቀምጡላቸው። ቀጥሎ የሚያደርጉት በየወንበራቸው በስነ ስርአት በአንድ ቦታ ተረጋግተው ሳይገፋፉና ሳይነጣጠቁ የወሰዱትን የተቀላቀሉ ነገሮች በባህሪያቸው መለየት ይሆናል። ለምሳሌ ፍደልን በፊደል፣ ቅርጾችን ከቅርፆች፣ ነፍሳትና እና የቤት እንስሳት፣ ጠረጴዛ ላይ መመደብ። ሁሉም ሲጨርሱ እዚያው ባሉበት የቡድኑ አባላት የሰሩት /የለዩትን ስንት አይነት ቁሶችን እንደለዩ ቆጥረው ለሌሎች ቡድን ያሳዩ። በትክክል ያልተለየ ካለ ደግሞ ከነሱ መካካል ለሚያስተካክል እድል ይስጡ። ሲጨርሱ እያንዳንዱ ቡድን ተራ በተራ እቃውን በየቦታው ይመልሱ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የፊደል፣ የቁጥር፣ የእንስሳት፣ የነፍሳት እና የቤት ቁሳቁስ (ወንበር፣ ጠረጴዛ) ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ(ምሳሌ፡- ስንት ቦታ መደባችሁ፣ ስንት ፊደላት መደባችሁ፣የፊደላቱን ስም ተናገሩ)

## ተግባር 2፡- የግል ተግባር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. 9 ቁጥርን መለየትና መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መቁጠር፣ መደርደር፣ ዘጠኝ ቁጥር፣ መፃፍ፣ መቀባት፣ ቅደም ተከተል መደርደር በአግባቡ መቀመጥ፣ቀለማትን ከተፈጥሮ እና ሰውሰራሽ ጋር ማዛመድ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ከአንድ እስከ ዘጠኝ ያሉትን ቁጥሮች በየጠረጴዛቸው ላይ

ይስቀምጡላቸው፡፡ ህጻናቱ በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎ የደረደሩትን ቁጥር እየነኩ ይቁጠሩ፡፡ ከዚያም ደብተር /ወረቀት፣ እርሳስ ይስጧቸው እና ቁጥር ዘጠኝን መርጠው ደጋግመው እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡ ሲፅፉ በአግባቡ መስመር ጠብቀው መሆን አለበት፡፡ በመቀጠል በሞዴል የተሰራ ዘጠኝ ቁጥር በመስጠት አስደግፈው ካነሱ በኋላ ከለር ይቀቡ፡፡ ሲጨርሱ የፃፉትን ቁጥር ምን አይነት ከለር እንደቀቡ ይናገሩ፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- እርሳስ፣ ከለር፣ የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣ ደብተር፣ ወረቀት
- የምዘና ስልት፡- ምልከታ (ለምሳሌ፡- በትክክል ቁጥሩን መጻፋቸውን መከታተል ቁጥሩን ከድምጹ ጋር እያዘመዱ መሆኑን ማረጋገጥ)

### ለ. ፊደላትን መፃፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ መፃፍ፣ ማንበብ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! የመምህር ተግባር /ሚና/፡- ውድ መምህር! ህጻናቱ በትምህርት ቤት መማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ያሉ የትም/ት ቁሳቁስ ምን ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ያድርጓቸው ( ለምሳሌ፡- ፍላሽ ካርዶች፣ የተለያዩ የመጫዎቻ ቁሶች.... )፡፡ ደብተራቸውን በአግባቡ እንዴት መያዝ እንዳለባቸው ያሳዮቸው፡፡ በፍለሽ ካርድ (በአሸዋ የተሰሩ) “ሐ ፣ ጠ እና ጨ” ፊደላትን አዘጋጅተው የፊደላቱን ድምፅና ቅርፅ እንዲለዩ ያድርጉ፣ በመቀጠል መለማመጃ ደብተራቸዉ ላይ በነጠብጣብ የተጻፉ “ሐ ፣ ጠ እና ጨ” ፊደላትን እንዲያያይዙ ያድርጉ፣
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- እርሳስ፣ መለማመጃ ደብተር፣ የተቀረፀ ፊደል/ፍላሽ ካርድ/፣ እርሳስ
- የምዘና ስልት፡- ምልከታ (ለምሳሌ፡- አቀማመጣቸውን፣ ጓደኛቸውን ማክበራቸውን፣ በአግባቡ ፊደሏን መፃፋቸው፣ ማንበባቸውን) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የጻፋችሁት ፊደል ማናት፣ የጻፋችሁት ፊደላት ብዛት ስንት ነው? ...)

## ተግባር 3፡- የመስሎ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ጎረቤት (4 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ጎረቤት፣ መዋዋስ፣ ቤተሰብ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በጨዋታ
- የመምህር ሚና፡- መምህር! የድራማውን ታሪክ ለሁሉም ህፃናት ካስጠኑ በኋላ ቡድን በመመስረት ለድራማው የሚሆኑ ሁለት ቤተሰብ ማዕዘናትን ያዘጋጁ፣ ጎረቤት/ ልጆቹን በመጋበዝ እንዲተውኑ ማድረግ፣ መከታተል ማረም፣ መደገፍ

የድራማው ሀሳብ፡- ሁለት ጎረቤታሞች አሉ ሴት እና ወንድ ልጅ አላቸው አንደኛው ቤት የምርቃት ድግስ አለ፣ እቃ ይዋዋሳሉ፣ ልጆቹ በጋራ እየተሯሯጡ ይጫወታሉ፡፡

ቤት 1 እናት፡- ቤት ውስጥ ስራ ሲሰሩ ይታያሉ ከዚያም ወደጎረቤታቸው ቤት እቃ ለመዋስ ይሄዳሉ ቡሩን አንኳኩተው ሰላምታ ይሰጣሉ ‹‹ የአቡሽ እናት እንዴት አደራቹ

ቤት 2 እናት፡- ደህና አደርሽ የሚጣ እናት ነይ ግቢ ስራው እንዴት አረገሽ

ቤት 1 እናት፡- አረ ድክም ብያለሁ ቢሆንም እያለቀ ነው

ቤት 2 እናት፡- አይዞሽ እኔም እኮ አሁን ለልጆቹ ምሳ ሰርቼ መጥቼ ላግዝሽ እየተዘጋጀው ነው

ቤት 1 እናት፡- በጣም አመሰግናለሁ አሁን የመጣሁት ትንሽ እቃ ስለጎደለኝ እንድትሰጪኝ ነው ብረት ድስት 1፣ ፕላስቲክ ኩባያ 4 እና ብርጭቆ ደግሞ 4

ቤት 2 እናት፡- ምንም ችግር የለም እኔ አጥቤ አመጣልሻለሁ

ቤት 1 እናት፡- አመሰግናለሁ ጎረቤቴ በቃ ልሂድና የቀረውን ስራ ልጨርስ በማለት ወደቤታቸው ይሄዳሉ

ቤት 2 እናት፡- እቃውን ከተቀመጠበት ሲያወጡ ነፍሳት ያያሉ ውይ ውይ እነዚህ በረሮዎች እቃውን በከሉት መድሃኒት መግዛት አለብኝ እያሉ በጫማቸው ይገድላሉ ከዚያ እቃውን አጥበው ለጎረቤታቸው ይወስዳሉ

ሚጣና አቡሽ፡-  ውጭ ላይ ቢራ ቢሮ ሳያት እያሉ ነይ ወደእኔ ነይ ወደኔ ነይ እያሉ ይሯሯጣሉ፡፡ ቢራ ቢሮ ስታምር ዥንጉርጉር እያሉ ሮጠው ሲደክማቸው መሬት ሳር ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ትንሽ ቁጭ እናዳሉ እየጮሁ ወይኔ ወይኔ ጉንዳን ጉንዳን ነከሰችኝ እያሉ ሁለቱም እግራቸውን እክክ እያደረጉ እማ ጉንዳን በላኝ ጉንዳን በላኝ በማለት ወደ ቤት ሲሮጡ ያልቃል

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቤተሰብ ማዕዘን፣ የቤት ቁሳቁስ (ወንበር ፣ጠረጴዛ ፣ ብረት ድስት፣ ፕላስቲክ ኩባያ እና ብርጭቆ የነፍሳት ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ድራማውን ሲሰሩ በአግባቡ የሚፈለገውን መልዕክት ማሳተላለፋቸውን በመመልከት) እና የቃል (ለምሳሌ፡- ከድራማው ምን ተማራቹ ፣ ሚጣና አቡሽ ያባረሩት ምን አይነት ነፍሳ ነበረጭ ፣የነከሳቸው ነፍሳት ምን ትባላለች ፣የአቡሽ እናት እቃ ለምን ተዋሱ ፣የተዋሱት እቅ ምን ነበር ፣ስንት የፕላስቲክ ኩባያ ስንት ብርጭቆ ስንት ብረት ድስት ነበር ...)

## ተግባር 4፡- የቤት ውስጥ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. እንቆቅልሽ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ነፍሳት፣ ሰው ሰራሽ ቁሳቁስ፣ የቤት ቁሳቁስ
- **የማስተማርያ  ዘዴ፡-** በእንቆቅልሽ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! እንቆቅልሹን በማዘጋጀት ይጠይቋቸው፡፡  እንዲጠያየቁ ያድርጉ፡፡ እንቆቅልሽ

1. ነፍሳት ነኝ፣ በጣም የሚያምር የተለያዩ ቀለማት ለብሻለሁ፣ በአበቦች ላይ ብር ብር እላለሁ፡፡ እኔ ማነኝ   ---- ቢራቢሮ

2. የቤት ቁሳቁስ ነኝ፣ ሰው ሰራሽ ነኝ፣ ከብረት እሰራለሁ፣ ሰዎች በቤታቸው ወጥ ይሰሩብኛል ፡፡ እኔ ማነኝ   ----የብረት ድስት

3. ሰው ሰራሽ ነኝ፣ ሰዎች እቤታቸውን፣ ጊቢያቸውን፣ የመማሪያ ክፍላቸውን ያፀዱብኛል፡፡ እኔ ማነኝ ------ መጥረጊያ

4. ከእንስሳት እመደባለሁ፡፡ ሚያው ሚያው እላለሁ ፡፡ አራት እግር አለኝ፡፡ ወተት በጣም ነው የምወደው፡፡ እኔ ማነኝ ----- ድመት

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የቤተሰብ ማዕዘን፣ የቤት ቁሳቁስ (ወንበር ፣ጠረጴዛ ፣ብረት ድስት፣ ፕላስቲክ ኩባያ እና ብርጭቆ፣ የነፍሳት ሥዕል
- የምዘና ስልት፡- ጥያቄ መጠየቅ (ምሳሌ፡- ድመት ስንት እግር ኣላት? ቢራቢሮ ምን አይነት ቀለም አላት? የብረት ድስት ለምን ይጠቅማል ?፤ ሰው ሰራሽ ነገሮችን ምን ምን ናቸው?)

## ተግባር 5፡- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

ሀ፣ መምህርት ደጊቱ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- የአካባቢ ፅዳት፣ የቦታ ግንዛቤ፣ ቁጥር
- የማስተማር ዘዴ፡- በተረት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ቀጥሎ የቀረበውን ተረት ህጻናቱን ዝግጁ በማድረግ ያንብቡላቸው፡፡

### ተረት ተርት

መምህርት ደጊቱ የህፃናት መምህርት ስትሆን በትምህርት ቤቱ ህፃናት በጣም የምትወደድ ነች፡፡ ከህፃናቱ ጋር ልክ እንደነሱ በመሆን ትጫወታለች፡፡ አንድ ቀን ከእረፍት ሲመለሱ የትምህርት ቤታቸው ግቢ በጣም ቆሽሾ ዝንቦች ተራብተው እና አበባዎቹም ደራርቀው አዩ በሁኔታው በጣም አዘነች፡፡ ስለዚህ ህጻናቱን በማስተባበር የተለያዩ ለፅዳት የሚያገለግሉ እቃዎችን (መጥረጊያ፣ ማፈሻ፣ መኮትኮቻ፣ የአትክልት መቁረጫ መቀስ) በመያዝ ለማፅዳት ወጡ፡፡ ህፃናቱን በተለያየ ስራዎች ላይ አሰማራች፡፡ አንድ ቡድን ድንጋይ እየለቀመ በአንድ አቅጣጫ በመውሰድ የተለያዩ ቅርፆችን ይሰራሉ፤ ሌላው ቡድን የደረቀውን አትክልት በመቀስ እየቆራረጠ ይኮተኩታሉ፣ ሌላው ቡድን ውሃ ያጠጣል፣ ሌሎች ደግሞ ጊቢውን ይጠርጋሉ፡፡ በጣም የሚገርመው ህፃናቱ ተግባራቱን ሲያከናውኑ ምንም ሳይገፋፉና ሳይጣሉ ነው፡፡ እንዲያውም ቁጥር መቁጠር ደስ ይላል 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 ፣9 የሚል መዝሙር እየዘመሩ ነበር፡፡ አካባቢው ጽዱ ሆነ፡፡ መምህርት ደጊቱ ህፃናቱ የሰሩትን አይታ በጣም ተደነቀች፡፡ ልጆች መተባበር ውጤታማ ያደርጋል፡፡ አያችሁ አንድ ሰው ብቻውን ቢሰራ ኖሮ እስካሁን አይጨርስም ደግሞም ይደክም ነበር ስለዚህ ሰዎች በትምህርት ቤትም ሆነ በሰፈር ከጎረቤቶቻችን ጋር በፍቅር እና በመከባበር እየተረዳዳን መኖር ያስፈልጋል አለች፡፡ ከዚያም የሀገር ባህል ዘፈኖችን ሲጨፍሩ ቆይተው የተጠቀሙበትን እቃዎች ቦታቸው በመመለስ እጃቸውን ታጥበው ወደ ክፍላቸው ሄዱ ይባላል፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የተለያዩ የፅዳት እቃዎች ፣ ባህላዊ ዘፈኖች ቅጂ፤ ሞባይል፣ ክብሪት፣ ከፕላስቲክ የተሰራ የአትክልት መቀስ፣ የአትክልት ውሃ ማጠጫ፣ የዘይት /የውሃ ጀሪካን

- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ ማድረግ እና የቃል ጥያቄ መጠይቅ (ለምሳሌ የመምህርቷ ስም ማን ይባላል፣ መምህርት ደጊቱ ለምን ተከፉ፣ ህፃናቶቹ በጋራ ምን ምን ተግባር አከናወኑ .... )

### ለ. ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፣ መግባባት
- **የማስተማር ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ቀጥሎ የቀረበውን ተረት ህጻናቱን ዝግጁ በማድረግ ያንብቡላቸው፡፡ ሲያነቡ ሳቢ እና ጉጉት እንዲያሳድር ድምፃትን እየቀያየሩ እና ስዕላዊ መግለጫ በመጠቀም ያንብቡ

## ተረት ተረት

ከዕለታት አንድ ቀን ተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ እንዲህ በማለት ተወያዩ፡፡ ተፈጥሮ እኔ እኮ ለሰው ልጅ እጅጉን አስፈላጊ ነኝ ሰዎች ምንም ሳይለፉ የሚያገኙኝ ነኝ፡፡ ስለዚህ እኔ ከአንተ እጅጉን እበልጣለሁ አለው፡፡ ሰው ሰራሹም እኔ ሰዎች አዕምሮአቸውን ተጠቅመው አስጊጠው እና አሳምረው በተለያየ አይነት የሚሰሩኝ ነኝ፡፡ አምርተው እራሳቸው ስለሚጠቀሙብኝ በጥንቃቄ እኮ ነው የሚይዙኝ፡፡ ለምሳሌ ቤት ወንበር ቴሌቪዥን እኔ ነኝ አለ፡፡ ጠፈጥሮ ኪ ኪ ኪ ብሎ በመሳቅ በጣም ትገርማለህ! አንተን ሰዎች የሚሰሩህ እኔ ስላለሁ ነው፡፡ ለምሳሌ ወንበር ለመስራት እንጨት ያስፈልጋል ዛፍን በተፈጥሮ ካላገኙ በምን ይሰሩኻል፡፡ አንተ ቂል! ሁሉንም ነገር ለመስራት በመጀመሪያ በተፈጥሮ መገኘት አለበት አለው፡፡ ሰው ሰራሽም ልክ ነህ እኔ ካለተፈጥሮ ምንም ማለት ነኝ አለው፡፡ ተፈጥሮም እኔ እና አንተ እኮ ተስማምተን እና ተግባብተን መኖር አለብን አለው ይባላል፡፡ አንዳችን ለአንዳችን ልክ እንደጎረቤታሞች እናስፈልግጋለን በማለት ተፈጥሮ እኔ ያለ አንተ አንተም ያለእኔ መኖር አንችልም በማለት እርስ በእርሳቸው ተነጋግረው አንድ ላይ ለመኖር ተስማሙ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አከባቢን የሚያሳዩ ስዕሎች / የተቀረፁ ምስሎች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- በተፈጥሮ የምናገኘው ምንድ ነው፣ ሰው ሰራሽ የሚባሉት የትኞቹ ናቸው ....) እና ምልከታ (ለምሳሌ:- ተረቱን መልሰው ሲያወሩ በመመልከት)፡፡

## ተግባር 6፡- መዝሙር (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. አከባቢያችንን እንከባከበው (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** አካባቢን መንከባከብ፣ተፈጥሮ፣ ሰውሰራሽ፣ ቁጥር
- **የማስተማር ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! መዝሙሩን በቡድንና በግል እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

አከባቢያችንን እንንከባከበው

አከባቢያችንን እንከባከበው፣

ንጹህ ሲሆን ነው የሚያስደስተው፡፡

ዝንብና ትንኙን እንዳይራባብን፣

በጋራ እናጽዳ መኖሪያ አካባቢን፡፡

ተፈጥሮ ውብ ናት በጣም እናድንቃት፣

ከሷ ነው ሰው ሰራሽ የሚገኘው ብልሃት፡፡

ቁጥርና ፊደል መፃፍ እንዳወቅነው፣

አካባቢን ማፅደት መማር መጀመር ነው፡፡

አከባቢያችንን እንከባከበው፣

ንጹህ ሲሆን ነው የሚያስደስተው፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- ቴፕ/ሞባይል፣ ከመዝሙሩ መልዕክት ጋር ተያያዥነት ያለቸው ምስሎች
- የምዘና ስልት:- የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- አካባቢ ካልፀዳ ምን ይከሰታል ...)

ለ. ከበሮዬ (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- ድምጽ፣ መጋፋት
- የማስተማር ዘዴ:- በመዝሙር
- የመምህርሚና:- መምህር! ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር ተፈላጊውን ብቃት ለማሳካት እንዲሆን አድርገው ያስዘምሩ፡፡

ከበሮዬ

አንቺ ከበሮዬ ድምጽሽ ደስ ይለኛል፣
ዳንስ እንቅስቃሴ በጣም ያሰራኛል፡፡
ደግሞም እንሂድ እሩቅ ቦታ፣
ደስ እንዲለን ለጨዋታ፡፡
እንጨፍር ሳንጋፋ፣
ጓደኝነት እንዲሰፋ፡፡
እቃዎችን በመደርደር፣
በመመደብ በማሳመር፡፡
ጫወታችን ጀምረናል፣

ዛሬ ቀኑ ደስ ብሎናል፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- ቴፕ /ሞባይል/፣ ከመዝሙሩ መልዕክት ጋር ተያያዥነት ያለቸው ምስሎች
- የምዘና ስልት:- ምልከታ (ለምሳሌ:- ሲዘምሩ መከታተል) እና የሚያውቁትን ጭፈራ እንዲጨፍሩ መጠየቅ

# የአውድ ሶስት ምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም ------------------------------ጾታ-------- እድሜ ------ደረጃ-------

መግለጫ:- ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሚሉት ብቃት ትይዩ የ “√” ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ።

| ተ.ቁ | የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት | ጥሩ | በ/ጥሩ | እ/በ/ጥሩ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ማንበብ | | | | |
| 2 | ፊደላትን መለየት | | | | |
| 3 | በነጠብጣብ የተጻፉትን ፊደላት ይገጣጠማሉ ቀለም መቀባት | | | | |
| 4 | ከ1_9 ያሉቁጥሮችን መቁጠር፣ የተቆራረጡ መስመሮችን መገጣጠም | | | | |
| 5 | ነጠላ ንድፍ (sngle pattern) መስራት | | | | |
| 6 | የአትክልት ዓይነቶችን መለየት | | | | |
| 7 | ስለሚያውቋቸው ነፍሳት መናገር | | | | |
| 8 | ስሜቶቻቸውን ለመምህራኖቻቸው መግለጽ | | | | |
| 9 | የቤተሰብአባላትን ስሞችን መጥራት | | | | |
| 10 | ተራ ጠብቀው መናገር | | | | |
| 11 | የተለይዩየሰውአካልክፍሎችንይጠራሉ | | | | |
| 12 | ከምግብ በፊትና በኋላ እጃቸውን መታጠብ | | | | |
| 13 | አፍንጫቸውን በክንዳቸው ሸፍነው ማስነጠስ | | | | |
| 14 | የሀገራቸውን ሰንደቅ ዓላማ ቀለማት መለየት | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፦ ______________________________

______________________________________________

____________________

# አውድ አራት

# ቀለማት

አጠቃላይየተሰጠጊዜ- 5 ሳምንት

ክፍለ ጊዜ ብዛት- 150

## 4.1 መግቢያ

ህፃናት ቀለማት በሚለው ዓውድ ውስጥ የተጠቀሱትን የትኩረት ነጥቦች ማለትም፡- ራስን ማወቅ፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ የግል ንፅህናን መጠበቅ፣ አካላዊ ገፅታቸውን መግለጽ የሚያስችላቸውን መሰረታዊ ክህልቶች የሚያዳብሩበትና አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ስሜታዊ እና ማህበራዊ ዕድገታቸውን ሊያጎለብቱ የሚችሉበት የትምህርት መስኮች ተካተዋል፡፡በአምስቱ ሳምንታት ውስጥ ለመማር ዓውዱ የተቀመጡትን አጥጋቢ የመማር ብቃቶች እና ዝርዝር የአተገባበር ስልቶችን መሰረት በማድረግ መምህራን የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ሲገቡ ህፃናት በክፍል ውስጥ እና በክፍል ውጪ የዕለት ዕለት ተግባራት (የግል ተግባር፣ ተረት፣ መዝሙር፣ የክፍል ውጭ ጨዋታ፣ በፕሮጀክት መማር፣ በስራ መማር፣ ውይይት፣ የመስክ ጉብኝት፣ የክፍል ውስጥ ጨዋታ) ራሳቸውን እና ጓደኞቻቸውን ማስተዋወቅ እንዳለባቸው ትህትናን በተላበሱ የአገላለፅ ስልቶች ሰላምታ እና ስንብትን በተገቢው ሰዓት መጠቀምን እንዲችሉ እንዲሁም ራሳቸውን ከአደጋ ተጋላጭ ከሆኑ ነገሮች እና በራስ መተማመንን የሚያዳብሩበት አውድ በመሆኑ አስፈላጊዉን ድጋፍ ማድረግ ከመምህራን ይጠበቃል፡፡

## 4.2 የአውዱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- ስለቀለም ምርጫቸው ይናገራሉ
- ከ1-5 ያሉ ቁጥሮችን ይቆጥራሉ፤ አስመስለው ይጽፋሉ
- የአደጋ መንስኤዎችን ይለያሉ
- ፐዝሎችን ይገጣጥማሉ
- መካፈል፣ መተባበርና ሌሎችን ማክበር ይተገብራሉ
- ከ3-5 የሚደርሱ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ይሰራሉ
- ነጠብጣብ ፊደላትን ያያይዛሉ
- የፍራፍሬና የአትክልት ስሞችን ይጠራሉ

- ፊደላትን አስመስለው ይጽፋሉ
- የጆኦሜትሪክ ምስሎችን ቀለም ይቀባሉ
- የአትክልትን ምስሎችን ይስላሉ፤ ቀለም ይቀባሉ
- የጫማ ማሰሪያቸውን ያስራሉ ፤ይፈታሉ
- ሞዴል እቃዎችን ይሰራሉ(ለምሳሌ-፡ መኪና)

## 4.3 የዓውዱ አበይት ይዘቶች

- አትክልትና ፍራፍሬ
- የቀለም ምርጫ
- ፊደላትን ማድመቅ
- ቃላት ማንበብ
- የቤት እንስሳት
- አደጋ የሚስከትሉ ነገሮችን ይለያሉ
- የግል ፍላጎት
- አካላዊ እንቅስቃሴዎች
- አትክልቶችን መሳልና ቀለም መቀባት

# አስራ ስድስተኛ ሳምንት

የተሰጠው ሰዓት--------10 ክፍለ ጊዜ (30)

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማርብቃት

- የቀለም እና የምግብ ምርጫቸውን ይገልጻሉ
- የቤተሰብ አባሎቻቸውን ስም ይናገራሉ
- ጸጉራቸውን ያበጥራሉ
- እስከ ዘጠኝ የሚደርሱ ቁሶችን ይቆጥራሉ
- የተለያዩ ስዕሎችን ቀለም ይቀባሉ
- ከ1-5 ቁጥሮችን ደጋግመው ይጽፋሉ
- ፊደላትን ደጋግመው ይጽፋሉ
- እናት ፊደላትን ተጠቅመው ቃላት ይመሰርታሉ (በሰለ፣በከለ)
- ዋና ዋና የቀለም አይነቶችን ይለያሉ
- መሰረታዊ የጂኦሜተሪ ቅርፆችን ይለያሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ስለራስ ማወቅ
- ራስን ማስተዋወቅ
- የሰውነት ክፍሎች
- ጤና
- ፊደላትን መጻፍ
- ማንበብ
- ቁጥሮችን መጻፍ
- ቁጥርና እና መቁጠር
- ጥበባዊ ግንዛቤ

## ተግባር 1- የግል ተግባር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የሰውነት ክፍሎችን ቀለም መቀባት (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ቀለም፣ ቤተሰብ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! የቤተሰብ ሥዕል አዘጋጅተው በመስጠት ህጻናቱ የተለያዩ ቀለሞችን እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡ ስዕሉን በትክክል እንዲቀቡ ከእርሳስ (ማርከር) አያያዝ ጀምሮ አስፈላጊውን እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** እርሳስ፣ ማርከር፣ የተለያዩ፣ የሰው ምስሎች
- **የምዘና ስልት፡- በምልከታ፤** በትክክል መቀባታቸውን መከታተል፣ የእርሳስ/ማርከር አያያዛቸውን መመልከት፣... የቃል ጥያቄ፤ የቀቡትንም ሥዕል የሰውነት ክፍሎችን ስም መጠየቅ፣ ምን አይነት ቀለም እንደሚወዱ መጠየቅ፣ ስንት ዓይነት ቀለሞች እንደ ቀቡ መጠየቅ፣ ስንት የሰውነት ክፍሎችን እንደቀቡ መጠየቅ...።

### ለ.ቁጥር መጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቅርጽ፣ የቀለም ምርጫ፣ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ቁጥር “1ን” በመጻፍ ተግባር ውስጥ ህጻናቱ የቁጥሮቹን ቅርጽ የመለየት፣ የቀለም ምርጫቸውን የመግለጽ፣ የጽሁፍ ልምምድ ማድረግ፣ ስለቀለም አይነቶች መገንዝብ የመሳሰሉት ብቃቶችን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ተግባሩን በአግባቡ እንዲፈጽሙ ያግዟቸው። በመለማመጃ ድብተራቸው ላይ ቁጥር “1ን” ጎላ አድርገው ይጻፉላቸውና ደጋግመው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ
- **የምዘና ስልት፡- ምልከታ፣** ቁጥሮቹን በአግባቡ መጻፋቸውን መመልከት፣በቃል መጠይቅ (የቀለም ምርጫቸውን መጠየቅ፣ ቁጥር 1ን ጽፎ ማን ናት ብሎ መጠየቅ)

### ለ. እናት ፊደላትን መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** እናት ፊደላት፣መጻፍ፣መቁጠር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በመጀመሪያ ከፊደል ገበታ ላይ የአማርኛ የመጀመሪያ ፊደላትን ያሳዩዋቸው። በመቀጠል ፊደል ረ፣ፈ፣ሀ፣ሠ በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ጎላ ጎላ አድርገው ይጻፉላቸው። ከዚያም እርሳስ በመስጠት ፊደላቱን በመደጋገም እንዲጽፉ ያበረታቷቸው። የጻፏቸውን ፊደላት እንዲቆጥሩ ያድርጉ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** እርሳስ፣ የፊደል ገበታ፣ መለማመጃ ደብተር
- **የምዘና ዘዴ፡-** የቃል ጥያቄ (ስንት ፊደላትን እንጻፉ መጠየቅ፣ የጻፏቸን ፊደላት ስም መጠየቅ፣ በጻፏቸው እናት ፊደላት ቃላት እንዲመሰርቱ መጠየቅ)።

## ተግባር 2- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ታታሪው አብጤና ቤተሰቦቹ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ጤና፣ ቀለማት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ከዚህ በታች ያለውን ተረት ለህጻናቱ ይንገሯቸው።

## ተረት ተረት!

“አብጤ” የሚባል ጎበዝ ልጅ ነበር፡፡ አብጤ እድሜው 4 ዓመት ሲሆን በጸባዩ በጣም ምስጉን ልጅ ነበር፡፡ አቢጤ 3 እህቶችና 2 ወንድሞችም አሉት የሁሉንም ቤተሰቦቹን ስም መናገር ይችላል፡ ፡ ሁልጊዜ በእርፍት ጊዜው ከእህትና ከወንድሞቹ ጋር እግር ኳስ ይጫወታል ፡፡ እናቱና አባቱ እግርኳስ መጫወት መውደዱን ስለሚያወቁ የተለያየ መጠን ያላቸው ቀይ፣ ቢጫ፣ ሰማያዊና አረንጓዴ ኳሶች ተገዝቶለታል፡፡ ብዙ ኳሶች ስለአሉት በጣም ደስተኛ ነው፡፡ በኳሶቹ ከጓደኞቹ ጋር ይጫወታል፡፡ ኳስ ተጫውቶ ከጨረሰ በኋላ እጆቹን በውሃና በሳሙና ይታጠባል፡፡ አብጤ ጤነኛና በትምህርቱም ጎበዝ ልጅ ነው፡፡

- **የመማያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ኳሶች፣ ወሃና ሳሙና
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (አብጤ ስንት ኳሶች አሉት? የአብጤ ኳሶች ቀለሞች ምን ምን አይነቶች ናቸው? አብጤ ስንት ወንድም እና እህቶች አሉት?አቢጤ ኳስ የሚጫወተው ከማን ጋር ነው ?

### ለ. ሊሊ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፀጉር፣ ማበጠር፣ የቀለም ምርጫ፣ ጤና
- **የማስተማያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ቀጣዩን ተረት ለህጻናቱ ያንብቡላቸው፡፡

## ተረት ተረት

ሊሊ የምትባል ፀጉሯን ማበጠር የማትወድ ልጅ ነበረች፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን እናቷ ጸጉርሽን ላበጥርልሽ ስትላት አልፈልግም እያለች ጮኸች፡፡ እናቷም ጸጉርሽ ሲበጠር በጣም ጤነኛና ደስተኛ ልጅ ትሆኛለሽ፡፡ ለጸጉርሽ ማበጠሪያ እና ፀጉር ማስያዣ ገዝቼልሻለሁ አለቻት፡፡ሊሊም አስኪ አሳዩኝ ስትላት እናቷም የገዛችላትን የፀጉር ማበጠሪያና ማስያዣ አሳየቻት፡፡ ሊሊም በጣም የምወደውን ሰማያዊ ቀለም ማበጠሪያና ቀይ የፀጉር ማስያዥያ ነው የገዛሽልኝ በማለት እናቷን አቅፋ ሳመቻት፡፡ ሊሊም ፀጉሯ ከተበጠረላት በኋላ በጣም ቆንጆ ሆና ወደ ትምህርት ቤት ሄደች ይባላል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ማበጠሪያ፣ ጸጉር ሲበጠሩ የሚያሳይ ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ሊሊ የተገዛላት የጸጉር ማበጠሪያ ቀለምምን አይነት ነው? ሊሊ የምትወደው ምን አይነት ቀለም ነው?

## ተግባር 3፡- መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቤቱሰቦቼ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቤተሰብ፣ ቁጥር፣ ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡

ቤቴሰቦቼ

እናትና አባቴን እወዳለሁ፣

ትዕዛዛቸውን ፈጽማለው፡፡

እህት ወንድሜን እወዳለሁ፣

ከነሱ ጋራ እጫወታለው፣

ቤተሰቦቼን አከብራለሁ፡፡/2/

ፀጉሬን ታጥቤ አበጥራለሁ፣

በቀይዋ አበባ አስይዣለሁ፡፡

ከአንድ እስከ ዘጠኝ እቆጥራለሁ፣

ጎበዝ ስለሆንኩ እኮራለሁ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** አበባ፣ የቤተሰብ ሥዕል፣ ተቆጣሪ ቁሶች
- **የምዘናስልት፡-** ምልከታ፣ መዘመር መቻላቸውን በመመልከት... የቃል ጥያቄ (በመዝሙሩ ውሰጥ ያሉት የቤተሰብ አባላት ስንት ናቸው?ፀጉሯን ያስያዘችው አበባ ቀለም ምን አይነት ነው?)

## ሀ. ፊደል በ፣ ሰ፣ ለ (4 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደላት፣መቁጠር፣የቤት እቃ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በጋራና በግል እንዲዘምሩ አብረው በመዘመር ያለማምዱዋቸው፡፡

በ፣ ሰ፣ ለ

በ - በሩን ስከፍት፤

ሰ - ሰው መጣ ድንገት፡፡

ለ - ለብሶ ልብሱን

ሱሪው ቢጫ ነው ሹራቡ ቀይ

ሰማያዊ ነው ደግሞ ከላይ

መቁጠር  ጀመርኩኝ ቁሳቁስን

ከ1 እስከ 9 የቤት ዕቃን

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቁጥር ሎቶ ፣ የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ የተለያዩ ቀለማት ካርድ

- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ፤በቡድንና በግል ሲዘምሩ መከታተል፣ ጥያቄ መጠየቅ( ከመዝሙሩ የወጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ/ለምሳሌ ከ1-9 በቃል እንዲቆጥሩ መጠየቅ፣ የቀለማት ዓይነት መጠየቅ

## ተግባር 4፡ የውይይት ግዜ (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቤተሰብ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቤተሰብ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በውይይት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱን ከክፍል ውጭ ይዘው በመውጣት በራሳቸው በቡድን እንዲደራጁ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ከዚያም ህፃናቱ የአባት፣ የእናት፣ የወንድምና የእህታቸውን ስም እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ በተጨማሪም ወደ ሰንደቅ ዓላመው መስቀያው በመሄድ ስለ ሰንደቅ ዓላማ ቀለም በመመልከት ለቡድን አባላታቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቤተሰብ ሥዕል፣ ሰንደቅ ዓላማ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ ፡- በትልቅ ወረቀት ላይ የተሳለ የቤተሰብ ሥዕል በማሳየት አባት፣ እናት፣ ወንድ ህጻናት እና ሴት ህጻናት የትኞቹ እንደሆኑ መጠየቅ፡፡ የለበሱትን የልብስ ቀለም መጠየቅ፡፡ የሀገራቸውን ሰንደቅ ዓላማ ቀለም መጠየቅ፡፡

## ተግባር 5- የክፍል ውጭ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የጋራ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ጂኦሜትሪ ቅርጽ፣ የምግብ ምርጫ፣ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በመቀጠልም የተለያየ ቀለም ያላቸው 5 ትንንሽ ኳሶች እና ጣሳዎች (የተለያየ ቀለም መቀባት ይቻላል) ያዘጋጁ፡፡ ህፃናቱን ከክፍል ውጭ ይዘው በመውጣት እጅ ለእጅ ተያይዘው ክብ ሰርተው እንዲቀመጡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ጣሳዎቹን በአራት ጎን ቅርፅ፣ ኳሶቹን በሶስት ጎን ቅርፅ፣ ህጻናቱ በሰሩት ክብ መሃል ላይ መሬት ላይ ይደርድሩ፡፡ በህጻናቱ፣ በጣሳዎቹ እና በኳሶቹ የተሰሩትን ቅርፆች ስም ይንገሯቸው፡፡ ከዚያም በህጻናቱ፣ በጣሳዎቹ እና በኳሶቹ የተሰሩትን ቅርፆች እየጠየቁ ያወቁ ህጻናት ኳሶቹን እያነሱ ተመሳሳይ ቀለም ባላቸው ጣሳዎች ውስጥ እንዲያስቀምጡ ያድርጉ፡፡ ቀለማቱን በትክክል ያላዛመደ ህጻን ለጊዜው ከጨዋታ ውጪ ይሆናል፡፡ በዚህ መልኩ ሁሉንም ህጻናት ያጫውቱ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያየ ቀለም ያላቸው ኳሶች፣ ጣሳዎች
- **የምዘና ስልት፡-**ምልከታ (ጨዋታውን በመከታተል በትክክል የተገበሩና ያልተገበሩ ህጻናትን መለየት፣ ቀለሞችን መለየታቸውን ማረጋገጥ)፣ የቃል ጥያቄ (ቅርጾቹን ስም መጠየቅ)

# ተግባር 6- በፕሮጀክት መማር (4 ክፍለ ጊዜ)

## ሀ. ቀለም እና ቅርፆች ማዛመድ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ቀለም፣ ቅርጽ፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተግባር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ የተለያዩ ቀለሞችን በቀላሉ እንዲለዩ፣ የሚወዱትን ቀለም እንዲናገሩ፣ የተለያዩ ቀለም የያዙ ቁሳቁስን እንዲቆጥሩና ተመሳሳይ የሆኑትን እንዲለዩ፣ እና ሌሎች ከብቃቱ ጋር የተያያዙ ተግባራትን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው።

የፕሮጀክቱ አተገባበር

1. የተለያዩ ቀለማት የተቀቡ ክብ፣ ባለ ሦስት ጎን እና ባለአራት ጎን ትናንሽ የጣውላ ቁርጥራጮች አዘጋጅተው በአንድ ቅርጫት/የካርቶን ሣጥን ውስጥ ያስቀምጡ።
2. የተለያዩ ቀለማት የተቀቡ ክብ፣ ባለ ሦስት ጎን እና ባለ አራት ጎን የካርቶን/ባለ ቀለም ወረቀት ቁርጥራጮች ያዘጋጁ።
3. ያዘጋጁትን ክብ፣ ባለ ሦስት ጎን እና ባለ አራት ጎን የካርቶን ቁርጥራጮች ለህጻናቱ በየተራ ይስጧቸው።
4. ህጻናቱ በቅርጫት ውስጥ ያሉትን የጣውላ ቁርጥራጮች እያወጡ ከካርቶን ቁርጥራጮች ጋር ተመሳሳይ ቀለምና ቅርጽ ያላቸውን ያዛምዱ።
5. በትክክል ያዛመዱትን እንዲቆጥሩ ያድርጉ።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተለያዩ ቀለም እና ቅርፅ ያላቸው ቁርጥራጭ ጣውላ እና ካርቶኖች/ባለ ቀለም ወረቀት
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ (ተግባሩን በአግባቡ ማከናወናቸውን መመልከት ተግባሩን ለመስራት የተቸገሩ ህጻናትን በመለየት ድጋፍ ማድረግ)፣ የቃል ጥያቄ (ስንት ቀለማት እንዳዛመዱ መጠየቅ፣ ያዛመዷቸውን ቅርፆች ስም መጠየቅ፣ የምግብ ምርጫቸውን መጠየቅ፣ ስለሰሩት ፕሮጀክት እንዲገልጹና በየመሃሉ እንዴት እንደሰሩ ፣ከማን ጋር እንደሰሩ ፣ ሲሰሩ ምን ችግር እንደገጠማቸው ፣ እንዴት እንደፈቱ ...መጠየቅ)

# አሥራ ሰባተኛ ሳምንት

የተሰጠው ሰዓት-10 ክፍለ ጊዜ (30)

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ስሜታቸውን በተገቢው ሁኔታ መግለጽ ይጀምራሉ
- የግል ስሜትን ምስሎች በመሳል ቀለም ይቀባሉ
- በተለያዩ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ሰዎችን ድምጽ ይለያሉ
- የእንስሳትን ድምጽ ይለያሉ
- የቤት እቃዎችን ምስሎችና በማድመቅ ቀለም ይቀባሉ
- ፊደላትን በቀደም ተከተል ያነባሉ
- ፊደላትን በቀደም ተከተል ይጽፋሉ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- ሁለት ቁጥርን ደጋግመው ይጽፋሉ
- ቀላል የጂኦሜትሪ ምስሎችን ይሰራሉ

## ንዑስይዘቶች

- ራስንመምራት
- ድምጽንመለየት
- የቅርብአካባቢ
- የተመጣጠነምግብ
- ቁጥርመጻፍ
- ማንበብ
- ፊጠራን መግለጽ

## ተግባር 1.የግልተግባር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ስሜትን መግለጽ (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- የቤት ዕቃ፣ ስሜት መግለጽ፣ ማቅለም
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! የቤት ዕቃዎች ሥዕል ያቅርቡላቸውና የሚፈልጉትን እንዲመርጡ ያድርጉ:: ስሜታቸውን በተገቢው ሁኔታ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው:: የተለያየ ቀለም ያላቸውን ክራዮኖች አዘጋጅተው በመስጠት ህጻናቱ እቃዎቹን የሚወዱትን ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ:: ስዕሉን በትክክል መቀባት ላልቻሉ ህጻናት እገዛ ያድርጉላቸው:: የቀቡትን ሥዕል ለጓደኞቻቸው የቀለሙን ዓይነት እንዲናገሩ ያድርጉና ስንት የቤት ዕቃዎች

እንዲቀቡና ቆጥረው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

- **የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** እርሳስ፣ ክራዮን፣ የተለያዩ የቤት ዕቃዎች ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡ ምልከታ፡-** በትክክል መቀባታቸውን መከታተል፣ እርሳስ አያያዛቸውን መመልከት…፣ የቃል ጥያቄ፣የቀቡትን የቤት እቃዎች ስም መጠየቅ፣ ምን አይነት ቀለም እንደሚወዱ መጠየቅ፣ ስንት የቤትዕቃ እንደቀቡ መጠየቅ…

## ለ. ቁጥር መጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ ጽሁፍ፣ ስሜት መግለጽ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-መምህር!** “2” ቁጥርን በመጻፍ ተግባር ውስጥ ህጻናቱ የቁጥሮቹን ቅርጽ የመለየት፣ ስሜታቸውን በተገቢው ሁኔታ መግለጽ፣ የጽሁፍ ልምምድ ማድረግ፣ የመሳሰሉት ብቃቶችን እንዲያዳብሩ በማድረግ ተግባሩን በአግባቡ እንዲተገብሩ ያግዟቸው፡ ፡ በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ “2” ቁጥርን ጎላ አድርገው ይጻፉላቸውና ደጋግመው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- **የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ/ክራዮን
- **የምዘና ስልት፣-** ምልከታ “2” ቁጥርን በአግባቡ መጻፋቸውን መመልከት፣ ስሜታቸውን በተገቢው ሁኔታ መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣ የቁጥሮቹን ቅርጽ የመለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ

## ሐ. ፊደላትን ማንበብና መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደላት፣ በቅደም ተከተል፣ ማንበብ፣ መጻፍ፣ ቀላል ቃላት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ፊደል (ዐ ፣ ፀ ፣ ወ እና መ) በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ይጻፉላቸውና ደጋግመው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡ ፊደላትንም በተለያዩ ቀለማት እንዲቀቡ ያግዟቸው፣ የቀቧቸውን ፊደላት በቅደም ተከተል እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ፊደላቱን በመጠቀም ቀላል ቃላትን ማንበብ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- **የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** እርሳስ፣የመጀመሪያ ፊደላት የተፃፉባቸው ፍላሽ ካርዶች፣ የፊደል ገበታ፣ መለማመጃ ደብተር፣ የተለያዩ ቀለማት
- **የምዘና ዘዴ፡-** ስንት ፊደላትን እንዳቀለሙ መጠየቅ ( ቁጥራቸውን ካላወቁ ቁጥሩን ከፊደላቱ ጋር አቀናጅተው እንዲቆጥሩ ያድርጉ) ፡፡

# ተግባር 2. ተረት (6 ክፍለ ጊዜ )

## ሀ. ውሻና ድመቷ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የተመጣጠነ፣ ምግብ፣ጤናማ፣ ስሜት፣ የእንስሳት ድምጽ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት

- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ከታች ያለውን ተረት ከተረቱ ጋር የሚሄዱ ስሜቶችን በማሳየት ይንገሯቸው፡፡

## ተረት ተረት!

በድሮ ጊዜ አቤልና ሰላም የሚባሉ ወንድምና እህት አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ አቤል ቲና የምትባል ቀይ ውሻ፣ ሰላም ደግሞ ጃኪ የሚባል ጥቁር ድመት ነበራቸው፡፡ አቤልና ሰላም የውሻና የድመታቸውን ንጽህና ስለ ሚጠብቁላቸውና የሚመገቡትም ምግብ ንጽህናውን የጠበቀ ስለሆነ በጣም ደስ የሚሉና ጤነኞች ነበሩ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ቲና ውጭ ወጥታ የወደቀ ስጋ አግኝታ ይዛ መጥታ ከጃኪ ጋር ስጋውን በመብላታቸው ታመሙ፡፡ በህመማቸውም ምክኒያት እንደ ሌላው ጊዜ ድምጻቸውን ጮክ አድርገው መጮህ አልቻሉም ፡፡ አቤልና ሰላም በጣም ደንግጠው እና አዝነው ወደ ሀኪም ቤት ይዘዋቸው ሄዱ፡፡ ዶክተሩም “ምን በልታችሁ ነው የታመማችሁት?” ብሎ ጠየቃቸው፡፡ ጃኪም “ቲና የወደቀ ስጋ ይዛ መጥታ ያንን በልተን ነው የታመምነው” አለ፡፡ ዶክተሩም በሽታው በጣም ቃላል ነው የምሰጣችሁን መድሀኒት በአግበባቡ ከወሰዳችሁ ትድናለችሁ አላቸው፡፡ ቲናም የወደቀ ስጋ ይዛ መጥታ ጃኪን ስላበላችው ተጸጽታ ይቅርታ ጃኪ እኔ ነኝ እንድትታመም ያደረኩህ አለችው፡፡ጃኪም ምንም አትጨነቂ ለተንኮል አይደለም ያደረግሽው ይቅርታ አድርጌልሻለሁ አላት፡፡ አቤልና ሰላምም ውሻና ድመታቸው ስለዳኑላቸው በጣም ደስ አላቸው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የውሻና ድመት ሥዕል፣ ያዘኑና የተደሰቱ ህጻናት ስዕሎች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ- የውሻና የድመቱ ቀለም ምን ዓይነት ነው? ቲና እና ጃኪ ለምን ታመሙ?

### ለ. ሚሚና ቡጡ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የጂኦሜትሪ ሥዕሎች፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ተረቱን ሳቢ በሆነ አቀራረብ ይንገሯቸው፡፡

## ተረት ተረት!

ሚሚና ቡጡ የአራት ዓመት ልጆች ሲሆኑ ጓደኛሞችም ናቸው፡፡ ከትምህርት ቤት ሲመለሱ የተሰጣቸውን የቤት ስራ በጋራ በመጠያየቅ ከሰሩ በኋላ የተለያዩ ጨዋታዎችን የመጫዎት ልምድ አላቸው፡፡ የተሰጣቸው የቤት ስራ የጂኦሜትሪ ስዕሎችን ( ክብ፣መዓዘን ሰስትንና መዓዘን አራት) መሳል በመሆኑ ስራውን ጨርሰው መጫወት ጀመሩ፡፡ ቡጡ ሁለት ኳሶች ያሉት ሰሆን አንዱ ኳስ ቀይ ሲሆን አንዱ ደግሞ ቢጫ ነው፡፡ ሚሚ በቢጫው ኳስ መጫወት የምትወድ ሲሆን ቡጡ ደግሞ በቀዩ ኳስ መጫወት ይወዳል፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ከቤታቸው ቅርብ በሆነ አከባቢ በጋራ ሲጫወቱ ሚሚ ቡጡን ገፍታ ጣለችው፡፡ ቡጡ ጉልበቱ ስለ ደማበት አለቀሰ፡፡ ሚሚ በጣም ደንግጣ አውቄ አይደለም የገፋሁህ ይቅርታ አለችው፡፡ የቡጡ እናት መጣችና የቡጡን ጉልበት አሻሸችለትና አቀፈችው፡፡ የቡጡ እናት ሚሚ ጥሩ ልጅ ናት እንደማትገፈትርህ አውቃሁ ብላ ሚሚን ሳመቻት፡ ፡ ስትጫወቱ ቀስ ብላችሁ ተጫወቱ ብላ መከራቻቸው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ህጻናት ሲጫወቱ የሚያሳይ ሥዕል፣ የተለያየ ቀለም ያላቸው ኳሶች
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ፣ሚሚና ቡጡ ዕድሜያቸው ስንት ነው? ቡጡ ስንት ኳሶች አሉት? የቡጡ ኳሶች ቀለሞችን ምንምን አይነቶች ናቸው? የተነበበላቸውን ተረቱን መልሰው እንዲናገሩ ማበረታታት

## ተግባር 3:- መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. “ዐ ፣ ፀ ወ፣መ ” ነኝ እወቁኝ (4 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት:-** ፊደል፣ ድምጽ መለየት፣ ሥዕል፣ እንስሳት
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ በማለማመድ ስለራሳቸው መግለጽ፣ ራስን መምራት እና የፊደል ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ያግዟቸው፡፡

ዐ ፣ ፀ ወ ፣መ ነኝ እወቁኝ

“ዐ” ነኝ “ዐ” ነኝ ልጆች እወቁኝ

“ዐ” ነሽ “ዐ” እኛም አወቅንሽ

“ ወ” ነኝ “ ወ” ነኝ ልጆች እወቁኝ

“ ወ” ነሽ “ ወ” እኛም አወቅንሽ

ድምጽ መለየት ጀምሬያለሁ

“ወ” መሆንሽን አውቂያለሁ

ሥዕል እስላለሁ ቀለም እቀባለሁ

“ፀ” ነኝ “ፀ” ነኝ ልጆች እወቁኝ

“ፀ” ነሽ “ፀ” ነሽ እኛም አወቅንሽ

የሰው እንስሳትን ድምጽም እለያለሁ

የቤት እንስሳትን ድምጽም አሰማለሁ

ሚው፣ሚው…፣ ው…ው… ትችያለሽ

እኛም አወቅንሽ

”መ ” ነኝ “መ ” ነኝ ልጆች እወቁኝ

“መ ” ነሽ “መ ” እኛም አወቅንሽ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የፊደል ገበታ፣ ሞባይል/መቅረጸ ድምጽ
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ:- ሲዘምሩ መከታተል…የቃል ጥያቄ፤ ከመዝሙሩ የወጡ ያሉ ፊደላትን መጠየቅ ? ፊደላቱን አስመስለው መጻፋቸውን ማረጋገጥ፣የሚውቆቸውን እንሰሳት ድምጽ እንዳስለለሉ መጠየቅ፣የቤት እንስሳት ስሞችን ከስእል ጋር እንዳዛምዱ መጠየቅ

### ለ. ለይቻለሁ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ መጻፍ፣ ፊደል፣ ማንበብ፣ የእንስሳት ድምጽ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህራን ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያግዟቸው፡፡

ለይቻለሁ

ቁጥር መጻፍ ተምሬያለሁ

ፊደል ማንበብ ጀምሬያለሁ

የእንስሳትን ድምጽ እሰማለሁ

አንድ ላም "እምቧ! እምቧ!"

ሁለት ውሻው!ው!ው!

ሶስት ድመት ሚያው!ሚያው!

አራት ዶሮ አኩኩሉ! አኩኩሉ!

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-**የቤት እንስሳት ሥዕል፣ፍላሽ ካርዶች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ ለምሳሌ፤ በመዝሙሩ ውስጥ ስንት ላሞች?፣ ስንት ውሾች አሉ?፣ ስንት ድመቶች አሉ?፣ ስንት ዶሮዎች አሉ? ቁጥሮችን እንዲጽፉ መጠየቅ፤ምልከታ (የተሰጣቸውን ተግባር በአግባቡ መፈጸማቸውን መመልከት)

## ተግባር 4. የክፍል ውስጥ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. እንቆቅልሽ

- **ቁልፍ ቃላት፡-** እንስሳት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-**መምህር! ህጻናቱን እንቆቅልሽ በመጠየቅ መልሶቻቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ

**እንቆቅልሽ**

1. ሁለት እግሮች እና ሁለት ክንፎች አሉኝ ብዙ ላባዎችም አሉኝ፡፡ ሲነጋ ሲል እጮሀለሁ፣ ሰዎችም ድምጼን ሰምተው መንጋቱን ያውቃሉ.... እኔ ማን ነኝ ? መልስ.... አውራ ዶሮ
2. ሁለት አይኖች፣ አራት እግሮችና ረጅም ጅራት አለኝ፣ለሰው ልጅ ታማኝ ነኝ፣ የማላውቀው ሰው ሲመጣ ው... ው... ው... እያልኩኝ በመጮህ ቤት እጠብቃለሁ እኔ ማነኝ ? መልስ ውሻ
3. አራት እግሮች አሉኝ፣ሰዎች እርሻ ለማረስ ይገለገሉብኛል፣ ለምግበነትም እውላለሁ፣ ስሜ በ "በ" ፊደል ይጀምራል? እኔ ማን ነኝ...... መልስ በሬ
4. ሳር እመገባለሁ ፀጉሬ ለብርድ ልብስ መስሪያ ያገለግላል፣ለምግብነት እውላለሁ፤ እኔ ማን ነኝ?
5. እረጅም እግሮችና አንገት አለኝ፣ ጭነት እጫናለሁ፣ሰዎችንም ከቦታ ቦታ አንጉዛለሁ፣ሞቃታማ

ቦታ ለመኖር ይስማማኛል ... እኔ ማን ነኝ? መልስ:- ግመል

ማስታወሻ፣ መምህር የመማር ብቃቱን የሚያሳኩ ሌሎች እንቆቅልሾችን መጠየቅ ይችላሉ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** እንቆቅልሹን የሚወክሉ ምስሎች
- **የምዘና ስልት:-** ከእንቆቅልሹ የወጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ (ዶሮ ስንት እግር አላት?፣

የበግ ጸጉር ለምን ያገለግላል? እረኛጅም እግርና አንገት ያላት የቤት እንሰሳት ምን ትባላለች?) ምልከታ:- በመዝሙሩ ውስጥ ያሉ የቤት እንሰሳት ስእሎችን የተለያዩ ቀለም እንዳቀልሙ ተግባር በመስጠት በትክክል መስራታቸውን መመልከት

## ተግባር 5፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የአሸዋ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ምስል፣ፊደል፣ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱን ወደ ውጭ ይዘዋቸው ይውጡና የሚከተለውን ጨዋታ እንዲጫወቱ ያድርጓቸው፡፡ የአሸዋ ገበታ ያዘጋጁና በተዘጋጀው የአሸዋ ገበታ ላይ ህጻናቱ በጣታቸው አራት ጎን፣ ክብ፣ ሶስት ጎን ምስሎችን እንዲሰሩ እንዲሁም ፊደል በ፣ሰ እና ሁለት ቁጥርን እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ ስንት ሥዕሎችን እንደሰሩ ለጓደኞቻቸው እንዲነግሯቸው ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** አሸዋ፣ሳህን
- **የምዘና ስልት:-የቃል ጥያቄ:-** የሳሏቸውን ሥዕሎች ስም መጠየቅ፣ ስንት ሥዕሎችን እንደሳሉ መጠየቅ፣ በደብተራቸው ላይ ፊደላትን እንዲጽፉ ማበረታታት፣

## ተግባር 6. በፕሮጀክት መማር (2 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ቀለም መቀባት (2 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:** የቤት ዕቃ፣ ስሜት፣ ጂኦሜትሪ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! በትናንሽ ካርዶች ወይም ወረቀቶች ላይ ህጻናቱ ሊያውቋቸው የሚችሉ የቤት እቃዎችን፣ ሥሜትን የሚገልጹ ምስሎችን (ደስታ፣ ሀዘን፣ ብስጭት)፣ ቀላል የጂኦሜትሪ ምስሎችን መርጠው ይፈለጉትን ይሳሉ፡፡ ምን ያህል እንደሳሉ ቆጥረው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ ህጻናቱ ተግባሩን ሲጨርሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው አሳይተው ማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ያስቀምጡላቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** በነጠብጣብ የተሳሉ የተለያዩ የቤት ቁሳቁስ፣ የግል ስሜትን የሚያሳዩ ምስሎች፣ ቀላል የጂኦሜትሪ ምስሎች
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ:- የሳሉትን የቤት ቁሳቅስ ስም መጠየቅ፣ ቀላል የጂኦሜትሪ ስም መጠየቅ ፣የግል ስሜትን የሚያሳዩ ምስሎችን አይነት መጠየቅ...

# አሥራ ስምንተኛ ሳምንት

የተሰጠውሰዓት......10 ሰዓት　　　　ክፍለ ጊዜ (30)

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማርብቃት

- ቀላል የእለት ተእለት ተግባራትን ያከናውናሉ
- የቀለም አይነቶችን ይናገራሉ
- የቤት እንስሳት ስሞችን ይጠራሉ
- የጫማ ማሰሪያ በማስገባት ያስራሉ
- ቁሳቁስን በቁመታቸው ያወዳድራሉ
- "3" ቁጥርን ደግመው ይጽፋሉ
- ፊደላትን አስመስለው ይጽፋሉ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- መዝሙሮችን በማዳመጥ ይዘምራሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ራስን መቻል
- ቃላት
- እንስሳት
- ትንንሽ ጡንቻዎች መዳበር
- ማወዳደርና በቀደም ተከተላቸው መደርደር
- ፊደላትን መጻፍ
- ማንበብ
- ቁጥሮችን መጻፍቅርሶች

## ተግባር 1፡-የግልተግባር (6 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. "3" ቁጥር መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ መጻፍ፣ ቀለም፣ቀላል ቃላት፣ ማንበብ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! "3" ቁጥርን በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ነጣ አድርገው ይጻፉላቸውና ደጋግመው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡ የተለያዩ ቀለም ስሞችን እንዲናገሩና ቁጥሩንም እንዲቀቡ ያግዟቸው፣ ቀላል ቃላትን ማንበብ እንዲለማመዱም ያድርጓቸው፡፡
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- እርሳስ፣ ክራዮን፣ የቁጥርገበታ፣ የቀለም ቻርት
- የምዘና ስልት፡ ስንት ቁጥርን እንደጻፉ መጠየቅ፣ ተለያዩ የቀለም ስሞችን እንዲናገሩ

ማድረግ፣...ምልከታ፤ ቁጥሩን በትክክል መጻፋቸውን መከታተል፣ የጻፉትን በማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ማሰር...

## ለ. ፊደላትን አስመስለው መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ማንበብ፣ መጻፍ፣ ቃላት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ፊደላትን አስመስለው እንዲጽፉና ገጣጥመው እንዲያነቡ ልዩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ በተጨማሪም በሰበሰ፣ ሰበሰበ፣ ሸሸ የሚሉትን ቃላት እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡ እንዲሁም በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ቁጥር ጽፈው ደጋግመው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ(ማርከር)፣ ወረቀት፣ የፊደልገበታ
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ፤ፊደላት በትክክል መጻፋቸውን መመልከት፣ ቃላቱን ማንበባቸውን መከታተል...፤ የቃል ጥያቄ፤የጻፉት ፊደላት ብዛት ስንት እንደሆኑ መጠየቅ...

## ተግባር 2. ተረት (3 ክፍለ ጊዜ )

## ሀ. ዘሃራ (3 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቀላል፣ የዕለት፣ ተግባራት፣ ቀለም፣ ማዳመጥ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ተረቱን በሥዕል አስደግፈው በሚስብና በሚያጓጓ የንግግር ዘይቤ ይንገሯቸው

### ተረት ተረት!...

ዘሃራ የምትባል የአራት ዓመት ልጅ ስትሆን በቤተሰቦቿ እጅግ ተወዳጅ ልጅ ነበረች፡፡ ዘሃራ ቀላል የዕለት ተዕለት ተግባራትን ታከናውናለች ለምሳሌ፤ ልብሶን በአግበቡ መልበስ፣ ቦርሳዋን ማዘጋጀት፣ ጫማዋን ማሰርያ በማስገባት ማሰር ስራዎችን ትሰራለች፡፡ ዘሀራ ቢጫ፣ የዘሃራ እህት አረንጓዴ ወንድሟ ደግሞ ሰማያዊ ቀለሞችን ይወዳሉ ፡፡ ዘሃራ ቢጫ ቀለምን ከመውደዷ የተነሳ የጸጉር ማበጠሪያዋ፣ የፀጉር ማስያዣዋ፣ የአሻንጉሊቷ ቀሚስ ቢጫ ቀለም ነው ፡፡ በተጨማሪም ብዙ የቀለም አይነት ለምሳሌ፡- ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ሰማያዊ፣ ቢጫ፣ ብርቱካናማ፣ ወይነ ጠጅ የቀለም አይነት ስሞችን መጥራት ትችላለች ፡፡ ዘሀራ በእድሜዋ ልክ ስራዎችን በመስራት ቤሰቦቿን ትረዳለች፡፡ በትምህርቷም ጎበዝና ታታሪ ልጅ በመሆኗ በመምህራኖቿና በቤተሰቦቿ ተወዳጅ ልጅ ነበረች ይባላል ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ማበጠሪያ፣ ቀለም፣ ሥዕል፣ ሞባይል /መቅረጸ ድምጽ
- **የምዘና ስልት፡ የቃል ጥያቄ፤-** ዘሃራ ስንት አመቷ ነው? ምን አይነት ቀለም ትወዳለች? ዘሃራ ምን ምን ስራዎችን መስራት ትችላለች?

## ተግባር 3፡- መዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ሁሌ በጠዋት (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- እንሰሳት፣ ባሕላዊ ቅርሶች
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በመዝሙር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያግዟቸው፡፡

ሁሌ በጠዋት

ሁሌ በጠዋት እነሳለሁ

ቀላል እስፖርት እሰራለሁ

ጡንቻዎቼን ለማጠንከር

ሁሌም ምግብ እበላለሁ

ደመትና ውሻም አለኝ

የምወዳቸው የሚወዱኝ

ጥቁርና ነጩ ሚያምረው ቀላማቸው

በጣም ደስ ብሎኛል የኔ መሆናቸው

ባህላዊ ቅርሶቻችን ዘፈንና ታሪካችን

ልዩ እኮ ናት ለምለሚቷ ሃገራችን

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የእንሰሳት ሥዕል፣ባሕላዊ ቅርሶችን የሚያሳይ ሥዕል፣ የቀለማት ቻርት
- የምዘና ስልት፡- ምልከታ፤ ሲዘምሩ መከታተል...፣የቃል ጥያቄ፤ ከመዝሙሩ የወጡ የምታውቋቸው ባህላዊ ቅርጾች ምን ምን ናቸው? ምን ምን የቀለም አይነቶችን ታውቃላችሁ?

### ለ. እችላለሁ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ጫማ ማሰር፣ ቁጥር፣ መጻፍ፣ፊደላት
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በመዝሙር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህጻናቱ በጋራና በግል እንዲዘምሩ አብረው በመዘመር ያለማምዷቸው፡፡

እችላለሁ

ፊቴን መታጠብ እችላለሁ፣

ጥርሴን መቦረሽ እወዳለሁ፣

ጫማዬን ማሰር እችላለሁ፥

ትምህርት ቤትም እሄዳለሁ፣

ቁጥር መጻፍ ለምጃለሁ።

መዝሙሮችን በማዳመጥ፣

መዘመርም እችላለሁ፣

ቃላትን ማንበብ ተምሬያለሁ።

ወ፣ ዘ፣ ወ፣ ዘ

ሸ፣ ከ፣ ሸ፣ ከ

ደ፣ረ፣ ደ፣ ረ

መ፣ ረ፣ መ፣ ረ

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የጫማ ሞዴል፣ የልብስ ሞዴል፣ መጽሃፍ፣ የቁጥርና የቃላት ካርዶች
- የምዘና ስልት፡- በቡድንና በግል ሲዘምሩ መከታተል፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ ( በቀን ማከናወን የሚችሉትን ቀላል ተግባራት እንዲናገሩ መጠየቅ፣ ምልከታ፡- ጫማቸውን ማሰር እንደሚችሉ መመልከት፣ ቁጥሮችን፣ ፊደላትን መጻፍቸውን መመልከት…)

## ተግባር 4. የክፍል ውስጥ ጫወታ (7ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. እንቆቅልሽ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- እንስሳት፣አትክልት፣ ፍራፍሬ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በጨዋታ
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህጻናቱን የእንቆቅልሹን መልስ በመስጠት እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው

#### እንቆቅልሽ

1. አራት እግሮች አሉኝ የተለያየ መልክ አለኝ? ሳር እግጣለሁ፤ ወተት እለጣለሁ፤ ከቤት እንስሳት እመደባለሁ እኔ ማን ነኝ ?--------- ላም
2. ከአትክልት ውስጥ እመደባለሁ፤ቀለሜ ቀላ ያለ ነው፤ ቁመቴም አጠር ያለ ነው፤ ከመሬት ውስጥ እበቅላለሁ፤ በጥሬም በብስልም እበላለሁ፤ ለአይን ጤንነት እጠቅማሁ እኔ

ማንነኝ..........ካሮት

3. ከፍራፍሬ ውስጥ እመደባለሁ፤ ለጤና ጠቃሚነኝ ቅርፄ ክብነው፤ እኔማን፣ቀለሜ ብርቱናማ ነው፤ እኔ ማን ነኝ?...ብርቱካን፣ፖም

4. ቁጥር ነኝ ከ 2 ቀጥዬ እጠራለሁ፤ ከንደኛዬ 4 በፊት እገኛለሁ እኔ ማን ነኝ? 3/ሦስት/

- **የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የብርቱካን፣የካሮት፣የፖም፣የሀብ ሀብ፣ የላም ስዕሎች
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ፤ ከእንስሳት፣ ከአትክልትና ከፍራፍሬ ውስጥ የሚያውቁትን እንዲዘረዝሩ ይጠይቋቸው

## ለ. ዶቃ መሰካት (3 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት:-** ራስን መቻል፣ ቁጥር፣ የቀለም ስሞች
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና-** መምህር! የተለያዩ ቀለም ያላቸው ዶቃዎችን በማዘጋጀት ምንጣፍ/ መሬት ላይ በማድረግ ህጻናቱ ተራ በተራ “4” የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ዶቃዎች ክር ውስጥ እንዲያስገቡ ያበረታቷቸው። የሰኳቸውን ዶቃዎች ቀለም ስም እንዲናገሩና እንዲቆጥሩ ያበረታቷቸው ። ሁሉም ህጻናት እራሳቸውን ችለው ድርጊቱን እንዲተገብሩ ያድርጉ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ዶቃ፣ ክር፣ ምንጣፍ፣ የቁጥር ካርድ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ:- ስንት ዶቃ ሰካህ/ሽ/? የዶቃዎቹን ቀለም ምን ምን አይነት ነው? ምልከታ:- ዶቃውን በትክክል መሰካታቸውን መመልከት ፤ ዶቃውን የመሰካት ላልቻሉ ህጻናት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ።

## ተግባር 5:-የክፍል ውጭ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. የጋራጨዋታ (2ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት:-** ቁሶች፣ ማወዳደር፣ ቀለም ስም፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! የተለያየ መጠን ያላቸው አጫጭር፣ መካከለኛና ረጃጅም ዘንጎችን ያዘጋጁ። አጫጭሮቹን ቀይ ቀለም፣ መካከለኞቹን አረንጓዴና ረጃጅሞቹን ደግሞ ሰማያዊ ቀለሞች ይቀቧቸው። እንጨቶቹን በመቀላቀል ህጻናቱ እንጨቶቹን በመጠናቸው እንዲደረድሩ በማድረግ አጭር፣ መካከለኛ እና ረጅም እያሉ ያወዳድሩ። ሲጨርሱም ምን ያህል እንደቀቡ ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጓቸው።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተለያዩ መጠን ያላቸው እንጨቶች
- **የምዘና ስልት:-**ምልከታ፤ለምሳሌ /ዘንጎቹን በመጠናቸው በማወዳደር አጭር፣ መካከለኛና ረጅም መለየታቸውን ማረጋገጥ፤ ቃለ መጠይቅ፤ የዘንጎቹ ቀለም ምን አይነት ነው? ፣ የዘንጎቹ ብዛት ብዛት ስንት ነው? ተግባሩን በአግባቡ ማከናወን ላልቻሉ ህጻናት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ

## ተግባር 6፡- በፕሮጀክት መማር (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ጫማ ማሰር (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ጫማ፣ ማሰር፣ ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በፕሮጀክት

የመምህር ሚና፡- መምህር! ህጻናቱ ከዚህ በታች ያለውን ተግባር በየግላቸው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

የአሰራር ቀደም ተከተል

1. ህጻናቱን በምንጣፋቸው ላይ በክብ ማስቀመጥ
2. የተዘጋጀውን ጫማ ማቅረብ
3. በየግላቸው ጫማውን እንዲያስሩ ማበረታታት
4. ማሰር ካቃታቸው ማገዝ
5. ሲጨርሱ የጫማ ማሰርያውን ቀለም በስም እንዲናገሩ ማድረግ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ባለ ማሰሪያ ጫማ (በካርቶን መስራት ይቻላል) ቀይ፣ ቢጫ እና ሰማያዊ)፣ የተለያየ ቀለም ያላቸው ጫማ ማሰሪያዎች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ፣ የቀለሞቹን አይነት መጠየቅ፣ የማሰርያውን ቀለም በስም እንዲጠሩ መጠየቅ፣ ምልከታ፤ ተግባሩን አብረው መጫወት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣ ስራቸውን ፎቶ ማንሳትና ማህደረ ተገባራቸው ውስጥ ፋይል ማድረግ

# አሥራ ዘጠነኛ ሳምንት

የተሰጠው ሰዓት......10 ክፍለ ጊዜ (30 )

## አጥጋቢ የመማር ብቃት

- የፍራፍሬዎችንና የአትክልቶችን ስሞች ይጠራሉ
- ስለ ቀለም ምርጫቸው ይናገራሉ
- የተለያዩ ጂኦሜትሪ ምስሎችን( ክብ፣ሶስትማዕዘን፣አራትማዕዘን) ያቀልማሉ
- ቁሶችን በአንድ ረድፍ (መስመር) ይደረድራሉ
- 4 ቁጥርን አስመስለው ይጽፋሉ
- ፊደላትን ደጋግመው ይጽፋሉ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- አትክልቶችን በመሳል ቀለም ይቀባሉ
- ከ3 -5 የሚደርሱ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን (መተጣጠፍ፣መለጠጥ፣ሚዛንመጠበቅ) ይተገብራሉ
- አካላዊ እንቅስቃሴዎችን (መራመድ፣ መዝለል፣ መንቀሳቀስ) ሙዚቃዊ ምቶችን ጠብቃው ያከናውናሉ
- በአከባያቸው ያሉ ሰዎችን ይለያሉ

## ንዑስይዘቶች

- ማህበራዊ ግንዛቤ
- ራስን መግለጽ
- እጸዋት
- ፊደላትን መጻፍ
- ማንበብ
- ቁጥርንመጻፍ
- ትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር
- ሙዝቃዊ ምት
- መደርደር
- ቅርጽ
- ጥበባዊ ግንዛቤ

## ተግባር 1፦የግል ተግባር (7 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. 4 ቁጥርን መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት፦-** ቁጥር፣ መጻፍ፣ የቀለም ምርጫ፣ ራስን መግለጽ
- **የማስተማርያ ዘዴ፦-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፦-** መምህር! የዕለቱን ተግባር ከመጀመርዎት በፊት ራሳቸውን መግለጽ እንዲለማመዱ አድርጓቸው። በመቀጠል በወረቀት ላይ 4 ቁጥርን ይጻፉላቸው። ቁጥሩን አስመስለው በመደጋገም እንዲጽፉ ያበረታቷቸው። የጻፉትን ቁጥር በሚወዱት ቀለም እንዲያደምቁና የቀለም ምርጫቸውን እንዲናገሩ ያድረጉ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦-** እርሳስ፣ ክራዮን፣ ፍላሽ ካርድ
- **የምዘና ስልት፦-** ምልከታ፤ ራሳቸውን መግለጽ እንደሚችሉ ማረጋገጥ፣ ቁጥሩን በትክክል መጻፋቸውን መከታተል...፣ የቃል ጥያቄ፤ የቀለም ምርጫቸውን እንዲናገሩ መጠየቅ፣ የጻፉትን ቁጥር ቀን ጽፌውበት ማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ማስቀመጥ

### ለ. ፊደላትን ደግሞ መጻፍ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፦-** ፊደላት፣ ማንበብ፣ ማህበራዊ ግንዛቤ
- **የማስተማርያ ዘዴ፦-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፦-** መምህር! ለህጻናቱ የዕለቱን ተግባር ከመጀመርዎት በፊት ስለ ማህበራዊ ግንዛቤ ትንሽ ያስረዷቸው። ፊደላትን ደግመው እንዲጽፉና ገጣጥመው እንዲያነቡ ልዩ እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል። በመቀጠልም በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ሰ፣ሸ፣በ፣ተ በተለያየ መስመር ላይ ጎላ ጎላ አድርገው ይጻፉላቸው። ከዚያም ህጻናቱ ፊደላቱን አስመስለው እንዲጽፉ ያግዟቸው። በመጨረሻም ቀጥሎ ያሉትን ቀላል ቃላት ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ሸሸ፣ በሰለ፣ ሰበሰበ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣ የፊደል ገበታ
- **የምዘና ስልት፦-** በፊደላቱ የተመሰረቱ ቀላል ቃላትን እንዲያነቡ መጠየቅ... ምልከታ፤ ፊደላትን በትክክል መጻፋቸውን መመልከት...ምንባቡን ማንበብ የተቸገሩ ህጻናትን ስማቸውን ለይቶ በመያዝ ምንባቡን እንዲለማመዱ ትኩረት ሰጥቶ መስራት

## ተግባር 2. የክፍል ውስጥ ጨዋታ (8 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. እንቆቅልሽ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፦-** ፊደል፣ ቁጥር፣ የጂኦሜትሪ ቅርጽ
- **የማስተማርያ ዘዴ፦-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፦-** መምህር! ህጻናቱ እንቆቅልሹን በአግባቡ እንዲያዳምጡ እና እንዲመልሱ ያድርጉ። ተጨማሪ የመማር ብቃቱን ያማከለ እንቆቅልሽ ይንገሯቸው።

## እንቆቅልሽ

1. ፊደል ነኝ፣ሁለት እግር አለኝ፣ በእግሮቼ እቆማለሁ በግ እና በር ይጻፍብኛል እኔ ማን ነኝ? ….ፊደል“በ”
2. ቁጥር ነኝ ከ 3 ቁጥር ቀጥዬ እገኛለሁ ከኋላዬ 5 ቁጥር አለች እኔማን ነኝ? ቁጥር “4”
3. በአራት መስመሮች ተገጣጥሜ እሰራለሁ ከጂኦሜትሪ ቅርጽ ውስጥ አንዱ ነኝ እኔማን ነኝ? … ጎነ አራት

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ከእንቆቅልሹ ጋር የሚሄዱ ቁሳቁስ
- የምዘና ስልት፡- ከእንቆቅልሹ የወጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤ ለምሳሌ /”በ” እና “ሰ” እንዲጽፉ መጠየቅ… ምልከታ

## ለ. ውዝዋዜ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ሙዚቃዊ ምት፣ ጥበባዊ ግንዛቤ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በጨዋታ
- የመምህር ሚና፡- መምህር! የዕለቱን ተግባር ከመጀመርዎት በፊት ስለ ጥበባዊ ግንዛቤ ትንሽ ይግለጹላቸው። በመቀጠልም በሚኖሩበት አከባቢ በስፋት የሚታወቅ ባህላዊ ሙዚቃ ወይም ጭፈራ በቴፕ፣ በቴሌቪዥን ወይም በሞባይልዎ ይክፈቱላቸው። በመቀጠል ህጻናቱ ሙዚቃዊ ምቱን ተከትለው እንዲጨፍሩ ያድርጉ። በተጨማሪም ህጻናቱ የሚወዱትን መዝሙር/ ሙዚቃ/ ይጠይቋቸውና ዜማውን ጠብቀው ውዝዋዜ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው።
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ሬድዮ/ቴፕ፣ ቴሌቪዠን፣ ሞባይል
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ፣ የጭፈራውን አይነት መጠየቅ፣ ስለ ጥበባዊ ግንዛቤ ምን ያህል እንደተረዱ መጠየቅ

## ሐ. ቁጥርና ቀለም መለየት (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ፍራፍሬ፣ አትክልት፣ ቁጥር፣ ቀለም
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በጨዋታ
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ሞዴል የፍራፍሬና አትክልት አይነቶችን (ሙዝ፣ ብርቱካን፣ አፕል፣ ካሮት፣…) ከወረቀት ወይም (በፋብሪካ የተሰሩ ሊሆኑ ይችላሉ) ያዘጋጁ። በመቀጠል በተዘጋጁትን ሞዴል ፍራፍሬና አትክልት አይነቶች ላይ ከ1-4 ቁጥሮች ወረቀት ላይ በማርከር ጽፈው ይለጥፉባቸው። ቁጥር የተለጠፋባቸውን ፍራፍሬና አትክልት አይነቶችን በካርቶን ውስጥ ያቀላቅሉና ህጻናቱ ተራ በተራ እየተነሱ ከካርቶኑ ውስጥ እያነሱ ያነሱትን የፍራፍሬ/ የአትክልት ስም፣ የቀለም ምርጫቸውን/አይነት/፣ የተጻፈበት ቁጥር እንዲናገሩ ያድርጓቸው። በትክክል ለመለሱ ህጻናት ያስጨብጭቡላቸው ወይም ሌላ ሽልማት ይስጧቸው።
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ሙዝ፣ብርቱካን፣ አፕል፣ ካሮት ሥዕል /ሞዴል/ ካርቶን፣ የቁጥር ካርድ

- **የምዘና ስልት፡-** ከተግባሩ የወጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ ለምሳሌ/ ከ1-4 የተጻፉ ቁጥሮችን ደበላልቆ በማስቀመጥ እንዲለዩ መጠየቅ፣ የቀለም ምርጫቸውን/አይነት/መጠየቅ፣ የፍራፍሬና የአትክልት አይነቶችን መጠየቅ...

## ተግባር 3 ተረት (3ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. ዳንኤል (3 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት፡-** አካላዊ እንቅስቃሴ፣ የአትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ቀለማት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡** መምህር! ህጻናቱ ተረቱን በአግባቡ እንዲያዳምጡ ያድርጉ፡፡ ተረቱን በሥዕል አስደግፈው ይንገሯቸው፡፡

**ተረት ተረት!...**

ዳንኤል የሚባል ታታሪና ጎበዝ ልጅ ነበር፡፡ ዳንኤል ከእንቅልፉ በጠዋት ሲነሳ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ይሰራል ለምሳሌ፤ /መተጣጠፍ፣ መለጠጥ፣ ሚዛን መጠበቅ.../ የመሳሰሉ ስፖርቶችን ይሰራል ፡ ፡ የቤተሰቦቹን ትዕዛዝም ያከብራል፤ በጎረቤቶቹን ሲያገኛቸው በአክብሮት ሰላምታ ይሰጣቸዋል፡ ፡ ከዕለታት በአንዱ ቀን ምሳውን አትክልትና ፈራፍሬ መብላት ስለፈለገ እናቱን ጠየቃትና እሷም የሚፈልገውን አዘጋጅታ ሰጠችው፡፡ ዳንኤል ቁርሱን በልቶ በጣም ደስ ብሎት ቀዩን ቦርሳ ይዞ ወደ ትምህርት ቤት ሊሄድ ከቤት ሲወጣ ትንሽዋ ነጭ ውሻና ጥቁሩ ድመት ተከተሉት፡፡ ዳንኤልም እኔ ትምህርት ቤት ነው የምሄደው ተመለሱ ብሎ ተሰናብቷቸው ሄደ፡፡ ውሻውና ድመቱም ወደ ቤት ተመለሱ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የድመትና የውሻ ሥዕል፣ የቀለም ፍላሽ ካርድ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ፡- ከተረቱ የወጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ ለምሳሌ/ዳንኤል ትምህርት ቤት ከመሄዱ በፊት ምን ይሰራል እንደነበር መጠየቅ፣ዳንኤል ቦርሳ ምን አይነት ነው፤ዳንኤል ከቤት ሲወጣ የተከተሉት የቤት እንስሣትን መልክ መጠየቅ...

## ተግባር4፡- መዝሙር (8 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. እኔ ልሑል እባላለሁ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊገላት፣ ምርጫ፣ ማንበብ፣ ዕጻዋት፣ መሳል፣ ቁሶች፣ መደርደር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩያለማምዷቸው፡፡

እኔ ልሑል እባላለሁ

ትምህርት መማር እወዳለሁ

የምወደው ቢጫ ቀለም

የማልበላው ምግብ የለም

ፊደላትን አነባለሁ

እጸዋትን እስላለሁ

ቁሶችንም በመደርደር

ማዕዘናትን እሰራለሁ

ቤተሰቤን ለማስደሰት

ሁሌም ጎበዝ እሆናለሁ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቀለም ቻርት፣ፊደላት፣የዕጸዋት ሥዕል፣ቁሶች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ፤ ከመዝሙሩ የወጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ ለምሳሌ / የሚወዱትን ቀለም መጠየቅ፣ምልከታ፤ፊደላትን ከስእል ጋር በማያያዝ እንዲያነቡ ማድረግ ለምሳሌ፡- (ሀ…ሀብል፣ ለ…. ለበሰ፣ መ.. መኪና )፣ቁሶችን ሲደረድሩ መመልከት

## ለ. ፍራፍሬ መመገብ (4ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-**ፍራፍሬ፣ቁስ መደርደር፤ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! እባክዎ ከዚህ በታች ላለው መዝሙር ዜማ በማውጣት ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያለማምዷቸው፡፡

ፍራፍሬመመገብ

ፍራፍሬ መመገብ ጤናማ ያደርጋል፤

ከሁሉም አይነት መብላትያስፈልጋል፤

ጉንፋን እንዳይዘኝ ብርቱካን እበላለሁ፤

ሀይል እንዲሰጠኝ ሙዝ እመገባለሁ፤

ጤናማ ለመሆን እንቀሳቀሳለሁ፡፡

1--2--3--4 ትንሽ እዘላለሁ፤

1--2--3--4ቁጭብድግ እላለሁ፤

ቁስን በመደርደር መስመር እሰራለሁ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያዩ የፍራፍሬ አይነቶች ሥዕል የቁጥር ገበታ፣ ቁሶች
- **የምዘና ስልት፡-** ከመዝሙሩ የወጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣የተለያየ መጠን ያላቸው እቃዎችን በማቅረብ በረድፍ እንዲደረድሩ መጠየቅ፣የፍራፍሬን ጥቅም መጠየቅ፣እየቆጠሩ እንቅስቃሴ እንዲሰሩ መጠየቅ…

## ተግባር 5፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ (4ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. አካላዊ እንቅስቃሴ (4ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** አካላዊ እንቅስቃሴ፣ቁጥር፣ሙዚቃዊ ምት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡**መምህር! ህጻናቱን አሰልፈው ከክፍል ይዘዋቸው ይውጡ፡፡ በመቀጠል በሁለት ወይም በሶስት ረድፍ በቁመታቸው ያሰልፏቸው፡፡ሙዚቃ ይክፈቱላቸውና ሙዚቃዊ ምቱን ጠብቀው እንቅስቃሴውን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ እርስዎ ሁሉም ህጻናት ሊያይዎት የሚችል ቦታ ሆነው እርሰዎን ተከትለው እያንዳንዱን ስፖርታዊ  እንቅስቃሴ አራት አራት እየቆጠሩ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ የእንቅስቃሴውም አይነት ወገብን ወደ ኋላና ወደፊት በመጠኑ ማጠፍ (ህጻናቱ እንዳይወድቁ ይከታተሉ)፣ ወደፊት ማጎንበስና የእግር ጣትን በሁለት እጅ ጣት መንካት፣በአንድ እግር መቆም፣ ወደላይ እጅን ከፍ አድርጎ መለጠጥ፡፡ በመቀጠል በትምህርትቤቱ በሚገኙ የህጻናቱ መጫዎቻ ቁሳቁስ (መሳሪያያያዎች)፣ሸርተቴ፣በጎማ ውስጥ መሹለክ፣ዥዋዥዌ፣ መሰላል መውጣት የመሳሰሉት ስፖርታዊ ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ዥዋዥዌ፣መሰላል፣ሸርተቴ፣ ሞባይል/መቅረጸ ድምጽ....
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ስፖርቱን ሲሰሩ አራት አራት ጊዜ እየቆጠሩ መስራታቸውን መከታተል፣ሙዚቃዊ ምትን ተከትለው መስራታቸውን መከታተል...)

# ሀያኛ ሳምንት

**የተሰጠው ሰዓት……10** **ክፍለ ጊዜ (30)**

## አጥጋቢ የመማርብቃት

- ለሌሎች ያካፍላሉ፣ ይተባበራሉ፣ ሌሎችን ያከብራሉ
- የፊደላት ድምጾችን ይለያሉ
- ቀላል ቃልትን ያነባሉ
- ፊደላትን ደግመው ይጽፋሉ
- 5 ቁጥርን ደግመው ይጽፋሉ
- ስለሰው ሰራሽና ተፈጥሮ አካባቢ ይናገራሉ
- የሰውነት ክፍሎቻቸው ያሉበትን ቦታ ያሳያሉ
- ቁሶችን በአይነታቸው ይለያሉ
- የሰውነት ክፍሎችን ፐዝል ይገጣጥማሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- የድምጽ ግንዛቤ
- የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አከባቢ
- ቁጥሮችን መጻፍ
- ፊደላትን መጻፍ
- ማንበብ
- የቦታግንዛቤ
- መለየትና በአይነታቸው መከፋፈል
- መገናኘት፣ ግንኙነትና መተግበር

## ተግባር 1:-የግልተግባር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ፊደላትንመጻፍ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ፊደላት፣ መጻፍ፣ ቀላል ቃላት፣ ማንበብ፣ የፊደል ድምጽ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተግባር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ቀጥሎ ያሉትን ፊደላት (መ፣ረ፣ተ፣ቸ) በህጻናቱ ደብተር በአንድ መስመር ላይ አንድ ፊደል ጎላ ጎላ ጎላ አድርገው ይጻፉላቸው፡፡ ከዚያም ህጻናቱ የፊደላቱን ድምጽ እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡ ድምፆቹን መለየታቸውን ካረጋገጡ በኋላ አንዱን ፊደል አምስት ጊዜ በመስመሩ ላይ ደጋግመው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡በፊደላቱ ቃል ይመስርቱላቸውና እንዲያነቡ ያበረታቷቸው (መረመረ፣ተረተረ)፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- እርሳስ፣ ደብተር፣ የፊደል ገበታ፣ የፊደል ፍላሽ ካርድ
- የምዘና ስልት፡-ምልከታ፤ ፊደላቱን በትክክል መጻፋቸውን መከታተል፣ እያንዳንዳቸው የጻፏቸውን ቃላት ማንበባቸውን ማረጋገጥ፣ የቃል ጥያቄ፤ እያንዳንዱን ፊደል ስንት ጊዜ እንደጻፉ መጠየቅ።

### ለ. አምስት ቁጥርን መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- መጻፍ፣ ቁጥር፣ ማንበብ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! በወረቀት ላይ 5 ቁጥር ጽፈው ይስጧቸው። በመቀጠልቁጥሩን አስመስለው በመደጋገም እንዲጽፉ ያበረታቷቸው።የጻፉትንም በደንብ እንዲያነቡ ያድርጓቸው የጻፉትን ቁጥር የተሰራበትን ቀን በመጻፍ በመህደረ ተግባራቸው ውስጥ ያስቀምጡ።
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣ 5 ቁጥር የተጻፋባቸው ወረቀቶች
- የምዘና ስልት፣- ምልከታ፡- 5 ቁጥር በአግባቡ መጻፋቸውን ማረጋገጥ፣ ማንበብ መቻላቸውን ማረጋገጥ…፣የቃል ጥያቄ /ለምሳሌ፣የጻፉት ምን እንደሆነ መጠየቅ…።

## ተግባር 2. ተረት (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የቀለማት ውበት (4 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፣ ድምጽ፣ መተባበር፣ ማክበር፣
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተረት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ከዚህ በታች ያለውን ተረት ለህጻናቱ ድምጸን ከፍ በማድረግና በመቀያየር ሳቢ በሆነ አቀራረብ ይንገሯቸው።

## ተረት ተረት!

በድሮ ጊዜ ጓደኞች የሆኑ አምስት ቀለሞች ነበሩ።ቀለማቱ በጣም ይዋደዳሉ። አብረው ይጫወታሉ። ከዕለታት አንድ ቀን ቀይ ቀለም ከሁላችሁም የማምረውና ህጻናት የሚወዱኝ ቆንጆ ቀለም እኔ ነኝ አለ። ሌሎቹ አንተ አይደለህም ቆንጆ እኔነኝ፣እኔነኝ እያሉ መጮህ ጀመሩ ድምጻቸውም አከባቢውን ይረብሽ ነበር።ሰማያዊ ቀለም እዚህ ከምንጣላ ቆንጆ ማን እንደ ሆነ ዱዱን እንጠይቀው አለ።ቀለማቱ በዚህ ተስማምተው ወደ ዱዱ ቤት ሄዱ። ዱዱ በጣም ተደሰተ።ስታምሩ እንኳን ደህና መጣችሁ አላቸው። ቀለማቱም እናመሰግናለን! ዛሬ የመጣነው ቆንጆ ማን እንደሆነ እንድትነግረን ነው አሉት። ዱዱም እኛ ህጻናት የተለያዩ ቀለም አይነቶች እንወዳለን። ቢጫ ኳስ፣ቀይ ኳስ፣ነጭ አሻንጉሊት፣ነጭ መኪና፣ቀይ መኪና፣ አረንጓዴ ዛፍ፣ቢጫ አበባ፣ቀይ አበባ፣ሰማያዊ ሰማይ እንወዳለን ሁላችሁም ቆንጆ ናችሁ።ደግሞ ሰው ሰራሽና ተፈትሮ ቀለሞች ናችሁ ተባብራችሁ እኛ ህጻናትን ማስደሰት አለባችሁ አላቸው።ቀለማቱም ተቃቅፈው ሁላችንም ቆንጆ ነን አሉ።

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-ተረቱን የሚገልጹ ሥዕሎች፣የቀለማት ቻርት

- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ፤ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ የሆኑ ነገሮችንእንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣ ስለ መተባበር፣ ሌሎችን ማክበር ያላቸውን ግንዛቤ መጠየቅ...

## ተግባር 3፡- መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. እኔ ሀረግ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መስጠት፣ መገናኘት፣ ቀለም፣ ፊደላ፣ መጻፍ፣ ቃላት፣ ማንበብ፣
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያግዟቸው።

ሀረግ

እኔ ሀረግ እባላለሁ፤

ነጭ መልበስ እወዳለሁ።

ስመለከት አካባቢን፤

ስወዳቸው ቀለማቱን።

ደስ ይለኛል ለሰው መስጠት ፤

ከልጆች ጋር መገናኘት።

ወተት መሳይ ነጭ ጥርሳችን፤

ቀይኮ ነው ምላሳችን።

ደግሞ ስጽፍ ፊደላትን፤

አነባለሁ ውብ ቃላትን/።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የሰውነት ክፍሎችን የሚሳይ ሥዕል፣ ሰዎች ተባብረው ሲሰሩ የሚያሳይ ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** ከመዝሙሩ የወጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ ለምሳሌ/የሰውነት ክፍሎችን ስም በመጥራት እንዲያሳዩ መጠየቅ፣ የመረዳዳትን ጥቅም መጠየቅ...

### ለ. ኮከቦቹ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍቃላት፡-** ቁጥር፣ ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፣ መጻፍ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያግዟቸው።

ኮከቦቹ

ኮከቦቹን መቁጠር ጀመርኩ
ጥቁሩን ሰማይ ሳየው ወደድኩ
አምስት ኮከብ በአንድ ላይ
ውበታቸው ደምቆ ሲታይ
ጭል ጭል ጭል በሰማዩ ላይ (2)
ተፈጥሮ ነው ወይ ሰው ሰራሽ
አልገባኝም እኔስ ጭራሽ
ግን ሳያቸው ተደነኩኝ
እያንዳንዱን መቁጠር ያዝኩኝ
በደብተሬም እየጻፍኩኝ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ክዋክብትን የሚያሳይ ሥዕል፣ የቁጥር ሎቶ
- **የምዘና ስልት፡-** ከመዝሙሩ የወጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤- ለምሳሌ /ቁጥሮችን የያዙ ካርዶን ለህጻናቱ በማደል የያዙትን ቁጥሮቹን መጠየቅ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ...

## ሐ. እኔስ በጣም ተደነኩኝ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መገጣጠም፣ የሰውነት ክፍል፣ የድምጽ ግንዛቤ፣ ማካፈል
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩያግዟቸው፡

እኔስ በጣም ተደነኩኝ
እኔስ በጣም ተደነኩኝ
ፐዝሎቹን እየገጣጠምኩኝ
እኔ በጣም ጎበዝ ነኝ
የሰውነት ክፍሌን ለይቻለሁ
ያሉበትን እገልጻለሁ
ሁሌም በጣም አነባለሁ
ጓደኞቼን ስወዳቸው
ይሰሙኛል ስጠራቸው
መጫወቻ ስሠጣቸው
ያከብሩኛል ሳከብራቸው

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-የሰውነት ክፍሎችን የሚሳይ ሥዕል፣ ሰዎች ተባብረው ሲሰሩ የሚያሳይ ሥዕል፣ የሰውነት ክፍል ፐዝል
- የምዘና ስልት:-የቃል ጥያቄ:- የሰውነት ክፍሎችን ስም በመጥራት እንዲያሳዩ መጠየቅ፣ የመረዳዳትን ጥቅም መጠየቅ

## ተግባር 4:- የክፍል ውጭ ጨዋታ (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቁሶችን መለየት (6ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- ቁጥር፣ ቁሶች፣ መመደብ፣ የሰውነት ክፍል
- የማስተማርያ ዘዴ:- በጨዋታ
- የመምህር ሚና:- መምህር! ህጻናቱን በአምስት፤በአምስት በቡድን ይመድቡ።የተለያዩ የሰራ ደርሻ ይስጧቸው። ለአንዱ ቡድን  ማርከር፣ የተለያዩ ቀለም የተቀቡ እንጨቶች፣ የተለያዩ ቀለም ያላቸው እስክሪብቶ ቁፎዎችን ያዘጋጁ። በመቀጠል የተዘጋጁትን እስኪብርቶ ቁፎ፣ እንጨቶችና ማርከሮች ካርቶኖች ውስጥ ያስቀምጡና ህጻናቱ አንድ በአንድ እየተነሱ በየአይነታቸው እንዲለዩ ያደርጉ።ለሌላው ቡድን የሰውነት ክፍሎችን ፐዝል ይስጧቸውና ይገጣጥሙ ታድያ ሁሉንም እያቀያየሩ ያሰሯቸው
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- ማርከር፣እስኪብርቶቁፎ፣እንጨቶች፣ፐዝል
- የምዘና ስልት:- ምልከታ፤ጨዋታውን በመከታተል በትክክል የተገበሩና ያልተገበሩ ህጻናትን መለየት፣ የሰውነት ክፍሎችን ፐዝል መገጣጠም መቻላቸውን ማረጋገጥ።

## ተግባር 5  ፕሮጀክት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የሰው ሥዕል መገጣጠም (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:-  ማካፈል፣የሰውነት ክፍሎች፣ቁጥር
- የማስተማሪያ ዘዴ:- በፕሮጀክት
- የመምህር ሚና: መምህር! የዕለቱን ተግባር ከመጀመርዎት በፊት ለሌሎች ማካፈልን፣ መተባበርን፣ ሌሎችን ማክበርን በተመለከተ ግንዛቤ ያስጨብጡዋቸው ይህም በቀጣይ ተግባር በጋራ ለመሰራት ከፍተኛ ጥቅም ይኖረዋል። በመቀጠል ከሶስት እስከ አምስት በሚሆን ቡድን ያስቀምጧቸው። የተቆራረጡ የሰው ምስል፣ ፕላስቲኮች/ ካርቶኖች ለህጻናቱ ሰፋ ባለቦታ ያስቀምጡላቸው። ህጻናቱም በቡድንና በየተራ ምስሉን እንዲገጣጥሙ ያግዟቸው።
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- የተቆራረጡ የሰው ምስል፣ ፕላስቲኮች/ ካርቶኖች
- የምዘና ስልት:- ምልከታ፤ የሰውነት ቅርጽን ምስል ለመስራት ስንት ቁርጥራጮች እንደተጠቀሙ እንዲቆጥሩ ማድረግ፣መገጣጠም መቻላቸውን ማረጋገጥ፣ለሌሎች ማካፈልን፣መተባበርን፣ሌሎችን ማክበርን  መተግበራቸውን መከታተል...።

### ለ. የአሸዋ ላይ ጨዋታ (3ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፣ ቁጥር
- የማስተማርያ ዘዴ:- በፕሮጀክት
- የመምህር ሚና:- መምህር! አሸዋ፣ ካርቶን፣ የተለያዩ መጠን ያላቸው ኩባያዎችን በማዘጋጀት:-

1. አሸዋው ላይ ፊደላትንና፣ቁጥሮችን በእጃቸው እየጻፉ እንዲለማመዱ ያድርጉ
2. አሸዋውን በኩባያ እየሰፈሩ ሌላ ባዶ ካርቶን ውስጥ እንዲገለብጡ ያበረታቷቸው፡፡
3. አሸዋው የተፈጥሮ እንደሆነ የሰፈሩበት ኩባያ እና ካርቶኑ ደግሞ ሰውሰራሽ እንደሆነ ይግለጹላቸው
4. ደጋግመው ያሰሯቸውና ስንት ኩባያ እንደሰፈሩ ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጓቸው
5. ተጫውተው ሲጨርሱ እጃቸውን በሳሙናና በውሃ እንዲታጠቡ ያድርጉ

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- የተለያዩ ቀለምያላቸው ኩባያዎች፣ ካርቶን፣ አሸዋ
- የምዘና ስልት:-የቃል ጥያቄ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮችን በማቅረብ እንዲለዩ መጠየቅ......፡፡

## የአውድ አራት ምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም ------------------------------ጾታ-------- እድሜ ------ደረጃ-------

መግለጫ:- ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሟሉት ብቃት ትይዩ የ "√" ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ፡፡

| ተ.ቁ | የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት | ጥሩ | በ/ጥሩ | እ/በ/ጥሩ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ቀላል ቃላትን ማንበብ | | | | |
| 2 | ስለቀለም ምርጫቸው መናገር | | | | |
| 3 | ከ1-5 ያሉ ቁጥሮችን ይቆጥራሉ፤ አስመስለው መጻፍ | | | | |
| 4 | የአደጋ መንስኤዎችን መለየት | | | | |
| 5 | ፐዝሎችን መገጣጠም | | | | |
| 6 | መካፈል፣ መተባበርና ሌሎችን ማክበር መተግበር | | | | |
| 7 | ከ3-5 የሚደርሱ አካላዊ እንቅስቃሴዎች መስራት | | | | |
| 8 | ነጠብጣብ ፊደላትን ማያያዝ | | | | |
| 9 | የፍራፍሬና የአትክልት ስሞችን መጥራት | | | | |
| 10 | ፊደላትን አስመስለው መጻፍ | | | | |
| 11 | የጅኦሜትሪክ ምስሎችን ቀለም መቀባት | | | | |
| 12 | የአትክልትን ምስሎችን ይስላሉ፤ ቀለም መቀባት | | | | |
| 13 | የጫማ ማሰሪያቸውን ያስራሉ ፤መፍታት | | | | |
| 14 | ሞዴል እቃዎችን መስራት(ለምሳሌ-፡ መኪና) | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፦ ________________________________________________

______________________________________________________________

____________________________

# አውድ አምስት

# ጓደኝነት

አጠቃላይ የተሰጠ ጊዜ- 6 ሳምንት

የክፍለ ጊዜ ብዛት- 180 ክ/ጊዜ

## 5.1 መግቢያ

ህፃናት "ጓደኝነት" በሚለው ዓውድ ውስጥ የተካተቱ አበይት ጭብጦች ህጻናት ስለራሳቸው ማወቅ፣ ራሳቸውን ማስተዋወቅ፤ ጓደኝነት መመስረት፤ የግብረ-ገብ ዕሴቶች፣ የቤት እንስሳትንና በአካባቢ የሚገኙ ዕጸዋትን እንዲሁም ጠቃሚና ጎጂ ሁኔታዎችን መገንዘብ የሚችሉበት ዋና ዋና ጭብጦችን የያዘ ሲሆን ከ21ኛው እስከ 26ኛው ሳምንት ድረስ ከ 6 እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን መቁጠር፣ መጻፍ፣ የመደርደር ክህሎት የሚያዳብሩበትና ፊደላትን መጻፍና ቀላል ቃላቶችን ማንበብ እንዲሁም የአካባቢውን ማህበረሰብ ባህላዊ ውዝዋዜን በመጫወት በዕድሜያቸው ሊያጎለብቱ የሚገባቸው አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ዕድገታቸውን ሊያዳብሩ የሚችሉበት የትምህርት ይዘቶች ተካተዋል፡፡

በስድስቱ ሳምንታት ውስጥ ለመማር ዓውዱ የተቀመጡትን አጥጋቢ የመማር ብቃቶች ለማሳካት የሚረዱ ዝርዝር የአተገባበር ስልቶች የተቀመጡ ሲሆን መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት ላይ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ ለህጻናት የሚያስፈልጉ መጫወቻ ቁሳቁሶች ዝርዝር ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ ስለሆነም መምህራን ቀደም ብለው ዝግጅት በማድረግ በዕለት ተዕለት ተግባር የክትትልና ግምገማ በማድረግ ከመማር ብቃቶች አንጻር ህጻናቱ ምን ያህል ያበቋቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ልዩፍላጎት ያላቸውን ህጻናት እገዛና ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡

## 5.2 የእድገትና የመማር ውጤቶች

ህጻናት በአውዱ ስር የተዘረዘሩ ይዘቶች ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ልዩ ልዩ ጽሁፎችን/የተረት መጽሃፎች በማዳመጥ ምላሽ ይሰጣሉ፤
- የቤት ውስጥና የቤት ውጪ ቁሳቁሶችን ይለያሉ፤
- ፊደላትን ደጋግመው ይጽፋሉ፣
- ቀላል ቃላቶችን ያነባሉ፤
- ከ6 እስከ 9 ድረስ ያሉ ነገሮችን ይቆጥራሉ

- ከ6 እስከ 9 ድረስ ያሉ ቁጥሮችን ደጋግመው ይጽፋሉ፣
- ከ6 እስከ 9 ድረስ ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ይደረድራሉ፤
- ከ2 እስከ 3 የሚታወቁ የምግብና የመጠጥ ዓይነቶችን ይለያሉ፤
- የተወሰኑ የቤት እንስሳቶችን ስም ይጠራሉ፤
- በሸክላ ጭቃ ቅርጻ ቅርጾችን ይሰራሉ፤
- ትህትናን የተላበሰ ባህሪያቶችን ያሳያሉ፣
- የሚወዱትንና የሚጠሉትን ነገሮች ይገልጻሉ፤
- የሰው ፊት ምስል በማየት ደስተኛና ቁጡ ስሜት ይለያሉ፣
- ማህበራዊ ስሜቶችን በምልክት/በአካላዊ እንቅስቃሴ በማየት ይለያሉ፤
- የፕላስቲክ መቀሶችን በመጠቀም ቀጥታ መስመር ጠብቀው ይቆርጣሉ፤
- ለሌሎች ፍቅር ያሳያሉ፤
- ስሜታቸውን በተገቢው ሁኔታ ይገልጻሉ፤
- ጓደኝነት ይመመሰርታሉ ይችላሉ፣
- የጓደኞቻቸውን ስም ይጠራሉ፤
- የባህላዊ ውዝዋዜ/ጭፈራዎችን አስመስለው ይጫወታሉ

## 5.3 የአውዱ አበይት ይዘቶች

- ራስን ማወቅና ማስተዋወቅ
- የጽሁፍና ህትመት ግንዛቤ
- የሰውነት ክፍሎችና አካላዊ እድገት
- ፊደሎችንናቁጥሮችን መጻፍ፣ማንበብ
- ጥበብንና ፈጠራን መግለጽ
- ራስን መቆጣጠር/መግዛት
- ድምጾችን መለየትና አካባቢን መላመድ
- ጤናና የአመጋገብ ዘዴ
- ከሰዎች ጋር የመግባባት ክህሎት
- እንስሳትና እጽዋት
- ቁጥሮችን መደርደርና ማወዳደር
- ማህበራዊ ግንዛቤና ባህላዊ ቅርሶች
- አእምሮአዊ እድገትና የስነ-ምግባር እሴቶች
- የንግግር/የድምጽ ግንዛቤ
- የመግፋትና የመሳብ እንቅስቃሴን ማወዳደር
- እንግዳ ተቀባይነት
- የኢትዮጵያ ገንዘብና መለኪያዎች
- ራስን መጠበቅና ጉዳት መከላከ

# ሀያ አንድኛ ሳምንት

**የተመደበ ክ/ጊዜ ብዛት-30 የተሰጠው ሰዓት- 10 ሰዓት**

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ለሰውነታቸው ጥንቃቄን ያደርጋሉ፤
- ራሳቸውን ለጓደኞቻቸው ያስተዋውቃሉ፤
- አምስቱን የስሜት ህዋሳት ይጠራሉ፤
- ሲያስላቸውና ሲያስነጥሱ አፋቸውን ይሸፍናሉ፤
- የአካባቢያቸውን ባህላዊ ጨዋታ ይጫወታሉ፤
- ስድስት ነገሮችን ይቆጥራሉ፤
- 6 ቁጥርን ይጽፋሉ፣
- እናት ፊደላትን ያነባሉ
- እናት ፊደላትን ደጋግመው ይጽፋሉ፤
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ፤
- የተለያዩ ምስሎችን በማየት ምላሽ ይሰጣሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ራስን ማወቅ
- ራስን ማስተዋወቅ
- የጽሁፍ/ህትመት ግንዛቤ
- የሰውነት ክፍሎች
- ጤና
- ፊደሎችንና ቁጥሮችን መጻፍ
- ፊደሎችን ማንበብና ቁጥሮችን መቁጠር
- ጥበብን መግለጽ

## ተግባር 1- የግል ተግባር (6 /ክ/ጊዜ)

### ሀ. ፊደል “ቀ፣በ፣ሰ፣ተ፣አ”ን ንደግሞ መፃፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል፣ ቃላት፣ ቁሶች
- **የማስተማር ዘዴ ፡-** በተግባር
- **የመምህር ተግባር /ሚና፡-** ውድ መምህር! የዕለቱን ፊደል ከተሰጣቸው ፍላሽ ካርድ ውስጥ መርጠው በመውሰድ ደጋግመው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎ ከፍላሽ ካርዱ ፊደል እየገጣጠሙ ቃላት ይመስርቱ፡፡ የመሰረቱትን ቃል አከባቢያቸው ከሚገኙ ቁሶች መጠሪያ

ፊደል/ ስም ጋር እየፈለጉ ያዛምዱ (ለምሳሌ:-ቀ…ቀለም:-በ….በሬ፣በር ሰ…ሰብል፣ተ…. ተማሪ፣ አ….አበባ…..)

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** እርሳስ፣ ደብተር፣ ወረቀት፣ የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ የተለያዩ ስዕሎች
- **የምዘና ስልት:-** ሲሰሩ መከታተል፣ የቃል ጥያቄ (ፍላሽ ካርድ በማሳየት ይህቺ ፊደል ማናት፣ ከተደረደሩት ፊደላት በመምረጥ ቃላት እንዲመሰርቱ መጠየቅ፣ ስንት ቃላት ጻፍችሁ፣ ስንት ፊደል ፃፋችሁ ….)

### ለ. የስሜት ህዋሳት (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** የስሜት ህዋሳት፣ መቀባት
- **የማስተማር ዘዴ:-** በተግባር
- **የመምህር ተግባ /ሚና:-** ውድ መምህር! ለእያንዳንዱ ህጻን አምስቱን የስሜት ህዋሳት ስዕል በወረቀት ላይ በመሳል ህጻናቱ ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ። የስሜት ህዋሳቱን በስማቸው እንዲጠሩ ያበረታቷቸው። ስንት ስዕሎች እንደቀቡ ቁጥሩን እንዲጽፉ ይጠይቋቸው።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** እርሳስ፣ ወረቀት፣ ደብተር፣ ከለር
- **ምዘና:-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- የስሜት ህዋሳት ስንት ናቸው፣ ከአምስት ቀጥሎ ያለው ቁጥር ስንት ነው)

## ተግባር 2- ተረት (6 ክ/ጊዜ)

### ሀ. አምስቱ ጓደኞች (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** የስሜት ህዋሳት፣ ጓደኝነት፣ ማዕዳት
- **የማስተማሪያ ዘዴ:-** በተረት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ቀጥሎ የቀረበውን ተረት ከተረቱ ጋር የሚሄዱ ምስሎችን በማዘጋጀት ይተርቱላቸው።

## ተረት ተረት!

በድሮ ጊዜ አይን፣ አፍንጫ፣ ጆሮ፣ ምላስ እና እጅ የሚባሉ በጣም የሚዋደዱና የሚከባበሩ አምስት ጓደኛሞች ነበሩ። ከዕለታት አንድ ቀን አፍንጫ ጉንፋን አመመው። ከዚያም እጅን አንተ ነህ በቆሻሻ ነክተኸ ያሳመምከኝ አለው። እጅም በጣም ተናዶ ያሳመምኩህ እኔ ከሆንኩ ከዛሬ ጀምሮ አልነካህም አለው። አፍንጫ ንፍጡን የሚያጸዳለት፣ሶፍት የሚያቀብለው አጣ። ዝንቦች ከበቡት። በጣም ተቸገረ ከእጅ ጋር እንዲያስታርቀት ጓደኞቹን ለመናቸው። አይን ጆሮ እና ምላስ ሁለቱንም መክረው አፍንጫ ይቅርታ ጠይቆ አስታረቋቸው። ከዚያም እንደ ድሯቸው ተባብረውና ተከባብረው ኖሩ ይባላል።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የስሜት ህዋሳት ስዕል
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:- ጓደኞቹ ስንት ናቸው፣ ስማቸውን ዘርዝር/ሪ)

### ለ. አዲስ አበባ (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ጓደኝነት፣ ምግብ፣ ልብስ፣ ጭፈራ፣ የሙዚቃ መሳሪያ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! ተረቱን ድርጊቱን በሚያሳይ አካላዊ ገለጻ በመጠቀም ይተርቱላቸው፡፡ ህጻናቱ መከታተላቸውን ለማረጋገጥ በየመሀሉ ይጠይቋቸው፡፡

## ተረት ተረት

አዲስ አበባ የኢትዮጲያ ዋና ከተማ ነች፡፡ በአዲስ አበባ የሚኖሩ ሰዎች ከተለያዩ የሀገራችን ከተሞች የመጡ ናቸው፡፡ ደስ የሚሉ እና የተለያየ ባህል ያላቸው ናቸው፡፡ የተለያየ ቋንቋ፤ ልብስ፣ ምግብ፣ የሙዚቃ መሳሪያ፣ ጭፈራ አላቸው፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አዲስ አበባ ትልቅ ድግስ ደግሳ ጓደኞቿ የሆኑትን ሌሎች ከተሞች ጋበዘች፡፡ አዲስ አበባ የኢትዮጲያን የባህል አልባሳት ለብሳና አምራ እንግዶቿን ተቀበለች፡፡ ሁሉም ከተሞች ባህላዊ ልብሳቸውን ለብሰው የባህል ምግብ፣ መጠጥ፣ የባህል ጭፈራቸውን ለጓደኞቻው አቀረቡ፡፡ በግብዣው ስለተደሰቱ እንደዚህ ስንተባበር ያምርብናል ሁልጊዜ እየተገናኘን ባህላችንን ማሳደግ አለብን በማለት አዲስ አበባን አመስግነው ወደ አገራቸው ተመለሱ ይባላል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያዩ ከተረቱ ጋር የሚሄዱ ምስሎች፣ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ፣ በሞባይል /በቪዲዮ የተቀረጹ የተለያዩ ባህላዊ አልባሳት
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- በበአል ቀን የሚለብሱትን ልብስ፣ ቤታቸው የሚዘጋጀውን ምግብ እና መጠጥ የመሳሰሉትን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ)

## ተግባር 3- መዝሙር (9 ክ/ጊዜ)

### ሀ. እራሴን አውቄያለሁ (4 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ ፊደል፣ መፃፍ፣ የሚጎዱ፣
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱ በጋራ እና በግል እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡

እራሴን አውቄያለሁ

ፊደል ተሰባስበው ሲፈጥሩ ቃላት

ጥበብ ይሰራሉ ሆነው በአንድነት

ስለራሴ ላውራ ስሙኝ ጓደኞቼ

መጻፍን ችያለሁ ፊደልን ለይቼ

መጻፍን ችያለሁ ቁጥርን ለይቼ

ምስልም አይቼ በደንብ እለያለሁ

የምን እንደሆነ መናገር ችያለሁ

ሰውን የሚጎዱ ነገሮች አውቃለሁ

እራሴን ከነሱ በደንብ ጠብቃለሁ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** መቅረፀ ድምፅ /ሞባይል፣ ስዕሎች
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (አንተ/አንቺ ምን ትቺያለሽ /ትችላለህ፣ መዝሙሩ ውስጥ ያለችው /ያለው ልጅ ምንይችላል/ትችላለች..)

### ለ."ኑ-እንጫወት" (5 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ባህል፣ ጥንቃቄ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በመዝሙር
- **የመምህራን ሚና:-** መምህር! ከህጻናቱ ጋር ይዘምሩ። ከዚያም ህጻናቱ በጋራ እና በግል እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው።

ኑ - እንጫወት

ኑ እንጫወት ጓደኞቼ
ስማችሁን እንዳውቅ አጣርቼ
የባህል ጭፈራ እንጨፍር
እየመታን ከራር
ጉራጊኛ ነው ወይ ትግርኛ
እንጨፍር አፋርኛ
ኦሮምኛ ነው ወይ ሲዳምኛ
ሁሉም ናቸው ሀገርኛ
ስንጨፍር እንጠንቀቅ
ተደናቅፈን እንዳንወድቅ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተለያዩ የጭፈራ አይነቶችን የሚያሳይ (ጉራጊኛ፣ አፋርኛ፣ ሲዳምኛ፣ ኦሮሚኛ፤ ትግሪኛ ወዘተ) ቪዲዮ፣ ፍላሽ ወይም ሲዲ፤ ስፒከር
- **የምዘና ስልት:-** ሁሉም ህጻናት መዝሙሩን ሲዘምሩ መከታተል፣ የሚያውቁትን ባህላዊ ጭፈራ እንዲጨፍሩ መጠየቅ

## ተግባር 4- የውጪ ጫወታ (3 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ማመሳሰልና ማንበብ (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ጨዋታ፣ ቁጥር፣ ፊደል፣ጥንቃቄ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! በተቆራረጠ ክብ/አራት ማዕዘን/ሶስት ጎን ቅርጽ ላይ ከለር ወረቀት በመለጠፍ 1 ቁጥር እና ከዚህ በፊት ከተዋወቁት ፊደል አንድ፣ 2 ቁጥር እና

ፊደል ሁለት 3 ቁጥር እና ፊደል ሶስት፣ 4 ቁጥር እና ፊደል አራት፣ 5 ቁጥር እና ፊደል አምስት፣ 6 ቁጥር እና ፊደል ስድስት) ጎላ ብሎ በሚታይ መልኩ በሁለት ኮፒ በማዘጋጀት አንዱን ለዕጣ በሚሆን መልኩ በሳጥን /በሰሃን መያዝ። ሁለተኛውን ያለበትን ከጨዋታ መነሻ አምስት ሜትር እርቀት ላይ ጠረጴዛ ላይ መደርደር። ህጻናቱ በየተራ እጣ በማንሳት በፍጥነት ወደ ጠረጴዛው በመሄድ ከያዙት ቁጥር እና ፊደል ጋር ተመሳሳይ የሆነውን ይዘው በመመለስ የያዙትን ቁጥር እና ፊደል ይናገራሉ (ለምሳሌ 3 ቁጥር እና ፊደል ሸ):: በሚሮጡበት ጊዜ በጥንቃቄ መሮጥ እንዳለባቸው ይንገሯቸው። ሁሉንም ተግባር በአግባቡ ያከናወኑ የጨዋታው አሸናፊ ናቸው

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁሶች-** ቁጥር እና ፊደል የተፃፈበት ፍላሽ ካርድ፣ ጠረጴዛ፣ ሳጥን /ሳህን
- **የምዘና ስልት፡-** በምልከታ (ተግባራቱን ሲያከናውኑ ህግ መከተላቸውን ቁጥር እና ፊደሉን በትክክል መጥራታቸውን፣ አመሳስለው ማምጣታቸውን፣ በጥንቃቄ መጫወታቸውን ...) የቃል ጥይቁ (ከፊደል ሰ ጋር ያለው ቁጥር ስንት ነው፣ ከስድስት ቁጥር ጋር ያለው ፊደል ማነው...)

## ተግባር 5- የፕሮጀክት ስራ (3 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ከጭቃ ቁጥርን በመስራት መደርደር (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ ጤና
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በፕሮጀክት
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! ሁሉም ህጻናት የአሰራር ቅደም ተከተሉን ጠብቀው ከ1-6 ቁጥሮችን ከጭቃ እንዲሰሩ ያግዟቸው። የፕሮጀክቱን ስራ ካጠናቀቁ በኋላ እጃቸውን በውኃና በሳሙና እንዲታጠቡ ያድርጉ።

   የአሰራሩ ሂደት

   1. የሚሰሩበትን ቦታ ማመቻቸት
   2. ህጻናቱ ከሰው ሰራሽ/ከተፈጥሮ ጭቃ በማቡካት እንዴት መስራት እንዳለባቸው ያሳዩአቸው
   3. በመቀጠል ህጻናቱ ከ1-6 የፈለጉትን ቁጥር መርጠው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው
   4. የሰሩትን ቁጥር ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ያድርጉ
   5. ስራውን ከጨረሱ በኋላ ከ1-6 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል እንዲደረድሩ ያድርጉ
   6. በመጨረሻም በተገቢው ሁኔታ እጃቸውን እንዲታጠቡ ያድርጉ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ሰሀን፣ ጭቃ (የተፈጥሮ/ሰው ሰራሽ)
- **የምዘና ስልት፡-** ስንት ቁጥር እንደሰሩ መጠየቅ፣ ስራ ከሰሩ በኋላ እጃቸውን የመታጠብ ጥቅም መጠየቅ

# ሀያ ሁለተኛ ሳምንት

## የተመደበ ክ/ጊዜ ብዛት-30 10 ሰዓት

### የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ስሜታቸውን በአግባቡ ይገልጻሉ
- የተለያዩ ድምጾችን ያስመስላሉ
- የቤት ውስጥ እና የውጭ ቁሳቁሶችን ይለያሉ
- ለጤና ጠቃሚ የሆኑ የተለመዱ ምግቦችን ይለያሉ
- ከ1-7 ቁጥር በመቁጠር እንደገና ይጽፋሉ
- የተሰጧቸውን ፊደላት እንደገና ይጽፋሉ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- ቅርጻ ቅርጾችን በሸክላ ይሰራ

### ንዑስ ይዘቶች

- ራስን መቆጣጠር
- ድምጽ መለየት
- ቅርብ አካባቢ
- የተመጣጠነ ምግብ
- ቁጥር መጻፍ
- ሆሄያትን መጻፍ
- ማንበብ
- በፈጠራ መግለጽ

## ተግባር 1- የግል ተግባር (6 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ቁጥር ከ1-7 ያሉ ቁጥሮችን መፃፍ (2 ክፍለ ግዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ ጽሁፍ፣
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ከ 1-7 ቁጥር መጻፍ በመጀመሪያ በአየር ላይ ከተለማመዱ በኋላ በመለማመጃ ደብተራቸውን ላይ ይጻፉ፡፡ እንዲለማመዱ የእርሳስ አያያዝ እና አጻጻፍ ላይ ያግዟቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣ የቁጥር ፍላሽ ካርድ
- **የምዘና ስልት፡-** ህጻናቱ የተሰጣቸውን ቁጥር እንደገና መጻፋቸውን ማረጋገጥ፣ ከ1እስከ 7 ያሉ ቁጥሮችን መለየታቸውን ማረጋገጥ

## ለ. ፊደል “ወ፣ አ፣ ደ” ን መጻፍ (2 ክፍለ ግዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ ቃላት፣ ጽሁፍ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህሩ ሚና፡- መምህር! ህጻናቱ የመለማመጃ ደብተራቸውን እንዲያወጡ እና የተሰጣቸውን “ወ፣ ፀ፣ የ እና ደ” ን እንደገና እንዲጽፉ በማገዝ የጹሁፍ ልምምድ እንዲያደርጉና በፊደላቱ ቀላል ቃላትን ከስእል ጋር በማዛመድ እንዲያነቡ ለምሳሌ፡- ( ወ... ወፍ፣ ፀ...ፀሀይ ፣ ደ... ደብተር....) የፊደላትን ድምጽ ለይተው እንዲያውቁ ያግዟቸው።
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ፣ ወረቀት
- የምዘና ስልት፡- ህጻናቱ የተሰጣቸውን ፊደል እንደገና መጻፋቸውን ማረጋገጥ፣ ቀላል ቃላትን እንዲያነቡ መጠየቅ

## ሐ. ስሜት መግለጽ (1 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍቃላት፡- ስሜት፣ ሳቅ፣ ለቅሶ፣ ጩህት
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! የተለያዩ ድምጾችን ለጓደኞቻቸው እንዲያሰሙ ያድርጉ። (ሳቅ፣ ለቅሶ፣ ጩህት) በመቀጠልም ለእያንዳንዱ ህጻን ነጭ ወረቀት ያድሉ። የተለያዩ ስሜቶችን የሚያሳዩ ስዕሎችን እንዲስሉ ያበረታቷቸው። ስሜታቸውን ለመግለጽ እንዲረዳቸው የፈለጉትን እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው።
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ነጭ ወረቀት፣ ክራዮን፣ እርሳስ፣ ስሜት ገላጭ የሆኑ ስዕሎች የያዘ ካርድ
- የምዘና ስልት፡- የተለያዩ ስሜቶችን የሚወክሉ ስዕሎችን በማሳየት ስሜቶቹን እንዲገለጹ ማድረግ፣ የሳሉትን ስዕል ምንነት በመጠየቅ ማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ማሰር።

## መ. ስሜት መገመት (1 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ስሜት፣ ቃላት፣ ድምጽ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! እያንዳንዱ ህጻን ከተዘጋጁት የተለያዩ ስሜቶችን የሚወክሉ የስዕል ካርዶች ውስጥ አንዱን ወስደው ድምጽ ሳያሰሙ ስሜቱን እንዲያሳዩ ያድርጉ። ሌሎቹ ህጻናት ደግሞ ስሜቱን ይገምቱ።በመቀጠልም ቀላል ቃላቶችን እንዲያነቡ ያበረታቷቸው



ደስታ



ንዴት



ሀዘን

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተለያዩ ስሜቶችን የሚያሳዩ ካርዶች
- **የምዘና ስልት:-** የተለያዩ ስሜቶችን ያለድምጽ እንዲያሳዩና ስሜቶቹን እንዲናገሩ መጠየቅ

## ተግባር 2- ተረት (6 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ሰባት ትናንሽ ዳክዬዎች (6 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ቁጥር፣ ምግብ፣ አካባቢ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተረት
- **የመምህሩ ሚና:-** መምህር! ቀጥሎ የቀረበውን ተረት ከተረቱ ጋር የሚሄዱ ምስሎችን በመጠቀም ይንገሯቸው::

### ተረት ተረት!

በአንድ ኩሬ አጠገብ ከእናታቸው ጋር የሚኖሩ ሰባት ትናንሽ ዳክዬዎች ነበሩ:: ከዕለታት በአንዱ ቀን ዳክዬዎቹ ወደ ኩሬው ሄዱ:: በደስታ እየፈነደቁ በውሃ ውስጥ ተራጩ:: አንዷ ትንሽ ዳክዬ በቅርብ አካባቢ የሚያብረቀርቁ ቆንጆ ጠጠሮች አገኘች:: ሰባቱ ትናንሽ ዳክዬዎች ደስተኛ ሆነው ወደ ቤታቸው ተመለሱ:: ትንሸዋ ዳክዬ ያገኘቻቸውን የሚያበረቀርቁ ጠጠሮች ለእናታቸው አሳየች:: እናታቸውም ውይ! ሲያምሩ! እስቲ ማነው የሚቆጥርልኝ ስትላቸው ሁሉም ተራ በተራ እየቆጠሩ ጠጠሮቹ ሰባት መሆናቸውን አረጋገጡ:: ከዚያም እናታቸው በመደሰት ዛሬ ሽልማታችሁ የሚሆነው ሽክላ እያቦካን ቅርጻ ቅርጾችን መስራት ይሆናል በማለት እንዲያቦኩና ቅርጻ ቅርጾችን እንዲሰሩ አገዟቸው:: ሰርተው ሲጨርሱ በጣም ተደስተው የሰሩትን ቅርጻ ቅርጾች ለሌሎች ጓደኞቻቸው አሳዩ:: እናታቸውም በጣም ደስ ስላላት ጣፋጭ ምግብ ሰርታ ሰጠቻቸው ይባላል::

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተረት መጻሐፍ፣7 ዳክዬዎች ስዕል፣ የተለያዩ የተመጣጠነ ምግብ ቻርት
- **የምዘና ስልት:-** ተረቱን መልሰው እንዲናገሩ ማበረታታት፣ በወንዙ ዳር የሚኖሩት ዳክዬዎች ስንት ኛቸው፣ ጠጠሮችና ሌሎች ነገሮችን በማቅረብ እንዲቆጥሩ መጠየቅ

## ተግባር 3- መዝሙር (7 ክ/ጊዜ)

### ሀ. እኔ በጣም ደስተኛ ነኝ (4 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ምግብ፣ደስታ፣ፊደል፣ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በመዝሙር
- **የመምህሩ ሚና:-** መምህር! ህፃናቱ በጋራ እና በግል እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው::

እኔ በጣም ደስተኛ ነኝ

እኔ በጣም ደስተኛ ነኝ

ምመገበው ተመጣጣኝ
ምወዳቸው እህቶቼ
ማከብራቸው ወንድሞቼ
ሁሌ ተረት ያወራሉ
ፊደላትን ይጽፋሉ
ስንጫወት ደግሞ አብረን
ተደስተን ተሳስቀን
ሳናስበው ከተጣላን
ቶሎ ይቅር እንላለን
ቁጥር መቁጠር ደስ ይለናል
ጎበዝ እንድሆን ያደርገናል

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመዝሙር ቅጂ የያዘ ተንቀሳቃሽ ስልክ
- **የምዘና ስልት፡-** ህጻናቱ መዝሙሩን በግል እንዲዘምሩ ማድረግ፣ የምግብን ጥቅም እንዲናገሩ መጠየቅ፣ የሚወዱትን ምግብ መጠየቅ

## ለ. ድምጽ (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ድምጽ፣ የቤት ቁሳቁስ፣ ጓደኝነት፣ ፈጠራ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህሩ ሚና፡-** መምህር! መጀመሪያ ከህጻናቱ ጋር በመዘመር በመቀጠል ህጻናቱ በጋራና በግል እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

### ድምጽ

ከውጭ ድምጽ ሰምቻለው
የሌላ አይደለም የእናቴ ነው
እሷ ሳትኖር ይከፋኛል
ሳገኛትም ደስ ይለኛል
ጓደኞቼ ሰፈር ያሉት
ይጠሩኛል ለመጫወት
ደስ ይሚል ነው ጓደኝነት
የቤት እቃ እንሰራለን
ፈጠራንም እንፈጥራለን
የቤት ስራም እንሰራለን

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመዝሙር ቅጂ የያዘ ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ የቤት ቁሳቁስ
- **የምዘና ስልት፡-** ህጻናቱ በየግል እንዲዘምሩ በማድረግ መመልከት፣ በመዝሙሩ ውስጥ ያሉ ስሜቶችን መጠየቅ፣ የሚያውቁትን የቤት ቁሳቁስ እንዲዘረዝሩ መጠየቅ

# ተግባር 4- የክፍል ውጪ ጨዋታ (4 ክ/ጊዜ)

## ሀ. ሥዕል ማንበብ (2 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** የተመጣጠነ፣ ምግብ፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁስ፣ የውጭ ቁሳቁስ፣ ቁጥር፣ ፊደል፣ ቃላት
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህሩ ሚና:-** መምህር! ህጻናቱን ከክፍል ውጪ በማስወጣት ከታች ባለው ቅደም ተከተል መሰረት ያጫውቷቸው፡፡ህጻናቱን በሁለት ምድብ በመክፈል ሰባት ህጻናት አንድ ትልቅ ክብ እና በውስጡ ደግሞ አራት ህጻናት ትንሽ ክብ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ በትንሹ ክብ ውስጥ ስድስት የተለያዩ ካርዶችን ማለትም ( የተመጣጠነ ምግቦችን የሚገልጹ ስዕሎች፣ የቤት ውስጥ እና የውጭ ቁሳቁሶች፣ ከ1-7 ቁጥር የተጻፈባቸው ካርዶች፣ ፊደል ካርዶች፣ ከዚህ በፊት በተማሩት ፊደላት የተመሰረቱ ቃለት የያዙ ስዕሎች) በመሬት ላይ ራቅ ራቅ አድርገው በክብ ያስቀምጡ ትንሹ ክብ ዱብ ዱብ እያሉ ሲዞሩ፣ ትልቁ ክብ በማጨብጨብ አረንጓዴ አረንጓዴ እንዲሉ ማድረግ፡፡ ህፃናቱ ትንሽ እንደሮጡ እርሶ ድምጽዎትን ከፍ በማድረግ ቀይ ሲሉ 7ቱ ህፃናት መሬት ላይ ከተቀመጡት ካርዶች አንድ አንድ እንዲያነሱ ማድረግ
  1. እያንዳንዱ ህፃን የያዘውን ካርድ ከፍ በማድረግ ስሙን ወይም ተግባሩን ተራ በተራ እንዲገልፅ ማድረግ፡፡
  2. ይህንን ተግባር ሁሉንም ህጻናት በማሳተፍ ቦታቸውን በመቀያየር ጨዋታውን እንዲጫወቱ ማድረግ
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተመጣጠነ ምግቦችን የሚገልጹ ስዕሎች፣ የቤት ውስጥ እና የውጭ ቁሳቁሶች፣ ከ1-7 የቁጥር የተጻፈባቸው ካርዶች፣ ፊደል ካርዶች፣ ከዚህ በፊት በተማሩት ፊደላት የተመሰረቱ ቃለት የያዙ ስዕሎች
- **የምዘና ዘዴ:-** ህፃናቱ የያዙትን ስዕል ምንነት፣ የስዕሉን ብዛት መጠየቅ

## ለ. የልየታ ጨዋታ (2 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ቤት ውስጥቁሳቁስ፣ የውጪ ቁሳቁስ፣ ምግቦች፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱን ከክፍል ውጪ በማስወጣት ሰባት ቡድኖችን ይመስርቱ፡ ፡ ቡድኑ ውስጥ ያሉትን በየተራ ተግባራቱን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም በ"ቤት ውስጥ" እና "ውጪ" ቁሳቁስ፣ የተመጣጠኑ ምግቦች፣ ከ1-7 ቁጥር፣ የሚወክል ምልክት የተደረገባቸው ሶስት ቅርጫቶች ያዘጋጁ፡፡ ከዚያም የተለያዩ እቃዎች ወይም የእቃዎች ስዕሎች ለልጆቹ ይስጡ እና በትክክለኛው ቅርጫት ውስጥ እንዲያስቀምጡ ይንገሯቸው፡፡ ሲጨርሱ እጃቸውን በውሃና ሳሙና ይታጠቡ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ኳስ፣ ቅጠል፣ መጽሐፍ፣ አበባ፣ ወንበሮች፣ አሻንጉሊቶች፣ ድንጋዮች፣ እንጨቶች፣ ሣር፣ የተመጣጠኑ ምግቦች ስዕል፣ ከ1-7 ቁጥር የተጻፉባቸው ካርዶች፣ ሶስት ቅርጫቶች
- **የምዘና ስልት:-** የተለያዩ እቃዎችን በማቅረብ "ቤት ውስጥ" እና "ውጪ" ቁሳቁስ በማለት እንዲለዩ መጠየቅ

## ተግባር 5- የፕሮጀክት ስራ (3 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ከጭቃ የቤት ውስጥ እና የውጪ ቁሳቁስ መስራት (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** የቤት ውስጥ ቁሳቁስ፣የውጪ ቁሳቁስ፣ ምግቦች
- **የማስተማርያ ዘዴ:-**በፕሮጀክት
- **የመምህሩ ሚና:-** መምህር! ሁሉም ህጻናት እንዲሳተፉና ቅደም ተከተሉን ጠብቀው እንዲሰሩ ያድርጉ።

የአሰራር ቅደም ተከተል:-

1. የሚሰሩበትን ቦታ ያዘጋጁ
2. ህጻናቱ በጭቃ የሚሰሩትን የቤት ውስጥ እና ውጪ ቁሳቁስ፣ ምግቦች ከሰው ሰራሽ/ ከተፈጥሮ ጭቃ በማቡካት እንዴት መስራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው
3. ህጻናቱ የቤት ውስጥ እና ውጪ ቁሳቁስ፣ ምግቦች እንዲሰሩ ያድርጓቸው።
4. የሰሩትን የቤት ውስጥ እና ውጪ ቁሳቁስ፣ ምግቦች ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ያድርጉ
5. የሰሩትን ቁሳቁስ በተገቢው ቦታ እንዲያስቀምጡ ያድርጉ። በመጨረሻም በተገቢው ሁኔታ እጃቸውን እንዲታጠቡ ያድርጉ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ሰሀን፣ ጭቃ (የተፈጥሮ/ሰው ሰራሽ)
- **የምዘና ስልት:-** የሰሩትን ቆጥረው እንዲናገሩ መጠየቅ፣ ስራ ከሰሩ በኋላ እጃቸውን የመታጠብ ጥቅም መጠየቅ

## ተግባር 6- የክፍል ውስጥ ጨዋታ (4 ክ/ጊዜ)

### ሀ. መስሎ ጨዋታ (4 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** የቤት ውስጥ ቁሳቁስ፣ የውጪ ቁሳቁስ፣ ምግቦች፣ ቅርፃ ቅርጾች
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ የሚሰጣቸውን የስራ ድርሻ እንዲወጡ ከታች የተዘረዘሩትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው።

1. የቤት ውስጥ እና ውጪ ቁሳቁስ፣ ምግቦች ቅርፃ ቅርጾች እና የብር ኖቶች ማዘጋጀት
2. ህጻናቱን በቡድን መመደብ እና ሀላፊነትን በፍላጎታቸው እንዲከፋፈሉ ማድረግ (ገዢ፣ ሻጭ)

3. ተግባራቱን እንዲያከናውኑ ማበረታታት
4. ተግባራቱን ያከናወኑበትን እቃዎች ወደ ነበሩበት እንዲመልሱ ማድረግ፡፡
5. ከተጫወቱ በኋላ ውሃና ሳሙና ተጠቅመው እጃቸውን በአግባቡ እንዲታጠቡ ያድርጉ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቤት ውስጥ እና ውጪ ቁሳቁስ፣ ምግቦች፣ ቅርፃ ቅርጾች፣ የብር ኖቶች፣ውሃ፣ ሳሙና
- **የምዘና ስልት፡** ምን ምን ገፀ- ባህሪ ተላብሰው እንደተጫወቱ፣ የቤት ውስጥ እና ውጪ ቁሳቁስ እንዲዘረዝሩ መጠየቅ

# ሀያ ሶስተኛ ሳምንት

## የተመደበ ክ/ጊዜ ብዛት-30 10 ሰዓት

### የሳምንቱ አጥጋቢ ብቃቶች

- ከሌሎች ጋር ጓደኝነትን ይፈጥራሉ
- ለሌሎች ፍቅርን ያሳያሉ
- ቤተሰቦቻቸውን እና ሌሎችን ያከብራሉ
- መቀስ በመጠቀም ቀጥ ባለመስመር ይቆርጣሉ
- የእንስሳት ዓይነቶችን ይለያሉ
- የቤት እንስሳትን እንቅስቃሴ አስመስለው ይሄዳሉ
- 8 ቁጥርን ይጽፋሉ
- ፊደላትን ይጻፍሉ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን በቀደም ተከተል ያስቀምጣሉ
- ባህላዊ ዳንሶችን አስመስለው ይደንሳሉ
- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ይለያሉ

ንዑስ ይዘቶች

- ከሌሎች ጋር መገናኘት
- ድምጾችን ይለያሉ
- እንሰሳት
- የትንንሽ ጡንቻዎች መዳበር
- ፊደላትን መጻፍ
- ማንበብ
- ቁጥሮችን መጻፍ
- ቁጥሮችን ማወዳደርና በቀደም ተከተል ማስቀመጥ
- የባህል ቅርጾች

## ተግባር 1- የግል ተግባር (8 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ቁጥር መጻፍ (4 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍቃላት:-** ቅደም ተከተል፣ቁጥር፣መጻፍ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተግባር

- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ከ1-9 ቁጥር የተጻፉባቸው የቁጥር ካርድ፣ እርሳስ እና ወረቀት/ ደብተር ያዘጋጁ፡፡ ቀጥሎ ቁጥሮቹን በቅደም ተከተል በጠረጴዛቸው ላይ ይደርድሩ፡፡ ከተደረደሩት ቁጥሮች ውስጥ ስምንት ቁጥርን በወረቀት/ ደብተር / ላይ ስምንት ጊዜ ደጋግመው ይፃፉ፡፡ ሲጨርሱ የፃፉት ቁጥር ስንት እንደሆነ፣ ስንት ጊዜ እንደፃፉ እና የቁጥሩን ቅደም ተከተል መጠበቃቸውን ያረጋግጡ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቁጥር ካርድ፣እርሳስ፣ወረቀት /ደብተር
- **የምዘና ስልት፡-** ከ1 እስከ 8 ያሉ ቁጥሮችን አዘበራርቆ በመስጠት በቅደም ተከተል እንዲፅፉ ማድረግ

### ለ. ጀ፣ገ፣ጠ፣ጨ ፊደላትን መጻፍ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል፣ መፃፍ፣ቃላት፣ ማንበብ፣ መቁጠር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱ የእናት ፊደላት፣ የፊደል ሳጥን እና ወረቀት /ደብተር / ያዘጋጁላቸው፡፡ ከሳጥኑ ውስጥ ‹ጠ› እና ‹ጨ› ፊደልን በማውጣት 4 ጊዜ ደጋግመው ይፃፉ፡፡ በመቀጠል ጀ፣ገ፣ጠ፣ጨ ፊደላትን መነሻ አድርገው ከስእል ጋር በማጣመር ቀላል ቃላትን ይመስርቱ (ለምሳሌ፡- ጀ..ጀበና፣ ገ…ገበሬ…ጠ….ጠጠር…ጨ….ጨረቃ)፡፡ በመጨረሻ የፃፉትን ፊደል ስም፣ ስንት ጊዜ እንደፃፉት፣ ስንት ቃላት እንደፃፉ ከዘረዘሩ በኂላ የተጠቀሙበትን ቁሰቁሶች በቦታቸው ይመልሱ፡፡ በመጨረሻ የፃፉትን ፊደል ስም፣ ስንት ጊዜ እንደፃፉት፣ ስንት ቃላት እንደፃፉ ከዘረዘሩ በኂላ የተጠቀሙበትን ቁሰቁሶች በቦታቸው ይመልሱ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የፊደል ሳጥን፣እርሳስ፣ወረቀት /ደብተር /
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ፣ ስንት ቃላት እንደ ጻፉ፤የጻፉትን ቃላት እንዲያነቡ መጠየቅ

## ተግባር 2- መዝሙር (8 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ስንገናኝ (4 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ጓደኝነት፣ጭፈራ፣ ከበሮ፣ክራር፣ማሲንቆ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡ መምህር!** ሁሉም ህጻናት እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡

ስንገናኝ

ስንገናኝ በፈገግታ ተጀመረ ሳቅ ጨዋታ

እንደንስ እንጨፍር ደግሞ በሙዚቃ

እየመታን ክራር እንበል ነቃ ነቃ

ክራሩ ታ ታ ታ በጣቴ ስመታ

መሰንቆ ዝ ዝ ዝ ድም ድም ከበሮ

ምታቸውም ያምራል ሲቀናጁ አብሮ

ምታቸው ሲዋሃድ እንደኛ ፍቅር

በጣም እናምራለን አብረን ስንጨፍር

ውድ ጓደኞቼ እወዳችኋለሁ

ከእናንተ ጋር ስሆን ሁሌ እደሰታለሁ

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- ክራር፣ማሲንቆ፣ከበሮ
- የምዘና ስልት:- የሚያውቁትን ጭፈራ እንዲያሳዩ መጠየቅ፣ የባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያ ድምፆች እንዲያሰሙ መጠየቅ

## ለ. የቤት እንስሳት (4 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- እንስሳት፣ እምቧ፣ኩኩሉ፣
- የማስተማርያ ዘዴ:- በመዝሙር
- የመምህር ሚና:- መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያድርጉ።

የቤት እንስሳት

ሶስት ላሞች አሉን፤ወተት የሚሰጡን

ሲሉ እምቧ እምቧ፤እኔም ሆዴ ባባ

አራት ዶሮች አሉን፤እንቁላል ሚሰጡን

ሲሉ ኩኩሉሉ፤ነጋ ብድግ በሉ

አንድ ውሻ አለን ሌባ የሚጠብቅ

ሌቦችና አውሬ ከሰፈር የሚያርቅ

የቤት እንስሳቶች በጣም ደስ ይላሉ

አብረውን ከኛ ጋር በጋራ ይኖራሉ።

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- የእንስሳት ስዕል /ፎቶ/፣የተቀረጸ የእንስሳት ድምፅ
- የምዘና ስልት:- ምልከታ፣ የቃል ጥያቄ ( በመዝሙሩ ውስጥ ስንት እንስሳት አሉ፣ የውሻ ድምጽ አሰማ/ሚ፣የላም ድምፅ አሰማ/ሚ...)

# ተግባር 3- ተረት (4 ክ/ጊዜ)

## ሀ. ጉብኝት (4 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- አክብሮት፣ የእንስሳት ድምጽ፣ የእንስሳት አካሄድ
- የማስተማርያ ዘዴ:- በተረት

- የመምህር ሚና፡- መምህር! የህጻናትን ስሜት በሚስብ አተራረክና ድርጊቱን በሚገልጽ የፊት ገጽታ ተረቱን ይንገሯቸው

## ተረት ተረት

ከዕለታት በአንዱ ቀን ትምህርት ቤት ሲዘጋ እኔና ቤተሰቦቼ ገጠር ዘመዶቻችን ለመጠየቅ ሄድን፡ ፡ድምፃችንን የሰሙት አያቴ እና አክስቴ በደስታ ተቀበሉን፡፡ እርጎ በቂጣ ተመገብን፡፡ እንዴት እንደሚጣፍጥ ልነግራቹ አልችልም፡፡እቤት ውስጥ ከአያቴ ጋር የሚኖሩት አጎቶቼ ከብቶቹን ለግጦሽ ወደ መስክ  ወስደዋቸው ስለነበር እቤት አልነበሩም፡፡ አጎቶቼ ከብቶቹን ይዘው መጡ የአያታችን ጉልበት ስመው ታላላቆቻቸውን እጅ ነስተው ተቀመጡ፡፡ እኔም ለአጎቶቼ የአክብሮት ሰላምታ ሰጥቼ እንስሳቶቹ ወደ ሚያድሩበት በመሄድ መቁጠር ጀመርኩኝ፡፡ አምስት ላም፣ሁለት ፍየል፣ሁለት በሬ፣አንድ ፈረስ፣ አንድ አህያ እንዲሁም  ብዙ ዶሮዎች እና  ሁለት ትንንሽ ጥጃዎች አሏቸው፡፡ ሲመሽ ሁላችንም ቡና ተፈልቶ ቆሎ እየበላን እኔ ከአክስቶቼ እና አጎቴቼ ጋር መስሎ እንቆቅልሽ /ህ/ መጫወት ጀመርን፡፡ መልስ የተሳሳተ  የእንስሳትን ድምፅና አካሄደቸውን በትክክል ማሳየት አለበት (ምሳሌ እንደላም መሄድ እና መጮህ.....) ነበር፡፡ እኔም አንድ እንቆቅልሽ ስለ ተሳሳትኩ እንደ አውራ ዶሮ እንድጮህ ተቀጣሁ፡፡

- የመማርያና  የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የእንስሳት ስዕል፣ ፎቶዎች (ቤተሰብ) የተቀረፀ የእንስሳት ደድምፅ
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ (በታሪኩ ውስጥ ስንት ላሞች አሉ፣ስንት በሬዎች አሉ)

## ተግባር 4- ጨዋታ (8 ክ/ጊዜ)

### ሀ. መስሎ ጨዋታ (4 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- አክስት፣ አጎት፣ ጎረቤት፣ እንስሳት
- የማስተማርያዘዴ፡-  በጨዋታ
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ከላይ ያለውን ተረት ወደ ተውኔት በመቀየር ለህጻናቱ ሚና በመስጠት  (ምሳሌ  አያት፣አክስት፣አጎት፣እንግዳ፣ጎረቤት፣የተለያዩ  እንስሳት  ...)  መስለው እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡
- የመማርያና  የመጫወቻ  ቁሳቁስ፡- የተለያዩ በገጠር ቤተሰብ የሚለበሱ ልብሶች፣ የተለያዩ እንስሳትን ፊት የሚያስመስል ማስክ
- የምዘና ስልት፡- ተውኔቱን ሲሰሩ መመልከት፣ የማንን ሚና እንደተጫወቱ መጠየቅ

### ለ. የጠፋውን ፈልግ (4 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ ቃላት
- የማስተማርያዘዴ፡- በጨዋታ
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህፃናቱ ቀጥሎ ያለውን ጨዋታ ለመጫወት የሚያስፈልጋቸውን

የእናት ፊደል ሳጥን፣ በቻርት ላይ በሶስትፊደል ሊመሰረቱ የሚችሉ ቃላት ውስጥ አንድ ፊደል በማጉደል ያዘጋጁ ( በ-----ለ፣ቀ----በ፣ ሸ-----ለ) ቻርቱን ጠረጴዛ ላይ ያስቀምጡ፡፡ ከዚያም የሚወዳደሩ ሶስት ተማሪዎች ይምረጡ፡፡ ለተወዳዳሪዎቹ የውድድሩን ህግ በተገቢ ይንገሩ፡፡ ጨዋታው የጠፋውን ፊደል ከሳጥኑ ውስጥ በመፈለግ በቻሩት ላይ ባሉት ክፍት ቦታ በማስቀመጥ ቃላት መመስረትና የመሰረቱትን ማንበብ ነው፡፡ የጠፋውን ፊደል ላገኙ ህጻናት የፍቅር ጭብጨባ ያስጨብጨቡና ቀጣይ ተረኛችን በተመሳሳይ ያጫውቱ፡፡

- **የመማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የፊደል ሳጥን፣ ቻርት፣እርሳስ፣ወንበርና ጠረጴዛ
- **ምዘና ስልት፡-** በእናት ፊደላት ቃላት በመመስረት እንዲያነቡ መጠየቅ

## ሐ. እንቆቅልሽ (2 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ፊደል፣እንሰሳት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በማጫወት
- **የመምህር ሚና፡-**መምህር! ህጻናቱን እንቆቅልሽ በመጠየቅ በመልሱ ላይ እንዲሳተፉ ያድርጉ፡፡ የመማር ብቃቶቹን መሰረት ያደረጉ ሌሎች እንቆቅልሾችን መጠየቅ ይችላሉ፡፡

### እንቆቅልሽ

1. ጭልፋ እመስላለሁ፡፡ እኔ ማነኝ ------ 6 ቁጥር
2. ከቁጥር እመደባለሁ፡፡ ከዘራ እመስላለሁ፡፡ እኔ ማነኝ------ 7 ቁጥር
3. ፊደል ነኝ፡፡ ወገቤን ይገፎ እስክስታ እወርዳለሁ፡፡ እኔ ማነኝ-------- ፊደል ቀ
4. የፊደል ዝርያ ነኝ፡፡ እጄን ወደጎን ዘርግቻለሁ፡፡ እኔ ማነኝ ----------- ፊደል ተ
5. የእንስሳት ምድብ ነኝ፡፡ እቤት ውስጥ እኖራለሁ፡፡ ወተት እሰጣለሁ እኔ ማነኝ -- ላም

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ከእንቆቅልሾቹ ጋር የሚሄዱ ምስሎች
- **የምዘና ስልት፡-** እንቆቅልሽ እየቀያየሩ መጠየቅ (የሰውነት ክፍል ነኝ እራመዳለሁ፣ ሰዎችን ከቦታ ቦታ እወስዳለሁ እኔ ማነኝ....)

# ሀያ አራተኛ ሳምንት

የተመደበ ክ/ጊዜ ብዛት- 30 10 ሰዓት

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ሌሎች ምን እንደሚሰማቸው ለማወቅ የጋራ መግባቢያ ምልክቶችን (በቃል፣ አካላዊ) ይለያሉ
- የቅርብ ጓደኞችቻቸውን ይገለጻሉ
- በአቅራቢያም ያሉ የአትክልት ዓይነቶችን ይለያሉ
- 9 ቁጥር ይቆጥራሉ እና እንደገና ይፃፉሉ
- ፊደላትን ደግመው ይጽፍ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- የኢትዮጵያን ብሄራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀለም ይቀባሉ
- ቢያንስ ከ3-5 አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ያከናውናሉ
- የተለያዩ ቁሶችን በነጠላ መስመር /pattern/ ይደረድራሉ
- የሚያዳምጡትን የድምፅ ምት ተከትለው አካላዊ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ
- በቦታቸው ሆነው እቃ ይዘው ወይም ሳይዙ ይንቀሳቀሳሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ራስን ማወቅ
- ራስን መግለጽ
- ተክሎች
- ቁጥርን መጻፍ
- ፊደላትን መጻፍ
- ማንበብ
- ትላልቅ ጡንቻዎች
- በመስመር መደርደ (ፓተርን)
- ጥበባዊ እሴት
- ሙዚቃዊ ምት እንቅስቃሴዎች

## ተግባር 1- የግል ተግባር (9 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ጓደኛሞች (3 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- ጓደኛ፣ ቁጥር፣ እንቅስቃሴ
- የማስተማርያ ዘዴ:- በተግባር
- የመምህር ሚና:- ለክፍለ ጊዜው አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፣ ህጻናቱ 9 ቁጥርን ደግመው

እንዲጽፉ፣ እንዲቆጥሩ፣ ስእሎችን አይተው እንዲናገሩ፣ የጓደኞቻቸዉን ስም እንዲጠሩ ማበረታታት፣ እንዲሁም 9 የተለያዩ አትክልት ሞዴሎች በማዘጋጀት እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡ ሲቆጥሩ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ የእጅና የእግር እንቅስቃሴ ያድርጉ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ጓደኛነትን የሚሳዩ ምስሎች፣ የቁጥር ገበታ፣ወረቀት /ደብተር ፣እርሳስ የቁጥር ፍላሽ ካርድ
- **የምዘና ስልት፡-** ሲጽፉ መመልከት፣ እስከ 9 ያሉ ነገሮችን እንዲቆጥሩ ማድረግ

### ለ. ፊደላትን መጻፍ (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል ፣ቃላት ፣መፃፍ፣ ማንበብ፣ ቀለማት
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የተለያዩ የፊደል ፍላሽ ካርድ በማዘጋጀት እናት ፊደላትን በቀደም ተከተል በመደርደር ፊደላቱን እያነሱ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል በተዋወቁት ፊደላት ቃላት ይመስርቱ፡፡ በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ያሉትን ፊደላትና ቃላት እንዲገናገሩ፣ እንዲጽፉ፣ እንዲያነቡ፣ ያድርጓቸው፡፡ለምሳሌ፡- ፊ…ፊረስ፣ ፀ…ፀሀይ፣
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የፊደል ገበታ፣ መለመማጃ ደብተር/ወረቀት፣ እርሳስ፣
- **የምዘና ስልት-** በመጠየቅ፣ ፊደላትን እንደገና ሲጽፉ በመከታተል፣ ቀላል ቃላትን እንዲያነቡ በማድረግ፣ ሲሰሩ በመመልከት

### ሐ. መቀባት (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሰንደቅ ዓላማ፣ ተክሎች፣ቁጥር፣ ጥበባዊ ግንዛቤ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-መምህር!** የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ምን እንደሚመስል ያሳዮቸው ስለቀለማቱ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ተክሎች ቀለም ጋር እያዛመዱ ይንገሯቸው (ለምሳሌ ቀዩ የጽጌረዳ አበባን ቢጫው- አደይ አበባን፣ አረንጓዴ ደግሞ የተለያዩ ቅጠላ ቅጠልን እንደሚመስል) ጥበባዊ ግንዛቤያቸውን ለማስፋት የተነገራቸውን ቀለማት ፈልገው በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ የኢትዮጲያ ሰንደቅ አላማ ይስሩላቸውና ይቀቡ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የመለማመጃ ደብተር፣ ከለር፣ ሰንደቅ አላማ፣ ቁጥር፣ የተለያዩ ቀለም ያላቸው ተክሎች
- **የምዘና ስልት፡-** በመጠየቅ ምንሰራቹ፣ እንዴት ሰራችሁ፣ የትኛው ቀለም ጽጌረዳን ይመስላል፣ አደይ አበባ ቅጠልን ይመስላል… ሲሰሩ የሚያከናውኑበትን መንገድ በመከታተል እንዲሁም ሰንደቅ ዓላማ ስንት አይነት ቀለም እንደተቀባ ቁጥሩን ይጠይቁ

## ተግባር 2- ተረት -(3 ክ/ጊዜ)

### ሀ. የአትክልት ስፍራ (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሰንደቅ አላማ፣ አትክልት፣ ደስታ

- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** ተረቱን በአግባቡ እንዲያዳምጡ መከታተል፣ የሰሙትን ተረት መልሰው እንዲናገሩ ማበረታታት

## ተረት ተረት!

በአንድ አከባቢ የሚኖሩ በጣም የሚዋደዱ ጓደኛሞች ነበሩ። አንድ ቀን በትምህርት ቤታቸው ግቢ ውስጥ በሚገኘው ሙዝ፣ፓፓያ፣ብርቱካን፣እንሰት፣ጎመን፣ቲማቲምና የተለያዩ ዛፎች ከሚገኙባቸው የአትክልት ስፍራ ከመምህራቸው ጋር ሄዱ።በአትክልት ስፍራው ሲደረሱ በጣም ደስ አላቸው። ምክንያቱም አትክልቶቹ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ሲሆን አንዳንዶቹ ቀይ፣አንዳንዶቹ አረንጓዴ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ቢጫ ናቸው። በዚህም በጣም ስለተደሰቱ ሙዝ ቢጫ ነው፣ ቲማትም ቀይ ነው፣ ቃሪያ አረንጓዴ ነው እያሉ ስለቀለም አይነቶች ያወሩ ነበር። እንዲሁም ስንት ሙዝ፣ ስንት ብርቱካን እንዳለ በፍጥነት ተራ በተራ እየቆጠሩ በወረቀታቸው ላይ ማስታወሻ ይይዙ ነበር። ቤቢ የተባለው ህጻን ጓደኞቹ አንድ ነገር ልንገራችሁ። እኔ እየተሰማኝ ያለው ደስታ ነው። ቀለማቱ ቅድም ከቀባነው የኢትዮያ ሰንደቅ ዓላማ ቀለም ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው። ባንዲራችን አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለም ነው።እዚህም ያሉት አትክልቶች ቀለማቸው አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለም ነው ብሎ ጮክ ብሎ ተናገረ። ህጻናቱ እውነቱን ነው እዉነቱን ነው ብለው አጨበጨቡለት። በመጨረሻ ከጉብኝት ሲመለሱ ያዩትን ተክሎች ስለው የራሳቸውን ቀለማት በመቀባትና ስማቸውን በመፃፍ በክፍላቸው ውስጥ ሰቀሉት። ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የጓደኛሞችን፤ የኢትዮያን ሰንደቅ ዓላማ፤ የአትክልት ምስሎች የተለያዩ ቀለማት፣ ወረቀት፣ እርሳስ
- **የምዘና ስልት፡-** ህጻናቱ በተረቱ ላይ የተዘረዘሩትን ቀለማትና አትክልቶችን ስሞች መጠየቅ፣ በአከባቢያቸው የሚያውቋቸውን የአትክልት አይነቶች ስሞችን መጠየቅ የሰሙትን በስዕል እንዲገልፁ ማድረግ

## ተግባር 3- መዝሙር …(6 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ሰንደቃችን (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሰንደቃላማ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡- መምህር!** ህፃናቱ በትኩረት እንዲያዳምጡ በማድረግ የመዝሙሩን ጭብጥ ያስይዟቸው ዜማውን በመደጋገም ያለማምዷቸው

ሰንደቃችን

አረንጓደ ቢጫቀይ ሰንደቃችን

እንወድሻለን ኢትዮጵያ ሀገራችን

አረንጓዴ ከላይ ቢጫው ከመሀል ነው

ቀዩ በታች ሆኖ መሀሉ ኮከብ ነው

ሰንደቃላማችን ይሄ ነው፤ይሄ ነው

በዚህማ ጉዳይ ሁላችን አንድ ነን

በጋራ መግባባት አንቺን እንወዳለን

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ከመዝሙሩ ጋር የሚሄድ ስእል፣ አረንጓደ ቢጫ ቀይ የተቀቡ ቁርጥራጭ ወረቀቶች፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ እርሳስ የተለያዩ ቀለማት ፣ ሞባይል፣ቴፐ /ሞንታርቦ/
- የምዘና ሥልት፡- ሁሉም ህጻናት ሲዘምሩ፣ሲንቀሳቀሱ፣ስዕል ሲስሉ፣ለጓደኛቸው የሚያሳዩትን ምላሽ መከታተል፣ የሰንደቅ አላማ ቀለማትን መጠየቅ፣ ሲዘምሩ ምን አይነት አካላዊ እንቅስቃሴ አደረግን ፣

## ለ. የኔማ ጓደኞች (3 ክ/ግዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ጓደኞች፣ ቁጥር፣ ሰንደቃላማ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በመዝሙር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህጻናቱ በመዝሙሩ እንዲሳተፉ ያድርጉ

የኔማ ጓደኞች

የኔማ ጓደኞች እጅግ ብዙ ናቸው

ማጥናት ይወዳሉ በጣም ጎበዝ ናቸው

እንዋደዳለን ፀብን እንጠላለን

1--2--3–4 ቁጥር እንጽፋለን

5--6--7--ቀላል ስፖርት መስራት

8--9 ብለን ቁጥር እንቆጥራለን

ለአረንጓዴ ቢጫ፣ቀዩ ሰንደቃችን

ትልቅ ክብር አለን

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ከመዝሙሩ ጋር የሚሄድ ጎደኝነትን የሚሳይ ስእል፣ የቁጥር ገበታ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ የተቀቡ ቁርጥራጭ ካርቶኖች፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ሞባይል
- የምዘና ስልት፣ ሁሉም ህጻናት ሲዘምሩ፣ ሲንቀሳቀሱ፣ ስዕል ሲስሉ፣ ለጓደኛቸው የሚያሳዩትን ምላሽ መከታተል፣ ቁጥሮችን መጠየቅ፣ የሰንደቅ አላማ ቀለማትን መጠየቅ፣ ሲዘምሩ ምን አይነት አካላዊ እንቅስቃሴ አደረግን

## ተግባር 4- የውጭ ጨዋታ (3 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ማን ይወጣል (ክ/ጊዜ 3)

- **ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣** እንቅስቃሴ፣ ስሜትን መረዳት፣ ምልክት፣ መለዋወጥ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-መምህር!** ይሄን ጨዋታ ከዚህ በፊት በሌሎች ቁጥሮችና በተመሳሳይ አካላዊ እንቅስቃሴ ተጫዉተዉታል፡፡ ይሁን እንጂ ቁጥሮችን በድግግሞሽ እንዲለማመዱ በሚከተለው አይነት እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡

**ማን ይወጣል**

የጨዋታዉ ህግ፡- እስከ 9 የሚደርሱ ህጻናት ቡድን ይሰራሉ፡፡ ቀጥሎ እጅ ለእጅ ተያይዘው ክብ ሰርተው ዱብ ዱብ እያሉ መሀሉን ሰፋ በማድረግ ይዞራሉ፡፡ ለጨዋታው የሚያስፈልጉ ቁጥሮች "5" "7" እና "9" ናቸው፡፡ አጫዋቹም "5' ሲባል ይሮጣሉ፣ "7" ሲባል ባሉበት ቆመው ወደላይ ይዘላሉ "9" ሲባል ይቀመጣሉ የተሳሳተ ህጻን ከጨዋታ ውጪ ይደረጋል፡፡ መሃል ገብተው ይቀመጣሉ ማለት ነው፡፡ ጫወታው አሸናፊ እስኪለይ ድረስ ይቀጥላል፡፡ ተራቸውን የሚጠብቁት ቡድኖች ተረኛውን ሞራል መስጠትና ማበረታታት እነሱም በእንቅስቃሴ ውስጥ የመሆን ስሜት ይፈጥርላቸዋል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ቁጥር የያዙ ካርዶች፣ የመጫወቻ ሜዳ፣ ሙዚቃ
- **የምዘና ስልት-** ምልከታ ( ሲጫወቱ የጓደኛቸውን እጅ ለመያዝ ሰው ይመርጡ ነበር ወይስ ከሁሉም ጋር በደስታ ተያይዘው ይጫወታሉ፣ ለመሸነፍ ሲሉ ሌሎችን ይገፋሉ ወይስ መስመራቸውን ጠብቀው ይጫወታሉ፣ መመሪያን ተከትለዋል ወይስ አልተከተሉም ...) የቃል ጥያቄ፡- የዘለላቹት ስንት ቁጥር ሲጠራ ነው ፣ ዱብዱብ ያላቹት ስንት ቁጥር ሲጠራ ነው፣ በጨዋታው ወቅት ከቡድኑ ያዘነ ሰው ነበር ወይ ለምን ፣ ቁጥሮችን በማሳየት ስንት እንደሆኑ ለይተው እንዲጠሩ ማድረግ

## ተግባር 5- የክፍል ጨዋታ (3 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ባህላዊ ጭፈራ (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ባህላዊ ጭፈራ፣ ባህላዊ እቃዎች
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-መምህር!** በመጀመሪያ በአከባቢው የሚታወቅ ባህላዊ ዘፍን ይምረጡ፡፡ በመቀጠል ከለሙዚቃው ጋር አብሮ የሚሄድ ባህላዊ እቃ( ዱላ፣ በእጅ የሚያዙ የተለያዩ ቁሶች) እንዲይዙ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል በአሉበት ቦታ ሆነው የሙዚቃውን ምት ተከትለው እንዲጨፍሩ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ቴፕ፣ ሞባይል፣ የባህላዊ ሙዝቃ ቅጅ፣ ባህላዊ የጭፈራ የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል፣ የተለያዩ ባህላዊ ቁሳቁሶች

- የምዘና ስልት- ምልከታ ሲጨፍሩ ባሉበት አካላቸውን እያንቀሳቀሱ መሆኑን ፣የጓደኞቻቸውን ስሜት እየጠበቁ መሆኑን ፣ምቱን በእኩል እየቆጠሩ ስለመሆኑእና የሰሙትን ድምጽ ተከትለው በአግባቡ ምላሽ እየሰጡ ስለመሆኑ ...) የቃል ጥያቄ አንዱን የባህል ቁስ በማሳየት ስሙ ምንድነው በማለት መጠየቅ

## ተግባር 6- የፕሮጀክት ስራ (6ክ/ጊዜ)

### ሀ. ቀለማትን በፓተርን ማስቀመጥ (3 /ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ፓተርን፣ ጓደኛ፣ ቀለም
- የማስተማሪያ ዘዴ፡- በፕሮጀክት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ይህን ፕሮጀክት ሁለት ሁለት ህፃናት በጋራ ሆነው በሚከተለዉ መመሪያ መሰረት እንዲሰሩ ያድርጉ

1. ለሁሉም ቡድን አረንጓዴ ቢጫ እና ቀይ ቀለም የተቀቡ 9 ጠጠሮችን እና በአራት መኣዘን የተቆራረጡ ካርቶኖች አዘጋጅተው ይስጡ
2. ለህጻናቱ ፓተርኑ እንዴት እንደሚቀመጥ ያሳዩዋቸው ( አረንጓዴ፣ ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ፣ ቀይ ቢጫ... )
3. በመቀጠል ሁለቱ ህፃናት በተራ በተራ በተባለው መሰረት እንዲደረድሩ ያድርጉ፡፡
4. ሲጨርሱ ተራ በተራ እየተነሱ አብሯቸው ስለሰሩት ጓደኛቸው ስም ፣የሚወደውን/ የምትወደውን ነገር ፣ ምንአይነት ጸባይ እንዳለው /እንዳላት እንዲገለጹ ያድርጉ፡፡

- የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡- አረንጓዴ ፣ቢጫ ፣ቀይቀለም የተቀቡ ጠጠሮች ፣በአራት ማዕዘን የጠቆራረጡ ጠንካራ ካርቶን
- የምዘና ስልት፡ የቃል ጥያቄ ስንት ጠጠር ነበራችሁ፣ አረንጓዴው ስንት ነው፣ ቀዩ ስንት ነው፣ ቢጫው ስንት ነው፣ አንድ ላይ ስንት ጠጠር ሆኑ ምልከታ ( ሲደረድሩ ተገቢውን ፓተርን እየተከተሉ መሆኑን ...

### ለ. ተክል መትከል (3 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ተክሎች፣ችግኝ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በፕሮጀክት
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህጻናቱ ከወላጆቻቸው ጋር በመሆን የፈለጉትን ተክል በቀላል እቃ ውስጥ እንዲተክሉ ይንገሯቸው፡፡ ተክሉን ለምን ያህል ጊዜ መንከባከብ እንዳለባቸውና መቼ ይዘው እንደሚመጡ ለወላጆቻቸው ማስታወሻ ይጻፉ፡፡
- የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡- የተለያዩ ችግኞች /ዘር/ ፣የአትክልት መትከያ ጣሳ /ፕላስቲክ ፣አፈር ፣ውሃ
- የምዘና ስልት- የቃል ጥያቄ (የተከሉትን ተክል ይዘው አንድ ቦታ በመቆም ስለ ተከሉት ተክል፣ ስም፣ መትከያ እቃው፣ ከማን ጋር እንደተከሉ፣ እንዴት እየተንከባከቡ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

# ሀያ አምስተኛ ሳምንት

የተመደበ ክ/ጊዜ ብዛት-30 10 ሰዓት

## የሳምንቱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ከሌሎች ጋር አወንታዊ ግንኙነት ለመፍጠር፣ የሥነ ምግባር እሴቶችን ይለያሉ
- እርስ በርስ ፍቅርን መግለጽ እንደሚቻል ይረዳሉ
- በር በመግፋት እና ቁሶችን መጎተት፣ የጃኬትን ዚፕ መክፈትና መዝጋት ተግባራትን ያከናውናሉ
- እንቆቅልሽ ጨዋታን ተርድተው ምላሽ ይሰጣሉ
- የሚነገራቸውን ቀላል መመሪያ ይረዳሉ
- የሰውነት ክፍሎቻቸውን በመጠቀም የተለያዩ ቅርጾችን ያሳያሉ
- እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን ይደረድራሉ
- ከ1-3 ያሉ ቁጥሮችን እንደገና ይጽፋሉ
- ፊደላትን ደግመው ይፃፉሉ፤ያነባሉ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- የሚመሳሰሉና የሚለያዩ ቁሶችን ለይተው ያስቀምጣሉ
- ስለተፍጥሮ ዉበት ቀለሞች በጋራ ይዘምራሉ፣ይደንሳሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- የድምጽ ዕውቀት
- የመግፋትና የመጎተት እንቅስቃሴዎችን ያወዳድራሉ
- የቦታ ግንዛቤ
- ፊደላትን መጻፍ
- ማንበብ
- ቁጥርን መጻፍ
- ግብረገብ እሴቶች
- መለየትና መመደብ
- መያያዝ፣ማገናኘትና

# ተግባር 1- የግል ተግባር (9 ክ/ጊዜ)

## ሀ. ቁጥር መደርደር እና ደግሞ መፃፍ (3 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- ቁጥር፣ መደርደር፣ መፃፍ
- የማስተማርያ ዘዴ:- በተግባር
- የመምህር ሚና:-መምህር! በመጀመሪያ ሀጻናቱ እርስ በእርስ ፍቅር መገላለጽን እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል ከ1-9 ቁጥሮችን የያዘ ፍላሽ ካርድ ማዘጋጀት እና በየጠረጴዛቸው ያስቀምጡላቸው፡፡ህፃናቱ በፍላሽ ካርድ የተሰጣቸውን ከ1-9 ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ይደርድሩ፡፡ ቀጥሎ ከተደረደሩት ውስጥ ከ1 እስከ 3 ያሉትን በወረቀት /በደብተር ደግመው ይፃፉ፡፡ እያንዳንዱን ቁጥር ሶስት ሶስት ጊዜ ይድገሙ (1፣1፣1 2፣2፣2 3፣3፣3) ሲጨርሱ የሰሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሳዩ
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁሶች:- ቁጥር የተጻፈባቸው ፍላሽ ካርድ፣ ወረቀት/ደብተር፣እርሳስ
- የምዘና ስልት:- የቃል ጥያቄ (ቁጥር እያነሱ ስንት ነው በማለት መጠየቅ፣ ከ2 ቀጥሎ ያለችው ቁጥር ስንት ናት፣ ከ4 ቀጥሎ …) ምልከታ (መምሪያው ተከትለው እየሰሩ መሆኑን መከታተል ፣ ሲፅፉ የእርሳስ አያያዛቸውን እና መስመር መጠበቃቸውን ማየት ፣ቁጥሩን በቅደም ተከተል መደርደራቸውን …)

## ለ. “ተ፣ ቸ፣ ቀ፣ መ እና ፈ” ፊደላትን መጻፍ (3 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- መፃፍ፣ ቃላት መመስረት፣ መቁጠር፣ ማንበብ
- የማስተማርያ ዘዴ:- በተግባር
- የመምህሩ ሚና:-- መምህር! የፊደል ገበታ ያዘጋጁ፡ የዕለቱን መሪ ፊደል መርጠው ደግመው ይጻፉ፡፡ በመቀጠል ከሌሎች መሪ ፊደላት ጋር በመቀላቀል ፍላሽ ካርዱን በመገጣጠም ቃላት ይመስርቱ፡፡ የመሰረቱትን ቃላት በደብተር/በወረቀት ለይ ይፃፉ፡፡ የፃፉትን ያንብቡ (ለምሳሌ:- ተበተበ፣ ቸበቸበ፣ ቀረቀረ፣ መለመለ፣ ፈረፈረ)
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:- የፊደል ገበታ፣ መለመማጃ ደብተር/ወረቀት፣ እርሳስ፣
- የምዘና ስልት- ጥያቄ (ስንት ቃላት እንደመሰረቱ መጠየቅ፣ የጻፉትን ቃላት አንዲያነቡ መጠየቅ)

## ሐ. ቁጥር ደግሞ መፃፍ (3 ክ/ ግዜ)

- ቁልፍ ቃላት:- ቁጥሮች፣ ቅደም ተከተል፣ መፃፍ፣ ፍቅርን መግለጽ
- የማስተማርያ ዘዴ:-በተግባር
- የመምህር ሚና:- መምህር! ከ1 እስከ 9 ቁጥሮችን ቀላቅለው በጠረጴዛቸው ላይ ያቀምጡላቸው፡፡ ቢያንስ ሶስት ህፃናት በጋራ እንዲሰሩ ያመቻቹ፡፡ ህፃናቱ በተግባቦትና በመከባበር ቁጥሩን በቅደም ተከተል እንዲደረድሩ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎ ወረቀት/ ደብተር በመስጠት ከ 1 እስከ 3 ያሉትን ብቻ ደግመው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ ሲጨርሱ እርማት ይስጡ የተደረደሩትን ቁጥሮች

በቅደም ተከተል እንዲቆጥሩ ያበረታቱ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣ እርሳስ፣ ወረቀት /ደብተር
- **የምዘና ስልት፡-** ህጻናት በትክክል መጻፋቸውን መከታተል፣ ቁጥሮቹን በቅደም ተከተል መደርደራቸውን እና መቁጠራቸውን መከታተል፡፡

## ተግባር 2- የውጭ ጨዋታ (4 ክ/ጊዜ)

### ሀ. በሰውነት ቅርጽ መስራት (4 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሰውነት፣ ቅርጽ፣ መከባበር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱን ወደ ውጭ ይዘው በመውጣት በሰውነት ክፍል የተለያዩ ቅርጾችን ያሰሩ፡፡

1. የሚሰራው ቅርፀ ሶስት ጎን ከሆነ "ስድስት" ህፃናት ያሉት አንድ ቡድን ያዘጋጁ
2. የሚሰራው ቅርጽ አራት ማዕዘን ከሆነ "ስምንት" ህፃናት ያሉት አንድ ቡድን ያዘጋጁ
3. የሚሰራው ቅርጽ ክብ ከሆነ "አምስት" ህፃናት ያሉት አንድ ቡድን ያዘጋጁ
4. የሚሰራው ቅርጽ ቀ ፊደል ከሆነ "ሁለት" ህፃናት ያሉት አንድ ቡድን ያዘጋጁ
5. የሚሰራው ቅርጽ ተ ፊደል ከሆነ "2" ህፃናት ያሉት አንድ ቡድን ያዘጋጁ
6. የሚሰራው ቅርጽ አንድ ቁጥር ከሆነ "2 " ህፃናት ያሉት አንድ ቡድን ያዘጋጁ

ሁሉም ህፃናት በቡድን እና በግል የተለያዩ ቅርፆችን እየሰሩ የቅርጾቹን ስም እንዲጠያየቁ ያድርጉ፡ ፡ በጨዋታ ውስጥ እርስ በርሳቸው ፍቅር እና አክብሮት የተሞለበት ግንኙነት እንዲኖራቸው እገዛ ያድርጉ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ የጂኦሜትሪ ቅርጾች
- **የምዘና ስልት፡-** በምልከታ ( ህፃናቱ ሲሰሩ እና የሰሩትን ለሌሎች የሚያስረዱበትን መንገድ በመመልከት ) ፣ የቃል ጥያቄ፡- ምን ሰራቹ ፣እንዴት ሰራቹ፣ ... )

## ተግባር 3- የክፍል ጨዋታ (4 ክ/ጊዜ)

### ሀ. መለየት፣ መመደብ እና መግፋትና መክፈት (4 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ባለቀለም ቁስ፣ መዝጋት፣ መክፈት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የተወሰኑ ወንድና ሴት ህፃናትን ያስወጡና ከታች ያሉትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ያድርጉ

1. ለተወሰኑ ህጻናት በጋራ ሆነው የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ቁሶች በቀለማቸው የመለየት ተግባር ይስጡ

2. የተወሰኑት ደግሞ የልብስ ዚፕ የመክፈትና የመዝጋት ተግባር ያከናውኑ
3. አንድ ህጻን በር ሲያንኳኳ ሌላ ህፃን በር ከፍቶ ሰላምታ በመለዋወጥና አብረው እንዲጫወቱ በመጋበዝ በሩን ይዝጋ።
4. ጨዋታውን ሲጫወቱ እርበርስ በፍቅርና በአክብሮት የተሞላበት ቃላት እንዲለዋወጡ ያድርጉ ( እባክህ ፣እባክሽ ፣አቀብለኝ /አቀቢይኝ ፣ አብረን ስለተጫወትን ደስ ብሎኛል ፣) እየተባባሉ ይጫወቱ።
5. ጨዋታውን ሁሉም ህፃናት በየተራ እንዲያከናውኑ ያልተጫወቱትን የጨዋታ አይነት እንዲጫወቱ ያድርጉ።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** በለቀለም የፕላስቲክ /የእንጨት ቁሳቁሶች፣ የዚፕ ፍሬም ፣ የክፍል ውስጥ ቁሳቁስ
- **የምዘና ስልት፡-** ሲሰሩ መመልከት፣ የሰሩትን መጠየቅ

## ተግባር 4- ተረት (6 ክ/ጊዜ)

### ሀ. ቢኒ ጥንቸሉ (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሥነ መግባር፣ አብሮ መኖር፣የሚወደድ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ተረቱን በአግባቡ እንዲያዳምጡ ማድረግ፣ ተረቱን በሥዕል አስደግፎ ማውራት፣የሰሙትን መልሰው እንዲተርቱ ማበረታታት

### ቢኒ ጥንቸሉ

የተለያዩ ቀላማት ባለቸው አበባና ተክሎች በሚገኙበት ሜዳማ ቦታ ቢኒ የሚባል ጥንቸል ይኖር ነበር። ቢኒ ጥንቸሉ የአበቦችን ቀለማት ማድነቅ ደስ ይለዋል። በውበታቸው ይማረካል፡፤ የቢኒ ጥንቸሉ ፀባይ በጣም ይገርማል። የማይረብሽ፣ የሌሎችን እንሰሳትን ምግብ የማይነካ፣ የማይጣላና ከሌሎች እንሰሳት ጋር አብሮ መጫወትና በፍቅር መኖር የሚወድ በጣም ተወዳጅ ጥንችል በመሆኑ በሌሎች እንሰሳት በጣም የሚወደድና የሚከበር ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ቢኒ የተበላሸ ፍራፍሬ አገኘና በልቶ በመታመሙ በቤቱ ተኛ። ሚሉ የተባለችዉ ሌላኛዋ ተወዳጅ ጥንቸል ቢኒ በጠዋት ተነስቶ እኛንም ሆነ ሌሎቹን እንሰሳት ሰላም ሲል አልሰማሁትም ምን ሁኖ ነው ብላ አሰበችና ወደ ቤቱ ስትሄድ ቢኒ ታሞ ተኝቷል።ሚሉም አይዞህ ብላ መድሀኒት ፍለጋ ወደ ጦጢት ሄደች፡ ፡ጦጢትም ሚሉ ምነው በጠዋት መጣሽ በሰላም ነው ስትላት እኔ ሰላም ነኝ ነገር ግን ቢኒ ታሞ መድሀኒት እንድትሰጭኝ ብየ ነው ስትላት ጦጢትም ቢኒ በስነ መግባሩ ሁሉም የሚወደው ጥንቸል ነው ብላ ከተለያዩ አበቦችና ፍራፍሬዎች መድሀኒት ቀምማ ሰጠችው። ቢኒም መድሀኒቱን ጠጥቶ ዳነ። ስለዚህ ልጆች እኛም ጓደኞቻችንና ሌሎች ሰዎች እንዲወዱን ጥሩ ስነ መግባር ሊኖረን ይገባል፡ ፡ ተረቱን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የጥንቸልና ሌሎች እንሰሳት ስዕል

- **የምዘና ስልት፡-** ቢኒ ጥንቸሉ ምን ይወዳል፣ ከሌሎች ጋር የሚኖረው እንዴት ነው ...

### ለ. ጓደኞቹ (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ መዋደድ፣ መከባበር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ተረቱን በአግባቡ እንዲያዳምጡ ያድርጉ

## ተረት ተረት!

አቢ፣ ቻሊና ኤማ የሚባሉ ጓደኞሞች ህጻናት ነበሩ፡፡ ጓደኞሞቹ በጣም የሚዋደዱና እርስ በእርስ የሚተሳሰቡ ነበሩ፡፡ በዚህም ባህሪያቸው በሰፈሩ ዉስጥ በጣም ይወደዳሉ፡፡ ብዙ መጫወቻዎች ያላቸው ሲሆን አንድ ቀን አቢ ብዙ መጫወቻ ነው ያለን እስኪ አንድ ላይ አድርገን እንቁጠረዉ አላቸው፡፡ ሲቆጥሩ 9 የሚያማምሩና የተለያዩ መጫዎች ሆነላቸው፡፡ በዚህም በጣም ደስተኛ ሆኑ፡ ፡ ቻሊ እንዲህ አለ "እኔ ሁላችሁንም በጣም ነው የምወዳችሁ፤እንደናንተ ያለ ጓደኛ ስላለኝ በጣም እድለኛ ነኝ አለ፡ አቢ እና ኤማም እኛም እኮ አንተን በጣም ነው የምንወድህ አሉት፡፡ እኛ በጣም የምንዋደድ ጓደኞሞች ነን አንድም ቀን ተጣልተን አናዉቅም ወደ ፊትም አንጣላም ተባባሉ፡፡ ይህን ሲያወሩ አንድ ትልቅ ሰዉዬ በአጠገባቸው ሲያልፉ ሰሚቸውና ልጆች የምታወሩቱን እየሰመኂችሁ ነበር፡፡ በጣም ነው ደስ ያለኝ ጎበዝ ልጆች መዋደድና መከባበር አብሮ ለመኖር አስፈላጊ ነው፡፡ እኔም እወዳችኂለሁ ብለው ሳሚቸውና መንገዳቸዉን ቀጠሉ፡፡ ልጆች እናንተም ለጓደኞቻችሁ ፍቅራችሁን መግለጽ አለባችሁ፡፡ ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የጓደኞሞችን የሚሳይ ስእል፤ እርስ በርስ ፍቅር እና አክብሮት ሲለዋወጡ የሚሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል /ስዕል/
- **የምዘና ስልት፡-** ህጻናቱ በተረቱ ውስጥ የተነሰውን ሀሳብ መልሰው እንዲናገሩ በማድረግ፣ ከተረቱ የወጡ ጥያቄዎች በመጠየቅ ስንት መጫወቻ ሆነላቸው፣ ስንት ጓደኞሞች ነበሩ፣ ጓደኞሞቹ እርስ በርስ ያለቸው ግንኙነት ምንአይነት ነው ...

## ተግባር 5- በፕሮጀክት መማር (2 ክ/ጊዜ)

### ሀ. መፃፍ (2 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቃላት፣ መፃፍ፣ ማከናወን፣ መወሰን
- **የማስተማርያ ዘዴ ፡-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናት በራሳቸው ቁጥር እና ቃላት የሚጽፉበት ጊዜ ነው ስለዚህ ይህንን ለማከናወን የሚረዳቸውን ቁሳቁስ እራሳቸው ወስነው እንዲያዘጋጁ ያድርጉ ቀጥሎ እስከ 9 የሚደርሱ ቁጥር እና የፊለጉትን ቃላት ይፃፉ ሲጨርሱ የሰሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡ
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** እርሳስ ፣ደብተር /ወረቀት /ቀለም ...

- የምዘና ስልት፡- ምልከታ ምን እየሰሩ እንደሆነ መከታተል፣ የቃል ጥያቄ፡- ስንት ቁጥር ጻፍክ/ሽ፣ ስንት ቃላት ፃፍክ/ሽ፣ ምን ይላል

## ተግባር 6- መዝሙር (6 ክ/ጊዜ)

### ሀ. የተፈጥሮ ፀጋ (3 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡-ተፈጥሮ፣ ቁጥር፣ ቀለም
- የማስተማርያ ዘዴ፡ በመዝሙር
- የመምህሩ ሚና፡- መምህር! ህፃናቱ በትኩረት እንዲያዳምጡ በማድረግ የመዝሙሩን ጭብጥ ያስይዟቸው፡፡

### የተፈጥሮ ፀጋ

ተፈጥሮ ውብ ናት እንከባከባት፣

በአንድነት ሆነን እንደስትባት፡፡

ዛፍና ቅጠሉ ሆሆሆ አምሮና ተውቦ ሆሆሆ፣

ሽታው ይማርካል ሆሆሆ አበባው አብቦ ሆሆሆ፣

ቀይ ቢጫ ቀለም ሆሆሆ በጣም አስደናቂ ሆሆሆ፣

ለሚያያቸው ሁሉ ሆሆሆ ናቸውኮ ማራኪ ሆሆሆ፡፡

እስቲ ልቁጠራቸው የተፈጥሮን ብዘት፣

1 2 3 4 5 6 7፡፡

ቀኑን ሙሉ ብውል ቆጥሬ አልጨርሰው፣

እንዲሁ ዝም ብዬ በፍቅር ማየት ነው፣

ተፈጥሮ ውብ እና እጅግ ማራኪ ነው፣

መኖራቸው ለእኛ አስፈላጊ እኮ ነው ፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የተፈጥሮ አካባቢ /ስዕሎች ፣መቅረፀ ድምጽ
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ (የተፈጥሮ ነገሮችን ዘርዝር/ሪ)

### ለ. እንማር (3 ክ/ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ ቃላት፣ ቁጥር
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በመዝሙር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! መዝሙሩን በመጀመሪያ በመዘመር ህፃናቱ እየተከተሉ እንዲዘምሩ ያድርጉ፣ ህፃናቱ በጋራ እንዲዘምሩ ያበረታቱ፣ መዘመር ያቃታቸውን ያግዙ

እንማር

ፊደላት እንማር/2/ እያልን በ፣ ሰ፣ ሸ፣ከ፣

ቁጥሮችን እንወቅ እያልን 1፣ 2፣ 3፣

ቃላትን እንመስርት ፊደላት ገጣጥመን፡፡

እያልን መሠለ እያልን ቀለለ፣

እያልን ሰለለ እያልን ሸለለ፡፡

እኛ ልጆች እኮ እንዋደዳለን፣

ስንማር በጋራ ስፖርት እንሰራለን፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቁጥር ገበታ፣ የፊደል ገበታ
- **የምዘና ስልት፡-** ቁጥሮችን መጠየቅ፣ ቃላትን መመስረት፣ቃላትን መስርተው እንዲያነቡ መጠየቅ፣

# ሀያ ስድስተኛ ሳምንት

የተመደበ ክ/ጊዜ ብዛት-30 10 ሰዓት

## የሳምንቱ ተፈላጊ የመማር ብቃቶች

- በመረዳዳት ጥሩ ባህርያትን ተረድተው ይከተላሉ
- የኢትዮጵያን ብሔራዊ መዝሙር በመምህራን እርዳታ ይዘምራሉ
- ረጅም፣አጭር፣ከባድ፣ቀላል፣ሙሉ፣ባዶ፣ግማሽ/ሙሉ፣አንድ አይነት ፣ቅርብ /እሩቅ በመጠቀም ሁለት ነገሮችን ያወዳድራሉ
- አካባቢያቸውን ይንከባከባሉ
- የትምህርት ቤት ግቢን ያጸዳሉ
- የአደጋ ምንጭን ይለያሉ፤ከአደጋ አና ከአደጋ የተጠበቁ ሁኔታዎችን ይለያሉ
- 4-6 ያሉ ቁጥሮችን እንደገና ይፅፋሉ
- ፊደላትን እንደገና ይፅፋሉ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- የኢትዮጵያ ሳንቲሞችን እና የብርኖቶችን ይለያሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ግብረገብ እሴት
- ሀገር ፍቅር
- ልኬት
- ገንዘብ
- እራስንና አካባቢን መንከባከብ
- ጥንቃቄና መከላከል
- ፊደላትን መፃፍ
- ማንበብ
- ቁጥር መፃፍ
- ቃላት

## ተግባር 1-የግል ተግባር (6 ክ/ግዜ)

### ሀ. ከ 4-6 ያሉ ቁጥችን ደግሞ መፃፍ (2 ክ/ ግዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ አካባቢ
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡-መምህር! ህጻናቱ እርሳስ እንዴት መያዝ እንዳለባቸው በማስታወስ የስ ከ

4-6 ቁጥር ቅርፅን ከመስመር ሳይወጡ እንዲያደምቁ ያድርጉ፡፡ እንዲሁም አካባቢያቸውን እንዲገነዘቡ ያግዟቸው፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- እርሳስ፣ ወረቀት፣ ብተር
- የምዘና ስልት፣ ህጻናቱ እርሳሳቸውን በአግባቡ መያዛቸውን እና በትክክል መጻፋቸውን መከታተል እና የፃፉት ቁጥር ስንት እንደሆነ መጠየቅ

### ለ. ፊደል "ነ፣ ከ፣ ኸ እና ዐ " ደግሞ መጻፍና ቃላት መመስረት (4 ክፍለ ጊዜ )

- ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ የአደጋ ምንጭ፣ ቀላል ቃላት
- የማስተማርያ ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! ህጻናቱን ስለ አደጋ ምንጮችና ከአደጋ የሚጠበቁበት ሁኔታዎች ላይ ግንዛቤ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል በአየርላይ ፊደል _____እዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡ ህጻናቱ የፊደላቱን ቅርፅ ከመስመር ሳይወጡ እንዲያደምቁ ያድርጉ፡፡በመጨረሻም ፊደላቱን በመደጋደገም ቀላል ቃላትን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- እርሳስ፣ ወረቀት፣ ደብተር
- የምዘና ስልት፣ ህጻናቱ እርሳሳቸውን በአግባቡ መያዛቸውን እና በመስመሩ ላይ ማድመቃቸውን መከታተል፡፡ የፃፏቸው ፊደላት ስም እና ስንት ፊደላት እንደጻፉ መጠየቅ፡፡

### ሐ. ቃላት መመስረት (2 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ ቃላት፣ ማጽዳት
- የማስተማር ዘዴ፡- በተግባር
- የመምህር ሚና፡- መምህር! የዕለቱን ተግባር ከመጀመርዎት በፊት ህጻናቱን ስለ አደጋ ምንጭና ከአደጋ የተጠበቁ ሁኔታዎችን ግንዛቤ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠልም ህጻናቱ የመለማመጃ ደብተራቸውን እንዲያወጡ ያድርጓቸውና በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ያሉ በእናት ፊደላት የተመሰረቱ ቀላል ቃላትን ( በረበረ፣ መጠጠ፣ ጠረጠረ፣ ደረደረ፣ ሰጠ....) ፊደላትን ገጣጥመው እንዲያነቡ በማደረግ የንባብ ልምምድ እንዲያደርጉ ይርዷቸው፡፡ በመቀጠል በእናት ፊደላትን የሚጀምሩ ቃላትን ስእሎችን በማጣመር ቃላትን በመጻፍ በቃላቸውእንዳነቡያድርጉ፡፡ ለምሳሌ፤(ገ...ገጠር...ወ...ወንዝ....ሰ....ሰዓት.....ተ....ተራራ...ነ....ነብር...አ....አንበሳ)
- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ እርሳስ፣ ጠመኔ፣ ሰሌዳ
- የምዘና ስልት፡- ፍደላቱን መለየታቸውን ማረጋገጥ፣ ቃላት እንዲመሰርቱ መጠየቅ

## ተግባር 2- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. እዮብ እና ሀሰን (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት፡- ምድጃ፣ ብሄራዊ፣ መዝሙር
- የማስተማር ዘዴ፡- በተረት
- የመምህሩ ሚና፡- መምህር! ህጻናቱ ተረቱን በጥሞና እንዲያዳምጡ እና ፍሬ ሓሳቦቹን መልሰው እንዲገልፁ ያግዟቸው፡፡

## እዮብ እና ሀሰን

እዮብና ሀሰን የሚዋደዱ ጓደኞች ናቸው፡፡ ት/ቤት የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ሲዘመር ሲሰሙ በጣም ደስ የላቸዋል፡፡ መዝሙሩ እስኪያልቅ ድረስም በመቆም ለሀገራቸው ያላቸውን ክብር የሳያሉ፡፡ አንድ ቀን ታዲያ እዮብ ቤተሰቦቹ ለሥራ ወደ ክፍለ ሀገር ሲሔዱ ጓደኛውን ሀሰንን በመጥራት አብረው እንዲያጠኑ፣ የተሰጣቸውን የቤት ስራ እንዲሰሩና እንዲጫወቱ ወደ ቤት ይዞት ይመጣል፡፡ እዮብም በል ሻይ ልጣድ መጣሁ ብሎ የማጥኛ ጠረጴዛ አስተካክሎ ወደ ውስጥ ይገባል፡፡ ሻይ ለመጣድ ምድጃውን ሲለኩስ ሳያስበው በመቃጠሉ የእሪታ ድምፅ ሲያሰማ ሀሰን እየሮጠ በመሄድ ጎረቤት ጠርቶ ወደ ሆስፒታል ይወስዱታል፡፡ የእዮብ ቤተሰቦች ከክፍለ ሀገር ሲመለሱ ልጃቸው እጁ ተቃጥሎ በማየታቸው ተደናግጠው ሁለተኛ ትልቅ ሰው በሌለበት ምድጃ ወይም ኤሌክትሪክ መለኮስ የለብህም ብለው አስጠነቀቁት ይባላል፡፡

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ- የተረት መፅሐፍ
- የምዘና ስልት፡- ከተረቱ ውስጥ የተውጣጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ

## ተግባር 3- መዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ሀገር ፍቅር (3 ክፍለ ጊዜ)

- ቁልፍ ቃላት- እናት ሀገር፣ ፍቅር
- የማስተማርያ ዘዴ- በመዘሙር
- የመምህር ሚና፡-መምህር! መዝሙሩን በመጀመሪያ በመዘመር ህፃናቱ እየተከተሉ እንዲዘምሩ ያድርጉ፣ ህፃናቱ በጋራ እንዲዘምሩ ያበረታቱ፣ መዝመር መዘመር ያቃታቸውን ያግዙ

## እምዬ ኢትዮጵያ

እምዬ ኢትዮጵያ ውድ እናት ሀገሬ፣

ዘላለም ኑሪልኝ ልክ የለውም ፍቅሬ፡፡

አንድ ሁለት ሶስት አራት ብዩ ቁጥር ቆጥሬ

ሀ ሁ ብዬ ፊደልን መማሬ

ብጠጣም ብበላም ብማርም ብሰራ፣

አንቺ ስላለሽ ነው ኢትዮጵያዬ ልኩራ፣

አንቺ ስላለሽ ነው ኢትዮጵያ ልኩራ፡፡

እምዬ ኢትዮጵያ ውድ እናት ሀገሬ/2/ ፣

ብድር እከፍላለሁ አድጌ ተምሬ፣/2/

- የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ካርዶች፣ ባንዲራ፣ ይቁጥር ካርድ

- **የምዘና ስልት፡-** በመዝሙሩ ውስጥ ስንት ፊደላት አሉ፣ ስንት ቁጥሮች አሉ

### ለ. ፊደል (3 ክ/ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት-** ፊደል፣ የአደጋ ምንጭ፣ ገንዘብ/ሳንቲም/
- **የማስተማር ዘዴ፡-** በመዘመር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! መዝሙሩን ህፃናቱ እንዲዘምሩ ማበረታታት መዝሙሩን መዘመር ያቃታቸውን ማገዝ ይጠበቅቦታል

## ፊደል

ፊደልን በመጻፍ ቃላት እሰራለሁ
እየደጋገምኩኝ ቁጥር እጽፋለሁ
ሁለት ነገሮችን አወዳድራለሁ
የአደጋ ምንጭን በደንብ ለይቻለሁ
መንገዴን እያየሁ እጠነቀቃለሁ
ለውዷ ሃገሬ አስፈልጋታለሁ
ልዩ ሳንቲሞቿ መገበያችን
እንገዛበታለን ምግብና ልብሳችን
ሁሌ ጽዱ ሆኖ ትምህርት ቤታችን
እንጫወታለን ከጓደኞቻችን

- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ፍላሽ ካርዶች፣ ሳንቲሞች
- **የምዘና ስልት፡-** የአደጋ ምንጮች ምን ምን ናቸው፣ ከአደጋ እንዴት እንከላከላለን

## ተግባር 4፡- የክፍል ዉጭ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ክብ ክብ ጨዋታ (4 ክ/ግዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ማወዳደር፤ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን ከክፍል በማስወጣት አንድ ትልቅ ክብ እና በውስጡ ደግሞ 6 በሚደርሱ ህጻናት ትንሽ ክብ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ በትንሹ ክብ ውስጥ ስድስት የተለያዩ ቁሶች (የተለያዩ መጠን ያላቸውን ቁሶች ረጅም፣ አጭር፣ ከባድ፣ ቀላል፣ ባዶ፣ ግማሽ፣ ሙሉ ነገሮችን በመሬት ላይ ራቅ ራቅ አድርገው ያስቀምጡ፡፡)

1. የትንሹ ክብ ህጻናት ዱብ ዱብ እያሉ ሲዞሩ የትልቁ ክብ ደግሞ በማጨብጨብ አረንጓዴ አረንጓዴ እንዲሉ ማድረግ፡፡ ህፃናቱ ትንሽ እንደሮጡ እርሶ ድምጽዎት ከፍ በማድረግ ቀይ ሲሉ 6ቱ ህፃናት መሬት ላይ የተቀመጡትን ነገሮች አንድ አንድ እንዲያነሱ ማድረግ
2. ህፃናቱ የያዙትን ቁስ ከፍ በማድረግ ስሙን ወይም ተግባሩን ተራ በተራ እንዲገልፁ እና እንዲያወዳድሩ ማድረግ፡፡

3. ይህንን ተግባር ሁሉንም ህጻናት በማሳተፍ በተራ ክቡን በመቀያየር ጨዋታውን እንዲጫወቱ ማድረግ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ረጅም፣ አጭር፣ ከባድ፣ ቀላል፣ ሙሉ፣ ባዶ፣ ግማሽ ቁሶች የያዘ ስዕሎች/ሞዴል
- **የምዘና ስልት:-** የቃል መጠይቅ፣ ምልከታ እያንዳንዱ ህፃነት የያዙትን ቁስ ስዕል ተግባር፣ ብዛት፣ መጠየቅ፣ ሲያቀርቡ/ሲገልፁ መመልከት ረጅም፣ አጭር ፣ከባድ፣ቀላል፣ ሙሉ፣ባዶ፣ግማሽ፣አንድ አይነት ፣ቅርብ፣እሩቅ በመጠቀም ሁለት ነገሮችን አወዳድረው እንዲናገሩ ይጠይቋቸው

## ተግባር 5:- በፕሮጀክት መማር (4 ክፍለ ግዜ)

### ሀ. መለጠፍ (4 ክፍለ ግዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** የብር ኖቶችን፣ ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! የኢትዮጵያን ሳንቲሞችና የብር ኖቶች ያሳዩአቸውና መለየት እንዲችሉ ያለማምዷቸው፡፡ በመቀጠልም ወረቀቶችን በመቆራረጥ የብር ኖቶችን በመሳል ህፃናቱ ማጣበቂያ ኮላ/ግሉ በመጠቀም ደብተራቸው ላይ እዲለጥፉ ያድርጉ፡፡ በጨረሻም እጃቸውን በውሃና በሳሙና መታጠብ እንዳለባቸው ይንገሯቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተቆራረጡ ወረቀቶችን (ስእሎችን) የብር ኖቶች ስዕል
- **የምዘና ስልት:-** ምን ያህል እንደሰሩ ቆጥረው እንዲናገሩ መጠየቅ፡፡

## ተግባር 6:- በስራ መማር (4 ክፍለ ግዜ)

### ሀ. አካባቢን ማፅዳት (4 ክፍለ ግዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** አካባቢን ማፅዳት
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** ስራ በመስራት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ሁሉንም ህፃናት በቡድን ሆነው እንዲደራጁ ይንገሯቸው፡፡ ይህንን ተግባር በራሳቸው እንዲያደርጉ እድል ይስጧቸው፡፡ ህፃናቱ ተመራርጠው ሲጨርሱ እርስ በርስ እንዲተዋወቁ ያድርጉ፡፡
  1. የጽዳት ሰራተኛን ሚናን በመወከል (የጽዳት ቁሳቁስን፣ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች፣ በመጠቀም የት/ቤት ግቢን ማፅዳት)
  2. ቡድኖቹ ስራቸውን ሲያጠናቅቁ የሰሩባቸውን ቁሳቁሶች በቦታቸው እንዲመልሱ ያድርጉ
  3. በመጨረሻም እጃቸውን እንዲታጠቡ ያድርጉ
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የጽዳት ቁሳቁስ፣ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች፣
- **የምዘና ስልት:-** በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ስንት የቡድን አባላት እናዳሉ ቆጥረው እንዲናገሩ መጠየቅ

# የአውድ አምስት ምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም -----------------------------ጾታ-------- እድሜ ------ደረጃ-------

መግለጫ:- ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሟሉት ብቃት ትይዩ የ "√" ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ።

| ተ.ቁ | የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት | ጥሩ | በ/ጥሩ | እ/በ/ጥሩ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቤት ውስጥና የቤት ውጪ ቁሳቁሶችን መለየት | | | | |
| 2 | ፊደላትን ደጋግመው መጻፍ | | | | |
| 3 | ቀላል ቃላቶችን ማንበብ | | | | |
| 4 | ከ6 እስከ 9 ድረስ ያሉ ነገሮችን መቁጠር | | | | |
| 5 | ከ6 እስከ 9 ድረስ ያሉ ቁጥሮችን ደጋግመው መጻፍ | | | | |
| 6 | ከ6 እስከ 9 ድረስ ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል መደርደር | | | | |
| 7 | የሚታወቁ የምግብና የመጠጥ ዓይነቶችን መለየት | | | | |
| 8 | የቤት እንስሳቶችን ስም መጥራት | | | | |
| 9 | ትህትናን የተላበሰ ባህሪያቶችን ማሳየት | | | | |
| 10 | የሚወዱትንና የሚጠሉትን ነገሮች መግለጽ | | | | |
| 11 | ስሜታቸውንበተገቢው ሁኔታ መግለጽ | | | | |
| 12 | ጓደኝነት መመስረት | | | | |
| 13 | የባህላዊ ውዝዋዜ/ጭፈራዎችን አስመስለው መጫወት | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፦ ______________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________

# አውድ ስድስት

# ጊዜ

አጠቃላይ የተሰጠ ጊዜ- 6 ሳምንት

የክፍለ ጊዜ ብዛት- 180 ክፍለ ጊዜ

## 6.1 መግቢያ

ህፃናት "ጊዜ" በሚለው ዓውድ ውስጥ የተጠቀሱትን ይዘቶች ማለትም፡- ራስን ማወቅ፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ ማንበብ፣ የሰውነት ክፍሎች፣ ንፅህናን መጠበቅ፣ ቁጥርን መቁጠር፣ ፊደላትን መጻፍ፣ ቁጥርን መጻፍ፣ ውበትን መግለጽ እና ገንዘብ የመሳሰሉትን የአውዱን ይዘቶችን ለመገንዘብ የሚያስችላቸውን መሰረታዊ ክህሎቶች የሚያዳብሩበትና በእድሜ ደረጃቸው ሊያጎለብቱ የሚገባቸውን አካላዊ፣ ሥነልቦናዊና ማህበራዊ ዕድገታቸውን ሊያዳብሩ የሚችሉበት የትምህርት መስኮች ተካተዋል፡ ፡ ለአውዱ ስድስት ሳምንታት የተመደለት ሲሆን በስድስቱ ሳምንታት ውስጥ የተቀመጡትን አጥጋቢ የመማር ብቃቶች እና ዝርዝር የአተገባበር ስልቶችን መሰረት በማድረግ መምህራን የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ሲገቡ ህፃናት በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ የዕለት ተዕለት ተግባራት (የግል ተግባር፣ ተረት/እንቆቅልሽ፣ መዝሙር፣ የክፍል ውጭ ጨዋታ፣ በፕሮጀክት መማር፣ በሥራ መማር፣ ውይይት፣ የመስክ ጉብኝት፣ የክፍል ውስጥ ጨዋታ) በማከናወን ራሳቸውን እና ጓደኞቻቸውን ስለ ጊዜ ጠቀሜታና አጠቃቀም እንዲያውቁና እንዲረዱ አስፈላጊውን ድጋፍ መምህሯ/ መምህሩ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

## 6.2 የመማር ውጤቶች፡-

- የፊደላት ድምጾችን ይለያሉ
- የት፣ ምን፣ መቼ፣ ማን እና የትኛው የሚሉትንቃላትንተጠቅመው ስለራሳቸው ይገልጻሉ
- ለድምጾች ምላሽ ይሰጣሉ
- ፊደላትን ደግመው ይጽፋሉ
- የተነገራቸውንተረትመልሰውይናገራሉ
- ከ1-5 የሆኑ ቁሶችን ተጠቅመው ይደምራሉ
- እስከ ዘጠኝ ያሉ ቁሶችን ይቆጥራሉ
- ነጠላ- ድርብ፣ ደርብ- ድርብ ሥርዓተ ጥለት(Pattern) ይደረድራሉ

- የቤታቸውንና ት/ቤታቸውን አቅጣጫ ይለያሉ
- በቤተቻውናት/ቤታቸውያሉ እጸዋትን ይለያሉ
- ጤናማ የሆኑ ምግቦችንና መጠጦችን ይገልጻሉ
- በግንባታ ብሎኮች ውስጥ በመሳተፍ ትንንሽ ቤቶችን ይገነባሉ፣ ቁሶቸን መልሰው በመጠቀም ለግንባታ ጥቅም ላይ ያዉላሉ
- 3D ምስል፣ ስማርትፎን፣ ላፕቶፕ፣ ቲቪየመሳሰሉየቴክኖሎጂመሳሪያዎችን ይለያሉ፡፡
- የሰውነትና የቦታ ግንኙነትን ከቁስና ከሌሎች አንጻር ያሳያሉ
- በአዋቂዎችድጋፍ ግጭቶችን ይፈታሉ
- የሚወዱትንየሚጠሉትንነገሮችይገልጻሉ
- የሚያወቆቸውን ጀግናዎቻቸውን ስም ይጠራሉ
- በሌሎች ድጋፍ ከሁለት አማራጮች  መካከል መምረጥ ይችላሉ
- ከ3-5 የሚሆኑ አካላዊ እንቅስቃሴ ለምሳሌመወርወር፣መያዝ፣መንከባለል፣ መምታት፣ መጠለዝ የመሳሰሉ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ፡፡
- የፕላስቲክ መቀሶችን በመጠቀም የትምህርት መማሪያ ቁሳቁስችን ይቆርጣሉ
- የሚወዱትን ቀለም፣ መጠን እና ቅርጽ ይመርጣሉ

## 6.3 የአውዱ አበይት ይዘቶች

- ራስን ማወቅ፣
- ራስን ማስተዋወቅ፣
- ማንበብ፣
- የሰውነት ክፍሎች፣
- ንፅህናን መጠበቅ፣
- ቁጥርን መቁጠር፣
- ፊደላትን መጻፍ፣
- ቁጥርን መጻፍ፣
- ውበትን መግለጽ፣እና
- የተመጣጠነ ምግብ
- የቅርብ አከካቢ
- ጥበባዊ  ዋጋ
- ሞራል እሴት
- መደመር
- ጥበብን መግለጽ
- የመግባባት ችሎታ
- እንሰሳት
- ትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር
- መሀበራዊ ግንዛቤ
- እጸዋት
- ትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር
- ሥርዓተ ጥለት
- የድምጽ ግንዛቤ
- የቦታ ግንዛቤ
- ማገናኘት፣ግንኙነትንና መተግባር
- መቀነስ
- ጥንቃቄና መከላከል
- የመወሰን ችሎታ
- ቴክኖሎጅ መጠቀምና ቅድመ ምህድስና ችሎት
- ጊዜ
- ሀገር ወዳድ
- ራስን መገንዘብ

# ሀያ ሰባተኛ ሳምንት

## የተሰጠው ሰዓት---10 ሠዓት (30 ክፍለ ጊዜ)

### የሳምንቱ አጥጋቢ መማር ብቃት

- መምህራናቸውንና ቤተሰባቸውን ያስተዋውቃሉ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- በቤተሰብ ውስጥ ያላቸውን ሚና ይገልጻሉ
- የአካባቢያቸውን ንጽህና ይጠብቃሉ
- ሻጭና ገዥን በሚና ጨዋታ ያሳያሉ
- እስከ ዘጠኝ ብዛት ያላቸውን በቁሳቁሶች ይቆጥራሉ
- ከሰባት እስከ ዘጠኝ ያሉ ቁጥሮችን ደጋግመው ይጽፋሉ
- ፊደላትን ደግመው ይጽፋሉ
- የተለያዩ የሰውነት ክፍል ቅርጾችን በመጠቀም የሰውን አካል ክፍሎች ይገጣጥማሉ
- የሰውነት ክፍሎችን ይስላሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ራስን ማወቅ
- ራስን ማስተዋወቅ
- የሰውነት ክፍሎች
- ንጽህና መጠበቅ
- ፊደል መለየት
- ቁጥር መቁጥር
- ጥበባዊ ግንዛቤ
- የገንዘብ ግንዛቤ
- ገንዘብ
- ጤና

## ተግባር 1፡- የግል ተግባር (7 ክፍለ ጊዜ )

### ሀ. ፊደላትን ደግመው መጻፍና ማንበብ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል፣ ቃላት፣ የሰውነት ክፍል፣ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የሰውነት ክፍል የሚያሳይ ቻርት በመጠቀም እርሶ ቻርቱን

በመንካት አይን ሲያሳዩ ልጆቹ የራሳቸውን አይን በመንካት እንዲያሳዩ፤ ግንባር ሲነኩ ህጻናቱን በተመሳሳይ የሰውነት ክፍላቸውን በመንካት እንዲያሳዩ ያድርጉ:: በመቀጠል ህጻናቱ በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ በእናት ፊደላት የሚጀምሩ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን የሚገልጹ ቃላት ከሥዕል ጋር በማጣመር እንዲያነቡ (ለምሳሌ:- አ ..አፍ. አ... አፍንጫ፣ አ... አይን፣ ወ... ወገብ፣....ደ...ደረት.../ እና እንዲጽፉ ያድርጉ:: በመጨረሻ ያነበቡትና የፃፉትን ቃላትና ፊደላት ስንት እንደሆኑ እንዲቆጥሩ ያድርጉ::

- **የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የሰውነት ክፍልን የሚገልጹ የቃላት ገበታ፣ የሰውነት ክፍል የሚሳይ ቻርት፣መለመማጃ ደብተር
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ (ለምሳሌ:- በትክክል የሰውነት ክፍላቸውን ማሳየታቸውን፣ፊደላት የተመሰረቱ ቃላትን በፍላሽ ካርድ እንዲያነቡ በማድረግ፣ የፃፉትን ቃላትና ፊደላት ስንት እንደሆኑ እንዲቆጥሩ በማድረግ...) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- ፊደላትን፣ ቃለት፣ የሰውነት ክፍሎችን....)

## ለ. ቁጥሮችን መጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ቁጥር፣ የገንዘብ ግንዛቤ፣ ሚና ጨዋታ
- የማስተማርያ ዘዴ:- በተግባር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ለህፃናቱ በቁጥር ሎቶ ላይ የተዘጋጁ ቁጥሮችን ተጠቅመው ቁጥሩን እያሳዩ ከ 7 እስከ 9 ያሉትን ደግመው እንዲፅፉ ያድርጉ:: በመቀጠል የተለያዩ የገንዘብ ኖት ሞዴል ያሳዩአቸው:: ቀጥሎ ህፃናቱን በቡድን አደራጅተው የሻጭ እና ገዥን ሚና እንዲከውኑ ያድርጉ::
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የቁጥር ሎቶ፣ የተለያዩ ገንዘብ ኖታዎች፣ወረቀት፣ እሳስ፣ደብተር የሻጭ እናየገዥ እቃዎች ያለበት የጨዋታ ማዕዘን...
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ (ለምሳሌ:- ገዥና ሻጭ ሆነው በአግባቡ ስለመከወናቸው) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- ቁጥሮችን መጠየቅ፣ ምን አይነት እቃ እንደገዙ መጠየቅ፣ እቃዉን ስንት ገዛኻው/ሽው? የብር ኖቶችን ዋጋ መጠየቅ)

## ሐ. ራስን ማስተዋወቅ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ራስን ማስተዋወቅ፣ ልብስ፣ ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተግባር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ በቤተሰብ ዉስጥ ስላላቸው ሚናና ራሳቸውን እንዴት እንደሚንከባከቡ ለክፍል ጓደኞቻቸው ከመቀመጫቸው ተነስተው እንዲገልጹ ወይም እንዲያስተዋዉቁ ያደርጉ:: ራሳቸውን ሲያስተዋውቁ ስለለበሱት ልብስ የቀለም አይነት (ለምሳሌ: - የለበስኩት ሱሪ ቀለም ቀይ ነው፣ ቀሚሴ ነጭ ነው......) እያሉ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው::
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የቤተሰብ አባላት ሥዕል፣ ራስን መንከባከብ የሚያሳይ ሥዕል፣ የአልባሳት ሥዕል

- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ(ለምሳሌ፡- ራሳቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን በተገቢው ሁኔታ ማስተዋወቃቸውን) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- እራስሽ/ክን እንዴት ትንከባከቢያለሽ/ህ ምን ዓይነት ስራ በመስራት ቤተሰብህን/ሽን ታግዛልህ/ሽ?)

## ተግባር 2- ተረት (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ታዛዡ ሀብታሙ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት**:- ቁጥር፣ ምስጉን፣ ስፖርት፣ደስተኛ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱ ተረቱን በምስል በማስደገፍ ያንብቡላቸው፡፡

ተረት ተረት!

አንድ ሀብታሙ የሚባል ልጅ ነበር፡፡ ሀብታሙ የ4 ዓመት ህጻን ሲሆን ለቤተሰቡ ታዛዥ በሥነ-ምግባሩ ምስጉን ልጅ ነው፡፡ ሀብታሙ በዕረፍት ቀኑ (ቅዳሜና እሁድ) በጠዋት በመነሳት በቤታቸው አከባቢ ባለው የስፖርት ሜዳ ከታላቅ እህቱ ጋር ስፖርት ይሰራል፡፡ ከሚሰራቸው የስፖርት አይነቶች ውስጥ አንዱ ገመድ መዝለል ሲሆን እህቱ ገመድ ስትዘል እሱ 1..2..3..4....5...6...7..8..9 እያለ በመቁጠር ስንት ጊዜ እንደዘለለች ይነግራታል፡፡ ሀብታሙ ስፖርት በመስራቱ በጣም ደስተኛና ጤናማ ነው፡፡ የተለያየ አይነት አካላዊ እንቅስቃሴ ካደረገ በኂላ ወደ ቤቱ ሲመለስ ገላውን ከታጠበ በኂላ ቁርስ በልቶ እናቱን በስራ ያግዛል፡፡ በዚህም ባህሪው በቤተሰቡ በጣም ተወዳጅ ልጅ ነው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቁጥር ሎቶ፣ እስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ስዕሎች፣ ህፃናት ቤተሰብን በስራ ሲያግዙ የሚያሳይ ሥዕል…
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የሀብታሙ እህት ገመድ እስከ ስንት ዘለለች? የሰሙትን ተረት እንዲናገሩ ማድረግ፣ ሀብታሙ ቤተሰቡ ውስጥ ተወዳጅ ልጅ የሆነው በምን ምክንያት ነው…)

### ለ. ጓደኞሞቹ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት**:- ሥዕል፣ ፊደላት፣ መፃፍ፣ ቃላት፣ ማንበብ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ተረቱን ለህጻናቱ በመሚመቻቸው መልኩ ያንብቡላቸው

ቀጥሎ ወረቀት/ደብተር፣ እርሳስ እና ቀለም በመስጠት የሰው ስዕል እንዲስሉ ያድርጉ፡፡

**ተረት ተረት!**

ዓሊ እና ናትናኤል የሚባሉ በጣም የሚዋደዱ ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ ከትምህርት ቤት ሲመለሱ ልብሳቸውን ቀይረው አንድ ላይ ይጫወታሉ፡፡ ከሚጫወቷቸው ጨዋታዎች መካከል በወረቀት ወይም በአሸዋ ላይ የህጻናት ሥዕል መሳል፣ የተለያዩ ሥዕሎችን በማየት ስዕሉ ምን እንደሆነ መናገር፣ መምህራቸው ያስተማሯቸውን ፊደላት በመገጣጠም ቃለት መመስረት፣ ቃላት ማንበብ ጥቂቶቹ ናቸው፡

፡ የሚጫወቱት ጨዋታ ከትምህርታቸው ጋር ግንኙነት ያለው በመሆኑ በትምህርታቸው በጣም ጎበዞች ስለሆኑ ከመምህራኖቻቸው የተለያዩ ሽልማቶችን በየጊዜው ይሸለሙ ነበር፡፡

- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ:-** እርሳስ፣ የሥዕል ወረቀት፣ ከለር፣ አሸዋ፣ የቃላት ፍላሽ ካርድ
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ተረቱን በአግባቡ ማዳመጣቸውን መመልከት፣ ሥዕሉን በአግባቡ መሳላቸውን መመልከት) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ዓሊ እና ናትናኤል የሚጫወቷቸው ጨዋታዎች ምን ምን ነበሩ? ተረቱን ለጓደኞቻቸው እንዲነግሯቸው መጠየቅ፣ የህጻን ምስል እንዲስሉና ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ማደረግ)

## ተግባር 3- መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የጊዜ ጥቅም (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቁጥር፣ ፊደል፣ ሰዓት
- **ማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ግጥሙንና ዜማውን እስኪይዙት ድረስ ደጋግመው ያስዘምሯቸው፡፡

**የጊዜ ጥቅም**

ጨለማው ተገፎ ፀሀይዋ ስትወጣ፣

ሰዓቱ ደርሶብን ከቤት ስንወጣ፡፡

ፊደልን ልንማር ክፍል ስንገባ፣

ቁጥሮች ተሰቅለዋል፣

በጣምም አምረዋል፡፡

ፊደሎችም አሉ እንዴት ደስ ይላሉ፣

መሸ እኮ ሰዓቱ እንሂድ ቤታችን፣

ስለሚጠብቁን ቤተሰቦቻችን፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የሰዓት ሥዕል፣ ጠዋትና ማታን የሚያሳይ ሥዕል፣ የቁጥር እና የፊደል/የቃላት ፍላሽ ካርድ/ቻርት
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ትምህርት ቤት የምንሄደው መቼ ነው፣ ወደ ቤት የምንሄደው መቼ ነው፣) እና ምልከታ (ለምሳሌ፡- ሲዘምሩ መከታተል)

### ለ. እንድሆን አንደኛ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሰዓት፣ ጠዋት፣ ጊዜ
- **ማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር

- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ ግጥሙና ዜማውን በአንድ ግዜ ላይዙት ችላሉ ስለዚህ ሁሉም ህጻናት እስኪይዙት ድረስ ደጋግመው ያሰሯቸው

እንድንሆን አንደኛ
ጠዋት በማላዳ፣ከአንቅልፌ እነቃና፣
የጠዋት ተግባርን አከናውንና፣
እራሴንም በደንብ እንከባከብና፣
አንድ ሰዓት ሲሆን ቦርሳዩን ይዝና፣
ወደ ትምህርት ቤት እያልኩ ዘና ዘና።
ፊደሉን ተምረን ቃላት አንብበን፣
ስድስት ሰዓት ሲሆን ምሳ እንበላለን።
ጊዜውም እሮጠ እየገሰገሰ፣
ዘጠኝ ሰዓት ሆነ መውጫችን ደረሰ።
እቤቴ ገብቼ ላግዝ ቤተሰቤን፣
ልብሴንም ላጣጥፍ ልጠበው ዕቃውን።
ደግሞም ተጣጥቤ በጊዜ ልተኛ፣
በጠዋት ተነስቼ እንድሆን አንደኛ። (2 ጊዜ)

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ጊዜያትን የሚሳዩ ሥዕሎች፣ የዘውትር ተግባርን የሚያሳዩ ሥዕሎች…
- **የምዘና ስልት:-** ምልከታ (ለምሳሌ:- መዝሙሩን በትክክል መዘመራቸውን መመልከት) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- ፀሀይ ስትወጣ ያለው ጊዜ ምን ይባላል? ጨለማ ሲሆን ያለው ግዜ ምን ይባላል? ጠዋት ምን ተግባር እናከናውናለን፣…)

## ተግባር 4- የክፍል ውጭ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ተከታዩን ቁጥር ማነው (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ቁጥር፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ መታጠብ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፦** መምህር! ህፃናቱን ወደውጭ ይዘው በመውጣት ሴትና ወንድ የተቀላቀሉበት ቡድን ያደራጁ። በመቀጠል ከ1-9 ቁጥሮች የተጻፉባቸውን ካርዶች በማዘጋጀት በጠረጴዛ ላይ አዘበራርቀው ደፍተው ያስቀምጡ። ቀጥሎ ሁለት ተወዳዳሪ ቡድኖችን ያስወጡ። ተወዳዳወሪ ቡድኖቹ ጎን ለጎን ይሰለፋሉ። ቁጥር የያዘው ጠረጴዛ መሃል ይደረጋል። ከዚያ ጨዋታውን ከመጀመራቸው በፊት የራሳቸውንና የቡድናቸው ስም ያስተዋውቃሉ። ጨዋታው ከተረኛ ቡድን ውስጥ አንድ ህጻን አንድ ካርድ አንስቶ የሳያል። የቀጣዩ ቡድን ተረኛ ደግሞ የተነሳውን ቁጥር ተከትሎ የሚመጣውን ቁጥር ፈልጎ ማሳየት ነው። የተሳሰተ ከቡድኑ ይቀነሳል መጨረሻ የቀሩት አሸናፊ ይሆናሉ። በዚህ መሰረት ሁሉም ቡድኖች በየተራ ይጫወታሉ። ሲጨርሱ ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት እጃቸውን እንዲታጠቡ ያድርጉ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የቁጥሮ ሎቶ፣ ጠረጴዛ

- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ጨዋታውን በአግባቡ መጫወታቸውን መመልከት) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ያነሱት ቁትር ስንት እንደነበር መጠየቅ)

## ተግባር 5 የክፍል ዉስጥ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. መስሎ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ንጽህና፣ እንክብካቤ፣ ሀኪም
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን ወደ ህክምና ኮርነር ይወስዱና ኮርነሩን ተጠቅመው እንዲጫወቱ ያድርጓቸው። ለምሳሌ አንድ ህጻን፣ ሀኪም፣ አንድ ህጻን እናት እና አንድ ሌላ ህጻን ደግሞ ልጅ በማድረግ ይመድቡ። ከዚያም እናትየዋ የልጇን የጸጉሯንና የልብሶቿን ንጽህና ስለማትጠብቅላት እንዲሁም ልጅቷም ራስዋን ስለማንትከባከብ ትታመማለች። ከዚያም ወደ ህክምና በመውሰድ ልጄን አሞብኝ ነው ብላ ለሃኪም ትነግራለች። ዶክተሯም የልጅሽ መታመም ዋናዉ መንስኤ የንጽህና አለመኖር እና እንክብካቤ ማጣት ነው። ንጽህናው ያልተጠበቀ ምግብ በመብላቷና ምግብ ከመመገቧ በፊት እጆቿን ስለማትታጠብ ነው በማለት ምክርና መድሀኒት በመስጠት ያሰናብቷቸዋል።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የህክምና ሞደል መሳሪያዎች፣ የግል ንፅህና አጠባበቅ የሚያሳይ ስዕል/ሞዴል..
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ጨዋታውን በመከታተል በትክክል የተገበሩና ያልተገበሩ ህጻናትን መለየትና መደገፍ) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡-ህጻኗ የታመመችው ምን ሆና ነው? እራሳቹን እንዴት ትንከባከባላችሁ፣ የግል ንጽህና እንዴት ይጠበቃል...)

## ተግባር 6- በፕሮጀክት መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የፕሮጀክት ስራ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል፣ጽዳት፣ ገለጻ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ተገቢውን ስራዎች እንዲሰሩ መከታተል ንፁህ አፈር፣ ውሃና ሣህን (አርቲፊሻል ጭቃ) ያዘጋጁላቸውና ሁሉም ህፃናት ቀድመው የተዋወቋቸውን ፊደላት ( ሀ ፣በ፣ ተ፣ ቸ፣ ቀ ....) እንዲሰሩ ያድርጉ። ሰርተው ሲጨርሱ የሰሩበትን አከባቢ በአግባቡ እንዲያጸዱና የተጠቀሙበትን ቁሶች በየቦታቸው እንዲመልሱ ማድረግ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም እጃቸውን እንዲታጠቡ ካደረጉ በኋላ ስለፕሮጀክታቸው ገለጻ እንዲያደርጉ እድሉን ያመቻቹላቸው። ከዚያም ስራቸውን በአግባቡ በሚታይበት ቦታ በክፍሉ ውስጥ ያስቀምጡላቸው።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** አፈር፣ አርተፊሸል ጭቃ፣ ውሃ፣ ሳህን
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- የፊደላቱን ሞደል በትክክል ስለ መስራታቸው) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ምን ሰራችሁ፣ የፊደላትን ቅርጽ ጠብቀው ስለ መስራታቸው)

# ሀያ ስምንተኛ ሳምንት

## የተሰጠው ሰዓት-----10 ሰዓት (30 ክፍለ ጊዜ)

### የሳምንቱ አጥጋቢ የዕድገትና የመማር ብቃት

- አስቸጋሪ ስሜቶችን ይቆጣጠራሉ
- ድምጽን ለይተው ምላሽ ይሰጣሉ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- የቤታቸውንና የትምህርት ቤታቸውን አቅጣጫ ይለያሉ
- ስለጤናማ ምግቦችና መጠጦች አይነቶች ይናገራሉ
- ከ1 - 9 የሚደርሱ ቁጥሮችን በቁስ/ በተቆጣሪ ነገሮች ይደምራሉ
- ፊደሎችን ደግመው ይፅፋሉ
- ሥዕሎችን ቀለም ይቀባሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ራስን መቆጣጠር
- ድምጽ መለየት
- ንባብ
- አካባቢን መገንዘብ
- ጤናማ ምግብና መጠጥ
- ፊደል መጻፍ
- መደመር
- ቀለማትን መለየት

## ተግባር 1፡- የግል ተግባር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቁስ መደመር (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መደመር፣ አስቸጋሪ ስሜት፣ጠጠር፣ብይ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን የመደመር ጽንሰ ሀሳብ ለማስተማር ቀላሉ ዘዴ ተቆጣሪ በሆኑ ቁሶች አማካኝነት ድምርን ማስተማር ነው፡፡ ለዚህ እንዲረዳን የተለያዩ ተቆጣሪ የሆኑ እና በአከባቢያቸው በቀላሉ የሚያገኟቸውን ነገሮች ለማሳሌ፡- (ጠጠር /ዘንጎች/ ቆርኪ/ ብይ) የመሳሰሉትን ቁሶች በማዘጋጀት በህጻናቱ ፊት ለፊት በትናንሽ ካርቶን ወይም ሳህን ላይ ካስቀመጡ በኋላ አንድ ህጻን በማስነሳት ከአንዱ ካርቶን ውስጥ 1 ጠጠር /ብይ/ ከሌላው ካርቶን ወስጥ ደግሞ 1 ጠጠር /ብይ/ በማስነሳት ስንት ጠጠር/ብይ/ እንዳለው እንዲናገር /እንድትናገር

ማድረግ፡፡ ሁሉንም ህጻናት በዚህ መልኩ እንዲሳተፉ ያድርጉ፡፡ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ህጻናት ካሉ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያድርጉ፡፡ እንዲሁም በሚሰሩበት ወቅት አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ተቋቁመው እና እራሳቸውን ተቆጣጥረው እንደገና መሞከር እንዲችሉ ይንገሯቸው፡፡ ከዚያም በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ተቆጣሪን የመደመር ተግባር ይስሩ፡፡ ለምሳሌ፡-



2 + 3 = □



2 + 2 = □

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያዩ የሚደመሩ ተቆጣሪ ቁሶች፣ እርሳስ ደብተር / ወረቀት / በቻርት የተዘጋጀ የተደማሪ ቁሶች
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ቁጥሮችን በአግባቡ መቁጠራቸውን፣) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ሁለት ነገር ላይ ሁለት ስንጨምር ስንት ይሆናል?)

### ለ. ፊደል መፃፍ እና ቃላት ማንበብ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መፃፍ፣ ማንበብ፣ ፊደላት፣ቃላት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለክፍለ ጊዜው የሚያስፈልገውን የፊደል ሳጥን፣ እርሳስ፣ ደብተር/ወረቀት ያዘጋጁና በጠረጴዛቸው ላይ ያስቀምጡ፡፡ ሁሉም ህጻናት በጠረጴዛቸው ላይ ከቀረበላቸው ሳጥን ውስጥ የሳምንቱን ፊደል በመውሰድ ተገቢዉን የአፃፃፍ ስርዓት ተከትለው ደጋግመው ይፃፉ፡፡ ሁሉም ህፃናት የፃፉትን መ፣ረ፣ወ፣ደ፣ጀ ፊደል ድምፅ ያሰሙ፡፡ እንዲሁም ፊደላቱን በአካባቢያቸው ካለ በፊደላቱ የሚጀምር ነገር ጋር ያዛምዱ (መ..መኪና፣ ወ....ወፍ... .ደ...ደስተኛ....)፣ በተዋወቋቸው ፊደላት የተመሰረቱ ቃላትን ያንብቡ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** እርሳስ፣ ደብተር /ወረቀት/፣ የፊደል ሳጥን፣ የቃላት ፍላሽ ካርድ...
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- በትክክል መጻፋቸውን) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የፃፍከው/ሽው ፊደል ማነው፣ድምፁ አሰማ/ሚ፣ ስትጽፉ የቱ አስቸገራችሁ)

### ሐ. ሥዕል መሳል እና መቀባት (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ምግብ፣ ቀለም፣ብዛት፣ሥዕል፣ትርጉም
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለህፃናቱ የመማሪያ ግብዓቶችን ለምሳሌ ጤናማ የሆኑ የምግብ/ ፍራፍሬ ስዕሎችንና/ሞዴል ቀለማትን ያቅርቡላቸው፡፡ የቀረበላቸው ፍራፍሬና የምግብ አይነቶች ጥቅም ያብራሩላቸው፡፡ የፍራፍሬ አይነቶቹን የቀለም ቅብ ስርዓቱን ጠብቀው እንዲቀቡ፣ የተቀባውን ሥዕል ትርጉም ሰጥተው እንዲያነቡና እንዲገልፁ ዕድል ይስጧቸው፡፡ የተቀቡትን ሥዕሎች ብዛት ይናገሩ፡፡ ተግባራቱን በየግላቸው ሲተገብሩ እርስዎ በተቻለ መጠን በተገቢው ሁኔታ እያከናወኑ መሆናቸውን አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያድርጉ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ቀለማት፣ የምግብ/ ፍራፍሬ ሥዕል ቻርት
- **የምዘና ስልት፡- ምልከታ (ለምሳሌ፡-** በአግባቡ መቀባታቸውን መመልከት…) እና የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የቀቡትን ሥዕል ምን እንደሆነ መጠየቅ፣ስንት ሥዕል እንደቀቡ፣ የቀለሙ አይነት)

## ተግባር 2- መዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቤቴን አየሁት (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ክረምት፣ሰማይ፣ አቅጣጫ
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! መዝሙሩን ከህጻናቱ አብሮ በጋራ መዘመር ያበረታቷቸው፡፡

**ቤቴን አየሁት**

ጊዜው ክረምት ስንጫወት፣
ጉም ጉም አለ ከላይ ካናት፡፡
ሰማዩን ስናይ ደግሞ ወደ ላይ፣
ዝናቡ ወረደ በላያችን ላይ፡፡
እንሩጥ እንጂ ወደ ቤታችን፣
እንዳይበሰብስ ደግሞ ልብሳችን፡፡
ቤቴ ጠፍቶብኝ ደግሞ እንዳልፈራ፣
በቀኝ በግራ እስቲ ላጣራ፡፡
ቤታችን በየት ነው አረ ንገሩኝ፣
መላ ፍጠሩ አቅጣጫው ጠፋኝ፡፡
ሱቁ አጠገብ ነው የእናንተ ቤት፣
የኛ ከእናንተ ነው ፊት ለፊት፡፡
ኑ ጓደኞቼ በቀኝ እንሩጥ፣
በዚህ በኩል ነው ቤቴን አየሁት፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያዩ አቅጣጫን የሚጠቁሙ ሥዕሎች፣ ዝናብ ሲመጣ እና ሲዘንብ የሚሰማ ድምፅ (የተቀረፀ)፣ መዝሙር (ከተቻለ የተቀረፀ)
- **የምዘና ስልት፡- ምልከታ (ለምሳሌ፡-** መዝሙሩን በአግባቡ መዘመራቸውን…..)የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ድምፁን የሰማችሁት ከየት አቅጣጫ ነው? ዝናብ ሲመጣ ምን አይነት ድምጽ ያሰማል? የአንደኛዋ ልጅ ቤት በየት በኩል ነበር?)

### ለ. ምግብ ጠቃሚ ነው (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ምግብ፣ ማመጣጠን፣ ጤና
- **የማስተማር ዘዴ፡-** በመዝሙር

- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለመዝሙሩ አስፈላጊ መጫወቻና መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ያዘምሩዋቸው፡፡

**ምግብ ጠቃሚ ነው**

ምግቦች፣ ምግቦች በጣም ይጥማሉ፣
ለሰው ልጆች ጤና በጣም ይጠቅማሉ፡፡
በገበታው ላይ ያለው ምግብ፣
አረንጓዴ ቀይ አቤት ሲያምር፡፡ /2/
ልጠጣው ስጡኝ ውሃና ወተት፣
አስፈላጊ ናቸው ሁሉም ለጤንነት፡፡
ምግብ ለሰው ልጅ አስፈላጊ ነው፣
ከሁሉም አይነት ማመጣጠን ነው፡፡ (2)

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የምግብ ስዕል /ምግብ/፣ የፍራፍሬ ስዕል /ፍራፍሬ/ ፣የሚጠጡ ነገሮች
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- መዝሙሩን በአግባቡ መዘመራቸውን መመልከት) የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡-ምግብና መጠጥ ጥቅማቸው ምንድን ነው…)

## ተግባር 3፡- ተረት (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ቃሊ እና ለቲ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት ፡-** አካባቢ፣ ምልክት፣ ጓደኛ፣ መደመር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ተግባር፡-** መምህር! ህጻናቱን ዝግጁ በማድረግ ተረቱን መንገር፣ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ እና ከተረቱ የወጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይኖርብዎታል፡፡

**ተረት ተረት!**

በድሮ ጊዜ ሁለት የሚዋደዱ ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ ስማቸውም ቃሊ እና ለቲ ይባላል፡፡ እነዚህ ጓደኛሞች በአንድ አከባቢ የሚኖሩ በአንድ ት/ቤት የሚማሩ ናቸው፡፡ ለቲና ቃሊ ሁልጊዜ በትምህርት ቤት በዕረፍት ሠዓት እየተገናኙ ይጫወታሉ፣ ጠቃሚ ምክሮችን ይለዋወጣሉ፡፡ አንድ ቀን በዕረፍት ሰዓታቸው በዛፍ ፍሬ ቁጥር መደመር መጫወት ጀመሩ፡፡ አንድ ፍሬ ሲደመር ሁለት ፍሬ ይሆናል ሶስት፤ አራት ፍሬ ሲደመር አንድ ፍሬ አምስት፡፡ እየተባባሉ ሲጫወቱ ቃሊ በመሃል ትናትና እኮ ውጭ ላይ ተጫውተን ወደ ቤት ልመለስ ስል ቤታችን ጠፍቶብኝ እናቴ መጥታ ወሰደችኝ አለቻት፡፡ ለቲ ደግሞ በጣም ያሳዝናል አንቺ በመንገድ ላይ ስትሄጂ በአካባቢሽ ያሉትን ነገሮች ምልክት ማድረግ አለብሽ እሺ! ሱቆቹን፣ ሃኪም ቤቱን፣ መስጊዱን፤ ቤተክርሲቲያኑን ምልክት አድርጊ! አለቻት፡፡ ቃሊም እሺ ጓደኛዬ አመሰግናለሁ አለቻት፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የዛፍ ፍሬ፣ የሱቅና የተለያዩ ተቋማት ሥዕል

- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ተረቱን እንዲተርቱ ማደረግ፣ የተለያዩ ፍራፍሬዎችንና ጠጠሮችን በመጠቀም እንዲደምሩ ማድረግ)

## ተግባር 4- የውጭ ጨዋታ (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ድምጽን ማስመሰል (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ድምፅ፣ ባህሪ፣ ማስመሰል
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱን ወደ ውጭ ያስወጡ እና በአምስት ቡድን ይክፈሏቸው፡፡ በመቀጠል ስለጨዋታው ህግ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ቡድን ቀጥሎ ያሉትን እንስሳት ባህሪ እንዲላበሱ (የአህያ፣ የጅብ፣ የዶሮ፣ የበቀቀን፣ የውሻ፣ የበግ ድምፅ አስመስለው እንዲያሰሙ ያድርጉ)፡፡

1. የጅብ ሚና የወሰዱት እንደ ጅብ እየጮሁ ወደ ሌሎቹ ህፃናት ይሄዳሉ፡፡ የተቀሩት እንደ እንስሳት እየሮጡ በአካባቢያቸው የሚገኙ ዛፎች ስር ይደበቃሉ፡፡
2. የአህያ ሚና የወሰዱት እንደ አህያ እየጮሁ ሳር ወዳለበት ይሄዱና ሳር እንደሚግጡ ያስመስሉ፡፡
3. የበቀቀን ሚና የተሰጣቸው ክንፋቸውን ዘርግተው እየበረሩ ሰው የተናገረውን መልሰው ይናገራሉ ( ሰላም .....ሰላም፣ በረረ ....በረረ)

- **መማሪያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተቀረጸ የተለያዩ እንስሳት ድምጾች፤ የእንስሳት ስዕል ( የበቀቀን ፣የጅብ ፣ ወዘተ)
- **የምዘና ስልት-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- የተሰጣቸውን ሚና በአግባቡ ስለመወጣታቸው) የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- እንስሳቶች እንዴት ጮሁ፣ ስለዕለቱ ጨዋታ መጠየቅ፣)

### ለ. ማዕዘን መበተን (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ድምፅ፣ ንጹህ፣ ማዕዘን፣መቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህርሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን ወደ ውጭ ይዘው በመውጣት በሁለት ቡድን ያደራጇቸው፡፡ በቡድናቸው ውስጥ ምን ያህል ህጻናት እንዳሉ ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በዚህ ጨዋታ ህጻናቱ የሚጫወቱበት ሜዳ ህጻናቱን ሊጎዳ ከሚችሉ ነገሮች የጸዳና ንጹህ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡ በመቀጠል አባራሪና ተባራሪ ሆነው በ2 ቡድን በመክፈል ተራ በተራ እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡ የአባራሪው አንድ ተጫዋች እጅ ለእጅ ተያይዘውና አራት ማዕዘን ሰርተው ከቆሙት ህጻናት አንዲነካ ይደረግና አራት ማዕዘኑ ይበተናል፡፡ አባራሪው በተራው ተባራሪ ይሆናል፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ከርዕሱ ጋር የሚጣጣም ምቹ አካባቢ
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ጨዋታውን በአግባቡ መጫወታቸውን መመልከት)

## ተግባር 5. በፕሮጀክት መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ምስል ማተም (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ቀለም፣ ቁጥር፣ፊደል፣ማተም፣መደመር
- **የማስተማሪያ ዘዴ:-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ቀለም በዝርግ ሰሀን ላይ ይበጥብጡ፡፡ በመቀጠል ወረቀት፣ ቅጠል ከካርቶን የተቀረጹ ቁጥሮች/ፊደሎች በማዘጋጀት የበጠበጡት ቀለም ላይ እየነከሩ ባዘጋጁላቸው ሰፊ ቻርት ወይም ወረቀት ላይ ቅርፁን ጠብቀው እንዲያትሙ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ያተሙትን ደምረው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ፊደለት፣ ቁጥሮች፣ ወረቀት፣ ቀለም፣ ቅጠል
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- ቁሶችን እንዲደምሩ መጠየቅ፣ያተሙትን ፊደል ስም መጠየቅ....) እና ምልከታ (ለምሳሌ:- ተግባሩን በትክክል መስራታቸውን መከታተል)

## ተግባር 6- በሰራ መማር (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. አከባቢ ንጽህና (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ኮርነር፣ማጽዳት፤ መደርደር፣ መታጠብ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በስራ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱን የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ያሉ ኮርነር እቃዎችን በየአይነታቸው እንዲደረድሩ/እንዲያዘጋጁ ያድርጉ፡፡ የኮርነር እቃዉን ደርድረው ከጨረሱ በኋላ በመማሪያ ክፍላቸው የወዳደቁ ወረቀቶችን በማንሳት ክፍላቸውን እንዲያጸዱ ያድርጉ፡፡ ስራቸውን ከጨረሱ በኋላ እጃቸውን በአግባቡ እንዲታጠቡ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት፣ ኮርነር እቃዎች
- **የምዘና ስልት:- የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:-** የአከባቢያችንን ንጽህና ለምን መጠበቅ ያስፈልጋል) እና ምልከታ(ለምሳሌ:- የተለያዩ ስራዎችን በአግባቡ መስራታቸውን መመልከት)

# ሀያ ዘጠነኛ ሳምንት

የተሰጠው ሰዓት-10 ሰዓት (30 ክ/ ጊዜ)

## አጥጋቢ የመማር ብቃት

- በአዋቂዎች ታግዘው ግጭቶችን ይፈታሉ
- የተለያዩ ሙዚቃዎችን ይዘምራሉ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- የእንስሳትን የሰውነት ክፍሎች ይለያሉ
- መቀስን ተጠቅመው የተለያዩ  የትምህርት ቁሳቁሶችን ይቆራርጣሉ፡፡
- ትንንሽ ቁሳቁሶች ይጠቀማሉ
- ባሕላዊ አልባሳትንና ቅርሶችን ይዘረዝራሉ
- ከ1-9 ያሉ ቁጥሮችን ይደምራሉ
- ሆሄያትን ደጋግመው ይጽፋሉ
- በህላዊ ዳንሶችን አስመስለው ይደንሳሉ
- ዋና ዋና የቀለም ዓይነቶችን በስም ይጠቅሳሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- ማኅበራዊ/የእርስ በርስ ተግባቦት
- ቃላትን ማወቅ
- ማንበብ
- እንስሳት
- ትንንሽ  ጡንቻዎችን ማዳበር
- ሆሔያትን መጻፍ
- መደመር
- ባህላዊ ቅረስ

## ተግባር1፡- የግል ተግባር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የክረምት ጊዜ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ክረምት፣በጋ፣ልብስ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በቅድሚያ ስለ ክረምት ጊዜ፣  ክረምትና በጋ የምንጠቀማቸው የአልባሳት ዓይነቶችና ቁሳቁሶች ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ሥዕሎችን በቻርት ላይ ይሳሉላቸውና

ብዛታቸውን እንዲቆጥሩና የአልባሳቱን ቀለም ዓይነት እንዲናገሩ ያድርጉ (ለምሳሌ በክረምት የሚለበሱ ካፖርት፣ ኮፍያ፣ ጃኬት በበጋ የሚለበሱ ቲሸረት፣ ሸሚዝ)።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተለያዩ የክረምትና በጋ አልባሳት፣ የጃንጥላ ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- በክረምትና በበጋ የሚለበሱ ልብሶችን አይነቶች መጠየቅ? ተቆጣሪ ነገሮችን እንዲደምሩ ማድረግ፣ በጋ፣ ጠዋት፣ ማታ የመሳሰሉ ቃላትን አስመስለው እንዲጽፉ መጠየቅ)

### ለ. ባህላዊ ውዝዋዜ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ባህል፣ሙዚቃ፣ውዝዋዜ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በቅድሚያ ህስጻናቱን ከክፍል ውጭ ይዘዋቸው ይውጡ። በአንድ ቡድን ውስጥ ዘጠኝ ሆነው እንዲደራጁ ያድርጓቸው። በመቀጠል ክብ ክብ እንዲሰሩ በማድረግ ለበዓላትና ለሰርግ የሚዘፈኑ ባህላዊ ሙዚቃዎችን ይክፈቱላቸው። በተከፈተላቸው ሙዚቃም ውዝዋዜ እንዲያቀርቡ ያድርጉ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የሙዚቃ ማጫወቻ፣ አልባሳት
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የተወዛወዙበት ሙዚቃ መቼ እንደሚጨፈርበት መጠየቅ) እና ምልከታ (ለምሳሌ፡- ሲወዛወዙ ምልከታ ማድረግ)

### ሐ. የቁጥር ሎቶ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መደመር፣መቁጠር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! በቅድሚያ ካርቶንና ጎድጓዳ ሳህኖች ያዘጋጁ። በመቀጠል በካርቶን ውስጥ አምስት ጠጠር፤ በጎድጓዳ ሳህን ዉስጥ ደግሞ አራት ጠጠር በማስቀመጥ ህጻናቱ ተራ በተራ ከካርቶኑ እና ከሳህኑ ውስጥ ጠጠሮች እያነሱ በአንድ ላይ ቆጥረው በመደመር ወደ ካርቶኑና ሳህኑ እንዲመልሱ ያድርጉ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ካርቶን፣ ሳህን፣ ጠጠር
- **የምዘና ስልት-** ጥያቄ (ለምሳሌ፡- በተለያዩ ነገሮች እንዲደምሩ መጠየቅ)

## ተግባር 2. ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ሁለት የሚዋደዱ ጓደኞች (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቤተሰብ፣ መደመር፣ሥዕል፣ እንስሳት፣ ባህላዊ፣ዳንስ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-**መምህር! ከዚህ በታች ያለውን ተረት ለህጻናቱ ይንገሯቸው።

## ተረት ተረት!

በድሮ ጊዜ ሣሙኤልና ሰለሞን የሚባሉ ሁለት የሚዋደዱ ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ ሣሙኤል 4 እህቶችና 3 ወንድሞች አሉት፡፡ እናትና አባቱን ጨምሮ ዘጠኝ ቤተሰቦች ሲኖሩት ሰለሞን ደግሞ 1 እህትና 1 ወንድም ከእናትና አባቱ ጋር በድምሩ 4 ቤተሰቦች አሉት፡፡ ሣሙኤል አብዝቶ የእንስሳትን ሥዕል መሳል  የሚያስደስተው ሲሆን ሰለሞን ደግሞ በህላዊ ዳንሶችን አስመስሎ መደነስ ይወዳል፡፡ ሰለሞንና ሣሙኤል በትምህርታቸውም ጎበዝ ስለነበሩ ሲያድጉ ሣሙኤል ሰዓሊ ሰለሞን ደግሞ ተዋቂ ዘፋኝና ተወዛዋዥ ሆኑ ይባላል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ተረት መጸሀፍ፣ የቤተሰብ ሥዕል፣ የእንስሳት ሥዕል፣ሞባይል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡-ሣሙኤልና ሰለሞን ስንት እህቶችና ወንድሞች አሏቸው?) ሣሙኤልና ሰለሞን ሲያድጉ ምን ሆኑ...)

### ለ. የጠፋው ጎረቤታችን (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ባህላዊ፣ አልባሳት፣ ባህላዊ ዳንስ፣ መቀስ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ተረቱን በአግባቡ ማዳመጣቸውን ይከታተሉ፡፡

ተረት ተረት!

በአንድ ወቅት ኪያ የምትባል እናቷን በሥራ የምታግዝ ልጅ ነበረች፡፡ አንድ ቀን በጠዋት ተነስታ ቁርስ በልታ ጥርሷን ቦርሻ፣ ከወንድሟ ጋር የህጻናት መቀስ በመጠቀም ከወረቀት የተሰራ የእጅ ሰዓት ሰርታ ወደ ትምህርት ቤት ስትሔድ ጎረቤቷ የሆነውና አብረው የሚማሩ  ሰይድ የሚባል ልጅ መጥፋቱን ሰማች፡፡  እንዴት ጠፋ ብላ እናቷን? ጠየቀቻት  ሰፈር ባህላዊ ዳንስ  መደነስ ሲለማመዱ መሸበትና ቤቱ ጠፋበት፡፡ በዕለቱ ሰይድ ባህላዊ ልብስ ልብሶ ስለነበር የለበሰውን ልብስ በመንገር የት አከባቢ ታይቶ እንደነበር በቀላሉ ለማወቅ አልተቸገሩም፡፡  በኋላ ሌላ ሰፈር  እንዳሳደሩትና በጠዋት እንደሚያመጡት ሰምቻልሁ አለቻት፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ ሰይድ ሳይመሽ ወደ ቤቱ መግባት ጀመረ ይባላል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ባህላዊ አልባሳት፣ ሞባይል፣ ከወረቀት የተሰራ የእጅ ሰዓት
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ሰይድ የጠፋው ምን ሁኖ ነው? ኪያ ከወረቀት ምን ሰራች?)

## ተግባር 3፡- መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ጠዋት ጠዋት (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሀገር፣ ማንበብ፣ መጻፍ፣ ባህል
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! መዝሙሩን በጋራና በግል እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

ጠዋት ጠዋት እነሳለሁ፣
ሆሄያትን ደጋግሜ እጽፋለሁ፡፡
እንዳልርሳም አነባለው፣
ሙዚቃዬን እከፍታለሁ፣
በማዳመጥ አደንቃለሁ፡፡
የምወደው ባህል አለኝ፣
በመጨፈር የሚያምርብኝ፡፡
ሃገሬንም እወዳለሁ፣
ታሪኳንም ጠብቃልሁ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ሞባይል/መቅርጸ ድምጽ/፣ደብተርና እርሳስ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- በመዝሙሩ ውስጥ ስላሉ ነገሮች መጠየቅ) እና ምልከታ (ለምሳሌ፡-ዜማውን ጠብቀው መዘመራቸውን መመልከት)

## ለ. ሰዓቴ ቁጠሪ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ጊዜ፣ ሳምንት፣ ቀን፣ ሌሊት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዘሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ማዘመር እና አብሮ መዘመር ይጠበቅቦታል፡፡

ሰዓቴ ቁጠሪ

ሰዓቴ ቁጠሪ፣ /2/
ጠዋት ቀን ማታን አብስሪ፡፡
ሰባት ቀናት አንድ ሳምንት፣
አንዴ ብርሃን አንዴ ለሊት፡፡
ነቃ ብዬ ተነስቼ፣
ሰውነቴን አፍታትቼ፣
በአንቺ ቁጥር ተግባብቼ፡፡
ያለሽ ቀለም ውይ ማማሩ፣
ቀለማትን ሲያስተምሩ፡፡
ደግሞ ማንበብ ደስ ይለኛል፣
መደመርም ይቀለኛል፡፡
ሁሌም ኑሪ ወድሻለሁ፣
ባንቺ ጊዜን አውቂያለሁ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የወረቀት ሰዓት፣የቀለማት ቻርት፣የቁጥር ካርድ፣ደብተር እርሳስ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- አንድ ሳምንት ስንት ቀን አለው...ቀን ምን እነሰራለን፣ ሌሊት ምን እንሰራለን...)

### ሐ. ፀሐይ ደመቀች (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መደመር፣ማስታረቅ፣ፀሐይ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- የመምህርሚና፡- መምህር! ሞባይል/መቅርጸ ድምጽ/ በመጥቀም ህጻናቱን መዝሙሩን ያለማምዱ።

ፀሐይ ደመቀች
ፀሐይ ወጣች በጠዋት፣
ዝልል ዝልል በህብረት።
ፀሐይ ደምቃ ስታበራ፣
እንጫወት በአንድ በጋራ።
ፀሐይ ጠፋች ምሽት ተካት፣
እንዘጋጅ ደግሞ ለዕራት።
የሰጡንን የቤት ስራ፣
እንጻፈው በየተራ።
ደግሞ ቁጥር ደምረን፣
ሆሄያትን እንጽፋለን፣
እንተኛ ተጣጥበን።
የተጣላም ነገ ታርቆ፣
አዲስ ዕለት አንጸባርቆ።

- መማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡- ሞባይል/መቅርጸ ድምጽ
- የምዘና ስልት፡- የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- በመዝሙሩ ውስጥ ስላሉ ነገሮች/ለምሳሌ ጸሃይ መቼ ትወጣለች...የተጣላ እናስታርቃለን...)

## ተግባር 4፡- ውይይት (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ውይይት (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ብዛት፣ መደነስ፣ መውደድ፣ ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በውይይት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን በቡድን ይመድቧቸው። በቡድኑ ውስጥ ስንት አባላት

እንዳሉ እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ መንገድ ላይ ያዩትን ነገር፣ ብዛታቸውን፣ቀለማቸውን፣የወደዱትን፣ያልወደዱትን እንዲዘረዝሩ እድል ይስጧቸው፡፡ ቀጥለው ባህላዊ እና ዘመናዊ ዘፈኖች ይክፈቱላቸውና ይወዛወዙ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃ፣አልባሳት የቁጥር ፍላሽ ካርድ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ውይይቱን እንዴት ተወያያችሁ?፣ስለ ምንና ምን ተወያያችሁ? በቡድናችሁ ውስጥ ስንት ነበራችሁ?...) ምልከታ (ለምሳሌ፡- በአግባቡ መወያየታቸውን መመልከት፣የተፈለገውን ተግባር መፈጸማቸውን መመልከት...)

## ተግባር 5፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የጋራ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-**መቆራረጥ፣ቁጥር፣ቀለም
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን በአምስት በአምስት በቡድን ይመድቧቸው፡፡ በመቀጠል በፕላስቲክ መቀስ በመጠቀም ወረቀቶችን እንዲቆራርጡና በቁርጥራጭ ወረቀቶች የእጅ ሠዓት እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡ በሰሩት ሰዓት ላይ ከ1 እስከ 9 ቁጥሮች ይጻፉባቸው፡፡ ሲጨርሱ ቀለም ይቀቡ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ማርከር፣ የሰዓት ሥዕል፣የህጻናት መቀስ፣የቁጥር ካርድ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- በሰዓቱ ላይ የተጻፈውን ቁጥር መጠየቅ፣ ሰዓቱን ምን አይነት ቀለም ቀባኸው?ሽው?...)

## ተግባር 6- በፕሮጀክት መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ማዛመድ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቀለም፣መቆራረጥ፣መገጣጠም፣መቁጠር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የተለያዩ የቤት እንስሳትን የሰውነት ክፍሎች ሥዕል በወረቀት ላይ ስለው ይስጧቸው፡፡ ህጻናቱም ትንንሽ መቀስ ተጠቅመው እንዲቆራርጡና ቀለም እንዲቀቡ ያድርጓቸው፡፡ የቀቡትንም ቀለም በስም እንዲጠቅሱ ያድርጉ፡፡ ከጨረሱ ብኋላ እርስዎ የእንስሳውን ሙሉ ሥዕል በመያዝ እያዩ እንዲገጣጥሙ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም ስንት እንደገጣጠሙ ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የእንስሳት የሰውነት ክፍሎች ሥዕል፣መቀስ፣ ቀለም
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ስንት የሰውነት ክፍል ቀለም ቀባችሁ?፣ስንት ቆራረጣችሁ?፣ስንት ገጣጠማችሁ?..)

# ሰላሳኛ ሳምንት

የተሰጠው ሰዓት...10 ሰዓት (30 ክፍለ ጊዜ )

## አጥጋቢ የመማር ብቃት

- በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ የሌሎችን ስሜት መገንዘብ፣
- ሰዎችን በስማቸው፣ በጾታቸው፣ በዕድሜያቸው፣ ወዘተ ይለያሉ፡፡
- የሰውነት ክፍሎቻቸውን ይዘረዝራሉ፡፡
- የምስሎችን ቅርፅና ዓይነት ምን እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡
- እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን በቃላቸው ይቆጥራሉ፡፡
- የመጀመሪያ ፊደላትና ቁጥሮችን ይፅፋሉ፡፡
- የግል ንጽህናቸውን ይጠብቃሉ፡፡

## ንዑስ ይዘቶች

- ማህበራዊ ግንዛቤ
- ማንበብ
- መቀነስ
- ተክሎች
- ትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር
- መስመሮች/pattern/ቅጥ
- ጥበባዊ እሴት

## ተግባር 1፡- የግል ተግባር (6 ክ/ ጊዜ)

### ሀ. ሥረዓተ ንድፍ (Pattern) (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ስርዓተ ንድፍ፣ ስሜት፣ ቀለም፣ መቀነስ
- **ማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናት የተለያየ ቀለም የተቀቡ ቆርኪ ያዘጋጁና ነጠላ ስርዓተ ንድፍ ይስሩ (ለምሳሌ፡- 1 ቀይ ቀለም የተቀባ ቆርኪ 2 አርንጓዴ የተቀቡ ቆርኪዎች፣ እንደገና 1 ቀይ ቀለም የተቀባ ቆረኪ፣ 2 አርንጓዴ የተቀቡ ቆርኪዎች፣እንደገና 1 ቀይ ቀለም የተቀባ ቆረኪ፣...)፡፡ ሥርዓተ ንድፉን ሰርተው ከጨረሱ በኂላ ካለው ላይ በመቀነስ ስንት እንደቀራቸው ለጓደኞቻቸውም ይንገሯቸው፡፡ ለሁሉም ተመሳሳይ ሰዓት ይስጧቸው፡፡ ይህም የጊዜ አጠቃቀምን ይለማመዳሉ፡፡ ህጻናቱ በተግባራቱ መሃል የሚያሳዩትን ስሜት ይመልከቱ፡፡ ሲጨርሱ ያመጡትን እቃ ወደ ቦታው ይመልሱና እጃቸውን በውሃና ሳሙና ይታጠቡ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ቆርኪ፣ቀለም

- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ከአንድ ቀይና ሁለት አረንጓዴ ቆርኪዎች ውስጥ 1 ቀይ ቆርኪ ስንቀንስ ስንት አረንጓዴ ቆርኪ ቀረ?) እና ምልከታ (ለምሳሌ፡- ሥርዓተ ንድፉን በአግባቡ ማከናወናቸውን መመልከት፣...)

## ለ. የግል ስራ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መቁጠር፣ ሥዕል፣ ማስተዋወቅ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን ወደ ውጭ ይዘው ይውጡ። አንድ በ10 ትናንሽ ኳሶች የተሞላ እና አንድ ባዶ ቅርጫት ያስቀምጡ። ኳሶቹ ላይ የተለያዩ ሥዕሎችን ይለጥፉ። በመቀጠል ህጻናቱን ተራ በተራ በማስነሳት ጓደኞቻቸውን ያስተዋውቁ (ለምሳሌ፡- ስማቸውን፣ ጾታቸውን፣ ዕድሜያቸውን) ከዚያም ከቅርጫቱ ውስጥ ኳስ በማንሳት ሥዕሉን በማየት ለጓደኞቻቸው በመንገር ያነሱትን ኳስ በባዶ ቅርጫት ውስጥ እየቆጠሩ ይክተቱ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ኳሶች፣ ቅርጫት
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ከ1 እስከ 9 እንዲቆጥሩ መጠየቅ..)

## ሐ. አካላዊ እንቅስቃሴ (2 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት-** እንቅስቃሴ፣ መታጠብ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን በማሰለፍ በማስወጣት ተግባራቱ የሚከናወኑበትን ሰፊ ቦታ ይምረጡ። ከሶስት እስከ አምስት የካርቶን ሳጥኖች በመጠኑ አራርቀው ያስቀምጡ፡ ፡ በመቀጠልም ህጻናቱ በየተራ እየዘለሉ አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ያሳዩዋቸው፡ ፡ ያለምንም መውደቅ ስንት ሳጥን እንደዘለሉና የቀረው ስንት እንደሆነ ለጓደኞቻቸው ይንገሯቸው። ሲጨርሱ እጃቸውን በውሃና ሳሙና ይታጠቡ
- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** አጫጭር ሳጥኖች
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ስንት ሳጥን እንዳወጡ፣ስንት ሳጥን እንደዘለሉ፣ስንት እንደቀራቸው መጠየቅ...)

# ተግባር 2- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

## ሀ. ሜሎና (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቤተሰብ፣ዘመድ፣ንጽህና
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ ተረቱን በአግባቡ እንዲያዳምጡ ማድረግ፣ ተረቱን በሥዕል አስደግፎ ማውራት ይጠበቅቦታል።

## ተረት ተረት!

አንድ ሜሎና የምትባል የ4 ዓመት ህጻን ልጅ ነበረች፡፡ በአከባቢዋና በቤተሰቦችዋ ዘንድ ተወዳጅ ነች፡፡ ሁልጊዜ በጥዋት በመነሳት ንጽህናዋን ትጠብቃለች፡፡ ሜሎና ቤተሰብ ማለት እናትና አባት ብቻ ናቸው ብላ ታስብ ነበር፡፡ ነገር ግን የጓደኛዋ ናኒ ቤተሰቦች በጣም ብዙ እንደሆኑ አስተዋለች፡፡ ግን ለምን እኛ ትንሽ ሆንን? ብላ እራስዋን ጠየቀች:: እቤት ስትገባ የኛ ቤተሰብ ቁጥር ለምን አነሰ ብላ እናቷን ጠየቀቻት፡፡ እናቷም 5 አክስትና 4 አጎት እንዲሁም 4 አያቶች እንዳሏት ትምህርት ሲዘጋ ክፍለ ሃገር ሄደው እንደሚያዩዋቸው አስረዳቻት፡፡ ሜሎናም በጣም ደስ አላት፡፡ ብዙ ዘመዶች እንዳላት ተረዳች፡፡ አመሰግናለሁ እማዬ በማለት አቅፋ ሳመቻቸው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቤተሰብ ስዕል፣ የተረት መጽሃፍ፣ውሃና ሳሙና
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ስንት ቤተሰብ አለን? ስንት አክስት አለን? ስንት አጎት አለን ? ሜሎና ስንት ዓመቷ ነው? ሜሎና በጥዋት በመነሳት ምን ታደርጋለች?)

### ለ. ፍቅር እና አያቷ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የግል ንጽህና፣ማዳመጥ፣ ሥዕል
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! እባክዎ ከዚህ በታች ያለውን ተረት ይነገሯቸው፡፡ ህጻናቱ ተረቱን በአግባቡ እንዲያዳምጡ ያድረጉ፡፡

## ተረት ተረት!

ከአያትዋ ጋር የምትኖር ፍቅር የምትባል ልጅ ነበረች፡፡ ፍቅር በጠዋት በመነሳት የግል ንጽህናዋን በመጠበቅ ወደ ት/ቤት መሄድ ትወዳለች፡፡ ከት/ቤት ስትመለስ አያቷ ማታ ማታ በጣም የሚያስደስት ተረት ከነገሯት በኂላ ተረቱን በአግባቡ ማዳመጥዋን ለማረጋገጥ ተረቱ የት ሃገር ተከናወነ፣ ማንና ማን አሉበት፣ ለምንና እንዴት ተፈጸመ፣ መቼ የሚሉትን ጥያቄዎች ይጠይቋታል፡፡ እሷም ጥያቄውን በአግባቡ ትመልስላቸው ነበር፡፡ ፍቅር ሁልጊዜ የነገሯትን ተረት በአግባቡ በማዳመጥና የተረቱን ምናባዊ ሥዕል በአዕምሮዋ በማንበብ ለጓደኞቿ መልሳ ትነግራቸው ነበር፡፡ በዚህም ጓደኟቿ በጣም ተወዳጅ ነበረች ይባላል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተረት መጽሃፍ፣ተረቱን የሚግልጽ ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ለፍቅር ተረት የሚነግሯት ምኗ ነበሩ? አያቷ ተረቱን የሚነግሯት መቼ ነበር?...)

## ተግባር 3- መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ማንበብ (4 ክፍለ ግዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ማንበብ፣ መግለጽ፣ስሜት፣መቁጠር
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በመዝሙር

- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! እባክዎ ከዚህ በታች ያለውን መዝሙር ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

ማንበብ

በማንበቤ አውቂያለሁ፣

ራሴን መግለጽ እችላለሁ፣

የሰው ስሜት እረዳለሁ፣

ትልቅ ዕውቀት ስላገኘሁ፣

በጊዜም እጠቀማለሁ፡፡

ቁጥር በቃል እቆጥራለሁ፣

ሥዕል መግለጽ እችላለሁ፡፡

ማንበብ በጣም ደስ ይለኛል፣

ሁሉን እንዳውቅ አድርጎኛል፡፡

ጠዋት ጠዋት በመነሳት፣

ደስ ይለኛል ስፖርት መስራት፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** መቅረጸ ድምጽ፣ የቁጥር ካርድ፣ የሚነበብ ሥዕል፣ መጽሃፍ...
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የማንበብ ጥቅሙ ምንድን ነው?) እና ምልከታ ማድረግ (ለምሳሌ፡- ሲዘምሩ መከታተል፣...)

### ለ. ስፖርት በመስራቴ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ስፖርት፣የግል ንጽህና፣ ስዕል መግለጽ፣እናት ፊደላት፣ቁጥር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህርሚና፡-** መምህር! ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር በእጅ ስልኮዎ /በመቅረፀ ድምፅ አማካኝነት እንዲለማመዱና እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

ስፖርት በመስራቴ

ስፖርት በመስራቴ ጉልበቴ በረታ፣

ጡንቻዬ ጠንክሮ ሆንኩኝ ማልረታ፡፡

የግል ንጽህናዬን ሁሌ ጠብቃለሁ፣

በሳምንት ከፍዬ ይህን አደርጋለሁ፡፡

ስዕልን በማየት መግለጽ እችላለሁ፣

ከ1እስከ 9 ቁጥር እቆጥራለሁ፡፡

በጾታና ዕድሜ ሰውን እለያለሁ፣

እናት ፊደላችን መጻፍ እችላለሁ፣

ወ፣ፈ፣ረ እያልኩኝ እደረድራለሁ፡፡

ስለዚህ ህጻናት በርቱና ተማሩ፣

ቁጥሮችን በመጻፍ ቀንሱ ደምሩ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ስልክ፣ መቅረፀ ድምፅ፣የእናት ፊደላትና የቁጥር ፍላሽ ካርድ...
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ስፖርት መስራት ለምን ይጠቅመናል? ከ1እስከ 9 ቁጥር እንዲቆጥሩ መጠየቅ...)

## ተግባር 4- የክፍል ውጭ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የወንበር ሽሚያ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቃላት፡-** መቀነስ፣መቁጠር፣መጻፍ
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱን ወደ ውጭ ይዘው በመውጣት በቡድን ተመራርጠው ክብ እንዲሰሩ ያድረጉ፡፡ በመቀጠልም በእያንዳንዳቸው ቡድን ውስጥ ስንት አባላት እንዳሉ ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በቡድኑ ውስጥ 9 ዘጠኝ አባላትና 8 መቀመጫ ወንበር እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡ የጨዋታውን ህግ አረንጓዴ መቀመጥ፣ ቀይ መቆም፣ ቢጫ መሮጥ ሲሆን አረንጓዴ ሲባል ወንበር ያላገኘ አንድ ህጻንና አንድ ወንበር ተማሪ ይቀነሳል፡፡ ለሁሉም ቡድን እኩል ጊዜ ይመድቡ በመጨረሻም በስንት ወንበር ጀምረው ስንት እንደ ቀነሱ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ወንበር፣ ፊሽካ
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ተግባሩን በትክክል መስራታቸውን መከታተል...) የቃል ጥያቄ (ስንት የቡድን አባላት እንዳሉ ቆጥረው እንዲናገሩ፣ አረንጓዴ፣ ቀይ፣ ቢጫ ሲባል ተግባራቱን ምን እንደሆነ ... መጠየቅ)

### ለ. እንጫወት (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቃላት፡-** ቁጥር፣ፊደል፣መቀነስ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱን ከክፍል በማስወጣት ክብ በመስራት አብረዋቸው በመጫወት ያበረታቷቸው፡፡ ህጻናቱ አምስት አምስት ሆነው ክብ ሰርተው ቁጭ እንዲሉ በማድረግ በመሀላቸው ለ1ኛው ቡድን አምስት እናት ፊደላት፣ ለ2ኛው ከ1 እስከ 9 ያሉ

ቁጥሮች፣ ለ3ኛው 8 ትንንሽ ኳሶች፣ ለ4ኛው 9 ዘንግ ወይም ብሎኮች፣ ለ5ኛው ሌሎች መጫወቻዎችን ያስቀምጡ። ከየቡድኑ አንድ ህጻን አንዱን ዘንግ ወይም ኳስ በማንሳት ሌላው ህጻን ስንት ቀረ ይላል/ትላለች። የተለያዩ ፊደላትን ከፊደል ገበታ ላይ በማንሳት ይህ ፊደል ማን ነው? ስንት ቀረ? ለሌቹ ደግሞ አራት ይላሉ በዚህ መልኩ ተነስተው እስከ ሚያልቁ ድረስ በማጫወት የመቀነስ ጽንሰ ሀሳብን እንዲያዳብሩ ያድርጉ።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ዘንጎች፣ኳሶች፣እናት ፊደላትና ከ1 እስከ9 ያሉ ቁጥሮች ፍላሽ ካርድ፣ መጫወቻዎች
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ጨዋታውን በመከታተል በትክክል የተገበሩና ያልተገበሩ ህጻናትን መለየት፣ የጊዜ አጠቃቀማቸውን መመዝገብ) የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የሚቀንሱትን ቁጥር በቃል እንዲጠሩ መጠየቅ፣ፊደላትን መጠየቅ)

## ተግባር 5- በፕሮጀክት መማር (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የሰዓት ሞዴሎችን በወረቀት መስራት (ክፍለ ጊዜ 2)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ሰዓት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለፕሮጀክቱ ስራ የሚስፈልጉ ቁሳቁሶች ያዘጋጁላቸው

1. ህጻናቱ የሚሰሩበትን ሰፋ ያለ ቦታ ያመቻቹ የሰዓት ሥዕል ያሳዩዋቸውና የምን እንደሆነ ይጠይቋቸው
2. ህጻናቱ የሰዓቱን ሞዴል በከለር ወረቀትና፣ ካርቶን፣ እንዴት መስራት እንዳለባቸው ያሳዩዋቸው።
3. የተዘጋጀውን ዕቃ በዕኩል አካፍለው የተዘጋጀው ጠረጴዛ ላይ ያድርጉላቸው
4. በመቀጠል በተሰጣቸው ካርቶን የሰዓት ቅርፅ እንዲሰሩ ይንገሯቸው።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ሞዴል ሰዓት፣ ከለር ወረቀት፣ ካርቶን፣ የልጆች መቀስ፣ ማጣበቂያ/ኮላ፣ ግሉ/
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- በአግባቡ መስራታቸውን መከታተል) የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ሰዓቱን ለመስራት ምን ምን ቁሳቁስ ተጠቀማችሁ? ስንት ቁጥሮችን ጻፋችሁ)

## ተግባር 6- የመስክ ምልከታ (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የመስክ ምልከታ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ተክሎች፣ አበባ፣ መንከባከብ
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በመስክ ጉብኝት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ቀጣዩን ተግባር ለመስራት አስፈላጊ የሆነ ግንዛቤ ይስጧቸው

1. ከ3 እስከ 5ያሉ ህጻናትን በቡድን መመደብ

2. ከክፍላቸዉ ዉጭ ያሉ ተክሎችን ምንነትና እንዴት ጠዋትና ማታ መንከባከብ እንዳለባቸው ያስገንዝቧቸው፡፡ ይህም በጋራ የሚሰሩት ተግባር በመሆኑ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ፡፡
3. ከተክሎቸ /አበባዎች/ መካከል የሚወዱትን የአበባ አይነትና ከፍሎቻቸውን ብዛትና ከለር እንዲናገሩ ያድርጉ
4. ለተክሎች አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን /መኮትኮቻ፣ ውሃ ማጠጫ፣ መከርከምያ መቀስ፣ የቁሻሻ ማጠራቀሚያ/እንደሚያስፈልጉ ይግለጹላቸው
5. ወደ መስክ ይውሰዷቸውና ያስገብኙዋቸው
6. ሁሉንም የመስክ ምልከታ ካጠናቀቁ በኂላ በውሃና ሳሙና ተጠቅመው እጃቸውን በአግባቡ እንዲታጠቡ ያድርጓቸው

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** መኮትኮቻ፣ ውሃ ማጠጫ፣ መከርከምያ መቀስ፣ የቁሻሻ ማጠራቀሚያ፣ ውሃ እና ሳሙና
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የወደዳችሁት ተክል ምንድን ነው? አትክልት ለመንከባከብ የሚስፈልጉን እቃዎች ምን ምን ናቸው? የተክል ከፍሎችን ብዛትና ከለር እንዲናገሩ መጠየቅ፣ ስራ ከሰራን በኂላ እጃችንን መታጠብ ለምን ይጠቅመናል?)

# ሰላሳ አንደኛ ሳምንት

## የተሰጠው ሰዓት......10 ሰዓት (30 ክፍለ ጊዜ)

### አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ከሌሎች ጋር በአዎንታዊ መልኩ እንድንገናኝ የሚረዱ የሞራል እሴቶችን ይለያሉ
- ከሌሎች ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር የግብረ ገብ ዕሴቶችን ይለያሉ
- የተለያዩ ታሪኮችን እና እንቆቅልሾችን በአግባቡ ያዳምጣሉ
- ከ1-9 የሚሆኑ ቁሶችን ይደምራሉ
- ቀላል ቃላትን እንደገና ያነባሉ
- ፊደላትን ያነባሉ እና እንደገና ይጽፋሉ
- የቦታ ጽንሰ ሀሳብ ይገልጻሉ
- ሚና ጨዋታ በቡድን ይጫወታሉ
- ስለ ነፍሳት፣ ወፎች፣ ትላትሎች፣ ወዘተ ይናገራሉ
- የደህንነት ደንቦችን ይለያሉ እና እራሳቸውን ከአደጋ ይጠብቃሉ
- ዋና ዋና የቀለም ዓይነቶችን በስም ይለያሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- የሞራል እሴት
- የንግግር የድምጽ ግንዛቤ
- የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አካባቢዎች
- ፊደላትን መጻፍ
- ማንበብ
- መቀነስ
- የቦታ  ግንዛቤ
- መያያዝ፣ ግንኙነት እና መተግበር
- ደህንነት እና መከላከል

## ተግባር 1- የግል ተግባር (5 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ህግ እና ደንቦች (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** እሴት፣ ታማኝነት፣ስነ ምግባር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተግባር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር!  በየተራ ከተዘጋጁ ማዕዘናት የተለያዩ የመማሪያ ቁሳቁሶችን ወደ

መቀመጫቸው እንዲያመጡ ያድርጉ፡፡ ያመጡትንም ቁሳቁሶች ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያደርጉ፡፡ የሞራል እሴትን የሚያዳብሩ ሀሳቦችን በማንሳት ህፃናት ያላቸውን ግንዛቤ ይገምግሙ፡፡ ለምሳሌ መስረቅ፣ መዋሸት፣ ታማኝነት፣ የመሳሰሉትን ምን ያህል እንደሚያውቁ ይጠይቋቸው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ማዕዘኖች፣ ቁሳቁሶች፣ ደብተር፣ እርሳስ
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡-ተግባራቱን በትክክል መፈጸም መቻላቸውን መከታተል) የቃል ጥያቄ( ስለ መልካም ስነ ምግባር መጠየቅ)

### ለ. የመስክ ምልከታ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መደመር፣ መልካም ግንኙነት፣ የተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመስክ ጉብኝት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የሚባሉትን ምን ምን እንደሆኑ ይግለጹላቸው፡፡ በመቀጠልም ወደ ውጭ ይዘዋቸው በመውጣት በአከባቢያቸው የሚገኙ በተፈጥሮ የምናገኛቸውና የሰው ልጅ የሚሰራቸውን እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ ያዩትን ለጓደኞቻቸው እንዲያስረዱ ያድርጉ፡፡ ይህም ከጓደኞቻቸው ጋር መልካም ግንኙነትን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል፡፡ ከአንድ እስከ ዘጠኝ ያሉ ሰው ሰራሽ ቁሶችን እንዲደምሩ፣ ቀለማቸውን እንዲናገሩና ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሥዕሎችና ሞዴሎች፣ ሰው ሰራሽ ቁሶች፣የቁጥር ካርድ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡-የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየታቸውን መጠየቅ)

## ተግባር 2- የክፍል ውስጥ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሐ. እንቆቅልሽ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ፊደል፣እንስሳት፣ነፍሳት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በእንቆቅልሽ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለህጻናቱ የእንቆቅልሽ ጨዋታውንና የጨዋታውን ህግና ደንብ ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠልም ህጻናቱን በቡድን ይከፋፍሏቸው፡፡ ቡድኖችንም የሚውቋቸውን እንቆቅልሽ እንዲጠያየቁ ያድርጉ፡፤ለምሳሌ፡-

1. አንድ እግር አለኝ ወገቤን ይዣለሁ እኔ ማን ነኝ መልስ "ቀ"
2. እግር የለኝም ቅርጼ መነጽር ይመስላል ከፊደላት እመደባለሁ እኔ ማን ነኝ? መልስ "መ"
3. በተለያዩ የሚያምሩ ቀለማት ተውቤያለሁ ከነፍሳት እመደባለሁ እኔ ማን ነኝ? መልስ ቢራቢሮ
4. ትንሽ ነኝ በሰማይ ላይ እበራለሁ ሰውነቴ በላባ ተሸፍኗል እኔ ማን ነኝ? መልስ፤ ወፍ

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የፊደል ሎቶ፣ የነፍሳት፣የወፎች ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- በቡድን መሳታፋቸውን ምልከታ ማድረግ) የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የሚያዉቁትን እንቆቅልሾች እንዲናገሩ መጠየቅ፣ የሚያውቋቸውን ነፍሳትና አዕዋፋት መጠየቅ)

# ተግባር 3- ተረት (6 ክፍለ ጊዜ)

## ሀ. የማያ የሽርሽር ጉዞ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** እንስሳት፣ ነፍሳት፣ ደህንነት፣ ደንቦች
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተረት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ከዚህ በታች ያለውን ተረት ለህጻናቱ ይንገሯቸው፡፡

### ተረት ተረት!

ማያ የአብዮት ፋና ተማሪ ነች፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በዕረፍት ቀን ከእናትዋ ጋር ሽርሽር በመሄድ ታሳልፋለች፡፡ ዛሬም እንደ ልማድዋ በጠዋት በመነሳት ልብሶቿን በመቀያየር ከእናትዋ ጋር ለመሄድ ተነሳች፡፡ በጉዞ ላይ እያሉ ማያ ብዙ ነገሮችን እየተመለከተች ነበር፡፡ መዝናኛ ሲደርሱ ማያ በጣም ተደሰተች፡፡ በመዝናኛ ግቢ ውስጥ ያሉትን ነገሮች እየተመለከተች ተደነቀች፡፡ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮችን፤ የዱር እንስሳት፣ ወፎች፣ ቢራቢሮ፣ ቀበሮ፣ ድኩላ የመሳሰሉትን ስትመለከት ደስታዋ ጨመረ፡፡ በጉዞዋ ስለ ደህንነት ደንቦች ቀበቶ ማሰር፣ በመዝናኛው ቦታ ብቻዋን መሄድ እንደሌለባት፣ በመዝናኛ ቦታ የተከለከሉ ነገሮች (ለምሳሌ አበባ መቁረጥና መርገጥ) ክልክል መሆኑን ተረዳች፡፡ ት/ቤት ስትሄድ ለጓደኞቿ ስለአየችውና ስለሰማችው ሁሉ አስረዳቻቸው ይባላል፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የተረት መጽሃፍ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ:-ማያ ከእናትዋ ጋር የሄደችው የት ነው? ምንምን እንስሳትን ተመለከተች? በመዝናኛ ቦታ የተከለከሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?...)

## ለ. ነፍሳቶቹና ገበሬዎቹ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ተስማምተው፣ ነፍሳት፣ ገበሬ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በተረት
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ ተረቱን መልሰው እንዲናገሩ ደጋመው ይተርቱላቸው፡፡

### ተረት ተረት!

በአንድ ገጠራማ አከባቢ ከጎረቤታቸው ጋር ተስማምተው የሚኖሩ እህትና ወንድም ገብሬዎች ነበሩ፡፡ በዚህ አመት የተለያየ የእህል አይነት ስለዘሩ ጓሯቸውና ማሳቸው በተለያዩ ቀለማት ተውበዋል፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን በግብርና ስራቸው ላይ እንዳሉ ብዛት ያለው አንበጣ የሚባል ነፍሳት የስንዴ ማሳቸውን ወረረባቸው፡፡ ለማባረር ቢሞክሩም ብዛት ያላው በመሆኑ ሊያባርሩት አልቻሉም፡፡ ስለዚህ በሃገሩ ደንብ መሰረት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ድረሱልን በማለት ጮሁ፡፡ ጩኸታቸውን የሰሙ ጎረቤቶቻቸውም እየተሯሯጡ በመምጣት አንበጣውን ማባረር አገዟቸው፡፡ በዚህም እህላቸውን በነፍሳት ከመበላት አተረፉላቸው፡፡ በዚህም በጣም ስለተደሰቱ ጎረቤቶቻቸውን በጣም አድርገው አመሰገኗቸው፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የአንበጣ ስእል፣ ገጠራማ አከባቢ የሚያሳይ ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ ስንዴውን ሲበላባቸው የመጣው ነፍሳት ምን ይባላል?፣ ገበሬዎቹ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ምን አሉ?፣ ገበሬዎቹ ምንና ምን ናቸው?

## ተግባር 4፡- መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ጠዋት ሲነጋ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቃላት፣ቁጥር፣ መደመር
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡

### ጠዋት ሲነጋ

ጠዋት ሲነጋ ጸሀይ ወጥታ፣

ማታ ሲመሽ ጸሀይ ገብታ፣

እኛ አንዋሽም እውነት አለን፣

መጥፎ ተግባር እንጠላለን፣

ክረምት ሲሆን ዝናብ ሲሆን፣

በጋ ሆኖ ትምህርት ገብተን፣

ቁጥር መቁጠር እንችላለን፡፡

8፤9 እንላለን እንደምራለን፣

ቀላል ቃላት እያነበብን፣

መረጠ፣ ጨፈረ እያልን፣

እየደገምን እንጽፋለን፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ወቅቶችን የሚያሳይ ሥዕል፣ቁጥርና ፊደል ፍላሽ ካርድ፣በወረቀት በእናት ፊደላት የተሰሩ ቃላት/ለምሳሌ፤ ነቀነቀ፣ ወፈረ፣ ሰለጠነ…
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- ፀሀይ የምትወጣው መቼ ነው? የምትገባውስ?)

### ለ. ቅዳሜና እሁድ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ቃላት፣ደንብ፣ ማንበብ፣መደመር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! መዝሙሩን በጋራና በግል እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

## ቅዳሜና እሁድ

ቅዳሜና እሁድን አወኳት፣
ሰኞ ስትመጣልኝ በጠዋት።
ፊቴን ታጥቤ ለባብሼ፣
ያገኘሁትን ቁርስ ቀምሼ።
ቦርሳና ምሳዬን ይዤ፣
ሚስ ጋር ለመድረስ በእግሬ ተጉዤ።
የናፈኩትን ትምህርት አገኘሁ፣
ቀላል ቃላትን ማንበብ ችያለሁ።
1-9 እየቆጠርኩኝ እደምራለሁ፣
ህግና ደንብን ተረድቻለሁ፣
ጎበዝ ተማሪ መሆን እሻለሁ።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** ቀላል ቃላት፣የቁጥር ፍላሽ ካርድ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- የሳምንቱን ቀናት መጠየቅ፣1-9 እንዲቆጥሩ መጠየቅ)

### ሐ. ትንሿ ጎጇችን (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፦** ቤተሰብ፣ ምሳሌ፣ ቀለም፣ባህል
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በመዝሙር
- **የመምህራን ሚና:-** መምህር! ከህጻናቱ ጋር በመዘመር ያለማምዷቸው።

ትንሿ ጎጇችን

ትንሿ ቤታችን ባለ ሳር ክዳኗ፣
እንኮራበታለን የኛ በመሆኗ።
በአከባቢው ያሉ ጥሩ ቤተሰቦች፣
ምሳሌዎች ናቸው ለአከባቢ ሰዎች።
የቤታቸው ቀለም አቤት ደስ ማለቱ፣
ውበትን ለግሷል ሲታይ መሰረቱ።
ውሸት ስርቆት የለም በዛ በባህሉ፣
የተገኘም ካለ አብረው ያወግዛሉ።

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፣-** የሳር ጎጆ ሞዴል፣የቀለም ስሌዳ
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ:- የቤታችሁ ቀለም ምን አይነት ነው?)

## ተግባር 5- የውይይት ግዜ (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ደህንነትና ደንቦች (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ደህንነት፣ መከላከል፣ደንብ
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡-** በውይይት
- **የመምህርሚና፡-** መምህር! ህፃናቱ ወደ ውጭ ይዘው በመውጣት ስለ ደህንነት የተለያዩ ተረቶች ወይም እንቆቅልሽ ይንገሯቸው፡፡ ካዳመጡ በኋላ ስለ ደህንነት ደንቦች እራሳቸውን ከአደጋ እንዴት መከላከል እንደሚችሉ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ አንድ ህጻን ተናገሮ/ተናግራ ለመጨረስ የጊዜ ገደብ ይቀመጥለት/ላት፡፡ በመቀጠል የዕለቱን ተግባር የሚያጠናክር በእናት ፊደላት ቀላል ቃላትን ያስነብቧቸው/ለምሳሌ፤አከበረ፣ ተጠነቀቀ…
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ትራፊክ መብራት፣ ጉድጎድ ወይም ገደል የሚያሳይ ስዕል፣የፊደላት ቻርት
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡- የመኪና አደጋ እንዳይደርስብን ምን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለብን ?...)

## ተግባር 6- የክፍል ውጭ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የትራፊክ ህግ (2 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የትራፊክ ህግ፣ የትራፊክ መብራት፣
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ስለትራፊክ መብራት ጠቀሜታና ህግጋት ማብራሪያ ካደረጉ አንድ ህጻን የትራፊክን ሚና እንዲጫወት፣ ሶስት ህጻናት አያንዳንዳቸው የትራፊክ መብራት ምልክት እንዲይዙና ሌሎች ህጻናት ደግሞ ሾፌርና እግረኛ በመሆን አረንጓዴ ካርድ የያዘው ህጻን አረንጓደውን ሲያሳይ መኪና ያልፋል፤ ቢጫ ካርድ የያዘው ህጻን ካርዱን ሲያሳይ ዝግጁ ይሆኑና ቀይ ካርድ የያዘው ህጻን ቀይ ሲያሳይ መኪና ይቆምና እግረኛ ይሄዳል፡፡ በዚህ መልኩ ሁሉንም ህጻናት ያጫውቷቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ከለር ወረቀት፣ ማርከር፣ መቀስ
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ለምሳሌ፡- ጨዋታውን በመከታተል በትክክል የተገበሩና ያልተገበሩ ህጻናትን መለየትና ተግባራቱን/ህጎቹን/ መለየታቸውን ማረጋገጥ፣ የተሰጣቸውን የትራፊክ ሚና በትክክል መጫወታቸውን መመልከት) የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- የትራፊክ መብራት ህግጋትን መጠየቅ፣ የትርፊክ መብራት ቀለሞችን መጠየቅ)

# ተግባር 7- በፕሮጀክት መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

## ሀ. መደመርና መቀነስ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መደመር፣ መቀነስ፣ዕሴት
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ከእንጨት ወይም መሬት ላይ ቆፍረው ገበጣ መጫወቻ ያዘጋጁ፡፡ በተዘጋጀው ገበጣ ጉድጓድ ዉስጥ ጠጠሮችን ይቁጠሩና በየጉድጓዱ በመክተት ያጫውቷቸው፡፡ ሲጫወቱ የሞራል ዕሴቶችን እንዲተገብሩ ያድርጉ ለምሳሌ መስረቅ፣ መዋሸት እነደሌለባቸው ያስረዷቸው፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ገበጣ፣ ጠጠር
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ (ሲጫወቱ መመልከት፣ ጠጠሩን ሲደምሩና ሲቀንሱ መመልከት...) የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- በየጉድጓዱ ውስጥ የሚቀመጡ ተጠሮች ስንት ናቸው?)

# ሰላሳ ሁለተኛ ሳምንት

**የተሰጠው ሰዓት……10** **(30 ክፍለ ጊዜ)**

## አጥጋቢ የመማር ብቃት

- በሁለት አማራጮች መካከል የሚፈልጉትን ይመርጣሉ
- ቀላል ቃላትን ያነባሉ
- ከ1-9 ቁሶችን ይደምራሉ፣ ይቀንሳሉ፣ ይጽፋሉ
- ፊደላትን እንደገና ይፅፋሉ
- ስለመውደድና አለመውደድ ይገልጻሉ
- ጊዜን (ጠዋት፡ ቀን፡ ለሊት) ይለያሉ
- በግንባታ ውስጥ በመሳተፍ
- ከወዳደቁ ነገሮች ትናንሽ ቤቶችን ይገነባሉ
- የምህንድስና መሳሪያዎችን ይለያሉ
- የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን ይለያሉ
- አርአያዎቻቸውን (ከቤተሰብ፣ ከትምህርት ቤት፣ ከማህበረሰብ) እነማን እንደሆኑ ይናገራሉ

## ንዑስ ይዘቶች

- የውሳኔ ችሎታ
- ማንበብ
- ደብዳቤ መፃፍ
- መደመር
- መቀነስ
- ጊዜ
- የሀገር ፍቅር ስሜት
- ራስን ማወቅ

## ተግባር 1 የክፍል ጨዋታ (10 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የፊደል ሳጥን (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ፊደል፣ ቃላት
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በጨዋታ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ቀለል ያሉ ቃላትን በካርድ ላይ ጽፈው በአንድ ሳህን ላይ እንዲሁም ፊደላትን በትንንሽ ወረቀት ላይ ጽፈው ሰፋ ባለ ሌላ ካርቶን ወይም ሳህን ላይ አድርገው ለህጻናቱ የቃላት ካርዱን በመስጠት የቃሉን ተመሳሳይ ፊደላት ከሳህን/ ውስጥ

ፈልገው እንዲያወጡና ቃላቱን ገጣጥመው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የቃላት ካርድ፣ የካርቶን ሳጥን፣ደብተር፣እርሳስ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ ስንት ቃላት በሳጥኑ ውስጥ ነበሩ?

### ለ. የሂሳብ ስሌት (6 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** መደመር፣ መቀነስ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በስራ
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱ ክፍላቸው ካለው ማዕዘን የቁጥር ካርድ ከ1 እስከ 9፣ የሚቆጠሩ ቁሶችን ዘጠኝ እርሳስና ወረቀት /ደብተር/ በመውሰድ በወረቀቱ ከአንድ እስከ ዘጠኝ በቅደም ተከተል ይፃፉ በቁስ የመደመር እና የመቀነስ ስሌትን በጠረጴዛቸው ላይ በመስራት የቁጥር ካርዶቹን ከተቆጣሪዎች ጋር እያዛመዱ ይሂዱ፡፡ ሁሉም ህፃናት በጠረጴዛቸው ላይ ይህን ተግባር ያከናውኑ፡፡ ስለሰሩት ተግባር ለክፍል ጓደኞቻቸው ይግለፁ፡፡ ሲጨርሱ የተጠቀሙበትን ቁሰቀቁሶች በቦታው መመለሳቸውን ያረጋግጡ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ቁሶች፣ የቁጥር ካርድ፣ እርሳስ፣ ወረቀት/ደብተር/
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ሁለት ኩባያና ሁለት ኩባያ ሲደመሩ ስንት ኩባያ ይሆናሉ፤ ከ5 ኩባያ 3 ኩባያ ሲቀነስ ስንት ኩባያ ይቀራል)

## ተግባር 2- ተረት (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ሰላም (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ማንበብ፣ ፈጠራ፣ ምግባር
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በተረት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር ተረቱን ሳቢ እና ማራኪ አድርገው ያንብቡላቸው

**ተረት ተረት!**

ሰላም የአዲስ ብርሃን ትምህርት ቤት ተማሪ ስትሆን በምግባሯ ጥሩ ሥነ ምግባር ያላት ልጅ ነች፡፡ ከጓደኞቿ ጋር ስትጫወት ትልቅ ሰው ዕቃ ይዞ ካየች የምትቀበል እንዲሁም ጓደኞቿ ሲጣሉ ለምን ትጣላላቹ ብላ የምታስታርቅና ጸብን የምትጠላ በመሆኗ ተወዳጅ ናት፡፡ ሰላም በፈጠራ ችሎታዋ ደግሞ ጎበዝ በመሆኗ አንድ ቀን ትምህርት ቤት በፈጠራ ስራ ውድድር በወዳደቁ ቁሳቁሶች ሰዓት ሰርታ ሜዳሊያ ተሸልማለች፡፡ በትርፍ ጊዜዋ ደግሞ ማንበብ ትወዳለች፡፡ የኔ ጀግና እናቴ ናት ትላለች፡ ፡ ምክንያቱም ወላጅ የሌላቸውን ህጻናት እንደ እናት ሆና አሳድጋ ለቁም ነገር አብቅታለች፡፡ ስለዚህ እንደሷ እኔም ሰዎችን መርዳት አለብኝ አለች፡፡

- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የተረት መፅሃፍ፣የሰዓት ሞዴል
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፤ ሰላም የተሸለመችው ምን ስርታ ነው? የሰላም ጀግና ማን ናት?)

## ተግባር 3- በስራ መማር (4 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የቤት ግንባታ (4 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት:-** ግንባታ፣ ደህንነት፣ በትብብር፣ስሜት
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በስራ
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! በወረቀት ላይ ህጻናቱ መስራት የሚፈልጉትን የቤት አይነት በስዕል ያስቀምጡ። ቀጥሎ የሳሉትን ቤት ለመስራት ምን እንደሚያስፈልጋቸው በክፍል ውስጥ ካለው የግንባታ ማዕዘን መሳሪያዎችን ይያዙ መቀስ፣ ማጣበቂያ፣ ካርቶን፣ ፕላስቲክ፣ ብሎክ የመሳሰሉትን እንዲመርጡ ያግዟቸው። እነዚህን ከያዙ በኂላ ወደ ውጭ በመውጣት በቡድን ሆነው የወሰኑትን የቤት አይነት ዘመናዊና ባህላዊ ቤት ይስሩ። ሁሉም በቡድን ስሜት በትብብር መስራት እንዳለባቸው መረዳት አለባቸው። በግንባታ ወቅት ከወረቀት ከካርቶን፣ ከፕላስቲክ የተዘጋጀ የደህንነት ኮፍያ ያድርጉ። በመጨረሻም በየቡድናቸው የተጠቀሙበትን የግንባታ ቁሳቁስ ቦታው ይመልሱ። በጋራ በመሆን ተገቢውን የፅዳት ቁሳቁስ ተጠቅመው የሰሩበትን አካባቢ ያፅዱ። ሲጨርሱ እጃቸውን በተገቢ እንዲታጠቡ ያድርጉ።
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ:-** የፕላስቲክ፣የካርቶን፣የግንባታ ቁሳቁስ፣ ጭቃ (የተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ)፣ ማጣባቂያ፣ ወረቀት እርሳስ፣ ከለር፣ የፅዳት ዕቃዎች (መጥረጊያ፣ ማፈሻ)
- **የምዘና ስልት:-** የቃል ጥያቄ ምን ሰራችሁ፣ቤቱ ከምን ከምን ተሰራ፤ ዘመናዊና ባህላዊ ቤት ከሁለቱ ምርጫቸውን መጠየቅ

## ተግባር 4- መዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. ልተጣጠብና (3 ክፍለ ጊዜ )

- **ቁልፍ ቃላት:-** ቀን፣ ምሽት፣ መታጠብ፣መደመር፣መቀነስ
- **የማስተማርያ ዘዴ:-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና:-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው።

### ልተጣጠብና

ልተጣጠብና ልሂድ ትምህርት ቤት፣

መከተል ይሻላል መንገድን በዕውቀት።

ልደምር ልቀንስ ላስላ ቁጥርን፣

ሳይንስን ልመርምር የምወደውን፣

ደግሞም እየጻፍኩኝ ፊደል ቃላትን።

ፀሀይ በጣም ሞቀች እኩለ ቀን ላይ፣

ታንፀባርቃለች ወደ ላይ ስናይ።

ትንሽ በረድ ስትል ደግሞ ከሰዓት፣

እንጫወታለን ሆነን በአንድነት።

ምሽቱ ደረሰ ጨለማ ነገሰ፣

የምንተኛበት ሰዓቱ ደረሰ።

ሌሊቱም ይነጋል ይመጣል ጠዋት፣

እንሂድ እንገስግስ ወደ እውቀት ቤት፣

በመማር ወደፊት መሀንዲስ ሆናለሁ።

- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የጊዜን ልዩነት የሚያሳዩ ሥዕሎች / ብርሃን እና ጨለማ/ የፊደልና ቃላት ፍላሽ ካርድ፣/ለምሳሌ;- ገ-ገመደ፣ ወ-ወሰደ፣ ጠ-ጠረገ፣ ሠ-ሠረዘ፣...ደብተር እርሳስ ፣
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ/ለምሳሌ፤ በመዝሙሩ ውስጥ ስላሉት ጊዜያት በመጠየቅ፣ ጠዋት ምን ይከናወናል፣ ቀንስ፣ ማታስ ምን ይታያል /

## ለ. ተማርኩኝ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** ማንበብ፣መደመር፣መቀነስ፣መውደድ፣ቴክኖሎጂ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በመዝሙር
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ ያግዟቸው።

## ተማርኩኝ

ተማርኩኝ ተመራመርኩኝ፣

ተደነኩኝ ተደሰትኩኝ።

ሀገር አለኝ የምወዳት፣

የምማርባት የምመካባት።

ቴክኖሎጂ ዕውቀት እና ምህንድስና፣

በደንብ አውቄያቸው እኮራለሁ ገና።

ፊደልን በማንበብ ቃላት እጽፋለሁ፣

መደመር መቀነስ ቁጥር ለይቻለሁ።

መጥላቴን መውደዴን፣

ምርጫዬን መለየት ይቻለሁ መንገዴን።

- **የመማርያና መጫወቻ ቁሳቁስ፡-** የፊደል ካርድ፣ ቁጥር የመደመር እና የመቀነስ ስሌት ምልክቶች የቃላት ካርድ፣ የቀለም ቻርት፣ ቴክኖሎጂና ምህንድስና መሳርያዎች ሥዕል
- **የምዘና ስልት፡-** የክፍል ስራ (ፊደሎችን ደጋግመው እንዲፅፉ ማድረግ፣ ቁሶችን እንዲደምሩና እንዲቀንሱ ማድረግ፣ የሚወዱትንና የሚጠሉትን መጠየቅ)

## ተግባር 5- ውይይት (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. አርዓያ ምን እያደረገ ነው? (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** አርዓያ፣ቴክኖሎጂ፣ምርጫ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በውይይት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ከህፃናቱ ጋር በጋራ ሃሳብ የምትለዋወጡበት ክፍለጊዜ ነው፡፡ ውይይቱን እርሶ ያስጀምሩ እርሶ አርዓያ የሚሏቸውን ለምሳሌ ሀገራቸውን ከጠላት የሚጠብቁ እና የሚወዱ፣ ቴክኖሎጂን (ስልክ፣ ኮምፒዩተር፣ ቴሌቪዥን) የፈጠሩ ሰዎችን ይንገሯቸው፡ ፡ በመቀጠል እነሱን በየተራ ለውይይት ይጋብዙ፡፡ ለእነሱ አርዓያ/ጀግና ምን የሰራ እንደሆነ? እነሱም ምን ሰርተው አርዓያ መሆን እንደሚፈልጉ? እና ከቤተሰባቸው፣ ከትምህርት ቤት፣ ከአካባቢያቸው አርዓያ የሚሏቸው ሰዎች ካሉና በምን አርዓያ/ጀግና እንደሆኑ ይጠይቋቸው፡፡ ሁሉም ህፃናት እድል አግኝተው በውይይቱ ይሳተፉ፡፡ እንዲሁም ስለ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የሚያውቁትን በውይይቱ እንዲናገሩ ያበረታቱ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ቴክኖሎጂ ሥዕሎች /ሞዴሎች/ የታዋቂ/አርዓያ ሰዎች ፎቶ
- **የምዘና ስልት፡-** የቃል ጥያቄ (ምን ሰርተው አርዓያ መሆን እንደሚፈልጉ፣ ከአካባቢያቸው አርዓያ የሚሏቸው ሰዎች ካሉ በምን አርዓያ/ጀግና እንደሆኑ፣ ከቴክኖሎጂ ውስጥ የሚወዱትንና የሚጠሉትን እንዲገልጹ መጠየቅ፡፡)

## ተግባር 6- በፕሮጀክት መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

### ሀ. የፈጠራ ስራ (3 ክፍለ ጊዜ)

- **ቁልፍ ቃላት፡-** የፈጠራ ስራ፣ አርዓያ፣ ቴክኖሎጂ
- **የማስተማርያ ዘዴ፡-** በፕሮጀክት
- **የመምህር ሚና፡-** መምህር! ህፃናቱ ከዚህ ክፍለ ጊዜ በፊት ስለ አርዓያ መረጃ እንዳገኙ ይታወሳል፡፡ በመሆኑም እነሱ የክፍሉ አርዓያ ለመሆን ከቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ (የስልክ፣ የኮምፒዩተር፣ የቴሌቪዥን፣ ፎቶ ካሜራ) የመሳሰሉትን ከአካባቢያቸው ከሚገኙ የወዳደቁ ነገሮች እቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ እና ለክፍል ጓደኞቻቸው ስለሰሩት ነገር ስለተጠቀሙት ቁሳቁሶች፣ ስለወሰደባቸው ጊዜ፣ ማን እንዳገዛቸው ገለፃ ያድርጉ፡፡
- **የመማርያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ህፃናቱ መስራት ለሚፈልጉት ፈጠራ የሚጠቀሙት (ለምሳሌ የውሃ ፕላስቲክ ኮዳ፣ ካርቶን፣ ወረቀት፣ ላስቲክ፣ ማጣበቂያ፣ ያገለገለ ባትሪ፣ እንጨት ...)
- **የምዘና ስልት፡-** ምልከታ የሰሩትን የፈጠራ ስራዎች መመልከት

# የአውድ ስድሰት ምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም ------------------------------ጾታ-------- እድሜ ------ደረጃ-------

መግለጫ:- ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሟሉት ብቃት ትይዩ የ "√" ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ።

| ተ.ቁ | የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት | ጥሩ | በ/ጥሩ | እ/በ/ጥሩ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የፊደላት ድምጾችን መለየት | | | | |
| 2 | ከ1-5 የሆኑ ቁሶችን ተጠቅመው መደመር | | | | |
| 3 | ነጠላ ሥርዓተ ንድፍ (Pattern) መስራት | | | | |
| 4 | የቤታቸውንና ት/ቤታቸውን አቅጣጫ መለየት | | | | |
| 5 | በብሎኮች ውስጥ ትንንሽ ቤቶችን መገንባት | | | | |
| 6 | ግጭቶችን መፍታት | | | | |
| 7 | የሚወዱትንና የሚጠሉትን መለየት | | | | |
| 8 | የጀግናዎቻቸውን ስም መጥራት | | | | |
| 9 | ከሁለት አማራጮች መካከል መምረጥ | | | | |
| 10 | አካላዊ እንቅስቃሴዎች ማድረግ | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፦ ______________________________________________

______________________________________________________________

______________________________

# አባሪ 1

## የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የዕለት ዕቅድ ናሙና

የት/ቤቱ ስም፡ ብሩህ ህጻናት ቅድመ-አንደኛ ደረጃ የመ/ር ስም፡ ሊድያ አሰፋ

ደረጃ፡ 1

አውድ፡ ስለእኔ ሳምንት፡ 1

የህጻናት ብዛት፡ ወ፡ 25 ሴ፡ 23 ድ ፡ 45 የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ፡ 20 ደቂቃ

**ዓላማዎች፡- ህጻናት ከዕለቱ ተግባራት በኋላ፡-**

- ስለ ራሳቸው ይናገራሉ
- ጓደኞቻቸውን ይለያሉ(በስማቸው፣ በጾታቸው፣በዕድሜያቸው፣ ወዘተ.)
- የሰውነት ክፍሎችን ይናገራሉ
- ምስል በማየት ድርጊቱን ይገልጻሉ
- ከአንድ እስከ አምስት ያሉ ቁጥሮችን በቃላቸው ይቆጥራሉ
- ያለገደብ ይሞነጫጭራሉ
- የግል ንጽህናቸውን መጠበቅ ይጀምራሉ

| ጊዜ | የተግባራት ርዕስ | የመምህር ሚና | የህጻናት ሚና | የትምህርት አቀራረብ ዘዴ | መማሪያና መጫዎቻ ቁሳቁስ | ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2:00-2:30 | የመቀበያ ጊዜ | ህጻናትን ጤንነታቸውንና<br>ስሜታቸውን እያዩ ከመግቢያ በር አቀባበል ማድረግ ፤የህዝብ መዝሙር እየዘመሩ የባንዲራ ሥነ-ሥርዓት እንዲያከብሩ ማድረግ፤ ነጻ ጨዋታ እንዲጫወቱ ማበረታታትወደ<br>መማሪያ ክፍል ማስገባት | ነጻ ጨዋታዎችን<br>መጫዎት፣የህዝብ መዝሙር መዘመርና ባንዲራ መስቀል፣ ወደ ክፍል መግባት | | | |
| 2:30-2:50 | ክፍለ ጊዜ 1፡ የግል ተግባር ርዕስ፦ እራስን ማስተዋወቅ | ህጻናትን ለተግባር ስራው ዝግጁ ማድረግ<br>-ራስዎን ለህፃናቱ በሚገባና በቀላል አገላለጽ ማስተዋወቅ፣ህጻናቱ ራሳቸውን ሲያስተዋዉቁ ስማቸውን መጀመሪያ በበመናገር እንዲጀሩ ማሳየት | ለተግባር ስራው ዝግጁ<br>መሆን፣ መምህረቸው ራሳቸውን ሲያስተዋዉቁ መስማት፣ ተከትለው ራሳቸውን ማስተዋወቅ፣የጓደኞቻቸውን ስሞች መናገር | -መንገር<br>-ማሳየት<br>-በተግባር ማለማመድ | ህጻናት እራሳቸውን ሲያስተዋውቁ የሚያሳይ ቪድዮ የተቀረጸበት ሲዲ፣/ፍላሽ/ ሚሞሪ/፣ቴሌቪዥን፣ ካሜራ፣ መቅረጽ ድምጸ/ሞባይል፣ ስዕላዊ መግለጫዎች | የቃል ጥያቄ (ስማቸውን፣ ዕድሜያቸውን፣ የአባታቸውን ስም መጠየቅ)፣ |
| 2:30-2:50 | ክፍለ ጊዜ 1፡ የግል ተግባር ርዕስ፦ እራስን ማስተዋወቅ | ህጻናትን ለተግባር ስራው ዝግጁ ማድረግ<br>ራስዎን ለህፃናቱ በሚገባና በቀላል አገላለጽ ማስተዋወቅ፣ህጻናቱ ራሳቸውን ሲያስተዋዉቁ ስማቸውን መጀመሪያ በበመናገር እንዲጀሩ ማሳየት | ለተግባር ስራው ዝግጁ<br>መሆን፣ መምህረቸው ራሳቸውን ሲያስተዋዉቁ መስማት፣ ተከትለው ራሳቸውን ማስተዋወቅ፣ የጓደኞቻቸውን ስሞች መናገር | -መንገር<br>-ማሳየት<br>-በተግባር ማለማመድ | ህጻናት እራሳቸውን ሲያስተዋውቁ የሚያሳይ ቪድዮ የተቀረጸበት ሲዲ፣/ፍላሽ/ ሚሞሪ/፣ቴሌቪዥን፣ ካሜራ፣ መቅረጽ ድምጸ/ ሞባይል፣ ስዕላዊ መግለጫዎች | የቃል ጥያቄ (ስማቸውን፣ ዕድሜያቸውን፣ የአባታቸውን ስም መጠየቅ)፣ |

| ጊዜ | የተግባራት ርዕስ | የመምህር ሚና | የህጻናት ሚና | የትምህ ርት አቀራረብ ዘዴ | መማሪያና መጫዎቻ ቁሳቁስ | ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2:50-3:10 | ክፍለ ጊዜ 2: ተረት<br>ርዕስ፡ ጎበዞ ተማሪ | ህጻናትን ለተረቱ ማዘጋጀት፣ ተረቱን ባህላዊ የአ ቀራረብ ስልት ጠብቀው ማቅረብ፣ ከተረቱ ላይ ጥያቄዎን መጠየቅና የተረቱን ፍሬ ሀሳብ በቃል መንገር | ተረቱን ለመስማት መዘጋጀት፣ ተረቱን ተቀባይ ሆነው መስማት፣ ጥያቄዎ ችን መመልስና የተረቱን ፍሬ ሀሳብ መከታተል | - መተረክ<br>- ማብራራት<br>- ውይይት | - በተረት፣ሥዕሎችን ማሳየት፣ተንቀሳቃሽ ሥዕል በማሳየት | - የቃል ጥያቄ<br>(ስንት እጅ አለን? ስንት እግር አለን?፣ የሰውነት ክፍሎቻቸውን እንዲያሳዩ መጠየቅ፣ በተረቱ ላይ እነማን አሉ?) |

| ጊዜ | የተግባራት ርዕስ | የመምህር ሚና | የህጻናት ሚና | የትምህርት አቀራረብ ዘዴ | መማሪያና መጫዎቻ ቁሳቁስ | ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3:10-3:40 | የቁርስ ሰዓት<br>• እጃቸውን በስነስርዓት እንዲታጠቡ ማድረግ<br>• ተረኛ ህፃናት በተረኝነት ስራ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ<br>• ምግባቸውን ተገቢውን የአመጋገብ ስርዓት ተከትለው እንዲመገቡ ማድረግ፣መከታተልና ማበረታታት<br>• ሲጨርሱ እጃቸውን በስነስርዓት እንዲታጠቡ ማድረግ | | | | | |
| 3:40-4:40 | ክፍለ ጊዜ 3፡ ተረት<br>ርዕስ፦ ኀበዞ ተማሪ | ህጻናትን ለተረቱ ማዘጋጀት፣ ተረቱን ባህላዊ የአቀራረብ ስልት ጠብቀው ማቅረብ፣ ከተረቱ ላይ ጥያቄዎን መጠየቅና የተረቱን ፍሬ ሀሳብ በቃል መንገር | ተረቱን ለመስማት መዘጋጀት፣ ተረቱን ተቀባይ ሆነው መስማት፣ ጥያቄዎችን መመልስና የተረቱን ፍሬ ሀሳብ መከታተል | - መተረክ<br>- ማብራራት<br>- ውይይት | - በተረት፣ሥዕሎችን ማሳየት፣ተንቀሳቃሽ ሥዕል በማሳየት | - የቃል ጥያቄ<br>(ስንት እጅ አለን? ስንት እግር አለን?፣ የሰውነት ክፍሎቻቸውን እንዲያሳዩ መጠየቅ፣ በተረቱ ላይ እነማን አሉ?) |
| 4:00-4:20 | ክፍለ ጊዜ 4፡ መዝሙር<br>ርዕስ፡- ልሂድ ትምህርት ቤት | ለመዝሙሩ ዜማ በማውጣት ህጻናቱ በግልና በጋራ እንዲዘምሩ በማለማመድ | • ቁሳቁሱን መቀበል፣ትዕዛዝ መከተል፣የመምህሁን ሥራ በትኩረት መከታተል፣ የራስ ስዕል መሳል<br>• ሁሉም ህጻናት ግጥሙና ዜማውን እስኪይዙት ድረስ ደጋግመው ያዘምሯቸው። | - መዘመር<br>- | ተቆጣሪ ነገሮች፣ ፊደል፣ ንጽህና አጠባበቅ የሚሳይ ምስል | - ምልከታ<br>- የቃል ጥያቄ<br>- ሲዘምሩ እየተከታተሉ እርማት መስጠት...፣ እና የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ፡- በመዝሙሩ ውስጥ ስላሉ ነገሮች መጠየቅ...) |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4:20-4:50 | እረፍት ሰዓት<br>▪ ነፃ ጨዋታ እንዲጫወቱ ማድረግና መከታተል<br>▪ ለዕለቱ በመምህር የጣቀደውን ጨዋታ አብሮ መጫወት<br>▪ ሀሳባቸውን ማሰባሰብና ወደ ክፍል በስርዓት እንዲገቡ ማድረግ | | | | | |
| 4:50-5:50 | የማሸለቢያ ሰዓት<br>▪ ጫማና ተደራቢ ልብሶቻቸውን አውልቀው በስነስርዓት እንዲያስቀምጡ ማድረግና ማስተኛት<br>▪ በመኝታቸው ላይ ጥበቃ ማድረግ<br>▪ የመነሻ ሰዓት ሲደርስ ቀስ ብሎ ከእንቅልፋቸው እንዲነቁ ማድረግ<br>▪ ተፀዳድተውና ፊታቸውን ታጥበው ወደ ክፍል እንዲገቡ ማድረግ | | | | | |
| 5:50-6:10 | ክፍለ ጊዜ 5፡ የውጭ ጨዋታ<br>ርዕስ፡ እጅ ለእጅ ተያይዘን | ህፃናቱ ወደ ውጭ ይዘው መውጣት ሁለት ክብ እንዲሰሩ ማድረግ:: መጀመሪያ ቡድን አንድ በመቀጠል ቡድን ሁለት እጅ ለእጅ ተያይዘን የሚለውን ጨዋታ ማጫዎት::በጫወታው ሁሉም በየተራ የራሳቸውን ስም እንዲሩ/እንዲያስተዋውቅ/ ማድረግ | • ጨዋታውን ህግ ማዳመጥ፣ ተራቸውን ጠብቀው እንዲ ጫዎቱ ማድረግ | - ገለጻ<br>- ማሳየት<br>- በጨዋታ | ህጻናት ክብ ሰርተው ሲጫውቱ የሚሳይ ሥዕል፣ ቪድዮ | - ምልከታ /ለምሳሌ፡<br>- በትክክል እየተጫወቱ መሆኑን መከታተል/ -<br>የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡<br>- የተዋወቋቸውን ጓደኞቻቸውን ስም፣ እድሜ፣ ያታ መጠየቅ) |
| 6:10-6:30 | ክፍለ ጊዜ 6፡ ፕሮጀክት<br>ርዕስ፡ የህጻን ምስልን ከጭቃ መስራት | ህጻናቱ የሚሰሩበትን ቦታ በማ መቻቸት፣የሚሰሩባቸውን ጭቃ ማቅረብ፣ | | የግል ፕሮጀክት በማሰራት | አፈር፣ ሰው ሰራሽ ጭቃ (ከተገኘ)፣ ሳህን | የቃል ጥያቄ (ለምሳሌ፡<br>- የሰሩትን ምስል ጾታ፣ ስንት ምስል እንደሰሩ፣ የሰሩትን ምስል የሰውነት ክፍሎችን እንዲያሳዩ፣ ስራ ከሰሩ በኋላ እጃቸውን መታጠብ ለምን እንደሚጠቅም መጠየቅ...) |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6፡00 | የመሸኛ ጊዜ | ህጻናት ቁሳቁሳቸውን መያዛቸውን ማረጋገጥ፣በተራ ከክፍል እንዲወጡ ማድረግ፣ እስከበር ድረስ መውሰድና ከወላጅ ወይም አሳዳጊ ጋር ማገናኘት | ቁሳቁሳቸውን መሰብሰብ፣ በሥርዓት ከክፍል መውጣት፣ ከወላጅ ጋር መገናኘትና መምህራቸውን መሰናበት | | | |

የር/መ/ር አስተያየት:________________________________________

ስም: ____________________ ፊርማ: _______________ ቀን: _______________

የራስ ግምገማ:____________________________________________

ጠንካራ ጎኖቼ: ____________________________________________

____________________________________________

ማሻሻል ያለብኝ: ____________________________________________

____________________________________________

የኢ.ፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር 2017/2024

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

# የተቀናጀ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህር መምሪያ

## ደረጃ አንድ

ዋጋ____________________________